# ማውጫ

**ቀጣዩ ዕትማችን ቁጥር 7
ጥቅምት 24/2005 ዓ.ም
ቅዳሜ ይጠብቁ**


ከኦሮሞ ህዝብ ጀርባ... ገፅ 3

አቶ ስብሐትና የተንኮል ፖለቲካ ገፅ 4

ይድረስ ‹‹ለባለቅኔ›› በረከት ስምኦን ገፅ 5

የ“አዲሱ መንግስት” ተግዳሮት እና የአቶ ኃይለማሪያም አጣብቂኝ ገፅ 6

ደቡብ ሱዳን ቀጣይቱ የኢትዮጵያ ፈተና ገፅ 8

የመለስ ስብዕናና የህወሓት ታሪክ ግንባታ ሥነ-ልቦና ገፅ 10

የልማታዊ መንግስት ምንነትና በኢትዮጵያ አተገባበሩ ሲፈተሽ ገፅ 12

ኬኒያን በድርበቡ! ገፅ 13

የአጻጻፍ ስርዓትን ስለማሻሻል ገፅ 14

...ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንሶች እና ሰለሞን ተካልኞች... ገፅ 16

ደንታቢስነታችን ምን ያህል ነው? ገፅ 17

መፈንቅለ-መንግስት ያሰጋናል? ገፅ 18

ሃሣብ...ማሠብ ... አሳቢነት... ገፅ 25

የኦሮሞ ፖለቲካ ጉዳይ (ከትናንት እስከ ዛሬ) ገፅ 33

አዲስ ተስፋ ለኦጋዴን ገፅ 35

‹‹ቃሊቲ››ን በጨረፍታ ክፍል-፪ ገፅ 36

## ርዕሰ አንቀፅ

# የብሄራዊ ቡድናችን ድል የህዝብ ወይስ የመንግስት?

ስፖርት ከአካላዊ እንቅስቃሴነት ባሻገር በውድድር መልክ ሲሆን ሀገራዊ ፋይዳው በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡ ህዝቦች የብሔርና የፖለቲካ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን በመተው አንድነታቸውን ጎልቶ ከሚበራባቸው አጋጣሚዎች መካከል ስፖርታዊ ውድድሮች ዋነኞቹ ተጠቃሽ ነው፡፡ ሀገራችን በአትሌቲክሱ /በሩጫው/ አለማቀፍ ድሎችን ባስመዘገበች ቁጥር የአንድነታችን ስሜት በተደጋጋሚ ለማየት የታደልንበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም፡፡ አሁን ደግሞ የእግር ኳስ ብሄራዊ ቡድናችን ከሰላሳ አንድ ዓመት በኂላ ለአፍሪካ ዋንጫ ውድድር አልፏል፡፡ በተገኘው ውጤትም መላው ኢትዮጵያውያንን እንኳን ደስ አሏችሁ፣ እንኳን ደስ አለን እንላለን፡፡

ይህ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ብሔራዊ ቡድን ድል ከ31 ዓመታት በኂላ ከጠፋንበት የአፍሪካ ዋንጫ አደባባይ እንደገና እንድንመለስ በማድረጉ ለአዲስ-ታይምስ ዝግጅት ክፍልና ለመላው ህዝባችን ታላቅ ሀሴትን ፈጥሯል፡፡ ከፉክክሩ መድረክ ከጠፋንባቸው ከነዚህ ሶስት አስርታት ውስጥ ሁለቱ አስርታት በኢህአዴግ ዘመን መሆኑ ግን ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል፡፡ በነዚህ አመታት መካከል የስፖርቱን እድገት የሚጎትቱ አያሌ ስህተቶች ሲሰሩ እንደነበር ሁላችንም ያስተዋልነው ሃቅ ነው፡፡ በእድሜያችን እንኳ የምናውቃቸው የቀበሌና የሰፈር ሜዳዎች መታጠራቸውና ወደ ወረዳ /ቀበሌ/ ህንፃነት መቀየራቸው፣ በእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ ላይ የሚታዩ ፖለቲካዊ ጣልቃገብነት አለመቆማቸው፣ በጥናትና ምርምር ያልተደገፉ ስልጠናዎች አለመዘጋጀታቸው፣ ስር የሰደደ ሙስና፣ ታዳጊዎች ላይ የሚጀመሩ የፕሮጀክት ስራዎች ዘላቂነት አለመኖርና በመንግስት አካላት ብቻ ፍቃድ የሚሰጣቸው የሚዲያ ባለሙያዎች ከሀገር ውስጥ ይልቅ ለውጭ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ትኩረት መስጠታቸው ለእስከዛሬው ችግሮቻችን ከሚነሱ አበይት ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

የእግር ኳሳችን ትንሳኤ እንዲዘገይ የሆነበትም መነሾ ይህንን መሰል አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ሳንካዎች ስፖርታዊ ጉዳዮች ውስጥ በመሰንቀራቸው እንደሆነ ለማንም አይጠፋውም፡፡ ሀገርና ስፖርት ወዳድ የሆነው ህዝባችን ከሱዳን ብሔራዊ ቡድን ጋር ባደረግነው ጨዋታ ላይ ባሳየው ድጋፍ ይሄ ድል እንደሚያንሰው አስመስክሯል፡፡ ታሪክ እንደሚመሰክረው ለአፍሪካ እግር ኳስ እዚህ መድረስ ቀዳሚ ተጠቃሽ ኢትዮጵያ ነበረች፡፡ እግር ኳሳችን በአፍሪካ ዋንጫ ውድድሮች መጀመሪያ አመታት ላይ በመሳተፍ፣ በማዘጋጀትና ዋንጫውንም በማንሳት ወርቃማ ጊዜያቶችን አሳልፏል፡፡ በወቅቱ የነበረን የስፖርቱ የበላይነት ዛሬ ላይ ሆነን ስናስበው አንገታችንን እንድንደፋ ሲያደርጉን የነበሩት የመንግስታቶቻችን የጣልቃገብነት እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ ዛሬ ስፖርቱ ልክ እንደ ህዝባችን የነፃነት ያለህ እያለ ነው፡፡ የዛሬው ድላችንም ለእስከዛሬው ውድቀታችን ተጠያቂ የሆነውን መንግስት ያለምንም ተጠያቂነት በአመራርነት ባገለገሉት በአቶ መለስ መሰየሙ አንድም ድሉ ይገባቸዋል ወይ የሚለውን ጥያቄ ሲያስነሳ ሁለትም የስፖርቱ ጥገኝነት አሁንም ቢሆን ፖለቲካዊ ማንነት ያላቸውን ግለሰቦች ማጉያና መጠቀሚያ እየሆነ መቀጠሉን እንደማስረጃ ሊያሳየን ይችላል፡፡

የብሄራዊ ቡድናችን ድል ለዘመናት ፀሀይና ብርድ እየተፈራረቀበት፤ የሞተውን እግር ኳስ ለማንሳት ብርቱ ተጋድሎ ያደረገው ህዝብ እንጂ አቶ መለስ እና ድርጅታቸው ኢህአዴግ የሚኩራራበት ‹‹ራዕያቸው›› አለመሆኑ መታወቅ አለበት፤ የሚለው የመጽሔታችን ርዕሰ አንቀጽ ዋነኛ መልዕክት ነው፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር ለሃያ አንድ ዓመታት በስልጣን ላይ ሲቆዩ አንድም ቀን አዲስ አበባ ስታዲዮም ተገኝተው ብሄራዊ ቡድናችንን ሲደግፉና ሲያበረታቱ ታይተው አያውቁም፤ እግር ኳሳችን እንዲያድግ ከማበረታታት ይልቅም በየመንደሩ ያሉ ኳስ ሜዳዎችን ለኢንቨስተር መሸጥ ዋነኛ የገቢ ምንጭ አድርገውትም ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ራሱ ከባለሙያ ይልቅ በካድሬዎቻቸው እንዲሞላ በማመቻቸታቸው ወደአፍሪካ ዋንጫ የመመለሻ ዕድሜያችን የዚህን ያህል እንዲረዝም ምክንያት የሆነው የእርሳቸው አስተዳደር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከሀይሌ ገብረስላሴ እና ቀነኒሳ በቀለ ወይም ከጥሩነሽ ዲባባ እና ከመሰረት ደፋር የኦሎምፒክ ድል ጀርባ መንግስትና መለስ እንዳልነበሩት ሁሉ ከእግር ኳሱም ጀርባ የሉም፡፡

እናም በቡድኑ ጥረት እና በህዝባችን ያላሰለሰ ድጋፍ የተገኘውን ድል ‹‹የአቶ መለስ መታሰቢያ ነው››ም ሆነ ለድሉ ‹‹ህዳሴው ነው መሰረቱ›› ማለቱ የውጤቱን ህዝባዊነት ከመናቅ ባለፈ ፋይዳ የሌለው ተራ ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ ሰማይ ከፍ፣ ምድር ዝቅ ቢል ከድሉ ጀርባ ያለው ህዝብና የቡድኑ ጥንካሬ ብቻ ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን መንግስት እጁን ከእግር ኳሱ ላይ ያንሳ፣ ስፖርትና ፖለቲካ፣ ባለሙያ እና ካድሬ ይለዩልን እንላለን፡፡ ፌዴሬሽኑ በሙያተኞች ይመራ፣ አንዴ በታጋይ፣ ሌላ ጊዜ በጥርስ ሀኪም፣ አሁን ደግሞ በካድሬ ሸካራ መዳፍ ስር ይውል ዘንድ መገደዱን አጥብቀን እንቃወማለን፡፡

በአዲስ-ታይምስ እምነት በየትኛውም መስክ ሊታዩ የሚችሉ ስፖርታዊ ድሎቻችን ከጊዜያዊ ደስታ ይልቅ ዘላለማዊ ሊሆኑ የሚችሉት ፖለቲካዊ ማነቆዎች ስፖርቱን ከሚመሩት ፌዴሬሽኖችና ከአስተዳደራዊ አካላት ትከሻ ላይ ሲነሱ እንደሆነ ነው፡፡ የውድቀት ታሪካችንም የሚያሳየን ይህንኑ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም ታዳጊዎች ላይ የሚሰሩ ተግባራት ለነገው ድላችን መሰረቶች መሆናቸው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ አለበለዚያ ሀሴታችን የዛሬ ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ በስፖርቱ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ሚዲያዎችም ሀገራዊ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ቅድሚያ በመስጠት የሚተቸውን በመንቀፍ፣ የሚመሰገነውን በማበረታታት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አዲስ-ታይምስ ታስገነዝባለች፡፡ ለስኬቱ ቀጣይነትም ህዝብ በስታዲየሞች ላይ ለሚያሳየው የትዕይንት ድጋፍ ብቻም ሳይሆን በቀጥታ ተሳታፊ በማድረግ ከፖለቲካዊ ማንነት ይልቅ የሀገራዊ ክብር መገለጫ እንዲሆን እንበርታ እንላለን፡፡

*በድጋሚ መላው ኢትዮጵያዊያን እንኳን ደስ አላችሁ!*
*የድሉ መታወሻም ሆነ መታሰቢያ የሚገባው ለእናንተው ብቻ ነው!*

**አዲስ ታይምስ**

*ሃገራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ኪነ ጥበባዊ ጉዳዮች ላይ የምታተኩር መጽሔት*

**አሳታሚ:-**
አዱ ህትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር:-**
ተመስገን ደሳለኝ

**ም/ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ሙሉነህ አያሌው

**ስራአስኪያጅ**
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

**ዋና አዘጋጅ:-**
ዳዊት ታደሰ
አድራሻ አቃ/ቃ/ክ/ከተማ
ወረዳ 8
የቤት ቁጥር 003
E-mail nigusdawit@yahoo.com

**ግራፊክ ዲዛይን**
በአዲስ ታይምስ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ:-**
አራዳ ክ/ከተማ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር አዲስ
ስልክ ቁጥር
+251 922 87 19 37
+251 911 55 49 01
E-mail addistimes@yahoo.com
www.fetehe.com

**አታሚ**
ሔርቴጅ ሕትመትና ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር
አድራሻ:- ቂርቆስ ክ/ከተማ
ቀበሌ 10፣ ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 006



ተመስገን ደሳለኝ

# ከኦሮሞ ህዝብ ጀርባ…

## እንደመግቢያ

1975 ዓ.ም.፡፡ በመሀል ሀገር የነበረው የፖለቲካ ግለት ከብዙ ደም መፋሰስ በኋላ ወደ ጠረፍ እና የገጠር ከተሞች አፈገፈገ፡፡ በ‹‹ምርጥ መኮንኖች›› የተመሰረተው መንግስትም አንፃራዊ ሰላም ያገኘ መሰለ፡፡ አስቀድሞ ‹‹ወታደራዊ ክንፍ›› አቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) በሀገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች ለማቀጣጠል ሞክሮት የነበረው አብዮት ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎት ከሸፈ፡፡ ለክፉ ቀን ‹‹አማራጩ›› ያለው ወታደራዊ ክንፉም ቢሆን ለሶስት በመከፈሉ በእጅጉ ተዳከመ (ትግል በቃን ብለው ወደ ምዕራብ ሀገራት ለመሰደድ በወሰኑ፣ ኢህአፓን ይዘን እስከመጨረሻው እንፋለማለን ባሉና ‹‹ኢህአፓ ዴሞክራት አይደለም›› በሚል ተገንጥለው ‹‹ኢህዴን›› የተባለ አዲስ ድርጅት በመሰረቱ) ከዚህ በተቃራኒው በመገንጠል እና በብሄር ጥያቄ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሻዕቢያ፣ ህወሓት እና በሽብርተኝነት የተፈረጀው ኦነግ የተሻለ ድርጅታዊ አቅም መፍጠር ቻሉ፡፡

…በሁለት ወጣት ታጋዮች የሚመራ ከህወሓት የጦር ሰፈር (ደደቢት) የተነሳ አንድ ልኡክ ከኢትዮጵያ መንግስት የመረጃ ሰራተኞች እና የገጠር ካድሬዎች አይን ተሸሽጎ በከፍተኛ ጥንቃቄ ጉዞ ጀምሯል፡፡ መድረሻ ነጥቡ ‹‹ደባዜን›› የተሰኘች ከተማ ነች፡፡ ልኡኩ ከብዙ ቀናት በኋላ የኦሮሚያ ገጠር ከተማ በሆነችው ደባዜን ደረሰ፡፡ በወቅቱ ደባዜን የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር /ኦነግ/ ወታደራዊ ቤዝ ስትሆን ትግረኛ ተናጋሪ ታጋዮቹ ወደ አካባቢው የመጡት በድርጅታቸው ህወሓት እና ኦነግ መካከል በተፈረመ ስምምነት መሰረት ነው፤ የስምምነቱ ይዘት ‹‹የህወሓት ታጋዮች ለኦነግ ታጋዮች ወታደራዊ ስልጠና እንዲሰጡ፣ ካድሬዎችን እንዲያነቁ እና ሁለቱ ድርጅቶች በትጥቅ ትግሉም ሆነ ከትጥቅ ትግሉ በኋላ በጋራ እንዲሰሩ›› የሚል ነው፡፡ ሆኖም በሁለት የህወሓት አመራር አባል የተመራው ልዑክ ደባዜን ከደረሰ በኋላ ከኦነግ የጠበቀው አቀባበል የስምምነቱ ተቃራኒ ሆነ፡፡

ኦነግ በግልፅ ከህወሓት የተላኩትን ‹‹መርሲነሪዎች›› (ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዮች) ሲል አውግዞ ከወታደራዊ ሰፈሩ በፍጥነት እንዲወጡ አደረገ፡፡ በሁለቱ የአመራር አባላት የተመራው ቡድንም ወደ ትግራይ ተመለሰ፡፡ የቡድኑ መሪዎችም መላው የህወሓት የአመራር አባላት በተገኙበት ሪፖርታቸውን አቀረቡ፡፡ ሁለቱ የአመራር አባላት ክንፈ ገ/መድህን እና ሙሉጌታ ጫልቱ ነበሩ፡፡ ከዚህ ሪፖርት በኋላም ህወሓት ከኦነግ ጋር ለመስራት የነበረው ተስፋ መክነ፡፡


## የኦሮሞን ድርጅት ፍለጋ

ህወሓት ከኦነግ ጋር መስራት (በርሱ መጠቀም) እንደማይችል ከተረዳ በኋላ ‹‹ኦሮሞን የሚወክል ‹አሻንጉሊት› ድርጅት መመስረት›› የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የትጥቅ ትግሉ እየተስፋፋ በመሄዱ ከትግራይ አልፎ ወደሌሎች የሀገሪቱ ከተሞችም ይሳብ ዘንድ የግድ ኦሮምኛ ተናጋሪ ድርጅት በማስፈለጉ ነው፤ እናም የኦሮሞ ተወላጆች የሆኑ ታጋዮችን ያስሱ ጀመር፡፡ በአሰሳውም የደርግ ወታደር ሆነው በተሰለፉበት ግንባር በሻዕቢያ ተማርከው በኋላ ለኢህዴን የተሰጡ ጥቂት ኦሮሞዎች ተገኙ፡፡ እነዚህን ኦሮሞዎች በወቅቱ ከሻዕቢያ የምርኮኛ ማጎሪያ ያመጧቸው የኢህዴን የወቅቱ ሊቀመንበር ያሬድ ጥበቡ ሁኔታውን ለዚህ ፅሁፍ ሲገልፁ ‹‹እ.አ.አ. በ1983 ዓ.ም ትህሳስ ወር ወደኤርትራ ከታደሰ ጥንቅሹ ጋር ሄድን፤ በጊዜው ‹የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር /ሻዕቢያ/› ሊቀመንበር የነበረውን ሮመዳን መሀመድ ኑርን አገኘሁትና የጦር ምርኮኞችን መጎብኘት እንደምፈልግ ጠይቀው ተፈቀደልኝ፡፡ በወቅቱ ወደዘጠኝ ሺህ ምርኮኞች በእጃቸው ላይ ነበሩ፡፡ መንገድና ድልድይ ያሰሯቸው ነበር፡፡ እኔም ለእነዚህ ምርኮኞች ስለኢህዴን ማብራሪያ ሰጠኋቸው፡፡ አብዛኞዎቹም ትግሉን ለመቀላቀል በጣም እንደሚፈልጉ ነገሩኝ፡፡ እንደገና ተመልሼ ሮመዳንን አገኘሁትና ከምርኮኞቹ ውስጥ ከእኛ ጋር መታገል የሚፈልጉትን ይዤ ለመሄድ እንደምፈልግ አስረዳሁት… ህዝባዊ ግንባር በሃሳቡ ተስማምቶ ይዣቸው ለምሄደው 300 ምርኮኞች፣ 300 ክላሽንኮቭ መሳሪያ፣ ጥቂት PRC77 የረጅም ርቀት መገናኛ ራዲዮ እና ከ100 ሺህ በላይ ጥይቶችን እንደሚሰጠን ነገረን፤…በዚህ ሁኔታ ነበር የኦህዴድ መስራቾች ኢህዴንን የተቀላቀሉት፤ በደንብ የሰለጠኑ ወታደሮች ነበሩ፣ ልዩ ችሎታም ያላቸው ነበሩበት፤ ጀነራል ባጫ ደበሌ ኃበዝ ጊታርና ኪቦርድ ከመጫወቱም በላይ የኦሮምኛ ዘፈን ይዘፍንልን ነበር፤ ከመሀላቸው በሻዕቢያ ዕስር ቤት ሳሉ ፉርኖ ዳቦ መጋገር የለመዱ ነበሩና ለእኛም ይጋግሩልን ነበር›› በዚህ ቀመር መሰረት በ1982 ዓ.ም. በኢህዴን/ኢህአዴግ ውስጥ ሆነው በትግል ሜዳ የነበሩ የኦሮሞ ተወላጆች ተሰባስበው እንዲደራጁ ተደረገና ‹‹የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኦህዴድ/›› ተመሰረተ፡፡ ኩማ ደመቅሳ፣ አባዱላ ገመዳ፣ ባጫ ደበሌ፣ ዮናታን ዲቢሳ፣ ዲሪባ ሀረቆ…

…ኦህዴድ ዘንድሮ በወረሃ መጋቢት ሃያ ሶስተኛ ዓመት የምስረታ በአሉን ያከብራል፡፡ በድህረ-መለስ ዜናዊ የፖለቲካው ርዕሰ ጉዳይ ከሆኑት መሀከልም አንዱ መሆን ችሏል፡፡ ኦህዴድ ለሶስት ተከፈለ (በአባዱላ ገመዳ፣ በኩማ ደመቅሳ እና በጁነዲን ሳዶ የቡድን አባትነት) ከሚለው አንስቶ የኦህዴድ አመራር ‹‹የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቦታ ለእኛ ነው የሚገባን›› በሚል በኢህአዴግ ውስጥ ልዩነት ፈጠሩ እስከሚለው ወሬ ድረስ እየተሰማ ነው፡፡ ሁናቴውን ይበልጥ ያከረረው ደግሞ ባለፈው ሳምንት በአሜሪካ ድምፅ የኦሮምኛ ፕሮግራም ላይ ድምፃቸውን ቀይረው ቀርበው የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነኝ ያሉት ግለሰብ ‹‹የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቦታ ለእኛ ነው የሚገባው›› ማለታቸው ነው፡፡ ወሬው እውነት ከሆነ ወይም ንግሩ ከስመረ በቅርቡ ‹‹ሶስተኛውን አብዮት›› የማየት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ይህ አይነቱ የፖለቲካ ጥያቄ ለኦህዴድ አዲስና ያልተለመደ ነው፡፡ ኦህዴድ የተመሰረተው የራሳቸውን የፖለቲካ አጀንዳ ባነገቡ ታጋዮች ካለመሆኑም በላይ ያለፉትን ሃያ አንድ የስልጣን አመት የራሱ የሆነ የፖለቲካ ቁመና ለመያዝ አልታደለም፡፡ በእርግጥ የኦህዴድ ችግር ይህ ብቻ አይደለም፤ ከኦነግ ጋር በተያያዘ ብዙ ሺ የኦሮሞ ተወላጆች ወደእስር ቤት ሲላኩና እንደወጡ ሲቀሩ ‹‹በህግ አምላክ›› ብሎ ከመቃወም ይልቅ መንገድ መሪና ዋነኛ ተዋናይ መሆኑ ነው፡፡ ጳውሎስ ሚልኪያስ የተባሉ የፖለቲካ ተንታኝ በአንድ ጥናታቸው ኦህዴድ የተመሰረተበትን ምክንያት የገለፁት "The TPLF leadership to utilized it as a Trojan horse" (የህወሓት አመራር እንደ ትሮይ ፈረስ ሊጠቀምበት ፈልጎ ነው) በማለት ነው፡፡

ይህንን ሁኔታ ይበልጥ የሚያጠናክረው ኦህዴድ በነቢብ ያነሳቸው (እንዲያነሳቸው የተደረገው) ጥያቄዎች ከመገንጠል በቀር በሙሉ ኦነግ አስቀድሞ ያነሳቸውና የኦሮሞ ተወላጆችን ልብ ማማለል የቻሉባቸው ብቻ ተመርጠው መሆናቸው ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የድርጅቱ ባንዲራ ሳይቀር ከኦነግ ጋር እንዲመሳሰል ተደርጓል፡፡ ዛሬ ኦህዴድ የሚያስተዳድረው የኦሮሚያ ክልል መጠሪያ ቃል ስረው ግንዱ ራሱ ኦነግ ነው፤ ምክንያቱም ‹‹ኦሮሚያ›› የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በስራ ላይ የዋለው ኦነግ እ.አ.አ በ1974 ዓ.ም በህቡዕ በበተነው ‹‹The voice under tyranny›› በሚለው ፅሁፍ ላይ ከተጠቀመበት በኋላ ነውና፡፡ የቀቤ ክርክርንም በማራመድ የሚታወቀው ኦነግ ነበር (ጀማሪው ሀይሌ ፊዳ ቢሆንም ቅሉ)፤ እነዚህ ‹‹በነበዝ ተማሪ›› ተሰርተው ለኦህዴድ የተሰጡ የቤት ስራዎች የመጀመሪያና የመጨረሻ ግባቸው ከድል በኋላ ‹‹ኦነግን ከኦሮሚያ ክልል ማስወጣት›› የሚለውን የህወሓትን ያደረ አላማ ማሳካት ብቻ በመሆኑ ግባቸውን ከመቱ በኋላ ጥያቄዎቹ በኢህአዴግ መዝገብ ቤት በሰላም ያርፉ ዘንድ ተደርገዋል፡፡ ኦህዴድም ቢሆን ሲጀመርም ከእነዚህ ጥያቄዎች ጋር ዝምድና ስለሌለው ‹‹ከወዴት ደረሱ?›› ብሎ የጠየቀበትና ያፈላለገበት ሁኔታ የለም፡፡ ለዚህም መሰለኝ መለስ በ1986 ዓ.ም የኦህዴድ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ‹‹ከኦሮሞ ጋር ለመገናኘት ህልም ነበረን፡፡ ተሳክቶልናል በቁጥር አነስተኛ ነበሩ፡፡ የትግል ልምድ አልነበራቸውም፤ የኃይል ምንጩ መሳሪያ ወይም ቁጥር አልነበረም፡፡ አብዮታዊ

ወደ ገፅ 20 ዞሯል



# አቶ ስብሐትና የተንኮል ፖለቲካ

ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም

አቶ ስብሐት ነጋ ሙሉ ነፃነቱን የሚወድ ሰው መሆኑን አደንቅለታለሁ፤ አስቦም ይሁን ሳያስብ እንደልቡ የመናገር ባሕርይ አለው፤ በበኩሌ ይህንን ባሕርዩንና በመብቱ መጠቀሙን አከብርለታለሁ፤ ሀሳቡ የተሳሳተ ይሁንም አይሁንም፣ እኔ የምስማማበት ሆነ አልሆነም፣ እኔ ልቀበለውም አልቀበለው ስብሐት ነጋ በሙሉ ነጻነቱ ተጠቅሞ ሀሳቡን ሁሉ መግለጹን አከብርለታለሁ፤ እሱም የእኔን ሀሳብ የመግለጽ ነፃነት እንደሚያከብርልኝና እንደሚያስከብርልኝ ተስፋ አለኝ፤ ከዚያም በላይ ነፃነት ሁልጊዜም፣ የትም ቦታ ከኃላፊነት ጋር የተቆራኘ መሆኑን እንድንገነዘብ ያሻል፤ ኃላፊነት የሌለበት ነፃነት የለም፣ ኃላፊነት የሌለበት ነፃነት ስሙ ሌላ ነው።

በቅርቡ አቶ ስብሐት በአደረገው ቃለ መጠይቅ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የተሾመው ወያኔ ዱሮም አስቦበት ወንበሩን ከአማርኛ ተናጋሪዎችና ከኦርቶዶክስ አማኞች ለማጽዳት በተዘጋጀበት እቅድ ነበር ብሎአል፤ ልብ ላለው አነጋገሩ በሁለት በኩል ስለት ያለው ቂል የያዘው ሰይፍ ነው፤ ከፊት ለፊት የተሰነዘረው አማርኛ ተናጋሪውንና የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን አማኙን ለመምተር ነው፤ ቂል የሚያደርገው አማራ የሚባል ጎሣ ቢኖርም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት በአማርኛ ተናጋሪዎች ታጥሮ ትግሬንና ኦሮሞን፣ ወላይታንና ጉራጌን፣ ሌሎችንም የማይነካ መስሎት ከባድ ስሕተት ላይ መውደቁ ነው፤ ከሁሉም በላይ እሱን የሚያህል ሰው የተክለ ሃይማኖትን ታሪክ አለማወቁ ያሳዝናል።

አማራንና የኦርቶዶክስ ተከታዮችን መትሮ ሲመለስ ደግሞ ሰይፉ የሚቀላው ወላይታንና ጴንጤነትን፣ ምናልባትም እስልምናን ይሆናል፤ አማራን ለመምተር ተነሥቶ ሌላውን ስንቱን ቀላው! እስልምናን በጥርጣሬ ያስገባሁት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስላም ነው የሚባል ያልተጣራ ወሬ በመስማቴ ነው።

አቶ ስብሐት በፊት ለፊት የተናገረው ገና የዛሬ ሃያ አንድ ዓመት «እንዳያንሰራራ አድርገን አከርካሪቱን እንሰብረዋለን›› ተብሎ ያለቀለትን አማራ ዛሬ ወንበር ማጣቱን ለማብሰር አልነበረም፤ ይህ በጣም ግልፅና ከማንም ያልተሰወረ እውነት ነበር፤ ስውር ዓላማም አለው፤ ያንን ብዙ ሰው አይገነዘበውም ይሆናል፤ በአቶ ስብሐት አነጋገር ውስጥ ዋናውና ተንኮልን ያዘለው ዓላማ ወንበሩን የያዘው ዋናው የወላይታ ጴንጤ ሲሆን ምክትሉ ደግሞ እስላም መሆናቸውን ለመናገር ያለው ፍላጎት ላይ ነው፤ ከአቶ ስብሐት ነጋ በቀር የአዲሶቹን ሹሞች ዘርና ሃይማኖት ከጉዳይ ያስገባ ያለ አይመስለኝም፤ አቶ ስብሐት በፊት-ለፊት ዓላማው ተስፈንጣሪ ተራማጅ ሲመስል በስውሩ የተንኮል ዓላማው ግን ኋላ-ቀር ወግ-አጥባቂ ይሆናል፤ በዘርና በሃይማኖት ላይ ሲያተኩር ዋናውን ቁም-ነገር ጠቅላይ ሚኒስትሩና ምክትሉ ሰዎች፣ ከዚያም ቀጥሎ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ፈጽሞ ዘንግቶታል፤ ለእኛ ትልቁ ነገር ይህ ነው፤ በሁለታችን መሀከል ያለው ልዩነት ስብሐት ኢትዮጵያውያንን የሚያዛምዳቸውን ሁሉ አያይም፤ እኔ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን የሚለያያቸውን ሁሉ አላይም።

ለነገሩ ስብሐት ነጋ በራሱ ስም ብቻ የተናገረ አይመስለኝም፤ በግሉ እንዲህ ያለ የአገር አመራር ጉዳይ የሚናገር አይመስለኝም፤ በምስጢር የተያዘ የወያኔ/ኢህአዴግ ዓላማ ነበረ ማለት ከሆነ የገዢው ፓርቲ ለኢትዮጵያ ያለውን እኩይና ከፋፋይ እቅድ በግልጽ ያመለክታል፤ የገዢው ፓርቲ ቃል አቀባይ ካላስተባበለ በቀር ይህንን አፈትልኮ የወጣ ምሥጢር የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ሊያውቀው ይገባል፤

> ...የአቶ ኃይለማርያም ቃለ-መጠይቅ ትዝ አለኝ፤ ‹‹ገና ስላልዳነች ለእናቴ እጸልይላታለሁ›› ይላል፤ ክርስትና አስነሥተው ኃይለማርያም የሚል የክርስትና ስም (የኔም የክርስትና ስም ያው ነው፤) ያስሰጡትን እናቱን ‹‹አልዳነችም›› ማለት ክርክር ያስነሣል፤ ነገር ግን አስተሳሰቡ በእናቱ የሚቀር አይመስለኝም...

ከዚህ በፊት የነበሩት ሁለት ጠቅላይ ሚኒስትሮች ጎሣቸው ምን ነበረ? ሃይማኖታቸውስ? የቀድሞው ፕሬዚደንት ሃይማኖቱ ምን ነበረ? ለምን አቶ ስብሐት የእነዚህን ጎሣና ሃይማኖት አልነገረንም? ከስብሐት የተለየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ከዚህ በፊት የነበሩትንም ሆነ አሁንም ያሉትን ባለወንበሮች ኢትዮጵያውያን አድርገው ይመለከቷቸዋል፤ ሃይማኖታቸውን አምላካቸው ይጠይቃቸው።

እዚህ ላይ የአቶ ኃይለማርያም ቃለ-መጠይቅ ትዝ አለኝ፤ ‹‹ገና ስላልዳነች ለእናቴ እጸልይላታለሁ›› ይላል፤ ክርስትና አስነሥተው ኃይለማርያም የሚል የክርስትና ስም (የኔም የክርስትና ስም ያው ነው፤) ያስሰጡትን እናቱን ‹‹አልዳነችም›› ማለት ክርክር ያስነሣል፤ ነገር ግን አስተሳሰቡ በእናቱ የሚቀር አይመስለኝም፤ በአቶ ኃይለማርያም ሃይማኖት ያላመነ ሁሉ የመንግሥተ ሰማያት በር ተዘግቶበታል ወደሚል መደምደሚያ የሚያመራ ይመስላል፤ በዓለም ታሪክ ውስጥ ብዙ ችግሮችንና ጦርነቶችን የፈጠሩ ሰዎች የአምላክ ልዩ መልክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን መሆናቸውን ያወጁ ናቸው፤ ስለዚህም ‹‹እናቴ አልዳነችም›› ማለት ያሰጋል፤ ያስፈራል፤ በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ስም ሲጠራበት ባልሰማንበት ወንበር ላይ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ፣ ከሱ በላይ ሆኖ ፍርድ የሚሰጥ አምላክ መኖሩን የሚያምን ሰው መቀመጡ አንድ እርምጃ ነው፤ አዲሶቹ ሹሞች ለእግዚአብሔር የሚገዙ፣ ለሕጋዊ ሥርዓት የቆሙ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከ‹‹መንግሥት ሌቦች›› የሚያድኑ እንዲሆኑ የእውነትን ኃይልና የኅሊና ብርታት እግዚአብሔር ይስጣቸው።



ዓለማየሁ ገላጋይ

# ይድረስ ‹‹ለባለቅኔ›› በረከት ስምኦን

ለባለቅኔ በረከት ስምኦን…

…‹‹ባለቅኔ›› ስልዎ ጥቂት ግር እንደሚሰኙ እገምታለሁ፡፡ እንደእኔ፣ እንደእኔ ባለቅኔነት የየቀልብና የየስሜታችን ግለሰባዊ ብያኔ እንጂ የአገልግሎት ብዛት የሚያስገኘው የስምምነት ማዕረግ አይደለም፡፡ እርስዎ ለእኔ በአንዲት ግጥምዎ ባለቅኔዬ ሆነዋል ብል መመዘኛነቱ የእኔ እንጂ የሌላ ሰው ሊሆን አይችልም፡፡ ባለቅኔነትዎ ለእኔ ነዋ!

የእርስዎን ግጥም ከማቅረቤ በፊት አንዲት ግጥም ያላትን ዋጋ በህንዳዊው ባለቅኔ በካቢር አስደግፌ ላሳይ፡፡ ካቢር ህይወቱን ሙሉ ተቆጥሮ የማይዘለቅ የተፈጥሮ-መወድስ ግጥሞችን ፅፏል፡፡ ይሁንና መላ-ዕድሜውን ጠቅልላ የያዘችው አንዲት ባለሁለት ስንኝ ግጥም ናት፡፡ የግጥሟን የመጀመሪያ ስንኝ የፃፋት ወጣት ሳለ ነበር፡፡ እንዲህ ትላለች፡-

‹‹ትንሽ ጠብታ
ጠፋች ከባህር ገብታ››

ካቢር ይቺ ግጥም በእንጥልጥል እንደቀረች ይሰማው ስለነበር ህይወቱን ሙሉ ሲያንቀራብጣት ኖረ ይባላል፡፡ በመጨረሻ በአልጋ ቁራኛ ተይዞ ለመሞት ደቂቃዎች ሲቀሩት ትልቁን ልጁን አስጠራው፡፡

‹‹አቤት?››

‹‹ያቺን ግጥሜን አስተካክልልኝ ከስር እንዲህ የሚል ስንኝ አክልበት፡-

‹‹ያቺው ጠብታ ነች
ባህሩን ውጣ ያስቀረች›› በልልኝ፡፡

ይሄን ተናግሮ ወዲያው ህይወቱ አለፈች፡፡ ቅኔዋ የካቢር ከፈን ነበረች፡፡ ተጠቅልሎባት ኖረ፣ ተጠቅልሎባት ሞተ፡፡ ካቢር ይቺን ግጥም ብቻ የፃፈ ቢሆን ኖሮ ባለቅኔ ሳንለው ልንቀር ኖሯልን? አይመስለኝም፡፡ እንደውም ካቢር ለእኔ ባለቅኔ የሆነው በዚ ነጠላ ስራው ብቻ ነው፡፡ እንደእርስዎ!

የእርስዎም ግጥም የዋዛ አይደለችምና ‹‹ባለቅኔ ነዎት›› ማለቴ አይደበዝዝብኝም የሚል ተስፋ አለኝ፡፡ እንደ ካቢር ቅኔ ባለሁለት ስንኝ የሆነችው ግጥምዎን ያገኘኋት ‹‹ሶረኔ›› የተሰኘ መጽሐፍ ላይ በሰማኒያዎቹ መገባደጃ ላይ ነው፡፡ ግጥሟ እንደተዋጣለት ሰላይ ደብዛዋን አጥፍታ፣ ምንጯን አድበስብሳ ነበር ‹‹ሶረኔ›› ላይ የወጣችው፡፡ ማለቴ የእርስዎ መሆኗ ሳይገለፅ፤ ስምዎን ሳታገለድም መለመላዋን ለተደራሲ እይታ ተጋለጠች፡፡ ‹‹የማነች?›› የወቅቱ ጥያቄያችን ነበር፡፡ ከሁለት ይሁን ከሶስት አመታት በኋላ ሁነኛ ሰው አግኝተን ግጥሟ የእርስዎ መሆኗን አረጋገጥን፡፡ ያኔ ስለእርስዎ የነበረን ግምት እንደማሽላ እንጀራ እምሽክሽክ ብሎ ከእጃችን ጠፋ፡፡ ፊትዎና ንግግርዎ ውስጥ ደም የማይረጭ፣ህያውነት የተነፈገ ልብ ይታየን ስለነበር፤ ግጥሟ ከርሶ መመንጨቷን ስንሰማ ድንጋሬ ቢመታን አይፈረድብንም፡፡ እንደምን እርስዎ ልብ ላይ ፍቅርና ናፍቆት በቀሉ? አሁንም ጥያቄአችን ቢሆን አይፈረድብንም፡፡ ለማንኛውም ግጥሟ ይቺ ናት፤

እንደተፋቀርን ሳንተያይ - ሳንተያይም ልንፋቀር፣
እንደመናን ካለም ነገር - ከስሙ-ተራ ስንባረር፣
በታጋይ ህግ ተገድበን - በአጉል ሥርዓት ስንጠፈር፣
መቸስ ምን እንላለን - በተስፋ ከመሞት በቀር፤

ግጥሟ የነባራዊ ሁነት ቋሚ ላይ ተጠምጥማ የምትለመልም የሐረግ ህልውና ያላት ቅኔ ናት፡፡ ብቻዋን መሬት ለመሬት ትሳብ እንደሆን እንጂ ቆሞ የመስተዋል ዕድል አይኖራትም፡፡ ነባራዊ ሁነቱ የትጥቅ ትግል ዘመን ነው፡፡ ታጋዮች እርስ-በእርሳቸው ፆታዊ ፍቅር ሆነ ጉድኝት እንዳይኖራቸው በጥብቅ የተከለከሉበት ወቅት ባለቅኔ በረከት ልቡና ላይ አርፎ ያቆጠቆጠው ተሃዝቦ ለግጥሟ ህልውናዋ ሆኗል፡፡ የግጥሟ መልእክት ከቁጭትና ከመብከንከን ድሪያ ቢወለድም እንደፉከራ ከርሮ ሳይሆን በጠባዩ ለዝቦና ለስልሶ የወላጆቹ ልጅ መሆኑን ያስተናል፡፡ የሚገርመው ደግሞ ልዝብነቱና ልስላሴው ከፍርሃት ሳይሆን ከድፍረት መገኘቱ ነው፡፡ ባለቅኔው (ተራኪው) የቆመለትን ዓላማ የሚያስፈፅመውን ህግ ‹‹አጉል ጠፋሪ ስርዓት›› አድርጐ ለመፈረጅ ፍርሃት አልሸበበውም፡፡ እንደውም ከተገቢው በላይ ደፍሯል ማለት ይቻላል፡፡ ግጥሟ ላይ ታጋዮቹ የአለማዊ ህይወት ‹‹አዳምና ሄዋን›› ሆነው ከሥጋዊው የፍቅር ዕድቅ፣ በምድራዊው መልአክ (የትግል ህግና ስርዓት) ሲባረሩ ምስል ትከስትልናለች…

ይሄንና ሌላውንም ምክንያቴን ዋቢ አድርጌ፣ የበረከት ስምኦንን ባለቅኔነት ብቀበል የሚያስፈርድብኝ ጥፋት ሆኖ አይታየኝም፡፡ እንደውም ትግሉና ስልጣኑ ገዳፍ (እንቅፋት) ባይሆንብዎ ባለቅኔነትዎ ካሉንና ከነበሩን ገጣሚዎች ጋር የሚያወዳድርዎ በሆነ ነበር እላለሁ፡፡ ግን ምን ይሆናል? እንደ ካርል ማርክስና እንደማኦ ሴቱንግ ሁሉ የእርስዎም ባለቅኔነት ትግልና ስልጣን ጥልቅ ውስጥ ተጣለ፡፡

ባለቅኔ በረከት ስምኦን…

…ከትግልና ከስልጣን ጥልቅ አምልጠው የወጡ ሌሎች ጥቂት ቅኔዎች እንዳልዎት ስጠረጥር ኖሬአለሁ፡፡ ይሁንና እንደባሪያ ድንግል ተድበስብሰው ከቀሩ ቅኔዎችዎ ቀድሞ ሌላ የህይወት ቅኔዎ ደረሰኝ፡፡ የዚህ ደብዳቤ መነሻም ይሄ የህይወት ቅኔዎ ነው፡፡ የህይወት ቅኔዎን ፍንጭ ያገኘሁት ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› የተሰኘው መጽሐፍዎ ሲታተም ነው፡፡ በመጀመሪያ በ2003 ዓ.ም. ብቻ ሳይሆን አሁን በቅርቡ ሁለተኛ ህትመት ያዘዙት ከኢትዮጵያ ሸሽተው ኬንያ ነው አሉ፡፡ ኢትዮጵያ እኮ ህልምዎ ናት፣ ኢትዮጵያ እኮ የገዛ ፍላጐትዎ የፈጠራት ቅገርት ናት፡፡ ታዲያ ከገዛ ህልም ይሸሻል? የገዛ ፍላጐት ካስገኘው ቅገርት ይመለጣል?...

እርግጥ አይካድም፤ ኢትዮጵያ የህትመት ብቻ ሳይሆን የኑሮም ረመጥ ናት፡፡ ታዲያ ማን ባጋማት ማን ይጠበስባት ብለው ሸሿት? ይሄ የህይወት ቅኔዎ አንድ በውል ያላወኩትን የትግል አጋርዎን ግጥም አስታወሰኝ፡፡ ግጥሙ ለኢህአፓ የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ ርዕሱ ‹‹ሞናሊዛ›› ነው፡፡

‹‹…አንተ ሊዎናርዶ የሮማ ልጅ
የሰራሃትን ልታሻሽል
ልታፈርሳት ልትገነባት
ደግመህ ደጋግመህ ልትሰራት
ሰልስህ ልትሰራ ስትችል
ጣዖት አደረግካት በሞትህ አጉል
አጉል
ለራስህ ፍጡር እግዚኦ ልትል
…የሮማ የዋህ ሰው ሊዎናርዶ
በፍቅር ትንታግ ተማግዶ
የቀረፀውን አጉል ወድዶ
ራሱን በራሱ ንዶ---ርዶ--- የሚል፡፡

የእርስዎ የህይወት ቅኔ የዚህ ተቃራኒው ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተፀፀተ እንደተባለ እርስዎም በኢትዮጵያ ሳይፀፀቱ እንዳልቀሩ ነው የህይወት ቅኔዎ የሚመሰክረው፡፡ ይሄንኑ የ‹‹ሞናሊዛ››ን ላህይ ተከትለን የእርስዎን የህይወት ቅኔ እንግለጠው ብንል፡-

…ሰልስህ ልትሰራ ስትችል
እርግፍ አደረግካት በሽሽትህ
አጉል-አጉል
በራስህ ፍጡር እግዚኦ ልትል
…የሮማ የዋህ ሰው ሊዎናርዶ
በህልም ትንታግ ተሞልቶ
የፈጠረውን አጉል ጠልቶ
እራሱን በራሱ ሸሽቶ…

እርግጥ አይካድም፣ ኬንያ የህትመት ብቻ ሳይሆን የኑሮ ርካሽነቷ ከኢትዮጵያ በእጥፍ እጥፍ ዝቅ ይላል፡፡ ለዚህ የህትመትም ሆነ የኑሮ ርካሽነት አንድ ኢትዮጵያዊ ቢማልል አይፈረድበትም፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያን በዚህ መልኩ ለሰራትና ለገነባት ብቻ ሳይሆን ሊያሻሽላትና ሊያፈርሳት በሚችል እንደርስዎ ባለግለሰብ ሸሽቱ ሲከናወን የሥነ-ምግባር ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ኮልኩለው፣ ኮልኩለው ባሳበዷት መኪና (ኢትዮጵያ) ላይ የተሳፈርነውን፣ ዕጣ-ፈንታችን መሆኑን አምነን ሳይሆን ተገደን የተቀበልነውን እኛን ባለንበት ሁኔታ ሹፍርናዎን ጥለው እንደመውረድ ያለ ድርጊት ነው የሰሩት፡፡ እኛስ? ይሄን በእርስዎ ሹፍርና ያበደ መኪና (አገር) ጥለን የት እንሂድ?

እንዳልኩት ኢትዮጵያ ላይ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ኬንያን ለሚመለከት ያቺ ጎረቤት አገር ታማልላለች፡፡ የዶሮ አርስቶ 16 ሽልንግ ዋጋ አለው አሉ፡፡ በእኛ ወደ ሁለት ብር ከስድሳ ሳንቲም ማለት ነው፡፡ ይሄ የኬንያውያን አኗኗር በኛ በኢትዮጵያውያን አኗኗር ሲተረጎም ወደ ኋላ አሽቀንጥሮ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ላይ ያደርሰናል፡፡ አፕልና ወይን ጨምሮ ሌሎች ፍራፍሬዎች የደሃ ኬንያውያን መተከዣዎች ናቸው አሉ፡፡ እኛ አገር ቅቅል በቆሎና ቆሎ እንኳን ደሃ-አይደርስብሽ ምግብ ከሆኑ ሰነባብተዋል፡፡ እኛ ዘንድ አንድ ኮስማና በቆሎ መንገድ ዳር ተጠብሶ ስንት እንደሚሸጥ ያውቃሉ? ከሦስት ብር ከሃምሳ እስከ አራት ብር፡፡ ኬንያ ሄደን አንድ ብር ከ20 ሳንቲም ብንጨምር፤ የእኛዋ ጉስቋል ጉዳና ተዳዳሪ በቆሎ የሁለት ዶሮ አርስቶ ጌታ ትሆናለች፡፡ እርስዎና ጓዶችዎ በዚ አገር ላይ አስማት ነው የሰራችሁት ማለት ይቻላል፡፡ እንዴት አስባችሁ፣ እንዲህ ተሳካላችሁ? እውነትን ወደ ቅዠትነት የመለወጥ ተአምር ነው የሰራችሁት፡፡

እና ይኸውልዎ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ እርስዎ ባለቤቱ ያቀለሉትን አሞሌ እኛ ባለዕዳዎች እንቀበል ዘንድ ግድ ሆኖብናል፡፡ የግፍ ዘመን ነውና ምን እናድርጋለን? እርስዎ ወላጅዋ የሸሸዋትን ኢትዮጵያ እኛ ባለዕዳዎቹ እናዝላለን፣ እሹሩሩ እንላለን፣ እናጠባለን…

ባለቅኔ በረከት ስምኦን…

…ከጥበባዊ ቅኔዎ፣ ህይወታዊ ሰምናወርቅዎ ገዘፈ መሰል? መጽሐፍዎን ኬንያ ማሳተምዎ ሌጣውን ይሄን ያህል አያናግር ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ድርጊትዎ ጀርባ እንደ ውቅያኖስ ውስጥ የበረዶ ተራራ ጫፍ ኢምንት የሆነው ችግር ውስጥ-ውስጡን የመንሰራፋቱ ምክንያት ስለሆነብኝ ነው፡፡ እርስዎ ለሃምሳና ስድሳ ሺህ ብር ትርፍ በመጽሐፍዎ የሸሿትን ኢትዮጵያ እኛ በኑሮና በሕይወት እየተቤዠናት አለን፡፡ ረሃብና እርዛታችንን እንደቦረንትቻ እየቀለብን አብረናት እንኖራለን፡፡ ደግነቱ ኑሯችን ወደ ‹‹ተስፋይቱ ምድር›› የሚደረግ ጉዞ እንደሆነ እየተነገረን ነው፡፡ ቢሆን እንኳ ‹‹ገብስ የሚደርሰው ለፍልሰታ፣ እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ›› እንዳለው ገበሬ ያለ ዕጣ-ፈንታ ውስጥ ነን፡፡

በእናንተ ዘንድ እኛ ሲያጥቡን የሚያለቅስ ጨቅላ አይነት ነን፡፡ እርግጥ ነው፤ በዘመን አመጣሽ ዋግምትዎ እየታከምን ሊሆን ይችላል፡፡ ስንታገም ደም እየፈሰሰን እንደምንታከምም እናውቃለን፡፡ የእርስዎና ጓዶችዎ ማገም ግን ከደም በላይ ቅስምና ጅስም የሚያፈስ ሆነ፡፡ ከቅዠት የሚቆጠረው እውነታችን እናንተን አስፈሪ ተዋናይ እያደረገ ማቅረብ ከጀመረ ሰነባበተ፡፡ እርግጠኛ ነኝ እርስዎም ህልም ውስጥ እኛ አስፈሪ ገፀባህርይ ሆነናል፡፡ የህይወት ቅኔዎ የሚመነጨው ከዚህ ይሆን? በሰበብ ባስባቡ ውጭውን የመማተር ድብቅ ሽሽትዎስ ?ይሆን ይሆናል!!



# የ"አዲሱ መንግስት" ተግዳሮት እና የአቶ ኃይለማሪያም አጣብቂኝ

*ዘሪሁን ተስፋዬ*
*(የቀድሞ የአዲስ ነገር ጋዜጣ ባልደረባ)*

መስከረም 2፤ 2005 ዓ.ም ሎንዶን:: ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ የተወከሉ ባለስልጣናት የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተናል ከሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች፣ ጋዜጠኞች እና የምሥራቅ አፍሪካ ፖለቲካ ተወካይ ግለሰቦች ጋር ለውይይት ተቀምጠዋል:: ወቅቱ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ማን ይተካ ይኾን የሚለው ጉዳይ የሚብሰለሰልበት ነበር:: በርግጥ ለእንግሊዝ ተወካዮች የሚያብሰለስል ጉዳይ አልነበረም፤ ምስጢራቸውን በልባቸው ሸሽገው ከባለሞያዎቹ ተጨማሪ ሃሳቦችን ይሰበስባሉ:: ሁሉም ባለድርሻ የሚመስለውን እና ጥናቱ ያመላከተውን ሐሳብ ሰነዘረ:: ተንታኞችን በሚያስማማ መልኩ የአቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ተተኪነት አነጋጋሪ አልነበረም:: በጠቅላይ ሚኒስትር ተተኪ ማንነት ላይ ላይ ጥርጣሬ የነበረው ማንም አልነበረም:: የድሕረ መለስ የፖለቲካ ኹኔታ እንዲሁ ትኩረት ያገኘ ነበር::

የተለየ ጉዳይ የተከሰተው ግን ተሳታፊዎች ውይይታቸውን አጠናቀው በሻይ ሰዓት የግል ጭውውት ሲያደርጉ ነበር:: የውጭ ጉዳይ ተወካዮቹ የያዟትን ምስጢር ለመተንፈስ እድል ያገኙ መሰሉ:: ከእንግሊዝ ተወካዮች መካከል አንዱ የምስራቅ አፍሪካን ፖለቲካ አብጠርጥሮ ያውቃል ብለው ወደገመቱት የፖለቲካ ባለሞያ ቀረብ ብለው "ስለ ደመቀ መኮንን የምታውቀውን ንገረኝ?" አሉት:: ለዓመታት የምሥራቅ አፍሪካን የፖለቲካ ግለት ሲለካ ለነበረው ባለሞያ ጥያቄው ዱብ ዕዳ ብቻ ሳይኾን፤ በአዲስ አበባ ከተማ በአንድ ቀበሌ ስለሚኖር አንድ ተራ ግለሰብ ዝርዝር ጉዳይ የመጠየቅ ጉዳይ ኾኖ ተሰማው:: ስለአቶ ደመቀ የሚያውቀው ጉዳይ ቢኖርም ለበሰለ የፖለቲካ ተዋስኦ የሚበቃ አልነበረም:: መረጃ በሌለው ጉዳይ ላይ ዝምታን ቢመርጥም ጉዳዩ ከንክኖት ስለነበር በተራው ጠያቂ ኾነ፤ "ደመቀን በተመለከተ ምን አዲስ ነገር አለ?" ምላሹም በዲፕሎማሲያዊ ቃና የታሸ ነበር:: " [ደመቀ] ቦታ ሳይያዝለት አልቀረም"- አጠር ምጥን ያለ ምላሽ::

ባለሞያው ተጨማሪ ማብራሪያ አላሻውም:: ይልቁንም ነገሮች ከጠበቀው ውጪ እየተራመዱ እንደኾኑ ይበልጥ ግልጽ ኾነው ታዩት:: በእርግጥም የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደወትሮው ሁሉ ከግምት ውጪ የኾኑ ክስተቶችን እያስተናገደ ነበር:: አቶ ደመቀን እንዲህ ላለ ከፍተኛ ስልጣን ማንም የገመተ አልነበረም:: በአብዛኛው የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ማዕረግ ከሕወሓት ወይም ከኦሕዴድ እጅ ያመልጣል የሚል ግምት አልነበረም:: በተለይ ለአመታት «ከስልጣኑ ስገለል ኖሪያለሁ» የሚለው ኦሕዴድ ከስልጣን ቅብብሎሹ ተጋሪ ይኾናል የሚል ዕምነት በብዙዎች ዘንድ ነበር::

ይኹንና የቅርብ ተንታኞችም ኾኑ የአገሬው ዜጋ ሳይሰማ የብአዴን ተወካይ አቶ ደመቀ ትልቁን የሥልጣን እርከን እንደሚቆጣጠሩ እንግሊዞች "ደርሰውበት" ኖሯል:: ከቀናት በኋላም የኾነው ይህ ነበር:: በእነው ማምንት ቅዳሜ ምሽት ኢህአዴግ አቶ ደመቀን የግንባሩ ምክትል ሊቀመንበር አድርጎ "መረጠ":: በእለቱ የተሰራጨው ዜና ለብዙሃኑ የፖለቲካው ነፋስ አቅጣጫ ተንባዮች እና ዜጎች አዲስ ቢኾንም ቀመሩን ለሠሩት ለአሜሪካ፣ ለእንግሊዝ፣ ለአቶ ስዩም መስፍን እና ለአቶ በረከት ስምዖን ግን የቤት ሥራው በወጉ መጠናቀቁን "የሚያበስር" ነበር:: "ቦታ ሳይያዝለት አልቀረም" የምትለዋ ዲፕሎማሲያዊ ሐረግም ፍቺዋን አገኘች::

ምስጢራዊነት ትልቁ የፖለቲካው ማቀንቀኛ መድረኩ የኾነ የፖለቲካ አመራር ሥፍራውን በተቆጣጠረበት አገር ግምቶች ሁሉ ፋርሽ ናቸው:: ኢህአዴግ እና ምስጢረኝነት ደግሞ የዘመናት ቁርኝት አላቸው:: ግንባሩ በትጥቅ ትግል ወቅት ስኬታማ ከኾነባቸው መንገዶች አንዱ የኾነውን ጥብቅ የምስጢር ጠባቂነት ወግ የመንግሥት ሥልጣኑንም በእጁ ካስገባባት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሙጥኝ ብሎ ይዟል:: የሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር አልጋ ላይ መዋልን ተከትሎም በተለያዩ የብዙሐን መገናኛ ዘዴዎች ሲወራ የነበረውን "ዜና እረፍት" በዚሁ የምስጢረኝነት ጠባዩ በመጽናናት እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ሲያስተባብል ቆይቷል:: በማስተባበሉ ሂደትም ግንባሩ የሥልጣን ሽግግሩን ጉዳይ አፍኖ ቢይዝም ውስጥ ውስጡን ግን ከለጋሽ አገራት በተለይም ከእንግሊዝ እና አሜሪካ ጋር በመኾን ቀመሩን ሲያሰላ ነበር::

ምስጢራዊነቱ የተዋጣለት ለተባለ ግምት በሩን የከፈተ ስላልነበርም የቀመሩ ስሌት የሕ.ወ.ሓ.ትን የዓመታት የበላይነት ያስወገደ በሚመስል ሁኔታ ለአደባባይ ወሬ በቃ:: የደ.ሕ.ዴ.ን ሊቀመንበር ኃይለማሪያም ደሳለኝን ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም ፍጹም ቦታ አይኖረውም ተብሎ ተግመቶ የነበረው ብ.አ.ዴ.ን አቶ ደመቀ መኮንን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ በማሾም ቀመሩ የ.ሕወ.ሓ.ትን የበላይነት አደብዝዞ አሳየ:: ይህም የተጭበረበረ ምስል የአንድ ብሔር ልሂቃን የበላይነት ለዘመናት ሠፍኖባት ለነበረባት አገር የፖለቲካውን አቅጣጫ ይለውጠው ይኾናል የሚል እምነት በነበራቸው ዜጎች እና በለጋሽ አገራት ዘንድ ትልቅ ስኬት ተደርጎ ተወሰደ:: በርግጥም የበርካታ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስብስብ የኾነው የደቡብ ክልል የሥልጣን ተቋዳሽ መኾኑ፤ እንዲሁም በሥልጣን ክፍፍሉ "ምንም ዓይነት" ሽራፊ ስልጣን ላይኖረው ይችላል ተብሎ ተገምቶ የነበረው የአማራ ክልል "ትልቁን" ድርሻ ማንሳቱ የስልጣን ሽግግሩ ከተገቢ ለውጥ ጋር ተሳሂሏል ለሚሉት ሰዎች ማሳያ ሊኾን ይችላል::

በተለይ ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የሥልጣን ሽግግሩን በአዎንታዊ መልኩ እንዲወስድ ያስገደደው ብሔርን ያማከለው ፌዴራሊዝም አዳዲስ ፊቶችን ከተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች ማካተቱ ነው:: ይኹንና የተለያየ የፖለቲካ ስብዕና የተላበሱ አመራሮች ወደ ሥልጣን መምጣታቸው እና የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ የሥልጣን ሽግግር ሰላማዊ መኾን የአገዛዙን መሠረታዊ መለያ ጠባያት የለወጠ አይደለም:: ይልቁንም በግልጽ የሚታይ የአመራር ክፍተት እና ከሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር የተወረሱ ሕጸጾች የፖለቲካው መለያ ጠባያት ኾነው እንዲቀጥሉ አድርጓል:: አቶ ሃይለማሪያምም በቀላሉ ለመፍታት ከሚቸግሯቸው ተግዳሮቶች ጋር መፋጠጣቸው የግድ ነው::

## ስንኩል አመራር

የአቶ ኃይለማርያም አስተዳደር ከሚገመተው በላይ በጣም ደካማ ነው:: ከመነሻውም ቢኾን የቀድሞ ዋነኛ የሕ.ወ.ሓ.ት እንዲሁም የኢሕአዴግ አመራር አባላትን ይኹንታ ያላገኙት የደቡቡ ሰው፤ ከስሙ በስተቀር የአመራር ብቃታቸውን የሚያሳዩበትን ስልጣን ከእጃቸው አላስገቡም:: አቶ መለስ ዜናዊ ሞት ባይቀድማቸው ቃል እንደገቡት በቀጣዩ ምርጫ ሥልጣናቸውን የማስረከብ ዕድል ቢኖራቸው ኖሮ ምንአልባት ከሕወሓት አፈና መጠነኛ የኾነ መተንፈሻ ያገኙ እንደነበር የተነገረላቸው አቶ ኃይለማሪያም ነጻ የመኾንን ዕድል ተነፍገዋል:: የደህንነት፣ የአገር መከላከያ ሠራዊት እና የአገሪቷን የደህንነት እና ስለላ ሥራ የሚያግዘው የቴሌኮሙኒኬሽን ክፍል አሁንም በሕወሓት እጅ የተያዙ እና ከአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ቁጥጥር ውጪ የኾኑ ናቸው::

በተጨማሪም የውጭ ጉዳይ እንዲሁም የኢኮኖሚ የአማካሪነት ሥፍራዎች ዋነኛ እና ጠንካራ ትግራዋይነትን በሚያቀነቅኑ የሕወሓት አባላት አሁንም የተያዙ ናቸው:: በጉምሩክ፣ በንግድ እና ኢንቨስትመንት ቢሮዎች እና በመካከለኛ የሥልጣን ዕርከን በፌዴራል ቢሮዎች የሚሠሩ የፖለቲካ ሹመኞች በብዛት የሕወሓት አባላት ሲኾኑ የማይገሰስ የበላይነትን ያሰፈኑ ናቸው:: ብዙዎቹም ሥርዓቱ የፈጠረላቸውን አጋጣሚ ተጠቅመው አግባብ ያልኾነ ሐብት ያካበቱ በመኾናቸው በቀላሉ ሥፍራውን ለአዲሱ አመራር ለመልቀቅ የተዘጋጁ አይደሉም:: ከዚህም ባሻገር በአቶ መለስ ቀጥታ አመራር ሥር የነበረው እና ሙሉ ለሙሉ የሕወሓት ቅርጽ እና መልክ የተላበሰው አምስት ሺህ የሚገመተው አግዓዚ ኮማንዶ እጣው ፈንታው ያለየ ሌላው የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራስምታት ነው:: ይህም የአቶ ኃይለማሪያም መንግሥት አሁንም የሕወሓት የበላይነት የሰፈነበትን የፖለቲካ ሥርዓት ከለላ በመኾን ዕድሜ ከማራዘም ተሻግሮ ይህ ነው የሚባል ፋይዳ እንዳያስመዘግብ እንቅፋት ይኾናል::

## ከግለሰብ አምባገነንነት ወደ ቡድን አምባገነንነት

አቶ መለስ ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወዲህ ሕወሓት የሚታወቅበትን "ዴሞክራሲያው ማዕከላዊነትን" አፈር አልብሰው ሲያበቁ በብቸኝነት አመራሩን ተቆናጠው ኖረዋል:: ጠያቂ በሌለበት እንዳሻቸውም ገዝተዋል:: ከትልቁ የፖለቲካ ሥልጣን እስከ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ያለው የሥልጣን ተዋረድ ከእርሳቸው ቁጥጥር ውጭ አልነበረም:: ይህም ታዛዥ እና ተገገር እንጂ በራሱ የሚተማመን አመራርን ለኢሕአዴግ አልፈጠረም:: ከዚህም ባሻገር ሁሉም የኢሕአዴግ አመራር አባላት በሚባል ደረጃ ☞

የሕዝብ ተቀባይነት የሌላቸው ሲኾኑ አንዳንዶቹም መርጦናል ብለው ለሚደሰኩሩለት ማኅበረሰብ ባዕድ ናቸው፡፡

አቶ መለስም ጥለው የሄዱት ኢሕአዴግ ገና ወደ ፖለቲካው መድረክ እንደተቀላቀለ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ በመዳህ ላይ ያለ ነው፡፡ ይህ ኹኔታም አደገኛ መዘዝን ይዞ ነው የመጣው፡፡ ለዘመናት በአንድ ግለሰብ አምባገነንነት ከሚመራ ግንባር የሥልጣን ሽኩቻ ወደበዛበት እና የግለሰቦች ፉክክር ወዳየለበት የአንጃዎች ጥርቅም የግንባሩን ቅርጽ ይለውጠዋል፡፡ "እኔ ከማን አንሼ" የሚለው የፉክክር መንፈስ የፖለቲካውን መድረክ ይቆጣጠረዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ለውጥ የግል ወይም የብሄር ጥቅማቸው ያስተሳሰራቸው በአንድነት ጥላ ሥር የተሰባሰቡ አባላት ብዛት መገለጫው ይኾናል፡፡ ግንባሩም የይስሙላ "አንድነት" ቢኖረውም ልል እና አማካይ የአመራር ሥፍራ እንዳይኖረው ያደርገዋል፡፡

አማካይ ሥፍራ የሌለው አመራር ተጠያቂነትን የሚያዳፍን እና የቡድን አምባገነንነትን የሚያሰፍን ነው፡፡ አቶ ኃለማሪያምም እንዲተውኑ የተሰጣቸውን "ሥልጣን" በአንድ እርምጃ ለማራመድ ቁርጠኝነቱን ለማሳየት እስካሁን አልደፈሩም፡፡ ለመጥቀስ ያህል ሕገ መንግሥቱ የፈቀደላቸውን በቤተ መንግሥት የመኖር መብት እንኳ ለመጠየቅ ድፍረቱን አላገኙም፡፡ ከርሳቸው ይልቅ ከወይዘሮ አዜብ መስፍን ጋር ቅሬታ አላቸው የሚባሉት የሕወሓት አባላት እና አቶ በረከት ስምዖን እመቤቲቱን ለማስወጣት ደፋ ቀና ሲሉ ይስተዋላሉ፡፡ አቶ ኃይለማሪያም ለውሳኔ በዘገዩ እና የተተበተቡበትን ሠንሠለት ለመበጣጠስ በአቅማሙ እና በዘገዩ ቁጥር የአንጃዎቹ መበርታት የያዙትንም ቦታ ሊያሳጣቸው ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የግንባሩ መፍረክረክ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ባለበት አገር እንደ መልካም አጋጣሚ የሚቆጠር ነው፡፡ የተሻለ ታክቲክ በመንደፍ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ አመቺ ነው፡፡ ይኹንና አሁን ባለው ኹኔታ በጥንካሬ የሚጠቀስ ተቃዋሚ በአገር ውስጥ የለም፡፡ የአማራጭ ሃይሎች በፖለቲካው መድረክ አለመታየት ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ውስጥ ከሚታየው የሥልጣን ሽኩቻ ጋር ተደማምሮ አጠቃላይ አገራዊ የአመራር ቀውስ ሊፈጥር ይችላል፡፡

## ኦ.ሕ.ዴ.ድ- "ሲሞቅ በማንኪያ . . ."

የአቶ መለስ ዜናዊ አልጋ ላይ መዋልን ተከትሎ ከበሮ ይመታባቸው ከነበሩ ሥፍራዎች ሁለቱ ተጠቃሽ ናቸው- ጎረቤት ሶማሊያ እና የግንኙ አጋር ድርጅት ኦ.ሕ.ዴ.ድ፡፡ በተለይ የሶማሊያ ታጣቂዎች (ሽብርተኛውን አል-ሻባብን ጨምሮ) የመለስን መሞት በጉጉት ይጠብቁ ነበር፡፡ ከተለያዩ የሚዲያ ባለሞያዎች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያደርጉትን ያላሰለሰ ጥረት የተመለከተ ጠባቸው ከአቶ መለስ ጋር ብቻ የኾነ ያህል እንዲሰማው ያደርጋል፡፡ የኦ.ሕ.ዴ.ድ ከበሮ ግን የአል-ሻባብን ያህል ባይደምቅም አጋጣሚውን ተጠቅሞ ሥልጣን ለመጋራት ያለውን ፍላጎት ያሳይ ነበር፡፡

ከሁለት ወራት በፊት የመጀመሪያውን ሙከራ ያደረገው በኦሮሚያ ክልል ተቀባይነት አላቸው የሚባሉትን አቶ አባ ዱላ ገመዳን ለድርጅቱ ሊቀመንበርነት በማጨት ነበር፡፡ ወትሮውኑም ቀድሞ የነበራቸው ወጣ ያለ ተሳትፎ በኢሕዴግ ያልተወደደላቸው አባ ዱላ አፈ ጉባዔነቱን እንዲይዙ የተደረገው ኾን ተብሎ ከኦሮሚያ ክልል ለማራቅ መኾኑን ማንም አላጣውም፡፡ በወቅቱም ድርጅቱ እርሳቸውን ወደፊት ለማምጣት ፍላጎቱን ሲያሳይ ከፍተኛ ተቃውሞ የመጣው ከ.ሕ.ወ.ሓ.ት ነበር፡፡

ኦ.ሕ.ዴ.ድ ለሕ.ወ.ሓ.ት "ቀኑን የሚጠብቅ ኦ.ነ.ግ" ማለት ነው፡፡ እምነት ሊጥሉበት አልቻሉም፡፡ ሽብርተኛ ተብሎ የተፈረጀው የኦ.ነ.ግ አባላት መሰግሰጊያ ነው ሲሉ ይሟገታሉ፡፡ በመኾኑም ድርጅቱ በተሻለ ሰው እንዳይወከል የመንግሥት ከፍተኛ አመራር አካላት ሌት ተቀን ደክመዋል፡፡ ለዚህም ይመስላል በቅርቡ ድርጅቱ ባደረገው ስብሰባ አቶ አለማየሁ አቶምሳን ለድርጅቱ በከፍተኛ ሥልጣን ደረጃ አለመወከል ተጠያቂ በማድረግ የህወሓትን ሴራ ለማደፋፈን እየተሞከረ ያለው፡፡ "አቶ አለማየሁ ሁለቱንም ሥልጣን ደርቦ በመያዝ ኦሮሚያ ከፍተኛ ሥልጣን በፌደራል መንግሥቱ እንዳይኖረው አድርጓል" የሚል ወቀሳ ከአባሎቻቸው የደረሰባቸው፡፡ ነገሩ ግን ግልጽ ነው፡፡ የአቶ በረከት እና መሰሎቻቸው ሴራን ለመሸፈን እና ችግሩን ወደ ድርጅቱ ለማምጣት ነው፡፡

ከኦሕዴድ ጋር ያለው ትግል በአጭሩ የሚቋጭ አይመስልም፡፡ በቀጣይ ከፍተኛ ሹም ሽር ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በርካታ የድርጅቱ አባላት ጥርስ የተነከሰባቸው እና በቅርቡ ከፓርቲው የሚሰናበቱ ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን የሕወሓት ሙሉ ተሳትፎ እንጂ የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚና እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ከቀጥጥራቸው ውጪ የኾኑ ነገሮች እየተካሄዱ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ኦሕዴድን ከከፍተኛ ሥልጣን ማግለሉ የአቶ ኃይለማሪያምን የሥልጣን ዘመን ተጨማሪ ፈተና ይሰጠዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት አንኳር ነጥቦች እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች ወሳኝ አመራርን የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለትክክለኛ ለውጥ የቆሙ ከኾነ ከፊታቸው የተጋረዱትን ፈተናዎች በብልሃት እና በትዕግስት መፍታት ይኖርባቸዋል፡፡ አዳዲስ ሰዎችን ወደ ሥልጣን ማምጣት፣ ለተቃዋሚዎች መድረኩን መክፈት፣ ለነጻው ፕሬስ አመቺ ሁኔታን መፍጠር እንዲሁም የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት የተግባሮቻቸው ሁሉ መጀመሪያ ሊኾኑ ይገባል፡፡

## የመለስ....

(ከገፅ 11 የዞረ)

ናቸው፡፡ ከጸሐፊው የቀድሞ ሥራ አንጻርም ሆነ ከመሰል ጸሐፊዎች በዚህ ስራቸው የተሻለ ፅንሰአሳቦችን የመረዳትና ክስተቶችን በፅንሰ አሳብ ለማብራራት የመሞከር ጥረት ተስተውሎበታል፡፡

ይሁን እንጂ መጽሐፉ ከዚህ በፊት እንደነበሩት እንደማንኛዎቹም ጸሐፊዎች ስለድርጅቱ ርታዊነት ተከላካይ ሆኖ የቀረበ ሥራ ነው፡ ፡ ጸሐፊው በህወሓት ትግል ጉዞ ትክክለኛነት ቅንጣት ታህል ጥርጥር የሌላቸው መሆናቸውንና አልፎ ተርፎ ህወሓት ማለት እኔ ነኝ ብለው ለመመስከር ያላመነቱ ናቸው(ገጽ iv)፡፡ ስለዚህ ራሳቸውን የሚያጋልጥ ነገር በራሳቸው እንዲመሰከር ማድረግ ቢቻል እንኳን ተገቢ አይሆንም ይሆናል፡ ፡ የግል ልምዳቸውን ሳይሆን የድርጅቱን ታሪክ እጽፋለሁ ብለው እንደመነሳታቸው የሚቻላቸውን ያህል ራሳቸውን ከቅርጫቱ አውጥተው ቢጽፉ ጥፋቶች ይቀነሱ ነበር፡፡ አቀራረባቸው በመጽሐፉ በርካታ ቦታዎች ስለታሪክና ሐቀኛ አጻጻፉ ከሚያነሱት ሽጋ ሽጋ አሳብ ጋር የሚመጣጠን አለመሆኑ ይታያል፡ ፡ ወገንተኝነታቸውን ያንጸባረቁትም አንዳንድ ድክመቶችን (በተለይ ለክፉ የማይሰጡትን) ‹‹በመቀበል››ና በአከራካሪ ርዕሰጉዳዮች ዙሪያ ድርጅቱ ላይ የሚነሱ ትችቶችን ግነት የበዛባቸው ስለመሆናቸው፣ ስህተቶቹ ያልተለመዱ ስላለመሆናቸው፣ ካለመብሰል የመጡ ብቻ እንደሆኑና በዝንባሌ አንጻር ብቻ የሚታዩ በመሆናቸው፣ ረዥም ጊዜ የቆዩ ባለመሆናቸው፣ ወቅታዊ ሁኔታ ስላስገደዱ የተፈጸሙ መሆናቸውንና የመሳሰሉ ምክንያቶችን በመዘርዘርና በማጣጣል ነው፡፡ ከዚያም አልፎ በተለይ መለስ ላይ የሚነሱ ትችቶችን በመገልበጥ ተጠያቂዎቹ ሌሎች (እነአረጋዊ በርሄ) እንደሆኑ በማስመር ነው፡፡

**የድርጅቱ ጠባዮችና የመንግሥትነቱ ባህሪዎች ምንና ምን?**

መቼም እንደማንኛውም ‹የነጻ አውጪ› ጸሐፊ ከአንዳንድ የአተገባበር ችግሮቹ በስተቀር ለእሳቸው ህወሓት ዲሞክራሲያዊ ነው፡፡ እዚህ ላይ በተለያየ አጋጣሚ የተጠቀሰውን የእንግሊዛዊው የፓትሪክ ጊልክስን ስለነጻ አውጪዎች ታሪክ ጠባያት ማስታወስና የኮ/ሉን መነሻ መረዳት ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ይሄን ማድረግ ከቻልን ደግሞ ድርጅቱ እነዚህን ጠባያት ያሳየው በትግል ወቅትና ከባቢ ውስጥ በመሆኑ ብቻ አድርገን ልንወስድ እንችላለን፡፡ ከ1977 ወዲህ እስከ 83 የተፈጠረ ለውጥ ካለ ወደፊት ጸሐፊው በቅጽ 2 የሚነግሩን ይመስለኛል፡፡ ለጊዜው ግን ድርጅቱ በጫካ ሲያሳያቸው ከነበሩት አመሉ በመጽሐፉ የተጠቀሱትን በጣም ጥቂቱን ላንሳና አንባቢ ከ1983 ወዲህ ድርጅቱ በመንግሥትነት ስልጣኑ ከሚያደርጋቸው ጋር እያሰላሰለ ይረዳቸው፡፡

የተለየ ሃሳብን የማይቀበል ስለመሆኑ፡- ስለድክመቱ መጻፍ ምስጢር እንደማውጣት የሚቆጥሩ አባላት አሉት (ገጽ 87)፡፡ በአመራሩ ውስጥ ... የአቋም ልዩነት መንጸባረቁ በወቅቱ ለማንም ቢሆን የሚታወቅ ነገር አልነበረም(ገጽ 264ና 293)፡፡

ከድርጅቱ ጋር መሰለፍን ምርጫው ያላደረገ ወጣትና ቤተሰቦቹ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ እንዲጠሉና እንዲገለሉ የሚያደርጉ ጫናን የሚፈጥሩ (ገጽ223)፡፡ ... የተለየና የተቃውሞ አስተሳሰብን ባለመቀበል ተቃዋሚዎችን በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በማስወገድና በማግለል፣ እንዲሁም አባላት የመረጃ ዕውቀት የሚያገኙበትን ዕድል በማጥበብና በመንፈግ፣ በዚህ ረገድ የአመራሩ ጥገኛ እንዲሆኑ የሚያደርጉ አካሄዶችን (ገጽ 298) ይከተል ነበር፡፡

**ውይይት ለይምሰል፡-** በታችኛው አባል ዘንድ ውይይት የሚካሄድበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም ሁሉም ነገሮች አልቀውና ተደምድመው፣ ድምዳሜውን ለማስያዝ ታሳቢ ተደርገው የሚወርዱና ውይይት የሚካሄድባቸው ነበሩ (ገጽ 298)፡፡ የ1969ኙ የውስጥ ቀውስ የተፈታበት መንገድ ያስከተለው ውጤትበአንድ በኩል ... ብቻውን የፈለገውን ማድረግ የሚችል አካል... ሲፈጥር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተሰጠውን ትዕዛዝ ሁሉ አለአንዳች ተቃውሞ... የሚፈጽም አካል ተፈጠረ(ገጽ 127)፡፡

**ፕሮፖጋንዳውና ማደራጀቱ ከበስተጀርባው ሌላ ነገር ያዘለና ለከት የሚያጣ ስለመሆኑ፡-** በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ድርጅቱ የሲጋራ ሬሽን ማከፋፈል ሲያቅተው ለችግሩ መወጫ አድርጎ የዘየደው መላ ‹‹ማጤስና አጫሽ ሆኖ መገኘትም፣ ማጤስ አላቆምም ብሎ አቋም መውሰድ ፖለቲካዊ ትርጉም እየተሰጠው... ተሰብስበው አቁመናል የሚል ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ በማድረግ ማስገድድ ነበር(ገጽ 226)፡፡ ማሌሊትን ለመፍጠር እንቅስቃሴ ሲጀመር የግንባር ቀደሞች አደረጃጀት ተፈጠረ (ገጽ 294)፡፡

እንግዲህ እነዚህ ጠባዮቹ የድርጅቱ የጫካው ባህል መገለጫ የሆኑ ይመስላል፡፡ ጸሐፊው ተዘረዘሩትን ችግሮች ለአንድ ጊዜ ብቻ እንደተፈጠሩ በሚመስል አንድምታ ያቀረቡት ቢሆንም፤ ድርጅቱ የመንግሥትነት ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ ከሚያሳያቸው ጠባያት አንጻር መገምገም እንደሚያስፈልግ ጠቋሚ ናቸው፡፡ አሁንም በጫካ (የትጥቅ ትግሉ)ባህል ስም ችግሮቹን እየከለሱ የሚኖሩ የገዢው ቡድን ሰዎች ካሉ እኒህ ጠባያት ለዲሞክራሲያዊነት ቀርቶ ለዘልማድ የመንግሥትነት ባህሪ የማይመጥኑና አሰቃቂ መሆናቸውን ማስገንዘብ ያሻኛል፡፡ ጸሐፊው ኮ/ል ኢያሱ መንገሻንም በነካ እጀት ቅጽ ሁለትን ከተገቢው ጥንቃቄ ጋር ለማለት እወዳለሁ፡፡



ልዩ-ዳሰሳ

# ደቡብ ሱዳን ቀጣይቱ የኢትዮጵያ ፈተና

ሙሉነህ አያሌው

ደቡብ ሱዳን ከሰሜኑ ጋር እዚህ አዲስ አበባ ላይ ያደረጋቸው የሰላም ስምምነት ለኢትዮጵያ ከሚያስገኘው ጥቅምና ጉዳት አንፃር ምን አንድምታ አለው? የሚለው ለጊዜው በመወያያ አጀንዳነት ገና ወደ አደባባይ አልመጣም፡፡ ኢትዮጵያ ለረጅም አመታት ሁለቱ አገራት በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተገናኝተው እርቅ ያወርዱ ዘንድ ያደረገችው አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ መቼም የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ሁሉ ዋጋ የከፈለው ለፅድቅ ነው ብለን የምንመፃደቅ አይመስለኝም፡፡ የየትኛውም አገር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የመጨረሻ ግቡ የራስን አገር ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡ የሱዳንና የደቡብ ሱዳን ወደ እርቅ መምጣት አገራችን ያሰላችው ፖለቲካዊም ይሁን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ይኖራል የሚል እምነት አለኝ፡፡ እነዚህ ስሌቶች አንዳንዴ መልካም ጐናቸው ሲያመዝን፤ በተቃራኒው ደግሞ ከተጠበቀው ይበልጥ የከፋ ቀውስ ይዘው የሚመጡባቸው አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ ደቡብ ሱዳን አሁን ላይ ሆነን ይሄንን በረከት ይዛ መጥታለች፤ አልያም ይህንን አይነት መርገምት አድርሳለች የምንልበት ወቅት ላይ ባንሆንም፤ ለወደፊቱ አገራችን እነዚህን ሁነቶች አስልታ የምትዘጋጅባቸውን አንዳንድ ነጥቦችን ማየት ተገቢ ነው፡፡

ሙላት ውብነህ እና ዮሐንስ አባተ በጋራ ባሳተሙት ‹‹Ethiopia transition and development in the horn of Africa›› በሚለው መጽሐፋቸው ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መካከል የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደውና በዋቢነት ትኩረት የሚያደርገው አፍሪካን በሚመለከት የሰፈረው ሃሳብ ነው፡፡ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው በአህጉሪቱ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ዙሪያ የአገራችንን ንቁ ተሳትፎ ማድረግን ቀዳሚ ግቧ አድርጎ ማስቀመጡ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

1960 በፊት

ከ1960ዎቹ በፊት ኢትዮጵያ አብዛኛውን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል ከጅቡቲ መንግስት ጋር የነበራት ግንኙነት ተጠቃሽ ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛው የግንኙነቱ ምክንያት ሁለቱን ሀገሮች በኢኮኖሚ አስተሳስሮ የያዘው የጅቡቲ አዲስ አበባ የባቡር ሀዲድ መስመር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በጊዜው በቅኝ ግዛት ስር ከነበሩት የጐረቤት ሀገራት ጋር ይህ ነው ሊባል የሚችል አይነት ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አልነበራትም፡፡

ከ1960ዎቹ በኋላ ግን አገራችን ከነዚህ አገራት ጋር ከጉርብትና ባለፈ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ቀርፃ ከቀሩት የቀጠናው ሀገራት ጋር ጥብቅ ግንኙነት ልትመሰርት ችላለች፡፡ በጊዜው አገራችን ካከናወነቻቸው ተግባራት መካከል በእንግሊዝና ፈረንሳይ ቅኝ ግዛቶች፣ በሰሜኑ አረብ አገራትና በተቀረው ጥቁር የአፍሪካ አገራት፣ እንዲሁም በካዛብላንካና በሞኖሮቪያ ቡድኖች መካከል የተነሱትን አምባጓሮዎች ለመፍታት የተጫወተችው ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ለየትኛውም ቡድን ወገንተኛ አለመሆኗ የሁሉም አጋር እንድትሆን ከማስቻሉም በላይ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ1963 ዓ.ም. ሲመሰረት ለመቀመጫነት ተመርጣ ሰፊ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞችን ለማግኘት ችላለች፡፡ ለዚህም እንደማሳያነት የሚጠቀሰው አፄ ኃ/ስላሴ በ1962 (እ.ኤ.አ) ዓ.ም. በሌጐስ ስብሰባ ላይ‹‹ኢትዮጵያ እራሷን እንደ አንድ ቡድን ብቻ ታያለች ይህም የአፍሪካ ቡድን ብቻ ነው›› ማለታቸው የሁሉም አይን ሀገሪቷ ላይ እንዲያርፍ አስችሏል፡፡

የኢትዮ-ሱዳን ግንኙነት

የረጅሙ የኢትዮ-ሱዳን ታሪካዊ ግንኙነት አንዴ በጥላቻ ሌላ ጊዜ በወዳጅነት ረጅም አመታትን አሳልፏል፡፡ የአፄ ኃ/ስላሴ መንግስት መውደቅ፤ በተለይም በ1956 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) የሱዳን መንግስት ነፃ መውጣትን ተከትሎ በሁለቱ አገራት ውስጥ የተገንጣይ ቡድኖች መስፋፋት፤ የድንበር ማካለልና የስደተኞች ጉዳይ ለግንኙነቱ እንደ ዋነኛ ችግር ፈጣሪ ተደርገው የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያ የሰሜኑ የኤርትራ ክፍል የፌዴራል ስርዓቱ መጣስና የኃ/ስላሴን የውህደት ፖሊሲ በመቃወም የተነሳው የተገንጣይ ቡድን አንዱ ሲሆን፤ በሱዳን ደግሞ የደቡብ ክፍል ከሰሜኑ አረብ አስተዳደር ጋር ባለመስማማት ነፍጥ ማንሳቱ በሁለቱ አገራት ፖለቲካዊ ግንኙነት ላይ የራሱን አሻራ ሊያስቀምጥ ችሏል፡፡ የኤርትራ ገንጣይ ቡድን የነበረው የጀብሐ አመራር ክፍል በአብዛኛው ከእስልምና ሃይማኖት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የአረብ አገራትን ቀልብ ለመግዛት አስችሎት ነበር፡፡ ለዚህም የ‹‹እስልምና ወንድማማችነት›› በሚለው የአጋርነት ፖሊሲ ምክንያት የሰሜኑ የሱዳን ክፍል የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖችን በከፍተኛ ሁኔታ መርዳት ጀመረ፡፡ ይህን አስመልክቶ አቢር ሞርደካይ “The continuous horn of Africa conflict” በሚለው መጽሐፋቸው ኢትዮጵያ ከአረቡ አገራት ጋር በመቆራረጥ በአዲስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አቅጣጫ ፊቷን ወደ እስራኤል ማቅናቷን ያብራራሉ፡፡ ‹‹ከዚህ በኋላ ነበር የአረቡ ሀገራት አጋርነት ከሃይማኖት በተጨማሪም የፖለቲካዊ ግንኙነት መልክ እየያዘ የመጣው›› ሲሉ አክለው ያብራራሉ፡፡

ይህን ተከትሎ ነበር የኢትዮጵያ መንግስት የሰሜኑን አረብ አገዛዝ ለማዳከም የደቡብ ሱዳን ግዛት (በአብዛኛው ክርስቲያን እንደሆነ የሚታመነው) ያነሳውን የአኒያ-ኒያ (Anya-Nya) እንቅስቃሴ መደገፍ የጀመረው፡፡ ሁለቱም ሀገሮች የውክልና ጦርነት (Proxy war) በማድረግና ተቃራኒ ቡድኖችን በመደገፍ እልህ ውስጥ የገቡት እንዲህ ብለው ነው፡፡

ይህንንና የመሳሰሉትን ሽካራ ግንኙነቶች አልፈው አሁን ኢትዮጵያ ሱዳን ድረስ ዘልቃ የሀገሪቱን ሰላምና ፀጥታ ለማረጋጋት የምታስፈልግበት ጊዜ ደረሰ፡፡ ደቡብ ሱዳንም ከሽምቅ ውጊያ ተላቃ ወደ አገር አደገች፡፡

ጋምቤላ-ደቡብ ሱዳን

በኢትዮጵያ እና በደቡብ ሱዳን ህዝቦች መካከል ወደፊት ሊፈጠር ስለሚችለው የሁለትዮሽ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ትስስር ለመረዳት ሁለት መንገዶች አሉ፡፡ ቀዳሚው ሁለቱ አገራት ከዚህ ቀደም የነበራቸውን የፖለቲካ-ታሪክ (Political History) በሚመለከት አጭር ዳሰሳ ማድረግ ሲሆን፤ በሁለቱ አገራት ድንበር አካባቢ ያሉትን ህዝቦች ነባር ግንኙነት መስመር ማጥናት ሌላኛው አማራጭ ነው፡፡

በማንኞቹም አገራት የሚኖሩ ድንበር ተጋሪ ህዝቦች የሚያመሳስላቸው አንድ እውነት አለ፡፡ ይህም የጋራ ቋንቋ፣ ባህል፣ የአየር ንብረት፣ የኢኮኖሚ ምንጭና ተመጋጋቢ የህዝብ ለህዝብ ትስስሮሽ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ በዙሪያዋ ከበዋት ካሉ የቀንዱ አባል አገራት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተሞክሮ አላት፡፡ ለምሳሌ በትግራይና ኤርትራ፣ በአፋርና ጅቡቲ፣ በኢትዮጵያ ሶማሌና በሱማሊያ፣ በኢትዮጵያ ሞያሌ እና ኬንያ ሞያሌ እያልን መዘርዘር እንችላለን፡፡

የደቡብ ሱዳንና የጋምቤላ ተሞክሮም ተመሳሳይ ነው፡፡ ስለአገራቱ ህዝቦች ቀጣይ እጣ ፋንታ ለመናገር አስቀድሞ በሁለቱ አገራት ህዝቦች መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት በሚገባ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ አሌክሳንደር ሜኬልበርግ “Changing Ethnic relations, a preliminary investigation of Gambella, south west Ethiopia” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው የጋምቤላን ህዝቦች አሰፋፈር ከደቡብ ሱዳን አንፃር አስተያይተው ያቀርባሉ፡፡ በጥቅሉ በጋምቤላ ውስጥ ወደ አምስት የሚጠጉ ብሔሮች ይገኛሉ (አኙዋክ፣ ኑዌር፣ መጀንገር፣ ኦፓ እና ኮሞ)፡፡ ከነዚህ አምስቱ ብሔሮች መካከል ኑዌር 40% የሚሆነውን አብዛኛውን ድርሻ ሲወስድ አኙዋክ 25%፣ መጀንገር 10% የሚሆነውን ይዘው በተከታይነት ተቀምጠዋል፡፡

በደቡብ ሱዳን ውስጥ ከሚገኙ ህዝቦች መካከል ኑዌር እና አኙዋክ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ የእነዚህ ህዝቦች በሁለቱ አገራት ውስጥ ያላቸው ተዋፅኦ በተናጠል ማየት እንችላለን፡፡ አብዛኛው የኑዌር ተወላጆች ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ቁጥራቸው የበዛ ሲሆን የቀረው ደግሞ በደቡብ ሱዳን ውስጥ የሚገኘው ነው፡፡ በተቃራኒው አብዛኛው የአኙዋክ ቤተሰቦች በደቡብ ሱዳን ሲገኝ የተቀረው የብሔሩ አባላት በጋምቤላ ውስጥ የሚኖሩትን ይጠቀልላል፡፡ ይህ ማለት በሁለቱ አገራት መካከል ተመሳሳይ የሆኑ ህዝቦች በተለያየ መጠን፣ በተለያየ አስተዳደር ስር ይኖራሉ ማለት ነው፡፡

ሰማያዊ ወርቅን በጥቁር ወርቅ

እንደ ተቀሩት የቀንዱ አገራት ሁሉ ደቡብ ሱዳንና ኢትዮጵያን የሚያመሳስላቸው ብዙ መለኪያዎችንም ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ሁለቱም ለህዝባቸው ሊያሟሉ የሚገባቸው ነገር ግን ያልቻሏቸው በርካታ ጐደሎ ነገር አላቸው፡፡ ሁለቱም በመካከለኛው የአገራቸው ክፍልና በድንበር አካባቢ ያሉ ህዝቦቻቸው እጅግ የተራራቁ ከመሆናቸው በተጨማሪ ለተቀረው የአገሬው ነዋሪ የምግብና የኃይል አቅርቦትን በበቂ ሁናቴ ለማዳረስ የተሳናቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ችግሮቻቸውን ለማስታረቅ ሁለቱም የግድ ተቀራርበው ሊሰሩባቸው የሚገቡ መደላደሎች መኖራቸው እሙን ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከደቡብ ሱዳን ጋር ወደፊት ለሚኖራት የጠበቀ ትስስር ስትል የሰሜኑን ወዳጅነት ማበላሸት እንደሌለባት ይታመናል፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት ከሰሜኑ የምናገኘው የወደብ አገልግሎትና

እስከዛሬም ድረስ ጥገኛ የሆነበት የነዳጅ አቅርቦት ከዋነኞቹ መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ሃርይ ቬርሆቨን “The case of regional energy integration: blue gold for black gold” በሚለው ፅሁፋቸው ኢትዮጵያ በተለይ ከሱዳን ጋር ያላትን አዎንታዊ ቁርኝት በሰፊው አብራርተዋል፡፡ እንደ እርሳቸው አገላለፅ ከሆነ በኢትዮጵያና ኤርትራ መንግስት መካከል የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ ኢትዮጵያ በኤርትራ ትገለገልበት የነበረው የወደብ አገልግሎት በመቋረጡ ምክንያት ፊቷን ወደ ጅቡቲና ሱዳን እንድታዞር ተገዳለች፡፡ ስለዚህ ፖርት ሱዳን ከጅቡቲ ቀጥሎ ሌላኛው የወጪና ገቢ ንግድ ማስተንፈሻ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡ ለዚህም ነው ደቡብ ሱዳንን ለማትረፍ በሚል የምንመርጠው አካሄድ ከሰሜን ሱዳን የምናገኘውን የወደብ አገልግሎት እንዳያስተጓጉል መጠንቀቅ ይገባል የምለው፡፡

ሁለተኛው የኢትዮጵያና ሱዳን ጥብቅ ቁርኝት የሚስተዋለው ጥቁሩን ወርቅ (ነዳጅ) በሚመለከት ሁለቱ አገራት የተጓዙበትን መንገድ በማየት ነው፡፡ ምንአልባት መረጃዎቹ ተተንትነው የቀረቡበት መንገድ ይለያይ ይሆናል ሰእንጂ በመግባቢያ ደረጃ ኢትዮጵያ ከ85-90% የሚሆነውን የነዳጅ ፍላጐት የምታሟላው በቀጥታ ከጐረቤት አገር ሱዳን ነው፡፡ ሁለቱ አገራት በደረሱበት ስምምነት መሰረት ሱዳን ለኢትዮጵያ የምታቀርበው ነዳጅ በዋጋ ደረጃ ከአለም መገበያያ አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ የሚባል ነው፡ ፡ ይህ ግብይት በዓመት ከ1.2 እስከ 2 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሲሆን፤አገራችን በጠቅላላው ከውጭ ንግድ ከምታገኘው ገቢ ሃምሳ በመቶ (50%) የሚሆነውን ነዳጅ ለመግዛት ታውለዋለች፡፡

በቀጣይ የአገራችን ነዳጅ የማግኛ እጣ ፈንታ ወደ ደቡብ ሱዳን የሚያጋድል ይመስላል፡፡ ኢትዮጵያ ለደቡብ ሱዳን መመስረት ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርጋለች፡ ፡ ደቡብ ሱዳን በበኩሏ ኢትዮጵያ አባይን በተመለከተ በምትወስደው ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ቅር እንደማትሰኝ መሪዎቿ በተደጋጋሚ ገልፀዋል፡፡ ኢትዮጵያ በአባይ ዙሪያ የምታመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል (ተንታኞቹ ሰማያዊው ወርቅ የሚሉት) ተከትሎ ደቡብ ሱዳን ለህዝቦቿ ከአጭር ርቀት ገዝታ ለመጠቀም ካላት ፍላጐት አንፃር ሁለቱ አገራት በኃይል አቅርቦት ዙሪያ ተመጋጋቢ ግንኙነት ሊፈጥሩ የሚችሉባቸው አማራጮች እየታዩ ይገኛሉ፡፡

## አዲሱ ውል

ከደቡብ ሱዳን ግዛቶች መካከል ዩኒቲ፣ የላይኛው አባይ (በደቡብ ሱዳን ድንበር ውስጥ የታጠሩ)፣ እና የአቢዬ ግዛት (የማን እንደሚሆን ገና ውሉ ያለየለት) በነዳጅ ሀብታቸው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ይሁንና ደቡብ ሱዳን የምታመርተውን ነዳጅ ለአለም አቀፍ ገበያ ለማቅረብ ይቻላት ዘንድ የምትጠቀመው ብቸኛው የነዳጅ ማስተላለፊያ ቱቦ በሰሜን ሱዳን የሚገኘው ነው፡፡ በቅርቡ ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ እና ከጅቡቲ መንግስታት ጋር አዲስ የነዳጅ ማስተላለፊያ ቱቦ ለመዘርጋት በእቅድ ላይ መሆኗን ይፋ አድርጋለች፡፡ የደቡብ ሱዳን ማዕድን ሚኒስትር የሆኑት ስቴፈን ዳዩ ዳኡ አዲሱን ፕሮጀክትና ፋይዳ አስመልክቶ በቀረበላቸው ጥያቄ ስለጠቀሜታው የሰጡት መልስ ሲጠቃለል ሁለት እንዳምታዎች አሉት፡፡

የመጀመሪያው፤ የቀድሞ ነዳጅ ማስተላለፊያ ለመተው (ምንም እንኳን የሶስት አመት ቀሪ ኮንትራት ከሱዳን ጋር ያላቸው ቢሆንም) አዲሱ ፕሮጀክት ተግባራዊ ሲሆን ለደቡብ ሱዳን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው በመታመኑ የሚነሳ ነው፡፡ አንድም ታሪካዊ ጠላት ከሆነችው ሱዳን ጋር በነዳጅ ማስተላለፍ ሂደት ውስጥ የተፈጠረው አለመተማመን ሲሆን በተጨማሪም ነዳጁ ከሚመረትበት አንስቶ እስከ ጅቡቲ ወደብ ያለው እርቀት ከዚህ ቀደም ፓርት ሱዳን ካለበት አንፃር ሲታይ አጭር የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

አዲሱ ፕሮጀክት ተግባራዊ ሲሆን ኢትዮጵያ ነዳጅን በሚመለከት ያላት ከፍተኛ ጥገኝነት ሰየተሻለ ጠቀሜታን እንድታገኝ መርዳቱ ሁለተኛው ምክንያት ነው፡፡ በነዳጅ ማስተላለፊያ ቱቦው አማካኝነት የኢትዮጵያ መንግስት ግዛቱን በመፍቀዱ የሚያገኘው የኪራይ ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮጀክቱ በነዳጅ ላይ ያለንን መተማመኛ ከረጅም ዓመት እቅድ አኳያ አስተማማኝ ያደርግልናል፡፡ እነዚህን አካሄዶች በስርዓት መያዝ ከተቻለ የደቡብ ሱዳን ወደ ቀጠናው መቀላቀል እውነትም ለአገራችን በረከትን ይዞ ይመጣል ብለን ተስፋ እንድናደርግ ይረዳናል፡፡

## ስጋቶች

ጋምቤላንና ደቡብ ሱዳንን በሚያዋስነው የድንበር አካባቢ ያለው ቀጠና ከረጅም ጊዜያት አንስቶ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭትና ብጥብጥ ያልተለየው እንደነበረ የተለያዩ ፀሐፊያን ባሰፈሯቸው ድርሳናት ላይ ገልፀዋል፡፡ በእዚህ አካባቢ መነሻቸውን ላደረጉ ግጭቶች የተለያዩ ምክንያቶች ማቅረብ ቢቻልም በጥቅሉ መሰረታዊ ምክንያት የሚባሉትን አንዳንድ እውነታዎች በሦስት የተለያዩ ደረጃዎች ከፋፍለን ማስቀመጥ እንችላለን፡፡ ቀዳሚው ምክንያት በጋምቤላ ክልል ውስጥ የሚነሱ ግጭቶች እና አለመግባባቶች ብሎም የለየላቸው ጦርነቶች በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ብሔሮች መካከል መነሻውን የሚያደርግ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ብሔሮች ከማዕከላዊው የፌዴራል መንግሥት ጋር የሚፈጥሩትን አለመግባባት ተከትሎ የሚከሰተው ግጭት ነው፡ ፡ ሶስተኛው የግጭት ምክንያት ድንበር ተሻጋሪ ምንጭ ያለው ነው፡፡ ይኸውም የጋምቤላን ክልል ታኮ ባለው የደቡብ ሱዳን ድንበር አካባቢ የሚኖሩ የሌላኛዋ አገር ዜጎች የተፈጥሮ ሀብትን ከጋምቤላ ነዋሪዎች ጋር ለመጋራትና በሀገራቸው የሚቀሰቀሱ የተለያዩ ግጭቶችን በመሸሽ ድንበር አቋርጠው የሚገቡ ስደተኞች ከነዋሪዎቹ ጋር የሚፈጥሩት ግጭት ነው፡፡

ደረጀ ፈይሳ የተባሉ በጋምቤላ ክልል ዙሪያ ሰፊ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ፀሐፊ ከላይ የጠቀስኳቸውን ተለዋዋጭ የግጭት ምክንያቶች ዘርዘር አድርገው ያስቀምጡታል፡፡ “A National perspective on the conflict in Gambella” በሚለው ጽሁፋቸው በተለያዩ ጊዜያት በጋምቤላ አካባቢና በደቡብ ሱዳን ድንበር አካባቢ የሚነሱ ግጭቶች አምስት መሰረታዊ መነሾ እንዳላቸው ያትታሉ፡፡

ቀዳሚው በጐሳዎች መካከል የሚነሳ የግጭት ነው፡፡ ይህ ትንተና በጋምቤላ ውስጥ በሚኖሩ የተለያዩ ብሔሮች መካከል የሚነሳውን ግጭት ይመለከታል፡፡ ለዚህ መሰሉ ግጭት ምክንያቶች የተለያዩ ቢሆኑም በተለይ የተፈጥሮ ሀብት ክፍፍል፣ አንዱ ብሔር ሌላኛው ብሔር በሚኖርበት አካባቢ የሚያደርገው ሰፈራ፣ በብሔሮች መካከል የሚከሰቱ የእርስ በርስ አለመግባባቶች በዋነኝነት ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡ ፡ በክልሉ ከሚገኙት ብሔሮች መካከል ኑዌሮች እና አኙዋኮች በእንዲህ አይነት ግጭት በተደጋጋሚ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በጐሳ መካከል የሚነሳው ግጭት ሁለተኛው ምክንያት ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች ከእርስ በርስ ግጭት አልፎ በውስጣቸው በያዟቸው ጐሳዎች መካከል የሚነሳው ግጭት ሌላኛው የቀውስ ምክንያት ነው፡፡ በጐሳ መካከል ለሚነሳው የእርስ በእርስ ግጭት በዋናነት ከሚቀመጡት ምክንያቶች መካከል የፖለቲካ ውክልና ለማግኘት የሚደረግ ፉክክር (በመጀንገር)፣ የተፈጥሮ ሀብትን በበላይነት ለመቆጣጠር ሲባል (በኑዌር)፣ ይጠቀሳሉ፡፡

ሌላኛው አገር በቀልና ህዳጣን በሚባሉት ዜጎች መካከል የሚነሳው ግጭት ሦስተኛው ነው፡፡ ጋምቤላ በማዕከላዊው መንግስት የግዛት ማስፋፋት ፖሊሲ ስር ከመጠቃለሏ በፊት በአካባቢው የነበሩ ብሔሮች በአንድ ወገን አገር በቀል (Natives) የሚባል ስያሜ ሲሰጣቸው፤ ግዛት ማስፋፋቱን ተከትሎ የሰፈሩና በንግድና በኋለኛው ዘመን በተካሄደዱ የሰፈራ ፕሮግራሞች አማካኝነት ወደ አካባቢው የመጡ ‹‹ሰፋሪዎች›› (Migrants) መካከል በቦታ ይዞታና የክልላዊ ማንነትን ጥያቄ መሰረት ያደረገው አለመግባባት ሌላው የግጭት መስመር ነው፡፡

ማዕከላዊ መንግስት በክልሉ ከሚገኙ ብሔሮች ጋር በሚፈጠረው አለመግባባት የሚከሰተው ግጭት አራተኛው ምክንያት ነው፡፡ ጋምቤላ ውስጥ ከሚገኙ ብሔሮች መካከል ማዕከላዊው መንግስት በተለይ በተደጋጋሚ የግጭት ሂደቶችን ያሳለፈው እና አሁንም እያሳለፈ ያለው ከአኙዋኮች ጋር ነው፡፡ የአኙዋኮች ጥያቄ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ቢሆንም በተደጋጋሚ ችግሩን ለመፍታት መንግስት የሄደበት መንገድ ለችግሩ ዘለቄታዊ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ይበልጥ እያጋጋለው ለመምጣቱ አሁንም ግጭቱ ላለመብረዱ ምስክር ነው፡፡

የመጨረሻው ምክንያት ድንበር ተሻጋሪ ግጭት የሚለው ነው፡፡በጋምቤላ ውስጥ ከሚነሱ ግጭቶች መካከል ድንበር ተሻጋሪው ግጭት ለየት ያለ ባህሪ አለው፡፡ ለዚህም ሁለት ምክንያቶችን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አንደኛው በግጭቱ ተሳታፊ የሚሆኑት ብሔሮች በሁለት የተለያየ ሉዓላዊ አገራት ውስጥ የሚገኙ የመሆናቸው ሁነት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ለግጭቶቹ መፍትሄ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች ችግሩን በቀላሉ የሚፈቱ አለመሆናቸውን መጥቀስ እንችላለን፡፡

ከላይ የተጠቀሱት በጋምቤላ አካባቢ በምክንያትነት የሚቀርቡ የግጭት መስመሮች ከዚህ ቀደም ተለምዷዊ በሆኑ የግጭት አፈታት ስልቶች መፍትሄ ሲበጅላቸው ቆይቷል፡፡ የማዕከላዊውም ይሁን የክልሉ መንግስት በመሰረታዊ የክልሉ ህዝቦች ቅሬታ በሚያቀርቡበት ወቅት ምላሽ ተደርገው የተወሰዱት ባልተመጣጠኑ የግጭት አፈታት እርምጃዎች ምክንያት የተለያየ ወቀሳ የደረሰባቸው ቢሆንም ለጉዳዩ እየሰጡ ያሉት ትኩረት ግን አሁም ድርስ እዚህ ግባ የሚባልና መፍትሄውም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እርምት መስጠት የሚችሉ አለመሆናቸው እስከዛሬም ድረስ እነዚህ ቀውሶች ተሸክመናቸው እንድንጓዝ ተገዳናል፡፡


## ደቡብ ሱዳን ከግጭት ጀርባ

የደቡብ ሱዳን በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ተጨማሪ አገር ሆና ብቅ ካለች ገና ለጋ እድሜ ላይ ነች ቢባልም ለወደፊቱ ግን በተለይ ጋምቤላን ታከው ለሚነሱ ግጭቶች የደቡብ ሱዳን ሚና እንደ ከዚህ ቀደሙ ከኢትዮጵያ ያነስና በቸልታ የሚታይ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም የጋምቤላን የግጭት ምክንያቶች ተንተርሶ እርምት ለመውሰድ ብሎም ግጭቱን ለማስታረቅ በሚጠቀምበት መሰረታዊ አካሄድ ዙሪያ ዳግም የተሻለ እና ከዚህ ቀደም ከሚከተለው የተለየ አካሄድ ማየት እንደሚገባው አምናለሁ፡፡

በአካባቢው በሚነሱ ግጭቶች ዙሪያ ለወደፊቱ የደቡብ ሱዳን እየተጠናከረች መምጣት የተለየ ትርጓሜ እንደሚኖረው ከወዲሁ መገመት ከባድ አይሆንም፡፡ ወደፊትም ደቡብ ሱዳን በአካባቢው የሚኖራት አስተዋፅኦ አንዳድ መሰረታዊ ምክንያቶችን ይዞ የሚነሳ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በሁለቱ አገራት (በኢትዮጵያ እና በደቡብ ሱዳን) ውስጥ የሚኖሩ የድንበር ተጋሪ ህዝቦች መካከል በተደጋጋሚ ለሚነሱ ግጭቶች መሰረታዊ ምክንያቶች ጠቅለል አድርገን ማስቀመጥ እንችላለን፡፡ በዚህ አካባቢ ያሉ ዜጐች ዋነኛ የኢኮኖሚ ገቢያቸው (መተዳደሪያቸው) በከብት ማርባት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እነዚህ ህዝቦች ለከብቶቻቸው የግጦሽ መሬት እና ውኃ ፍለጋ ሲሉ የአንዱን ድንበር አቋርጠው በማለፍ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጋራት የሚያደርጉት ሙከራ የግጭቱ አንዱ ምክንያት ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት በተለይም ከዚህ ቀደም እንደታየው ጋምቤላ ውስጥ ባሉት ኑዌርና በደቡብ ሱዳን በሚገኙት የሙርኔ ህዝቦች መካከል የሚፈጠሩ

ወደ ገፅ 32 ዞሯል



ብርሃኑ ደቦጭ *(የታሪክ ተመራማሪ)*

# የመለስ ስብዕናና የህወሓት ታሪክ ግንባታ ሥነ-ልቦና

ርዕስ፡- መለስ ዜናዊ እና የህወሓት የትግል ጉዞ (ቅጽ 1)
ጸሐፊ፡- ኢያሱ መንገሻ (ኮ/ል)
ገጽ፡- 313
የታተመበት ማተሚያ ቤት፡- ብራና ማተሚያ ድርጅት
የታተመበት ዘመን፡- 2002 ዓ.ም.
ዋጋ፡- ብር 60

የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ህመምና ሕልፈተ ሕይወት፣ ዜናው ለሕዝብ የተገለጸበት መንገድና በክስተቱ ዙሪያ የታዩ ሁነቶች ህወሓት/ኢህአዴግን (ገዢው ቡድን) በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ያለፈበት ሂደት የመንግሥትነት ሥልጣኑን ከሚያስፈጽምበት መንገድና ከወደፊቱ አቅጣጫው ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንደሆነ እንድንረዳ አድርጎናል፡፡ ስለዚህ ‹‹መለስ ዜናዊ እና የህወሓት የትግል ጉዞ (ቅጽ 1)›› በሚል ርዕስ በኮ/ል ኢያሱ መንገሻ የተጻፈውን መጽሐፍ ስለህወሓት ‹ታሪክ› ታሪክ አዘጋገብ፣ የመለስ ስብዕና አክብሮት ግንባታና በመንግሥታዊነት ኃላፊነቱ የድርጅቱ ጠባይ የሚለንን ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

### ጸሐፊውና የመጽሐፉ ይዘት

ጸሐፊው ኮ/ል ኢያሱ መንገሻ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ትጥቅ ትግሉን የተቀላቀሉና ከድል በኋላም በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ሲያገለግሉ ቆይተው ይህ መጽሐፍ በታተመበት ወቅት ወደግል ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡ መጽሐፉ ከጸሐፊው ማስታወሻና መግቢያ ውጪ 21 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን፤ ሁለቱ (ምዕራፍ 1 እና 2) ምዕራፎች የድርጅቱ መሪ (መጽሐፉ በተጻፈበት ወቅት) የአቶ መለስ ዜናዊ የልጅነትና የትምህርት ታሪክ ናቸው፡፡ አንዱ ምዕራፍ (ምእራፍ 6) ርዕሱ መለስና ያልተሳካው ዳግማዊ የኤርትራ ጉዞ በሚለው ስር ሁለቱንም ያካተተ ሽፋን ይሰጣል፡፡ የተቀሩት አሥራ ስምንት ምዕራፎች የድርጅቱ የትግል ታሪክን የሚሸፍኑ ሲሆኑ፤ ዋናዋናዎቹ ፍሬነገሮቻቸውም ስለድርጅቱ እድገት፣ ድርጅቱ ያካሄዳቸው ውጊያዎች፣ የድርጅቱ ጉባኤዎችና በጉባኤ የተወሰኑ መሪ ፅንሰ ሃሳቦችና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ስለነበረው ግንኙነት የሚያትቱ ናቸው፡፡ መጽሐፉ የሚሸፍነው ምጣኔ ጊዜም እስከ 1977 ዓ.ም. ድረስ ነው፡፡ የጊዜ ቀመሩ ተጠየቅ አቶ መለስ ወደአመራር የመጡበት ዘመን ነው፡፡

### የህወሓት ታሪክ አጻጻፍ ያለበት ደረጃ

ለብዙ ጊዜ የህወሓት ‹ታሪክ› አጻጻፍ አቀራረብ በድርጅቱ የቅስቀሳ ቁጥጥር ስር የቆየ ነበር፡፡ የድርጅቱ 20ኛ፣ 25ኛና 30ኛ ዓመት በዓላት አከባበር ላይ የወጡ መጽሐፎች፣ እነተስፋዬ ገብረአብ ያዘጋጇቸው የነበሩት የ‹‹ያ ትውልድ›› ቅጾችና ‹እፎይታ› መጽሔቶች ጥሩ ማሳያ ናቸው፡፡ እነዚህ ሥራዎች በድርጅቱ የታሪክ አቀራረብ የመጀመሪያው ሊሰኙ የሚችሉና ድርጅቱ የሚቀበላቸው የታሪክ ማገሮችን የሚያመላክቱ ብቻ ሳይሆን ዝርዝሮቹም ምን መምሰል እንዳለባቸው የሚበይኑና ገድላዊ ዓይነት ነበሩ፡፡ ይህ አቀራረብ እስከ ምርጫ 97 ድረስ የነበረውን ሁነት አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ በ1993 የተከሰተው መከፋፈል ግን ስለድርጅቱ ታሪክ በይፋ ከሚወሳው ያለፈ ነገር እንዳለ የሚጠቁም ክስተት መሆን ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከድርጅቱ በወጡ ሰዎች አማካኝነት ‹‹አባይ››ን በመሳሰሉ ጋዜጦች ከሚወጡ መጣጥፎች የዘለለ ሥራ አልታየም፡፡

ከ1997 በኋላ ምንም እንኳን ድርጅቱ ከሚፈልገው የተለየ ትርጉም ያላቸውን ጉዳዮች ለማንሳት የሚደፍሩ ባይሆኑም አንዳንድ የድርጅቱ ታጋዮች በግል ተነሳሽነት የጻፏቸው መጻሕፍት ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡ እነዚህን ሁለተኛው አቀራረብ ልንላቸው እንችላለን፡፡ በተቀሮችን ማግኘት ቢቻልም እነዚህ የድኅረ ምርጫ 97 ውጤት ናቸው፡፡ ለዚህኛው አቀራረብ ከቀደምቶቹ የእነ ዶ/ር ሰለሞን እንቋይን ‹‹The Agony and Ecstacy of Tigrai››ን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ እስከ 2000/1 ድረስ የታየው ግን የድርጅቱን ታሪክ በፊልም መዘገብ ነበር፡፡ ወደአራት የሚደርሱ ‹‹ያልተነገሩ ታሪኮች››፣ የሕዳሴው ዋዜማ›› እና በመሳሰሉት ርዕሶች የወጡ ‹‹ዶክመንታሪ ፊልሞች›› ነበሩ፡፡ ከ2000 በኋላ ደግሞ የፀጋይ ጠማለው ‹ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ›(2001)፣ የኮሎኔል ኢያሱ መንገሻ ‹‹ሠርዶ››(2001) ና የሙሉጌታ ደባልቀው ‹‹ጋላህቲ ሠጊ››ም (2002) እዚህ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ ይህ አቀራረብ የቀጠለ ብቻ ሳይሆን፤ በትጥቅ ትግሉ ውስጥ ያልነበሩ፤ ግን አድናቂ፣ ደጋፊና አፍቃሪ ድርጅቱ የሆኑ ጋዜጠኞች የተቀላቀሉበትና አቀራረቡ ተቋማዊ ድጋፍ ለማግኘት እንዲችል ገንዘብ እስከመበጀትና ከዩኒቨርሲቲ ጋር ትስስር እንዲኖረው የማድረግ እንቅስቃሴ የታየበት ነው፡፡ ከዚህ ወገን የእነሃይላይ ሐድጉን ‹‹ፅንአት››(2002) መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ በመንፈሳቸው የዚሁ የሁለተኛ አቀራረብ ውሉድ የሆኑ በአቅጣጫቸው ግን በአመዛኙ ወደፊት የምጠቅሰውን የሦስተኛውን አቀራረብ በማጣጣልና በማጣረስ የሚሞግቱትን መጥቀስም ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ወገን ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ዛሬ ለዚህ ዓምድ የተመረጠው ‹‹መለስ ዜናዊ እና የህወሓት የትግል ጉዞ (ቅጽ 1)›› (2002) መጽሐፍ ነው፡፡ በአጠቃላይ የእነዚህ ዓይነቶቹ ሥራዎች ይዘታቸው ብቻ ሳይሆን ለምርቃታቸው የሚደረገው ሽር ጉድ፣ የተጋባገሮቻቸው ማንነትና የስፖንሰሮቻቸው ጋጋታም መታወቂያቸው ነው፡፡

ሦስተኛው አቀራረብ እየተመጠነ፣ እየተቀመመና እየተጠረበ ከሚጻፈው በተለየ ተጻራሪ ትርጉሞችንም የያዙ በቀድሞ የድርጅቱ ታጋዮች መዘጋጀት የጀመሩት መጻሕፍት ናቸው፡፡ ከዚህ ወገን ቀደምቶቹ የእነአቶ አስገደ ገብረ ሥላሴ ‹‹ጋህዲ››ዎችና የወ/ሮ የውብማር አስፋው ‹‹ፊኒክስዋ ሞታም ትነሳለች›› ናቸው፡፡ እዚህ ውስጥም ከታጋዮቹ ትውልድ ያልሆኑ የድርጅቱ ሃያሲዎች ስለመሳተፋቸው የአስራት አብርሃምን ‹‹ከአገር በስተጀርባ... ››ን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ሦስቱን የህወሓት ታሪክ አቀራረብ ብየና ከማጠቃለላችን በፊት ከዚህ ውጪ ለአካዳሚያዊ ጥቅም የሚዘጋጁ ጥናቶችም እንዳሉ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ አጠቃላይ ታሪክ ላይ ባጠነጠኑ ሥራዎቻቸው ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ በተወሰነ ደረጃና ፕ/ር ገብሩ ታረቀ ሰፋ ባለ ደረጃ ስለድርጅቱ ያካተቷቸው ክፍሎችም አሉ፡፡ የድርጅቱ መስራችና መሪ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ ያዘጋጁት ‹‹The origin of TPLF››ም ከሦስተኛው አቀራረብ የሚጋራው ቢኖርም አካዳሚያዊ ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑ በዚሁ ክፍል የሚመደብ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በመመረቂያ ጽሑፍ ደረጃ ስለድርጅቱ አንዳንድ እንቅስቃሴ የተሰሩ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳን አሁን የት እንደደረሰ ባላውቅም በድርጅቱ ታሪክ ላይ የዶ/ሬት ዲግሪውን ለመሥራት ፕሮፖዛል ያቀረበ ወዳጄ ሥራውን በአግባቡ ከሠራም በዚህ ክፍል ውስጥ የሚመደብ ይሆናል፡፡

እንደ አቀራረቦቹና ጸሐፊዎቹ መብዛትም ተፈጥሯዊ የሆነ የ‹ታሪኩን› አተረጓጎም ዕይታ መብዛትን ማስከተሉ አይቀርም፡፡ ይህም ለታሪኩ ግንባታ መልካም አጋጣሚ ወይም ተግዳሮትን ይዞ እንደመጣ ልናስብ እንችላለን፡፡ እስካሁን እንኳን ሁለተኛውና ሦስተኛው አቀራረብ አቀንቃኞች ፍጭት ውስጥ መግባታቸው አልቀረም፡፡ አንዱ አንዱን ለጥቅም ፈልጎ ነው በሚል ይወቅሳል፡፡ ለምሳሌ የዛሬው ትኩረታችን የሆነው ‹‹መለስ እና ...›› መጽሐፍ ስለሁኔታው በሰጠው አስተያየት ‹ድሮ ያልነበረ ዛሬ ግን በአንድ ጉዳይ ላይ እንዲህ ዓይነት እርስ በእርሱ የሚጋጭ ... › ነገር ለምን መወሳት እንደጀመረ ይኮንናል (ገጽ39)፡፡ በአንጻሩ አሥራት በመጽሐፉ ሁነቱን የውሸት ታሪክ ለመገንባት በተደረገ ጥረት የተፈጠረ ክስረትን ለመደበቅ የ‹ታሪክ› ፈጠራና ማደናገር መዘፈቅ ውጤት እንደሆነ ያስረዳል (ከአገር በስተጀርባ... ገጽ 41)፡፡ ይህ ሁኔታ ግን እንደእኔ ዓይነቱን የታሪክ ተማሪ ጮቤ የሚያስረግጠው ሳይሆን አይቀርም፡፡ ልብ አድርጉ የደስታዬ ምንጭ እንደ ህወሓት ዓይነቱ ሚስጢራዊ ድርጅት አድበስብሶ ሊያስቀር የሚችለውን መረጃ ለታሪክ ጥናት ግልጽ ስለሚያደርገው ነው፡፡

### የህወሓት ታሪክ ግንባታ ሥነ-ልቦና

የህወሐት ታሪክ ግንባታን የድርጅቱ አባላት ሁሉ የሚሹት ጉዳይ ነው፡፡ ከምክንያቶቹ መካከል ድርጅቱ የመንግሥትነት ሕልውና ካገኘ በኋላ ከሚሰነዘርበት ትችት አንዱ ነው፡፡ በድርጅቱ ውስጥና ውጪ የተከሰቱ (የ1993ቱና 1997ቱ) ሁነቶችም ይሄን ፍላጎት አንረውታል፡፡ የሁለተኛው አቀራረብ አቀንቃኞች ሁሉ የድርጅቱ ታሪክ ስላለመጻፉ የሚቆጩ ናቸው፡፡ አዛውንቱ ዶ/ር ሰለሞን ድርጅቱ የፈጸመው ገድል በምዕራቡ ቢሆን ስንት መቶ መጽሐፍ በተጻፈ ብለው እንደሚቆጩ ሁሉ፤ ወጣቱ ጋዜጠኛ ሃይላይ ጓደኛውና በአጋጣሚ ያገኛት አየርላንዳዊት ጋዜጠኛ ስለድርጅቱና አንዳንድ ታጋዮች (በተለይ መለስ ዜናዊ) የነበራቸው አስተያየት የተዛባ መሆኑ ታሪኩ ባለመጻፉ እንደሆነ ይብሰለሰላል፤ ያዝናል፡፡ አቶ አስገደም (የሦስተኛው አቀራረብ ውኩል) ከተለየ ዕይታ ቢሆንም የድርጅቱ ‹ታሪክ› ባለመጻፉ ይብከነከናሉ፡፡ የእርሳቸውን ልዩ የሚያደርገው ቁጭታቸው የህወሓት አስተዋጽኦ ከህዝባዊ ግንባር(ህግዴፍ) እና ኢህዴን አንጻር በሴራና በይሉኝታ ጎልቶ እንዳይወጣ መደረጉን በማማረር ነው፡፡ ኮ/ል ኢያሱ በ‹‹ሠርዶ›› መጽሐፋቸው ደግሞ ታሪኩ የመላው የአገሪቱ ሕዝብ ታሪክ ሆኖ እያለ ሕዝቡ የማያውቀው መሆኑ ልክ አለመሆኑን ያሳስባቸዋል፡፡ ኮ/ሉ በአዲሱ መጽሐፋቸውም ልክ

እንደሃይላይ በጓደኛውና በአጋጣሚ ባወቃት ራዲ የተባለች አየርላንዳዊት ጋዜጠኛ ስለመለስ የትግል አስተዋፅኦ ያላቸው ዕይታ እንደሚያዝነውና እንደሚረብሸው ሁሉ፤ አንዳንድ የወጣቱ ትውልድ አባላት መለስን‹‹የድል አጥቢያ አርበኛ... ›› አድርገው ማየታቸው ያሳስባቸዋል፡፡ እንግዲህ ይህ ስነ-ልቦና እንዴት ተፈጠረና በተለምዶ አሸናፊ ድርጅቶች ‹ታሪካቸውን› በብዛትና በዓይነት በፈለጉት መልኩ ሲጽፉ ህወሓት ይሄን ማድረግ ያልቻለው ለምንድን ነው ብለን መጠየቃችን አይቀርም፡፡ የዚህ ስነልቦና በድርጅቱ የ‹ታሪክ› ግንባታም ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ የዓመታዊ በዓላት ገድላዊ መጽሐፎቹንና ያልተነገሩ ታሪኮች ፊልሞቹን የቀድሞው ጦር መኮንኖች የሚጽፏቸው መጻሕፍትም ምን ያህል እንደተገዳደሯቸው መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

## መለስን እንደማሻሻጫ?

ኮሎኔል ኢያሱ ከዚህኛው መጽሐፍ በፊት በአማርኛና ትግሪኛ ቋንቋ የጻፏቸው ሁለት መጽሐፎችም አሏቸው፡፡ ከዚህ በፊት በ2001 ዓ.ም. ‹‹ሠርዶ›› በሚል ርዕስ ስላሳተሙት መጽሐፍ የቀረበው ዋንኛ ትችት ርዕሰጉዳዩ በአፋር ልዩ ስሙ ሠርዶ በሚባል አካባቢ ስለተካሄደ ተልዕኮ የሚያወሳ ቢሆንም በመጽሐፉ የፊት ሽፋን የሓየሎም አርአያን (ፈንቅልን) ምስል መጠቀማቸው ነበር፡፡ በመሰረቱ ሜ/ጄ ኃየሎም የሠርዶ ውጊያ የተካሄደበት ሪጅን አዛዥ እንደመሆናቸው ስለተልዕኮው ለበላይ አካል ሪፖርቱን ያጠናቀሩት እሳቸው ቢሆኑም፤ በውጊያው ላይ አልተካፈሉም፡፡ የሠርዶ ውጊያ ዋና መለያው ደግሞ የውጊያው ቦታ ለመድረስ የሚኬድበት መንገድ ጫማ እስከሚያቀልጥ የሚደርስ ንዳድ ባለበት አካባቢ የተፈጸመ ጀብድ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የሠርዶ ባለገድሎች ውጊያው ላይ የተገኙት እንጂ ጸሐፊው በሽፋኑ ላይ እንዳስቀመጡት አልነበረም፡፡ በዚህ ምክንያት መረር ያለው ትችት ጸሐፊው ያንን ያደረጉት ለገበያ ጥቅም ነው የሚል ነበር፡፡

በተመሳሳይ የዛሬው መጽሐፍም ርዕስና የፊት ሽፋን ስዕልም ጸሐፊውን በመሰል ስህተት ተተቺ ሳያደርጋቸው አይቀርም፡፡ ምስሉንና ርዕሱን አይተን ወደውስጥ ስንገባ የተወሰኑ ስለመለስ በተናጠል ያካተቷቸው ምዕራፎች (ከ21 ምዕራፎች መካከል ምዕራፍ 1 እና 2 ብቻ ሌላ መጨመር ካስፈለገ ምዕራፍ 6) ካልሆነ በስተቀር ዝርዝሩ ስለአጠቃላይ ትግሉ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ታዲያ ርዕሱ ‹‹መለስና የህወሓት ትግል ጉዞ መባሉም ሆነ የመለስ ፎቶ በፊት ሽፋኑ ላይ መቀመጡ ተገቢነት ማጠያየቁ አይቀርም፡፡ እኒህ ሁለቱ ምዕራፎችም ቢሆኑ በቂ ሊባል የሚችል አዲስ ዝርዝር ያላቀረቡ መሆናቸው ግምት ውስጥ ሲገባማ ጥያቄው ይበልጥ ይጠነክራል፡፡ እንደዚህም ሆኖ መጽሐፉ እንደሽፋኑ ስዕልና ርዕሱ አወሳለታለሁ ያላቸውን ሰው ዝርዝር መረጃ ከራሳቸው አንደበት ለጉዳዩ በሚመጥን ደረጃ እንዲያካትት ማድረግ ለመቻሉ አሳማኝ መከራከሪያ ማቅረብ የሚከብደው ይሆናል፡፡ በኀትመት ደረጃም ለተጠቀሱት ሰው ክብር የሚመጥን ጥራት ያሟላ አይደለም፡፡ ጸሐፊውን ይበልጥ የሚያሳጣው ደግሞ በተቀሩት ምዕራፎች የድርጅቱን የትግል ጉዞ ለመተረክ ሲሞክሩ ለመጽሐፉ ለሰጡት ርዕስ ‹ታማኝ› ለመሆን ሲሉ የመለስን ስም እንደማጣፈጫ በያገኙበት ሁሉ መክተት ግድ እንደሆነባቸው ሲታይ ነው፡፡ የሚጠቅሷቸውም በዝርዝር ሁኔታ ሳይሆን፤ ‹‹መለስ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ነበሩ›› በማለት ስለሆነ፤ ‹ስለሚወሳላቸው› ሰው በቂ ነገር እንዳላገኙ አመላካች ናቸው፡፡ በእርግጥም ከሁለቱ/ሦስቱ ምዕራፎች ውጪ በመጽሐፉ የተካተቱት መለስን ብቻ በቀጥታ የሚመለከቱ የታሪክ ክስተቶች እጅግ ጥቂት ናቸው፡፡ መቼም ጸሐፊው ይሄ በራሱ በቂ ነው ብለው አምነዋል፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ምዕራፎች ውጪ የአቶ መለስ ስም በገቡባቸው በርካታ ቦታዎች የሌላ አንድ ታጋይ አባል ስም ቢተካ (ለምሳሌ የአቶ አባይ ፀሐዬ) የመጽሐፉን ርዕስ ሊያስቀይር የሚችል ይሆናል፡፡

የመጽሐፉ ርዕስ ‹ቅቡል› ሊሆን የሚችለው ስለአቶ መለስ በቀረበው ዝርዝር ሽፋን ሳይሆን፤ ጸሐፊው አቶ መለስ ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችን ለማስተባበል የለፉበት መሆኑ ሲታሰብ ነው፡፡ ይህ ልፋት ይመስላል ስለመጽሐፉ አስተያየት የሰጡትን ዶ/ር አረጋዊ በርሄ ከጽሑፉ ጀርባ ራሳቸው አቶ መለስ ስለመኖራቸው እንዲያምኑ ያደረጋቸው፡፡ በግሌ አቶ መለስ እዚህ ውስጥ ያሉበት አይመስለኝም፡፡ በእርግጥ ሁለት ቦታዎች ላይ ኮ/ሉ ልክ እራሳቸው መለስን የጠየቁ የሚመስሉበት ቦታ አጋጥሞኛል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ስለእሳቸው በደንብ እንዲጻፍ አልፈለጉም ማለት ነው፡፡ የአቶ መለስ ህልፈተ ሕይወት ከሚያስቆጨን ነገር አንዱ የራሳቸውን ግለታሪክ ሳይጽፉልን ማለፋቸው ነው፡፡ ለማንኛውም የኮ/ሉ መጽሐፍ እንደእኔ እንደእኔ እነዚያን 14 ገጾች (ፎቶዎቹን ሳይጨምር) የፈጁ ሁለት ምዕራፎች ስናወጣ የመጽሐፉ ርዕስ የህወሐት ትግል ጉዞ ብቻ መሰኘቱ ይበቃው ነበር እላለሁ፡፡ በርዕሱ የአቶ መለስን ስም ሳይጠቅሱ ስለመለስ አስተዋጽኦ አሁን ባለበት ደረጃ ማቅረብ እንደሚቻል የአቶ ሙሉጌታ ደባልቀው ‹‹ጋላህቲ ሠጊ›› ምስክር ይሆነናል፡፡ ለምሳሌ ‹‹ጋላህቲ ሠጊ›› አቶ መለስን በፖለቲካው ብቻ ሳይሆን የሚሊታሪ ዶክትሪኑም ነዳፊ/አስፋፊ አድርጎ ያቀርባቸዋል፡፡ ለማንኛውም የመጽሐፉ ርዕስ አመራረጥም ሆነ የይዘት አቀራረብ አንድምታ የሚያስገነዝበን ነገር አለ፡፡ እርሱም የአቶ መለስን ስብዕና ክብረት ግንባታ ሂደት ነው፡፡ ባሳለፍናቸው 2/3 ወራት ስለአቶ መለስ ከህልፈተ ሕይወታቸው ጋር ተያይዞ የሚደጋገመው የሁሉ ነገር አድራጊ ፈጣሪ አድርጎ ማቅረብ መንፈስ ፖለቲካዊ ፋይዳው እንደተጠበቀ፤ ከ1993 ወዲህ ቀስ እያለ ያቆጠቆጠው ስብዕናቸው ግንባታ ጥረት የመጨረሻ ደረጃ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ ይህ ግንባታ በ1997 ፈተና የገጠመው ቢሆንም አንሰራርቶ ከ2000 ወዲህ ያለማቋረጥ ማደግ ጀምሯል፡፡ እድገቱ በተለይ 2002ዓም ከፍተኛ ፍጥነት በማሳየት አሁን የደረሰበት ደርሷል፡፡ ስለዚህ በ2002 የታተሙት የአቶ ሙሉጌታ ደባልቀውና የኮ/ል ኢያሱ መጽሐፎች የግንባታው አካል ይሆኑ ብለን እንድናስብ የሚያደርጉን ናቸው፡፡

የኮ/ሉ መጽሐፍ ከይዘቱ ሽፋን ጋር ባይመጣጠንም ለርዕሱ የአቶ መለስን መምረጣቸው ለመጽሐፉ ቀልብ የሚስብ ብራንድ የመፍጠር ሙከራም አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ እንዲህ ከሆነ፤ በእርግጥ ዓላማቸውን ማሳካት እንደቻሉ ሊታሰብ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከምርቃቱ ጋር በተያያዘ አንድ ሰው ብቻ የመጽሐፉን 40,000 ቅጂ መግዛታቸው በወቅቱ መዘገቡ ጥሩ ማሳያ ይሆነናልና፡፡ በመሰረቱ ኮ/ሉ በ‹‹ሠርዶ››ውም ሆነ በዚህኛው መጽሐፍ የተለየ መደገፊያ ሳይሹ በመጽሐፎቻቸው ይዘት ብቻ ቢቀርቡ ይዘቶቹ በራሳቸው መቆም የሚችሉና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መሆናቸውን የምመሰክረው በእርግጠኝነት ነው፡፡

## የምንጭ አጠቃቀም

የህወሓትን ‹ታሪክ› ለመጻፍ የሞከሩ የትግሉ ተሳታፊዎች እስካሁን በድርጅቱ የተከማቹ ሰነዶችን በአግባቡ የመጠቀም ዕድል ያገኙ አይመስልም፡፡ አረጋዊ በርሄ (በሪሁ) ‹‹The origin of TPLF›› በተሰኘው መጽሐፋቸው ገጽ 579 ግርጌ ማስታወሻ ላይ ሕወሓትን አስመልክቶ አንዳንድ ምንጮችን ያለ ጠ/ሚሩ ፈቃድ እንደማይገኝ የገለጹት ሲታሰብ እነዚህን ምንጮች ለማግኘት ጥረት ማድረግ የግድ እንደሚል አመላካች ነው፡፡ ኮ/ል ኢያሱ መንገሻ ለ‹‹ሠርዶ›› መጽሐፋቸው ከተጠቀሟቸው ምንጮች አንዱ ስለተልዕኮው በሜ/ጄ ኃየሎም የተዘጋጀ ሪፖርት ነበር፡፡ በይዘቱ ላይ በግልጽ ባይንጸባረቅም፤ በመጽሐፉ የምንጭ ዝርዝር ላይ የህወሓት መረጃና ዶክመንቴሽን ክፍልን ለመጠቀም እንደቻሉ ይጠቁማል፡፡ ስለዚህ በዚህኛው መጽሐፋቸው ይሄን የበለጠ እንደሚያደርጉት ተስፋ ብናደርግ ስህተት አይሆንም፡፡ በተግባር ግን ይህ አልሆነም፡፡ ይህም መጽሐፉ ሌሎች መገለጫዎች ቢኖሩትም፤ ሦስተኛውን አቀራረብ ለመሞገት ያለመ እንደመሆኑ መጠን፤ የሚጠበቅበትን የበላይነት የሚያስገኝለት የምንጭ አጠቃቀም እንዳያሟላ እንዳደረገው ሙግት ያስነሳል፡፡ ስለዚህም አስገደ ወይም አረጋዊ በርሄ አሊያም የውብማር የጻፉትን አቦይ ስብሐት ነጋ ለእፎይታ በሰጡት ቃለመጠይቅ ወይም ሙሉጌታ ደባልቀው በጻፉት መጽሐፍ አሊያም ስሙን እንዲጠቀስ ካልፈለገ አንድ ታጋይ ባገኙት መረጃ ለማጣረስ እንደማይቻላቸው የታሪክ አጻጻፍ ስነዘዴ ያጋልጣል፡፡ ጸሐፊው ምንም እንኳን ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ በትግሉ ውስጥ የቆዩ ቢሆንም ‹‹... ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ... ከእኔና እኔን ከመሰሉ ታጋዮቹ ውጪ የማንንም ምስክርነት ይሻል ብየ አላስብም› በማለት ራስ ለራስ ምስክርነት እየሰጡ ታሪክ ሊጻፍ አይችልም(ገጽ 41)፡፡ ምክንያቱም ከሁለት ወገን በሚገኙ መረጃዎች መካከል አንዱ ከአንዱ የበለጠ የሚሆንበት ልዩ ጸጋ የለውምና፡፡ ይህም በመሆኑ በእንዲህ ዓይነት የሚጻፉ ‹ታሪኮች› በቀላሉ ተግዳሮት የሚገጥማቸው መሆናቸው አይቀርም፡፡ ኮ/ል ኢያሱ የኢህዴን/ብአዴንን ታሪክ አስመልክቶ የሚነሱ ትችቶችን ለመሟገት የሚያቀርቡት ማስረጃ በኢህዴን የተዘጋጀውን ‹‹ፅናት››ን ነው፡፡ ችግሩ ሲጀመር ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀበት መንገድና ይዘቱ ራሱ የትችቱ መነሻ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በአጠቃላይ እንዲህ በአከራካሪ ጉዳዮች ላይ ወደእውነታው ያደላና የማያፈናፍን ‹ታሪክ› ለማዘጋጀት ልዩነት መፍጠር የሚያስችል የሰነድ መረጃ አጠቃቀሙ የጎላበት እንዲሆን መጣሩ የግድ ይሆናል፡፡ በዚህኛው መጽሐፍ ግን ኮ/ል ኢያሱ መንገሻ ልዩነት መፍጠር አለመቻላቸውን እናያለን፡፡

## መጽሐፉ ሊያስተዋውቅ የሞከረው አዲሱ ዘይቤ

ኮ/ል ኢያሱ በድርጅቱና በአመራሩ ዙሪያ ስለሚነሱ አከራካሪ ርዕሰጉዳዮች የመረጡት አቀራረብ በዓይነቱ ለየት ያለ ልንለው የምንችለው ዓይነት ነው፡፡ መጽሐፉ የሚያጠነጥነው ድርጅቱ በተደጋጋሚ ከተቺዎቹም ሆነ ከተቃዋሚዎቹ ጣት የሚጠነቆልበት ርዕሰጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ከሌሎች ኃይሎች ጋር ስለነበረው ግንኙነት፣ ነጻ የትግራይ ሪፑብሊክ እንመሰርታለን ስለማለቱ፣ በተለያየ ጊዜ የውስጥ ችግሮቹን የፈታበት መንገድ፣ በኢትዮ ሶማሊያ ጦርነት ጊዜ ስለነበረው አቋም(የ1969)፣ የህወሓት ጦር ህግዴፍን ለመታደግ ወደኤርትራ የተላከበት ሁኔታ፣ የማሌሊት አመሰራረትና የመሳሰሉ ነጥቦች ላይ ነው፡፡ አንዳንድ ተቺዎች ስለይዘቱ በሰጡት አስተያየት ጸሐፊው የህወሓትን ታሪክ እንደገና ገልብጠው እየጻፉ እንደሆነ ይከራከራሉ፡፡ ለእኔ ግን ይሄን ለማድረግ የሞከሩበት መንገድ ይበልጥ ስቦኛል፡፡ እርሱም ባነሷቸው ጉዳዮች ኮ/ሉ ህወሓት አሳየ የሚሉትን ድክመት ለመጠቃቀስ መሞከራቸው ነው፡፡ በደፈናው የህወሓትን ድክመቶች ለመሸፈን የሚደረጉ ጥረቶች ስለመኖራቸው በማመን፤ ድርጊቱ ተገቢ አለመሆኑን ይተቻሉ፡፡ ይህም በጎራው ስላለው አዘጋገብ ከጭፍን ሽምጠጣ አንድ እርምጃ ወደፊት እንደመሄድ የሚቆጠር ልንለው እንችላለን፡፡ በተጨማሪም በድርጅቱ ደጋፊዎች የሚካተቱትን ጸሐፊዎች የሚፈጽሙት አንዳንድ የጭብጥ ስህተቶችን ለማረም የሚሞክርም ነው፡፡ ለምሳሌ በተለምዶ የሚወሰዱ ነገሮች በጥንቃቄ መታየት እንደሚገባ ያመለከቱባቸው (የህወሓት ምሥረታ ጊዜ ተብሎ በተደጋጋሚ የሚገለጸውና ድርጅቱ ራሱ የሚያከብረው ቀን ትክክለኛነት የፈተሸበት፣ በአንዳንድ ድርጊት ለምሳሌ እንደምሥረታ ያሉ ክስተቶች ላይ የተሳተፉ ሰዎች ‹ትክክለኛ› ስም ዝርዝርና ቁጥር እንዲታወቅ ለማድረግ ያደረጉት ጥረቶች ይሁን የሚያስብሉ

ወደ ገፅ 7 ዞሯል



# የልማታዊ መንግስት ምንነትና በኢትዮጵያ አተገባበሩ ሲፈተሽ

በአቻምየለህ ታምሩ እውነቱ

(በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ መምህር)

አገራችን ኢትዮጵያን ከኋላ ቀርነትና ከድህነት ለማላቀቅ በተለይም ያለፉት ሁለት መንግስታትና የአሁኑ የኢህአዴግ መንግስት የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን "ቀርፀዋል"፤የፖለቲካ-ኢኮኖሚ አስተሳሰቦችንና የተለያዩ "ርዕዮቶችን" ተከትለዋል፤ "በተግባርም" አውለዋል፡፡ በፖለቲካ-ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ረገድ ኢትዮጵያ ከአፄው አንፃራዊ የገበያ ስርዓት እስከ ባህል የቀየርንበትና ጥናት ሳናደርግ ዘለን የገባንበት የሊቀመንበር መንግስቱ ሃይለማሪያም የመጀመሪያው አስርት አመታት የስልጣን ዘመን የዕዝ የኢኮኖሚ ስርዓት፣ከኢህድሪው መባቻ የውህድ/ቅይጥ(Mixed Economy) የኢኮኖሚ ስርዓት እስከ ኢህአዴግ የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ "ፅንስ ሃሳባዊ" ፖሊሲዎችና ዛሬ የኢህአዴግ መንግስት እየሄደበት እስካለው የልማታዊ መንግስት (Developmental State) አስተሳሰቦችን "ተግብራለች"፡፡ እያንዳንዱ መንግስትና ስርዓትም ከአስር አመታት በላይ በስልጣን የቆየ ስለሆነ፣ አስተሳሰቦቹ መስራት እንደሚችሉና እንደማይችሉ ለመፈተሽ በቂ እድልና ጊዜ ስላገኙ፣ በሶስቱም መንግስታት "የተተገበሩት" አስተሳሰቦች ወይንም የተከተሏቸው ርዕዮተዓለሞች የወለዷቸው ፖሊሲዎች እንደሚሰሩና እንደማይሰሩ በበቂ ሁኔታ የመፈተሻ ጊዜ አግኝተዋል ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

የዚህ ፅሁፍ አላማ ዛሬ "በህይወት ያለው" የኢህአዴግ መንግስት እየተመራበት ያለውን የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ምንነት መፈተሽ፣ በሃገራችንም አተገባበሩ ምን እንደሚመስልና እየተሄደበት ያለውን ተመሳስሎና ተቃርኖ ማሳየት ይሆናል፡፡

ሃ ጁን ቻንግ የተባሉ ኮርያዊ የምጣኔ ሃብት ምሁር፣ የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብን ያዳበሩና ታዋቂ የሄትሮዶክስ የኢኮኖሚክስ ትምህርት አስትሳሰብ አቀንቃኝ እ.ኤ.አ በ1999 ዓ.ም 'The Economic theory of Developmental State' በሚል ባሳተሙት ጽሁፋቸው ስለ ልማታዊ መንግስት ብያኔዎችን አስፍረዋል፡፡ የዲሞክራሲያዊ መንግስት አስፈላጊነትን በተመለከተ በተነተኑበት ምዕራፋቸው፤ ዜጎች በትምህርት፣ በማህበራዊ ጉዳዮች፣ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው እንዲዳብርና የፖለቲካ ንቃተ-ህሊናቸው እንዲያድግ የዲሞክራሲያዊ መንግስት መኖር የማይተካ ሚና ይጫወታል ይሉና እነኝህን ወርቃማ ግቦች ለመምታት ደግሞ፣ በተለይም በ3ኛው የአለም ክፍል የሚገኙ አገራት መንግስታት የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብን ቢላበሱ ጠቃሚ ነው ብለው ይመክራሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተየያዘም ልማታዊ መንግስትን ሲያብራሩ፣ የአንድ አገር መንግስት በማክሮና በማይክሮ ኢኮኖሚው ላይ የአንበሳውን ድርሻ ይዞ ዕድገት ለማምጣትና ለማስቀጠል የሚያስችሉ አገራዊ እቅዶችን በማውጣት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት ነው ይላሉ፡፡ ይህንን የቻንግ አስተምህሮ እንደ ደቡብ ኮርያ፣ ሆንግ ኮንግ፣ ታይዋን፣ ቻይና፣ ሲንጋፖር ወዘተ... ያሉ አገሮች በመከተል ያስመዘገቡትን "እመርታ" ተከትሎ ባሁኑ ወቅት ኢትዮጵያም የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ "ተከታይ" ሆናለች፡፡

እዚህ ጋ የልማታዊ መንግስት ምንነትን በተመለከተ ቀጥታ የአማርኛ ቃሉን በመውሰድ የሚሰጠውን የተሳሳተ ግንዛቤ ላክል፡፡ ልማታዊ መንግስት የሚለው የአማርኛ አጠቃቀም ልማት ያመጣ ወይንም የሚያመጣ መንግስት አይነት እንደምታ ስላለው በብዙ ቦታ "ከልማታዊ መንግስታችን ጋር ወደፊት፣ ከልማታዊ መንግስታችን ጎን እንቆማለን፣ ወዘተ..." በማለት የኢህአዴግ መንግስትን "ልማት ያመጣ መንግስት" ለማለት ባብዛኛው ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ ይህ አጠቃቀምና አረዳድ ግን ስህተት ነው፡፡ ልማታዊ መንግስት ሃገራት እንደሌሎች ልማት ለማምጣት ይጠቅማሉ ብለው በልዩ ልዩ ሁኔታ እንደሚከተሏቸው ርዕዮተዓለሞች፣ ማለትም እንደ ነፃ ገበያ፣ የቅይጥና የዕዝ ስርዓት እዲሁም ሌሎች አይነት ስርዓቶች አንድ ራሱን የቻለ ርዕዮተዓለም ነው፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያ የነፃ ገበያ አራማጅ ብትሆን፣ "ልማታዊ መንግስታችን" የሚለው አጠራር ተመሳስሎው የነፃ ገበያ ስርዓት አራማጅ መንግስታችን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህ ልማታዊ መንግስታችን በምንልበት ወቅት ልክ ነፃ ገበያ ስርዓት አራማጅ መንግስታችን እንደማለት ነው፡፡ ልክ የገበያ ስርዓት ሁልጊዜ ልማት ሊያመጣ እንደማይችል ሁሉ፣ የልማታዊ መንግስት አስትሳሰብ አራማጅ የሆነ አንድ አገር ልማት ቢያምጣም፣ ባያመጣም ልማታዊ መንግስት ነው መባሉ አይቀርም፡፡

የነፃ ገበያ መስመር የሚከተሉ አገሮች የሚያሰፍኗቸው፣ቅድሚያ ታሳቢ የሚያደርጋቸውና የሚከተሏቸው እሙኖች፣ መሰረታዊ ምስሶዎች (basic fundamentals)፣ እርምጃዎችና አሰራሮች እንዳሉ ሁሉ፣ የልማታዊ መንግስት የኢኮኖሚ ርዕዮት በሚከተሉት አገራትም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እሙኖች፣ መሰረታዊ ምስሶዎት፣ እርምጃዎችና አሰራሮች መሬት ላይ መውረድ ይኖርባቸዋል፤

1. የመንግስት መዋቅር (ቢሮክራሲው፣ ለሃገር ብልፅግና ስትራቴጂካዊ ጥቅም ያላቸው የመንግስት ተቋማት፤ ለምሳሌ በኛ ሃገር ነባራዊ ሁኔታ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የውጭ ግንኙነት መስሪያቤቶችና በውስጡ ያሉ ዲፕሎማቶች፣ አምባሳደሮች፣ የፕላን ተቋማትና በመሳሰሉት በሃገር ውስጥ ወይንም በውጭ አገር በሚገኙ የታወቁ ምርጥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በላቀ ደረጃ የተማሩና በየዘርፉ የጠለቀ ሳይንሳዊ ክህሎት፣ የአመራር ብቃት ያላቸውና የላቁ ሳይንሳዊ ምርምሮችን ማድረግ የሚችሉ፣ በአጥጋቢ ሁኔታ አቅምና ብቃታቸውን ያስመሰከሩ፣ የሞያና የእውቀት ሰዎች (technocrats) መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ሳይሆን ግን በልማታዊ መንግስት አስትሳሰብ እድገትና ልማትን ማሰብ ፈረሱን ከኋላ ጋሪውን ከፊት አደርጎ ጋሪው ፈረሱን እየጎተተ ዳገቱን ይወጣል ብሎ እንደማሰብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚታሰብም፣ የሚታለምም አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዮኒቨርሲቲዎች እና የሞያና የቴክኒክ ተቋማት የሚያመርቷቸው የተማሩ የሰው ሃይሎች ባብዛኛው በሂሳብ፣ በሳይንስና በኮምፕዩተር የእውቀት ዘርፎች የተማሩ ቢሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግርን፣ የኢንዱስትሪ መስፋፋትንና እድገትን ሊያፋጥንና ሊያሳልጥ እንደሚችል ቻንግ ይመክራሉ፡፡ ማለትም፣ ከላይ የቀረበው የትኩረት አቅጣጫ የኢንዱስትሪውንና የአምራች (manufacturing) ዘርፉን በፍጥነት ላቅ ወዳለ ከፍታ ባጭር ጊዜ እንዲራመድ ይረዳዋል፡፡ በነገራችን ላይ ዛሬ በሀገራችን እየተሰራበት ያለው የ70/30 የተማሪዎች ቅበላ ምጣኔ (70% የተፈጥሮ ሳይንስና፣ 30%የማህበራዊ ሳይንስ) ከላይ ከቀረበው የትኩረት አቅጣጫ ጋር ተመሳስሎ ያለው ይመስላል፤ ምንም እንኳ የኛ 70% ባብዛኛው ወደ ምህንድስና የእውቀት ዘርፍ ያጋደለ ቢሆንም፡፡

ይህንን ካልን በኋላ ከላይ በቀረበው አኳኋን የእኛን አገር አካሄድ ወደ መመዘን እንሻገር፡፡ በኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ ከላይ በከፊል የተዘረዘሩትን ስትራቴጂካዊ ተቋማት የሚያንቀሳቅሱ አመራሮች የፓለቲካ ሹመኞች እንጂ በየዘርፉ ከላይ በቀረበው ጥልቀት ያህል መሰረታዊ ክህሎት እንዳላቸው ታሪካቸው አያሳይም፡፡ እዚህ ጋር እንግዲህ ወራጅ አለ ማለት ነው፤ የእኛ አገር በቁጥር 1 ስር ከላይ የቀረበውን እሙን አላሟላችምና፡፡ የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብን እስከተከተልን ድረስ፣ የአስተሳሰቡን ጥቅሞችና ግቦች ለመጎናፀፍ፣ ከላይ የቀረበውን አሰራር በማስፈን ረገድ ረጅም ርቀት መጓዝ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ በነገራችን ላይ ከላይ የተቀመጠውን እሙንና አሰራር በልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ በምትመራዋ ኢትዮጵያ አለመስፈን ማለት ልክ በነፃ የገበያ ስርዓት አስተሳሰብ በሚመራ እንደ አሜሪካ አይነት ሃገር ውስጥ፣ መንግስት በከፍተኛ ሁኔታ ጣልቃ በመግባት እንደሚፈፅመው አይነት የርዕዮተ አለም ጥሰት እንደማለት ነው፡፡

ከላይበሁለተኛደረጃየተቀመጠው ኢንዱስትሪውንና አምራች ዘርፉን ዮኒቨርሲቲዎች፣ የሞያና የቴክኒክ

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

...የሞያና የቴክኒክ ተቋማት የሚያመርቷቸው የተማሩ የሰው ሃይሎች ባብዛኛው በሂሳብ፣ በሳይንስና በኮምፕዩተር የእውቀት ዘርፎች የተማሩ ቢሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግርን፣ የኢንዱስትሪ መስፋፋትንና እድገትን ሊያፋጥንና ሊያሳልጥ እንደሚችል ቻንግ ይመክራሉ...



አቤ ቶኪቻው
abetokichaw@gmail.com

# ኬኒያን በድርበቡ!

ይምጡ ወዳጄ ወደ ኬኒያ ናይሮቢ ይገቡዎት ልሂድ… ብቻዎትን ግን እንዳይሞክሩት። የናይሮቢ ፖሊስ ሀበሻ ሲመለከት የርሃብ ስሜቱ ይመጣል… ከዛም ያዛጋል። አፉን እንደከፈተም ቀጥታ ወደ እርስዎ ይመጣል። ይሄኔ አፉን የሚዘጉበት ሽልንግ፣ ወይም ደግሞ ክሽን ያለች ኪሱዋሊ ቋንቋ፣ አለበለዛ ደግሞ ቆፍጠን ያለ እንግሊዘኛ ከሌልዎት በስተቀር ወደ ኬኒያ ለመሄድ አይሞክሩ። አንድ ዘዴም አለ፤ ሙሉ ልብስዎ ላውንደሪ ገብቷል? ከደረሰ እርሱን ባማረ ከረባት ግጥም አድርገው ይልበሱ። ይሄኔ የኬኒያ ፖሊስ ዘንድ የተከበሩ ኖት!

እስቲ መጀመሪያ ሰላምታው ይቅደም፤ እንዴት ከረሙልኝ…! "ፍትህ ጋዜጣ ከምትወጣ ቀዳማዊት እመቤት ከቤተመንግስት ቢወጡ ይቀላል!?" ተብሎ እየተወራ ባለበት ሰዓት ፍትህ በአዲስ ማሊያ በመምጣቷ ዳግም ተገናኝተናል። እሰይ እንኳንም ተገናኘን!

እኔ የምለው ወይዘሮ አዜብ ግን ምን አስበው ነው ከቤተ መንግስቱ አልወጣም ያሉት…? አንዳንዶች በአቋራጭ "ቤተመንግስቱን ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ተቆጣጥረነዋል!" እንዳንባል ሰጋን እያሉ በየጓዳው እያወሩ እኮ ነው። የምር ግን ማስጠንቀቂያ ደንገጥም የማያደርጋቸው ሴት እሳቸውን አየሁ… አሃ ለካስ ታንክ ተደግፈው መፅሐፍ ሲያነቡ የነበሩት ሰውዬ ባለቤት ናቸው!

ለማንኛውም ዛሬ ኬኒያን በድርበቡ ላሳይዎ ነው ሀሳቤ… እና እሜቴን ለቀቅ አድርገን ናይሮቢን ጠበቅ እናድርግ፤ ጎሽ አዲስ መስመር ላይ እንገናኝ፤

አርባ ሚሊዮን ህዝብ የሚኖርባት ኬኒያ ያለፈው አመት በጀቷ ከአስራ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ይበልጥ ነበር። ሰማኒያ ሚሊዮን ህዝብ ያላት ኢትዮጵያችን አስራ አንድ ቢሊዮን ዶላር በጅታ ከእኛ በግማሽ የሚያንሱት እነሱ እንዴት ይሄን ሁሉ በጀቱ ብለው አይሰማዎ… ሰዎቹ በበጀት ብቻ ሳይሆን በሙስናም ስለሚበልጡን ብዙ አይቆጩ። በነገራችን ላይ ለህዝብ ተወካይ አባላት ወይም እነርሱ MP (Members of parliament) ለሚሏቸው የፓርላማ ሰዎች ክፍያ በአለም ራሱ ከፍተኛው የኬኒያ ሳይሆን አይቀርም። ይህ የተደረገው ሙስናን ለመከላከል ነበር። ነገር ግን የኬንያ ባለስልጣናት ገንዘብ አይንቁም። የፈለገ ቢከፈላቸው ሌላም ይፈልጋሉ!

ፖሊሱም የዚህ ነፀብራቅ ነው። ብዙ ጊዜ ታድያ ፖሊስ የሚበረታው ስደተኛው ላይ በተለይም ሀበሻው ላይ ነው።

በናይሮቢ ከተማ በርካታ ሀበሾች አሉ። ብዙዎቹ "ከመንግስታችን ጋር ተኳርፈናል" በሚል በስደተኝነት ተመዝግበው ከአሁን አሁን ወደ አሜሪካ፣ ካናዳ እንዲሁም አውሮፓ ለመሄድ ያቆበቆቡ ናቸው።

እስቲ እኔ እኖርበት የነበረው የሀበሾች ሰፈር እንሂድማ…

ናይሮቢ በርካታ ኢንተርናሽናል ድርጅቶች ለዋና ቢሮነት የሚመርጧት አሪፍ የአፍሪካ ከተማ ብትመስልም እኔ እና ሌሎች ሀበሾች ያለንበት ሰፈር ሲመጡ ግን "ድንቄም የአለም አቀፍ ድርጅት መቀመጫ" ይሏታል።

ይህ ቦታ የከተማዋ ምስራቃዊ ክፍል ነው። "ኢስሊ" ይባላል። በተለይ አስረኛ የሚባለው ሰፈር ሲሄዱ መርካቶ የገቡ ነው የሚመስልዎ። ታድያ ማልደው አይሂዱ ማንም በጠዋት አይነሳም። በኢስሊ ነጋ የሚባለው ቢያንስ አራት ሰዓት አካባቢ ነው።

የናይሮቢ ምስራቃዊ ክፍል "ኢስሊ" በዝናብ ጊዜ ጭቃው በፀሀይ ጊዜ አቧራውን ሲያዩ የኬኒያን መንግስት ማማረር ይጀምራሉ። ትንሽ ሲቆዩ ግን ማማረሩን ይተዉታል። ምክንያቱም ይለምዱታል። ለማንኛውም ይህ ቦታ የኢትዮጵያውያን የሱማሌያዊያን እና የኤርትራዊያን መገኛ ነው።

ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ያሰቡት ተሳክቶ ወደ ፈረንጆቹ ሀገር ከማምራታቸው በፊት በኢስሊ የተለያየ ስራ ይሰራሉ። "ማታቱ" የተባለችው በመጠኗ ከሎንችና ጋር የምትስተካከል የትራንስፖርት መኪና ላይ ገንዘብ ተቀባይ ሆነው የሚሰሩት ብዙ ግዜ ኢትዮጵያውያን ወይም ኤርትራውያን ናቸው። ቀደም ባለው ጊዜ ሹፌርም ሆነው ይሰሩ እንደነበር ሰምቻለሁ። በኋላ ላይ ግን ኬኒያውያን አመፁ "እኛ በሀገራችን ስራ አጥ ሆነን እነርሱ እንዴት የማታቱ ሹፌር ይሆናሉ" ብለው "ቀወጡት" ከዛ ወድያው መንግስታቸው "ከዚህ በኋላ አበሻ የማታቱ ሹፌር አያሳየኝ" አለ እና ዜጎቹን አስደሰታቸው።

"ቀወጡት" የሚለው ቋንቋ በአራዳ ብሂረሰብ አባላት ዘንድ የተለመደ ሲሆን "ረበሹ፣ ሀገር ይያያዝ አሉ" የሚል ትርጓሜ አለው። በኬኒያ "መቀወጥ" ብርቅ አይደለም። ማታቱ ውስጥ ሲሳፈሩ ሙዚቃው "ቀውጢ" ነው። መምህራን እና ሌሎች ሰራተኞች በየግዜው ደሞዝ አነሰን እያሉ ይቀውጡታል። የትራንስፖርት ዋጋ ናረ ብሎ ተሳፋሪው ይቀውጠዋል። ወዘተ ሆነ ብለው እነ ወዘተም ይቀውጡታል። ታድያ አንድም ጊዜ "ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳ የሚያራምዱ ግለሰቦች" ሲባሉ ሰምተን አናውቅም። መንግስት ከቻለ ይመልስላቸዋል። ካልቻለ ምክንያቱን ያብራራል። አለቀ!

እናልዎ፤ በርካታ ኤርትራዊያን ወዳጆቻችን በናይሮቢ ኢስሊ የማታቱ ባለቤት ናቸው። ነገር ግን መኪናቸውን ለመዘወር ህጉ አይፈቅድላቸውም። ስለዚህ ኬኒያዊ ሹፌር መቅጠር አለባቸው ማለት ነው። ባይሆን ገንዘብ ተቀባዩ አበሻ ይደረጋል ወይም ራሱ ባለቤቱ ይሆናል። አንድ የአዲሳባ ታክሲ ሼፌር አባባል ትዝ አለችኝ "ቻንስ ከሌለህ በራስህ ታክሲ ረዳት ትሆናለህ!" የምትል!

ከማታቱ ሌላ አበሻ በኬኒያ የሚሰራው ስራ ጫት ንግድ ነው። ጫት ንግድ ብቻ ሳይሆን ጫት መቃምም ዋናው የሀበሻ ስራ ነው። ለዛውም ሰዓት ዝንፍ ሳይል በትጋት የሚሰራ የታታሪ ሰው ስራ ነው። ጫት ቅሚያ። ንጥቂያ አይደለም። መቃም ነው። የውበት ሳሎን፣ ሙዚቃ ቤት፣ አነስ ያሉ ምግብ ቤቶች እና አልፎ አልፎ ድለላም የአበሻ ስራ ናቸው። በኢስሊ ዋነኛ ሀብታም ሱማሌዎች ሲሆኑ፤ ከትልልቅ ህንፃዎች ጀምሮ እስከ ትንንሽ የህንፃ መሳሪያ መሸጫዎች ድረስ ሶማሊያውያን ተቆጣጥረዋቸዋል። ይሄ በኢስሊ አካባቢ ነው በጠቅላይ ናይሮቢ ግን ከፍተኛው ባለሃብቶች ህንዶች ሳይሆኑ እንደማይቀር እጠረጥራለሁ።

ኬኒያ ሱማሊያን "አረጋጋለሁ" ብላ ከአልሸባብ ጋር ጦርነት ከገጠመች ወዲህ ፍንዳታ የተለመደ የከተማዋ ክስተት ሆኗል። በቤተ ፀሎት ስፍራ እና በሱቅ አካባቢ "ዱ…. ደሽ" ማለት ተለምዷል። እዚህ ጋ ከአልሸባብ ጋር ኢትዮጵያስ ትፋለም የለ እንዴ!? የታለ ፍንዳታው? ብሎ የሚጠይቅ ይኖራል። ባይኖርም እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ አልሸባብ የማያፈነዳበትን ምክንያት መጠርጠሬ አይቀርም። ጠርጥሬም ለእርስዎ መናገር ግዴታዬ ነው፤ ይከተሉኝማ…

በኬኒያ ከተማዎች አልሸባብ ተደጋጋሚ ፍንዳታዎችን አድርሷል። በኢትዮጵያ ግን ምንም ሰምተን አናውቅም። ምክንያቱ በጣም ግልፅ ነው። የደህንነት ሀይሎቻችን ጥንካሬ አይምሰልዎ! ኢትዮጵያዊ የፈለገውን ገንዘብ ማባበያ ቢሰጠው በሀገሩ ላይ ጥቃት አይሰነዝርም።

በኬኒያ ግን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ "ፔሳ" ብቻ ነው የሚያስፈልገው። "ፔሳ" ማለት ገንዘብ ነው። ፔሳ ካለ በኬኒያ የፈለጉት ነገር ሁሉ አለ። አጋነንክ አይበሉኝና… ቢሉኝም ይበሉኝ፤ ኬኒያ ውስጥ ግን፤ የብሩ መጠን ይለያያል እንጂ የቤተመንግስቱም ቁልፍ ይሸጣል።

እዝችጋ አንዴ ወደ አዲሳባ ደረስ ብለን እንመለስ፤ ይህንን የኬኒያ ሁኔታ የነገርኩት አንድ ወዳጄ "…እንደዚህማ ከሆነ ወይዘሮ አዜብም አልወጣም ብለው ስላስቸገሩ ለአቶ ሃይለማሪያም የፈጀውን ብር ፈጅቶ በቦንድም ቢሆን አዋጥተን ለምን ከኬኒያ ቤተመንግስቱን አንገዛላቸውም" ብሎ አሽሟጦኛል። የምር ግን እኒህ ሰውዬ አሁንም ድረስ ከሰፈራቸው ቤተመንግስት እየተመላለሱ ነው የሚሰሩት አሉ። በጣም አንጀቴን ነው የበሉት። እስቲ አስቡት አንድ "የተከበሩ" ጠቅላይ ሚኒስቴር ምሳ ቋጥረው ስራ ውለው ሲመለሱ! ለነገሩ አንዳንዶች እንደሚሉት ቂም ቋጥሮ ስራ ከመስራት ምሳ ቋጥሮ ስራ መስራት በስንት ጣዕሙ! ማነው ቂም ቋጥሮ ሲሰራ የነበረው? ብለው እንዳያስጨንቁኝ… እኔ ስም አልጠራሁም። ነብስ ይማርም አላልኩም። ሆ ሆ… ወዳጄ ሌላ ነገር ሳይመጣ ወደ ናይሮቢ ወሬያችን እናሳልጥ…!

እናም በኬኒያ አልሸባብ ከሚያ ደርሰው ፍንዳታ ጀርባ፤ ብዙውን

ወደ ገፅ 30 ዞሯል



ጥበብና ማኅበራዊ

# የአጻጻፍ ስርዓትን ስለማሻሻል

በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)

ከረዥም ጊዜ አንስቶ የአማርኛን የአጻጻፍ ስርዓት፣ በተለይ ደግሞ የሞክሼ ሆሄያትን መቀነስ አስመልክቶ ብልጭ ድርግም የሚሉ ሙግቶች ይደረጋሉ፡፡ አሁን ደግሞ ይህ ሙግት ብልጭ ያለበት ጊዜ ነው፡፡ በቴሌቪዥን፣ በራዲዮ፣ በጋዜጦችና በመጽሔቶች የማሻሻያው ናፋቂዎችና ነቃፊዎች የመሚገቻ ነጥቦቻቸውን እያቀረቡ ነው፡፡ ይህንን መጣጥፍም ያነቃቁት እነዚህ ጽሁፎች ናቸውና ይመስገናሉ፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደጠቀሰው የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ሞክሼ ፊደላት በአማርኛ አያስፈልጉም የሚል እምነት አለው፡፡ ስለማያስፈልጉም ቢወገዱ የሚያስከትሉት ጉዳትና የሚገኘው ጥቅም ተጠንቶ ተገቢው የማሻሻያ ስራ ቢሰራ ይበጃል ይላል፡፡ ይህን ሀሳብ ከመሰረቱ በወጉ ለማቅረብ እንዲረዳ አቅራቢ ስለጽህፈት የማሻሻል ስራ ለምንነትና የተደረጉ አበይት የጽህፈት ማሻሻያዎችን በተመለከተ አነስተኛ ቅኝት አድርጓል፡፡

አንድ ቋንቋ የአፃፃፍ ስርዓቱን አንድ ጊዜ ካበጀ በሁዋላ የተበጀውን የአፃፃፍ ስርዓት ለማሻሻል የሚደረግ ውይይት ማህበረሰባዊ ትኩሳትን ያነሳሳል፡፡ የተለያዩ ሀገራት ለቋንቋዎቻቸው ያበጁትን የፅህፈት ስርዓት ለማሻሻል ያደረጉት ሙከራ ከሃይማኖት ጦርነት ጋር የሚመጣጠን ሙቀት የፈጠረባቸው የታሪክ አጋጣሚዎችም አሉ፡፡ "ፊደል ይሻሻል ወይስ አይሻሻል" የሚለው እንዴት ይሻሻል ከሚለው የበለጠ አከራካሪ ይሆናል፡፡

ፊደልን በማሻሻሉ ረገድ አዘውትረው የሚነሱ አራት ፍልስፍናዊ አመለንከቶች አሉ፡፡ እነሱም፡-

1. የመጀመሪያው አንድ የተለመደ መንገድ መኖሩ በቂ ነውነ (norm-postitivistic and point of view) የሚል አመለካከት ሲሆን፣ ዋናው የሚያስጨንቀው የተወሰነ ስር-ሰደድ ልማድ መኖሩ እንጂ የልማዱ የብቃት ደረጃ አይደለም፡፡

2. ሁለተኛው አንድ ስር-ሰደድ ስርዓት ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባው በተጠየቃዊ ድጋፍ ሲበለጽግ መሆን አለበት (Rational normative)ነ የሚል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ አመለካከት አንድ ስር-ሰደድ ልማድ በተጠየቃዊ ድጋፍ በበቂ እስኪበለፅግ ለለውጥ ክፍት መሆን አለበት፡፡

3. አንድ ስር-ሰደድ ስርዓት ጥሩም ሆነ መጥፎ መጠበቅ (መቀረስ) አለበት የሚል ነው (Plain conservatives)፡፡ ስርዓቱ ለአሰራር አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳ፣ ምክንያታዊ ባይሆንም እንኳን መቀረስ ይገባዋል የሚል እምነት ነው፡፡

4. ይህ አመለካከት የስር ሰደድ ስርዓት መኖር በራሱ የግለሰቦችን የፈጠራ ነፃነት ይገድባል የሚል ነው (Anarchitic)፡፡ ስለዚህ የስር-ሰደድ ልማዶች መኖር በአሉታዊነት ይጠይቃል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ አመለካከቶች የፅህፈትን ስርዓት ለማሻሻል በሚደረግ ውይይት በግልፅ ላይወጡ ይችላሉ፡፡ በአብዛኛው እነዚህ አመለካከቶች ከውይይቱ ጠረጴዛ ስር ይቀመጣሉ፤ በጠረጴዛው ላይ የሚቀርቡት ምክንያቶች ለማሻሻሉ ስራ እንቅፋት የሚሆኑ ቴክኒካዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በውይይቱ ዙሪያ የሚነሱ ሳይንሳዊና ፓለቲካዊ ምክንያቶችን ለይቶ በየፈርጁ ለመመደብ ያስቸግራል፡፡

የአፃፃፍ ስርዓት ማበጀት ወይም ማሻሻል ሁለት ዋና ዋና ቅደም ተከተሎችን ማለፍ ይጠይቃል፡፡

1. የፊደል መረጣ (አዲስ የአፈፃፀም ስርዓት ለሚያበጁ)

2. የአፃፃፍ ስርዓት ማበጀት (Orhography formation)

እስኪ ሀሳባችንን ግዝፍት ለመስጠት የተለያዩ የጽህፈት ማበጀት ወይም ማሻሻል ሙከራዎችንና የተገኙ ስኬቶችን እንመልከት፡፡

አንዱን ፊደልና የአፃፃፍ ስርዓት በሌላ አዲስ ፊደልና አፃፃፍ መተካት በብዙ ቋንቋዎች ላይ ታይቷል፡፡ በቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ለአጉር ቋንቋ ጽህፈት ያገለግል የነበረው የአረብኛ ፊደል በሮማን ፊደል ተተክቷል፡፡ ከአጉር በተጨማሪ በ1920ዎቹ በሶቭየት ህብረት በርካታ አነስተኛ ቋንቋዎች ፊደላቸውን ከአረብኛ ወደ ላቲን ቀይረዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በዚህ መእተ-ዓመት በጣም ውጤታማ የሚባለው የአፃፃፍ ስርዓት ለውጥ የቱርክ ቋንቋ ከአርብኛ ፊደል ወደ ላቲን ፊደል ያደረገው ለውጥ ነው፡፡

በቱርክ ቋንቋ ላይ የተደረገው የአፃፃፍ ስልት ለውጥ ከፊደል ለውጥ በላይ ነው፡፡ ይህ ለውጥ እርግጥም ባህለ-ፓለቲካዊ ለውጥ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በወቅቱ በአርብኛ ፊደል ይፃፍ የነበረው የቱርክ ቋንቋ የጽሁፍ ቋንቋው ከንግግር ቋንቋው ጋር የሰመረ ባለመሆኑ የስነ-ልሳን ምሁራን ችግሩን ለመታደግ በአርብኛ ፊደል ምትክ የላቲን ፊደል በስራ ላይ እንዲውል ሀሳብ አቀረቡ፡፡ ይሁን እንጂ የአረብኛ ፊደልና አፃፃፍ ከእስልምና ሀይማኖት ጋር በነበረው ቁርኝት የተነሳ፣ ጉዳዩ የፊደል ሳይሆን የሀይማኖት ለውጥ ተደርጎ በመወሰዱ፤ በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ውግዘት ደረሰበት፡፡ የአፃፃፍ ለውጡን ሀገሪቱን ከእስልምና ወደ ክርስትና ለመቀየር የተደረገ ሙከራ አድርገው የተረጎሙትም ብዙዎች ነበሩ፡፡ በዚህም የተነሳ የሀገሪቱ መንግስት ለተወሰኑ አመታት ለውጡን ተግባራዊ ሳያደርገው ቆይቷል፡፡ በመጨረሻም የችግሩን ምንጭ ምንነትና የተሰጠውን መፍትሄ አግባብነት በተመለከተ መንግስት የዜጎቹን ግንዛቤ ካዳበረ በኋላ ለውጡ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡

ብዙ ሀገሮች በእድሜ የበለፀገ ስር-ሰደድ የአጻጻፍ ስርዓት ባለቤት በመሆናቸው ጽሁፋቸውን መሻሻልና መለወጥ የማይፈልግ (አይቀየሬ) አድርገው ይገምቱታል፡፡ በእርግጥም እድሜ መሻሻልና ለውጥን ላላመቀበል ምክንያት ከሆነ እንደ ቻይና አጻጻፍ የማይደፈር ሊኖር አይችልም፡፡ ምንም እንኳን የአፃፃፍ ስርአቱ ውስብስብ ጉዳይ ተደርጎ መቆጠሩና በርካታ ተናጋሪዎች ያሉት መሆኑ፣ ማሻሻሉን ስራ ከባድ ቢያስመስለውም፤ ስርዓቱን ለማሻሻል የቋንቋውን መዝገበ ቃላት በሙሉ መከለስ/ ማሻሻል አስፈላጊ ቢሆንም፣ የቻይና አጻጻፍ ስርዓት ረዥምና ተከታታይ የማሻሻል ስራ ተከናውኖበታል፡፡

የቻይናን የአፃፃፍ ስርዓት ለማሻሻል ሙከራ የተጀመረው በ1890ዎቹ ውስጥ ነው (Francis 1977)፡፡ በቻይና የአፃፃፍ ስርዓት የማሻሻል ሂደት ከምዕተ ዓመት የዘለለ እድሜ ቢኖረውም ከ1918-19 ዓ.ም የተካሄደው ጽህፈትን የማሻሻል አብዮት ለቻይንኛ ጽህፈት መሻሻል በርካታ ተግባራት የተከናወኑበት ነው (Korad 1977)፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በቻይንኛ ቋንቋ የአፃፃፍ ስርዓት ላይ የተከናወኑት ለውጦች ሶስት አብይት ተግባራት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. ቋንቋው የሚፃፍባቸውን ፊደላት (character) መደበኛ እና ለአጠቃቀም የቀለለ ማድረግ፣

2. የሮማውያንን የአፃፃፍ ስርዓት (orthography) የተከተለ የአፃፃፍ ስርዓት መፍጠር፣

3. የአንድ መደበኛ ቋንቋን በሀገር አቀፍ ደረጃ አስፈላጊነት መስበክ ናቸው፡፡

እነዚህ ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ በማተኮር በተከናወኑ ተግባራት ውስብስብ የነበረውን የተለያዩ ዝርያዎች (variants) ያለው ሀንዚ ውስብስብነቱ እንዲቀልና የአንድ ሀንዚ (በቻይንኛ ለመጻፍ የሚያገለግለው አንዱ ምልክት ሀንዚ ይባላል) የተለያዩ ዝርያዎች እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡ በተለይ በ1956 በተደረገው የማሻሻል ስራ 2,238 ሀንዚዎች ተሻሽሏል፤ 1,055 የተለያዩ የሀንዚ ዝርያዎች ተወግደዋል፡፡ በተጨማሪም በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሀንዚዎች የተዋቀሩ ውህድ ሀንዚዎች በነጠላ ሀንዚ ተተክተዋል፡፡ ከዚያም በ1958 ዓ.ም የተደረገውን ማሻሻያ ጥናት መሰረት አድርጎ ለቻይና ኮንግረስ የቀረበውን ሀሳብ ኮንግረሱ ተቀብሎት፣ የቻይንኛ ስነ ልሳናዊ ፊደል (phonetic alphabet) የቋንቋው መደበኛ የጽሁፍ ስልት እንዲሆን አጽድቋል፡፡

እስካሁን ድረስ የጠቀስናቸው የጽህፈት ቋንቋን የማሻሻል ሂደት ምሳሌዎች የሚያሳዩት ዋና ጉዳይ አንድ የአጻጻፍ ስልት እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ማሻሻያ የሚደረግበት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የማሻሻል ሂደቱ እጅግ ከባድና እልህ አስጨራሽ ነው፡፡ በአብዛኛው የማሻሻል ስራው ከባድነትና እልህ አስጨራሽነት የሚመነጨው በማሻሻል ስራው ከባድነት ሳይሆን፣ የማሻሻል ስራውን አስፈላጊነት አስመልክቶ በሚደረገው ውይይትና ክርክር ርዝመት፣ መንቻካነትና ውጤት አልባነት የተነሳ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የጽህፈት ስርዓትን ለማሻሻል የሚነደፉ ፕሮጀክቶች ተቃውሞ ይበዛባቸዋል፡፡ ተግባራዊነታቸው አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በነበረው የፅህፈት ስርዓት ተኮትኩቶ ላደገው ትውልድ ማሻሻያው እንደመፍትሄ መሆኑ ቀርቶ እንደችግር ስለሚታይ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የጽህፈት ማሻሻያን ከመቀበል ይልቅ፣ ላለመቀበል ምክንያት ደርድሮ የሚከራከር ይበዛል፡፡ በየሀገሩ የጽህፈት ማሻሻያ ፕሮጀክቶች መቋጫ በሌለው ክርክር ተውጠው ይቀራሉ፡፡ ለምሳሌ የጀርመንኛ የፅሁፍ ማሻሻያ ፕሮጀክት ለረዥም አመታት የክርክር ምንጭ እንደሆነ አለ (August 1974)፡፡ በጣም ቀላል የሚመስለው የአብይ ፊደል (capital letter) አጠቃቀም እንኳ ትልቅ የሀገር ጉዳይ ሆኖ ትውልዱን በክርክር ወጥሮት አለ፡፡

አብዛኛውን ጊዜ የፅህፈት ስርዓት ማሻሻያዎች ፓለቲካዊ እሳት ይጭራሉ፡፡ ለምሳሌ ጀርመንኛ (ዶች) በጀርመን፣ በኦስትሪያና በሲዊዘርላድ መነገሩ የማሻሻያ ስራውን ፓለቲካዊ እሳት እንዲፈጥር አድርጎታል፡፡ እሳቱ ደግሞ ከብርሃኑ ሙቀቱ ያይላል፡፡ በአንድ በኩል በሶስቱም ሀገሮች ተቀባይነት ያለው በመደበኛ የአፃፃፍ ስርዓት ይፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ከየሀገራቱ የሚቀርቡት የማሻሻያ ሀሳቦች የየሀገራቱን ፍላጎት የሚያስቀድሙ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ሶስቱም ሀገራት የሚቀበሉት የማሻሻል ስራ ማከናወን ሳይቻል

ቀርቷል።

የሮማንን ፊደል የሚጠቀመው የማልያ ቋንቋ አፃፃፍ ሌላው የሀገሮች ማህበረ-ፓለቲካዊ ፍላጎት በጽህፈት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ማሳያ ነው። የማልያ አፃፃፍ ስርዓት በኢንዶኔዤያ እና በማሌዤያ ፍላጎት የተወጣጠረ ነው። በማሌዥያ ያለው የማልያ ቋንቋ አፃፃፍ የእንግሊዘኛን አፃፃፍ መሰረት አድርጎ ይጻፋል። በዚህም የተነሳ ሁለቱ ሀገራት ብዙ ነባርና የተውሶ ቃላትን በተለያየ ሁኔታ ይጽፋሉ። ለምሳሌ ማሌዥያውያን "Station" ብለው ሲጽፉ፣ ኢንዶኔዥያውያን ደግሞ "Stasion" ብለው ይጽፋሉ።

እንደቱርክ ሁሉ በ1959 የባህሳ ኢንዶኔዥያን ቋንቋ በማልያ ቋንቋ ለመጻፍ በስነ-ልሳን ምሁራን የቀረበውና በመንግስት ተቀባይነት ያገኘው የኢንዶኔዥያ ብሔራዊ ቋንቋ በህዝብ ዘንድ ትልቅ ተቃውሞ ቀስቅሷል። የሀገሪቱ ዜጎች የገዛ መንግስታቸው ለማሌዥያ አሳልፎ እንደሸጣቸው ቆጥረው በማምረራቸው ማሻሻያው አምስት አመታት እንዲዘገይ ተደርጎ ነበር (Rubin1977)።

በተለይ የበርካታ ቋንቋ ባለቤት የሆኑ ሀገሮች ቋንቋዎቻቸው ተመሳሳይ የአፃፃፍ ስልት እንዲከተሉ በሚያደርጉት ጥረት ላይ ፓለቲካዊ አመለካከት ትልቅ ተጽእኖ ማሳደሩ አዲስ ጉዳይ አይደለም። ለዚህ ደግሞ ኔዘርላንድና ቤልጂየም ድንበር ላይ የሚነገረው የደች ቋንቋ በሁለቱም ሀገሮች በተመሳሳይ ስርዓት እንዲፃፍ የተደረገው ሙከራ ጥሩ ማሳያ ነው። በሁለቱ ሀገራት ድንበር የቋንቋ ኮሚሽን በ1944 ተመስርቶ ስራ ቢጀምርም የሁለቱ ሀገሮች የፓለቲካ አመለካከት ትልቅ ተፅእኖ በማሳደሩ ፕሮጀክቱ ከባድ ሆኗል። ሁኔታው የተፈጠረው በሁለቱ ሀገሮች የሚኖሩ የደች ቋንቋ ተናጋሪዎች ለአጎራባች ቋንቋዎች ባላቸው አመለካከት የተነሳ ነው። ለምሳሌ የቤልጂየም ተናጋሪዎች Kultuur የሚለው ቃል ውስጥ "K" በ "C" ቢተካ ከፈረንሳይኛ ጋር ይመስላል ብለው ይሰጋሉ፤ ቋንቋቸው የፈረንሳይኛ ተጽእኖ እንዲያርፍበት አይሹም። በኔዘርላንድስ በኩል ያሉት ተናጋሪዎች ደግሞ Cultuur ብለው መፃፍ ይፈልጋሉ። ለእነሱ "K"ን መጠቀሙ በጀርመን ቋንቋ ተፅእኖ ስር መውደቅ ነው። ይህ የሚያሳየው የጽህፈትን ስርአት የሚወስነው የጽህፈት ስርአቱን ቀና ለማድረግ ታስቦ በነፃ አመለካከት ብቻ አለመሆኑን ነው። በአጠቃላይ የጽህፈት ማሻሻያ ስራን ሰፋ አድርገን እንደማህበረሰባዊ ሙከራ (Social experiment) ልንመለከተው ይገባል። በዚህም ሂደት ማህበረ-ስነ ልሳናዊ ጉዳዮች (Socio–linguistics factors) ጣልቃ መግባታቸው አይቀሬ ነው። በዚህም የተነሳ ለሁሉ አገልጋይ፣ ሁሉን አስደሳች የሆነ ታላሚ (ideal) የአፃፃፍ ስርዓት ማበጀት አዳጋች ነው። ይህ ማለት ግን ጽህፈትን የማሻሻል ስራ ፈፅሞ አይቻልም ማለት አይደለም፤ በርካታ ጥናቶች መደረግ አለባቸው፤ በርካታ ውይይቶች በጥናቶቹ ውጤት ላይ መካሄድ አለበት ማለት ነው። የትኞቹ ማህበረ-ፓለቲካዊና ማህበረ-ስነ ልሳናዊ ጉዳዮች የማሻሻሉ ፕሮጀክት ላይ የበለጠ ተጽእኖ እንደሚያደርሱ ተለይተው ሊታወቁና ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

የአማርኛ ፊደልን ስለማሻሻል

እስከዛሬ የሰው ልጅ ከሰራቸው ስርዓተ ምልክቶች ውስጥ እንደጽህፈት ለዝመናውና ላለበት ስልጣኔ አስተዋፅኦ ያበረከተ የለም፤ ወደፊትም ሊኖር ይችላል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። እስቲ አለምን ያለጽህፈት ለማሰብ እንሞክር፤ መጽሀፍ የለም፣ ጋዜጣ የለም፣ ደብዳቤ ወይም ኢሜል የለም፣ የእውቀት ሁሉ ምንጭ የሆነው ኢንሳይኪሎፒዲያ የለም፣ ታክስ ሪፓርት የለም፣ የኮንፒውተር፣ የቲቪ፣ እና የሌሎች ውስብስብ ፈጠራዎች ማንዋል የለም ... ያለ እነዚህ ሁሉ ደግሞ ዘመናዊውን አለም ማሰብ አይቻልም። አሁንም ሆነ ወደፊት ጽህፈት የዘመናዊው አለም የማዕዘን ድንጋይ ነው።

የሰው ልጅ ባህላዊና ማህበራዊ ታሪክ ስንመረምር ጽህፈት የቅርብ ጊዜ ግኝት እንደሆነ እንረዳለን። በተለይም ረዥም ዕድሜ ካለው ከንግግር ቋንቋ ጋር ስናስተያየው የሰው ልጅ ጽህፈትን መጠቀም ከጀመረ 10 ሺህ ዓመቱ (ቢበዛ 12 ሺህ ዓመት) ነው (Basserat, 1978)። በዓለም ላይ ተሰራጭቶ አለማቀፋዊ ይዘት የያዘበትን ጊዜ ከግምት ካስገባን ደግሞ የበለጠ የቅርብ ጊዜ ግኝት ሆኖ እናገኘዋለን።

ጽህፈት የተጀመረው ከአምልኮትና ከሀይማኖት ጋር ተያይዞ ነው። በዚህም የተነሳ በሰው ልጅ

ችሎታ አይቻሌ ተደርጎ ይገመት ነበር። ለምሳሌ በህንድ ሀገር የዝሆን ፊት ያለው አምላክ

የሚሽ የጽህፈት ጀማሪ እንደሆነ ይታመን ነበር። በግብጽም ቶት (Thoth) የተባለው አምላክ ጽህፈትን ንጉሱ ታመስ (Thamus) ይገለገልበት ዘንድ እንደፈጠረለት ፕላቶ ፌደረስ (Phaedrau) ውስጥ ይጠቅሳል። ለእንደዚህ አይነት አፈ ታሪኮች መሰረቱ ጽህፈት የተጀመረው በነገስታትና በ እነሱ ዙሪያ ባሉ ውስን የህብረተሰብ አባላት መሆኑ ነው።

በተለይ አብዛኛው ቀሳውስት ከመጀመሪያ ተጠቃሚዎች ውስጥ መሆናቸው ጽህፈት ከሀይማኖት ጋር የተያያዘ ተደርጎ እንዲወሰድ አድርጓል። ለአብዛኛው ህብረተሰብ (ሰፊው-ህዝብ) ጽህፈት እንደተአምር የሚቆጠር እጹብ ምስጢር ነው።

ጽህፈት ባህላዊ ፈጠራ ነው። ይህ ሲባል ከሰዎች ባህል ጋር ተያይዞ በምልክት ነገሮችን ከመግለጽ ተነስቶ እያዘገመ አሁን ያለበት ደረጃ የደረሰ እንጂ ሊቃውንት ተሰብስበውና ወጥነው ይህንን ድምጽ በዚህ ፊደል፣ ያንን በዚያኛው እንወክል ብለው የፈጠሩት አይደለም። የዛሬው ጽህፈት የረዥም ማሻሻል ተደርጎበት የተገኘ እንጂ፣ነአንድ ጊዜ አልቆበት የተፈጠረ አይደለም።

የጽህፈትን ማሻሻል የሚገባው ለምንድ ነው?

ቋንቋ ከጊዜ ጋር እየተለወጠ የሚሄድ መግባቢያ ነው። በአንድ ወቅት ለአንድ ቋንቋ ተስማሚ የነበረው የጽህፈት ስርዓት የቋንቋውን ለውጥ ተከትሎ ማሻሻያ ሊደረግለት ይገባል። ይህ ካልሆነ በቋንቋውና በጽሁፍ ስርዓቱ መካከል ያለው ዝምድና ጎርባጣ ሊሆን ይችላል።

በዚህም የተነሳ የሰው ልጅ የሚጠቀምባቸው የአፃፃፍ ስርአቶች በየጊዜው ማሻሻያ ይደረግላቸዋል። በጽህፈት ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው ማሻሻል አንድ ከዚህ ቀደም ጽህፈት ያልነበረው ቋንቋ ጽህፈት ለማበጀት በሌላ ቋንቋ በአገልግሎት ላይ የዋለን ፊደል ወስዶ ፊደሉንና የአፃፃፍ ስርዓቱን ለራሱ ቋንቋ እንዲስማማ ለማድረግ የሚደረገው ነው። አንዳንድ ጊዜ ከዚህ ቀደም የጽህፈት የነበራቸው ቋንቋዎችም የነበረውን ፊደልና የአፃፃፍ ስርዓት ትተው አዲስ ፊደልና የአፃፃፍ ስርዓት ለማበጀት የሚያደርጉት ማሻሻል በዚህ ስር ይመደባል። ለምሳሌ እዚሁ እኛ ሀገር የኦሮምኛ ቋንቋ የላቲንን ፊደል ወስዶ ከዚህ ቀደም የነበረውን በኢትዮጵያ ፊደል የመፃፍ ስርዓት ሲተካ ያደረገው ማሻሻል በዚህ ስር የሚካተት ነው።

ሁለተኛው የማሻሻል ሂደት የቋንቋውን ፊደል ሙሉ በሙሉ የመለወጥና አዲስ ስርዓት የማበጀት ሳይሆን፣ የነበረውን ፊደልና የአፃፃፍ ስርዓት የበለጠ የሰመረና ለአጠቃቀም አመቺ ለማድረግ የሚደረገው ማሻሻል ነው። በዚህ ምድብ የሚፈረጁት ማሻሻያዎች ደረጃቸው እጅግ የተለያየ ነው። ማሻሻያው በጣም ቀላል የፊደልን መጨመር ወይም መቀነስ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ከፊደል ያለፈ በአፃፃፍ ስርዓቱ ላይም ለውጥ ያከለ ሊሆን ይችላል።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ትኩረት የሚደረገው በሁለተኛው ምድብ በተጠቀሰው የማሻሻል አይነት ላይ ነው፤ የነበረን ፊደልና የአፃፃፍ ስርዓት ስለማሻሻል። ለመሆኑ ጽህፈትን ማሻሻል ለምን ያስፈልጋል?

ጽህፈትን ለማሻሻል የሚያነሳሱ ነጥቦች

አንድን የአፃፃፍ ስርዓት ለአንድ ቋንቋ ተስማሚ ነው የምንለው ሶስት አበይት መመዘኛዎችን ሲያሙዋላ ነው። እነዚህም መመዘኛዎች፣

1. የአፃፃፍ ስርዓቱ ኢኮኖሚያዊነት፣
2. የአፃፃፍ ስርዓቱ ለአጠቃቀም ያለው ቅለት (አለመወሳሰብ)
3. የአፃፃፍ ስርዓቱ አያሻሜነት (unequivocality ) ናቸው።

የአንድ አፃፃፍ ስርዓት ኢኮኖሚያዊነት በዋናነት የሚገለጸው ቋንቋው ለመፃፍ በሚጠቀምባቸው ምልክቶች ብዛት (ስንትነት) ነው። በጣም አነስተኛ ፊደላትን የሚጠቀም የአፃፃፍ ስርዓት ብዛት ያላቸው ፊደላትን ከሚጠቀመው የበለጠ ኢኮኖሚያዊ ነው።

ሁለተኛው መመዘኛ ማለትም የአጠቃቀም ቅለት (simplicity) በቋንቋው ድምጾችና ድምጾቹ በሚወከሉበት ምልክት/ ፊደል መካከል ያለውን ተዛምዶ የተመለከተ ነው። አንድ የአፃፃፍ ስርዓት ለአጠቃቀም ምቹ ነው የሚባለው በፊደላቱ እና በፊደላቱ ዋጋ መካከል ቀጥተኛ የአንድ-ለአንድ ግንኙነት ሲኖር ነው። አንድ ድምጽ በአንድ ምልክት ሲወከል፤ ወይም የአንድ ምልክት ዋጋ አንድ ድምጽ ብቻ ሲሆን።

ሶስተኛው መመዘኛ ደግሞ አያሻሜነት (Unequivolality) ነው። ይህ መመዘኛ የጽሁፍን መልዕክት የማስተላለፍ አቅም ይመለከታል። አያሻሜነት በጽሁፍ የሚተላለፈው መልእክት አረዳድ ሙሉ በሙሉ በፊደላቱ ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ መመዘኛ ነው። ይህ ማለት አንድ አንባቢ ፊደላቱን ገጣጥሞ፣ የአፃፃፍ ስርዓቱን ተከትሎ በማንበብ በትክክል ጸሀፊው ለማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት ይረዳል ማለት ነው።

እነዚህ ሶስት መመዘኛዎች እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ በአንዱ መመዘኛ ነጥብ ፍጹምነትን ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ሌላውን ሊጎዳ ይችላል። ለምሳሌ ኢኮኖሚያዊነትን ለመጠበቅ ሲባል ምልክቶችን በእጅጉ መቀነስ አንድ ምልክት ሁለት ድምፆችን እንዲወክል ማድረግን ሊያስከትል ይችላል። ይህ ደግሞ የአጠቃቀም ቅለትን ያውካል። ብሎም በንባብ ወቅት አያሻሜነቱን ይጨምራል። ኢኮኖሚካል የአፃፃፍ ስርዓት አሻሚነቱ ይጨምራል።

የአማርኛ የአፃፃፍ ስርዓቱ በሶስቱ መመዘኛዎች ሲመዘን

የአማርኛ ፊደል ምድቡ ከደቡብ ሴም ፊደላት ጎራ ቢሆንም በዚህ ጎራ ካሉት ቋንቋዎች አጻጻፍ የሚለይበት ባህርያት አሉት። ቀደም ባለው ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ ፊደል የሴም አፃፃፍ መሰረታዊ ባህርይ የሆነውን የአናባቢ ምልክት አለመያዝ ያሙዋላ ነበር። ነገር ግን በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት የኢትዮጵያ ፊደል ትልቅ ለውጥ በማድረግ በሌሎች የሴም የአፃፃፍ ስርዓት በማይታይ ሁኔታ በፊደላቱ ላይ የአናባቢ ምልክት ጨምሯል። አሁን ያለው የኢትዮጵያ ፊደል አናባቢን የሚገልጽበት ወጥ ስልት የያዘው በዚያን ጊዜ እንደሆነ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

አንድ የኢትዮጵያ ፊደል አንድ ተናባቢና አንድ አናባቢ የያዘ ነው። ይህ ጥምረት የተገነባበት ሂደት ወጥና የማያሻማ ነው። ይህን አይነቱን የኢትዮጵያ አፃፃፍ ከደቡብ ሴም አፃፃፍ ቀስ በቀስ እየተለየ ከጊዜ ጋር የመጣ ይሁን ወይም ሆን ተብሎ የተደረገ ለውጥ እስከ ዛሬ ተጨባጭ መረጃ የለም (Diringer, 1968)። በሴም የጽህፈት ስርዓት ጠለል ወስጥ የኢትዮጵያ አፃፃፍ እስከ ዛሬ በልዩነት የተቀመጠ ነው። የኢትዮጵያ አጻጻፍን የመሰለነ አናባቢን በቅጥያ የማመልከት የአፃፃፍ ስርአት በጥቅም ላይ ውሎ የሚገኘው በህንድ ሀገር ነው። በህንድ ሀገር ናህሮስቲ (Kharosthi) የተባለው የአፃፃፍ ስርዓት እንደኢትዮጵያ ፊደል ሁሉ አናባቢዎችን የሚያመለክተው

ወደ ገፅ 26 ዞሯል



# ...ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንሶች እና ሰለሞን ተካልኞች...

*እንዳለጌታ ከበደ*

ይህ ፅሁፍ፣ ባለፈው ጀምሬላችሁ ከነበረው፣ ‹አብዛኛውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በአንዳንድ ከያኒ ስመስለው...› ከሚለው መጣጥፍ የቀጠለ ነው፣ ከከያኒዎቻችን መካከል ሥራዎቻቸውን ከምንወድላቸው እና ወድደንላቸው ከነበሩ ሰዎች ጥቂቶቹን አንስቼ፣ ባሕርያቸውን ከባሕርያችን ጋር ለማመሳሰል እሞክራለሁ ብዬ ነበር።

...እንዳልኳችሁ እነዚህ ከያንያን በባህርያቸውና በፖለቲካዊ አቋማቸው አንድ አይደሉም፣ ይህንን ለማወቅ ደግሞ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም፣ ሥራዎቻቸው ውስጥ ይገኛሉ፣ በቃለ መጠይቅ ጊዜም ስለራሳቸው በሚሰጡት መረጃ ይመዘናሉ፣ ይህ ማለት ግን ድምጻውያኑ (ይርጋ ዱባለ፣ ሰለሞን ተካልኝና ቴዲ አፍሮ) ደራስያኑ (ተመስገን ገብሬና ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ) በሕዝቡ ዘንድ ያላቸው ዋጋ ከፍ ያለ ለመሆኑ ጥርጥር የለኝም፣ ርግጥ ነው ያንዳንዶቹ የዝና እድሜ እንደተወለደ የሚሞት እና ‹ስሄድ አየኋት ስመለስ አጣኋት› የሚያስብል ሲሆን፣ ያንዳንዶቹ ደግሞ ውሎ ሲያድር የሚፈካ እና ‹‹የመወደድ ለዛ የሰሚ ገድ ያላቸው...› ተብሎ የሚዘፈንላቸው ዓይነቶች ናቸው፣ ይሁን፣ የእኔ ጉዳይ ከዝናቸው ጋር አይደለም፣ የእኔ ጉዳይ በየባህርያቸው ለይተን ብናቆማቸው፣ የእኛ የሰልፍ ጉራ ከየትኛው ይመደባል? ብዬ ላነሳሁት ጥያቄ ራሴው መልስ ለመስጠት ነው- አብዛኛውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ባህርይ በ5 ከፍዬ፣ የ5ቱን ባህርይ ፊታውራሪዎች 5ቱን ከያንያን አድርጌ፣ የተቀረነው ከ5ቱ ጀርባ እንድንሰለፍ ብንደረግ (ብንገደድ) ቦታችን የት እንደሆነ ለመለየት...

ባለፈው እትም ‹ይርጋ ዱባላዎች›ን አይተናል፣ የእንጀራ ጉዳይ ሆኖብን ነው፣ ከማይመስለን ጋር የተባበርነው፣ ከማንወደው መንግስት ጋር ‹ወደፊት› ብለን የአብዮቱን ችቦ ያቀጣጠልነው፣ ኢሕአዴግ ሲመጣ ደግሞ ‹ጉሮ ወሸባዬ!› ብለን የድል መዝሙር የዘመርነው የሚሉትን። እነዚህን አይተናልና፣ ወዳላየናቸው ወደነ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንሶች እና ሰለሞን ተካልኞች ልውሰዳችሁ።

ለ) ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንሶች

...ወልደጊዮርጊስ ብዙ ስራ የሰሩ ናቸው፣ በፊተኛው ዘመን ለንባብ የበቁ ብዙ ድርሰቶች አሏቸው፣ በ1920ዎቹ መጨረሻ በ1930ዎቹ እና 40ዎቹ ‹አገር የቀና መንገድ እንድትከተል› ግጥሞች በመፃፍ እና ልቦለዶችን በመድረስ የታወቁ ናቸው፣ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ምዕራፍ ውስጥም ይጠቀሳሉ፣ ይህን እና ይህን የመሳሰለውን ትተን፣ በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ ከሰሯቸው (ህፀፆች? ጀብዶች?) አንዱን መዝገቤ፣ ራሳችንን የምናይባቸው መስታወት እንዲሆኑ ፈለግኩ፣ በመስታወቱ ውስጥ አንዳንዶቻችን አለንበትና፣ ውስጣዊ መልካቸው ከእኛ የውስጥ መልክ ጋር እጅጉን የተመሳሰለ ነውና!

...ወቅቱ ስመጥር የብዕር ሰዎቻችን እና አዝማሪዎቻችን፣ ጠላት እየመጣ መሆኑን የተገነዘቡበት ጊዜ ነበር፣ እንደ እነ ዮፍታሔ ንጉሴ ያሉ የቴአትር ሰዎች ‹ጣሊያን ድንበርህን ሊደፍረው፣ ክብርህን ሊያዋርደው፣ ባንዲራህን ዝቅ ሊያደርገው ነውና ንቃ፣ ተዘጋጅ፣ ልብስህንም ቤትህንም አቅንተህ ጠብቅ› የሚሉበት ጊዜ ነበር፣ በዚህ ጊዜ ነው፣ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ፣ እኔም ሐሳብ አለኝ ብለው የሚቀጥለውን ግጥም፣ የቤተመንግስት ሰዎች፣ አርበኞችና ሕዝቡ እንዲደርሰው ለንባብ ያበቁት።

...ጠላት በዋናው ላይ
ትርፍ አገኛለሁ ሲል
እኛስ ዋናችንን ስለምን እናጉድል
ተጋዳይ ተጋዳይ ተጋዳይ አርበኛ
እንዴት ያመልጥሃል ያገርህ ደመኛ...

አሉ፣ ይህን ያሉት ‹የወንድ ልጅ ኩራት ስለሀገር መሞት› በሚለው መጽሐፋቸው ነው፣ ዘመኑም 1927ዓ.ም። እኚህ ሰው በወቅቱ ሕዝቡን ‹በማነቃቃት እና በማደራጀት› የሚያህላቸው አልነበረም ልንል እንችላለን፣ እንዲህ አሉ፣ እንዲህ ተቀኙ የሚላቸው በዛ፣ ግጥሞቻቸው፣ ልክ እንደ ባላገር ስንቅ፣ በየአርበኞቹ ልብ ውስጥ ይታተም ያዘ።

መትረየስ ቢንጣጣ መድፍ
ቢደነፋ
ለጀግኖች ይመስላል አህያ
ያናፋ
የጉብዝናቶቹ እርሻና አዝመራ
ነፃነት ያፈራል ደም እየተዘራ
የተዘራው ደም ነፃነት ካፈራ
የጠላትን ግርማ ማነው
የሚፈራ?

አሉ፣ ግጥሞቻቸው ግራ ተጋብቶ በጨለማ ውስጥ ያለ ለመሰለው ባትሪ ሆነው፣ ሂድ ባሉት መንገድ ሄደበት፣ ተዋጋ ባሉት ጦርሜዳ ዋለበት፣ ቤቱን ዘግቶ ስንቁን ይዞ፣ ደም ካልተዘራ ነፃነት አያፈራም ያሉትን አስታውሶ ሄደ፣ ከጀግኖች ጋር ተቀላቀለ፣ በባሕላዊ የጦር መሳሪያ ‹ስልጡን ነኝና ላሰለጥናችሁ፣ በብርሃን መንገድ ላመላልሳችሁ ነው የመጣሁት› የሚለውን ፋሽስት ኢጣሊያን ሊወጋ...

በውጊያው መሐል ግን ወልደጊዮርጊስ የሉም፣ አይዞህ ተዋጋ ባሉት ወገናቸው መሐል የእሳቸው ሐሳብ እንጂ ሰውነታቸው እዚያ የለም፣ እሳቸው ከጣሊያን ጋር ናቸው፣ ንጉሱ ወደ እንግሊዝ ተሰደዋል፣ አሁን ያለው መንግሥት የጣሊያን ነው፣ ስለዚህ እሳቸው ማዕዳቸውን ከአዲሱ መንግስት ጋር አድርገዋል፣ ከጠላት ጋር አብረው፣ ጫካ በገቡት አርበኞች ይሳለቁ ጀምረዋል-ዱቼን የሚያመሰግኑበት ቃልም አነሳቸው።

...መክፈቻ እንደሌለው እንደ
ወርቅ ሳጥን
ተደፍና ስትኖር እስከብዙ ዘመን
ዱቼ መክፈቻውን ካምላክ
ተቀብሎ
የአፍሪካን ምድር ቤት
ቢከፍተው በቶሎ
ምድር ያባው ሁሉ ታየ ወለል
ብሎ...

እያሉ፣የፋሽስትንብልሃትአደነቁ፣ ለእልልታውም ለጭብጨባውም ጊዜና ቦታ አልበቃቸው ያለ መሰለ፣ ፋሽስት በዋለበት እየዋሉ፣ ዲስኩሩን እያደመጡ፣ አነጋገሩንና ሰላምታ አሰጣጡን አጀብ ነው እያሉ፣ ያልሰማ እንዲሰማ፣ ያላየ እንዲያይ መዋዕለ ዜናውን ይዘግቡ ቀጠሉ፣ ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ‹አጥንታችን በመድፍ እስኪፈላለጥ/ ነፃነት እንዳይሄድ አጥቁን መጋፈጥ› ብለው ገጥመው፣ ተነስ እንነሳ ያሉት አርበኛ፣ ለሀገሩ አይሆኑ መሆን እየሆነላት ነው፣ ለነፃነቱ ዋጋ እየከፈለ፣ እሳቸው ደግሞ እዚህ አዲስ አበባ፣ ፋሽስቶችን፣ የፍልሚያን ባለስልጣናትን በማሞካሸት ውዳሴ በማቅረብ ስራ ተጠምደዋል።

...አስተማሪ ጌታ አሰልጣኝ
መምህር
አግኝታ ተማረች የምስራቅ አገር
የኢጣሊያ አፍቃሪ የምትባለዋ
እሷ ምስራቅ ስትሆን ዱቼ ነው
ፀሐይዋ
መቆየት ደግ ነው ለብዙ ዘመን
አሮጌውን ሁሉ ሲታደስ አየን...

አሉ፣ ያሉትን በጊዜው ለሕዝብ ይሰራጭ በነበረው ‹የሮማ ብርሃን ጋዜጣ› ላይ ወጣ፣ ፋሽስት ደስ ተሰኘ፣ እሳቸውንና ሌሎች የሙያ ባልደረቦቻቸውን አመሰገነ፣ ምስጋናው ግን አልቀጠለም፣ ተደላድዬ እተኛበታለሁ ያለው የኢትዮጵያውያን አልጋ ቆረቆረው፣ የአርበኞቹ ተጋድሎ እንቅልፍ ነሳው፣ ለ40 ዓመታት ያህል ወጥኖ የመጣው እቅድ እየከሸፈ መሆኑ ገባው፣ በጫረው እሳት ነደደ፣ በቆፈረው ጉድጓድ ተቀበረ፣ እናም የገጣምያኑ እና የአዝማርያኑ ውዳሴ አጣጥሞ ሳይጨርስ ጓዙን ጉዝጓዙን ጠቅሎ፣ የ5 ዓመት ቆይታውን አጠናቆ ወጣ።

ሲያወድሱት የነበሩት ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ ግን ፋሽስቱን ተከትለው አልወጡም፣ የት ጥለኸኝ ልትሄድ ነው፣ ያላንተ መች ይሆንልኝና አላሉም፣ ከሄደ ሄደ ነው፣ ከቀሪው ጋር ነው መነጋገር፣ አሸንፎ ለመጣው ነው እጅ መንሳት፣ ሌሎችም እጅ እንዲነሱት ማድረግ፣ እና 5 ዓመት ሙሉ ሲታገልና ሲያታግል ቆይቶ፣ ጊዜውን ዕውቀቱንና ጉልበቱን ሰውቶ፣ አካሉን ቤተሰቡን በትኖ፣ የነፃነትን ጣዕም በመቅመሱ ደስ በተሰኘው ሕዝብ ፊት ቆሙ፣ የአፄ ኃይለሥላሴን ከስደት መመለስ የፈጠረባቸውን ሀሴት ገለፁ፣ ‹ጠላት ያኘከውን የዋጠውን ስጋ/ መንጥቆ አወጣልኝ ከጠላት መንጋጋ› አሉ፣ ደግሞም ቀጠሉ፣

...ጠላት የደም ግብር ጥሎብን
ፈሰሴ
ደማችን ክብር አየ በኃይለሥላሴ
አትዋል ይዋሉብህ አትምከር
ይምከሩ
በቆፈሩት ጉድጓድ ሳይገቡም
አይቀሩ
የተባለው ትንቢት ደረሰ በእግሩ
ክፋት በሄደበት ይከተላል ቅጣት
ጣሊያን በሰራው ግፍ ወረደበት
መዓት...

አሉ፣ ብዙ ነገር አሉ፣ ያሉትን ሁሉ ለማለት ቦታውም አይበቃ።

የሆነው ሆኖ፣ እኚህ በሥነፅሁፍ ስራዎቻቸው በቋንቋ ምሁራን ዘንድ ስማቸው የሚጠቀስልን የብዕር ሰው በአንድ ወቅት እንደዚያ ያለመልክ ነበራቸው፣ እሳቸው - ቀደም ሲል እንደገለፅኩላችሁ መስታወታችን ናቸው፣ በእሳቸው ውስጥ እኛም አለንበት ማለቴም፣ አንዳንዶቻችን፣ ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ራሳችንን እንክዳለን፣ ዘመን በተቀየረ፣ መሪ በተገለበጠ ቁጥር መስማት የሚፈልገውን ነው የምንናገረው፣ ልክ እንደ አንዳንድ አዝማሪዎች፣ አጠገባችን ላለው ገዢ፣ አጠገባችን ላለው ፈላጭ ቆራጭ፣ አጠገባችን ላለው ‹ድል አድራጊ› ነው ጥብቅና የምንቆመው፣ ትራፊ እንጀራና ሽራፊ ሽልማት ፍለጋ።

መልካችን ሶስት ነው፣ አንዳንዴም

ወደ ገፅ 27 ዞሯል



# ደንታቢስነታችን ምን ያህል ነው?

ዳዊት ታደሰ

አዶልፍ ሂትለር ወደ መንበረ ዙፋኑ ከወጣ በኋላ አውሮፓ እረፍትና እንቅልፍ ካጣች አመታት ተቆጠሩ፡፡ በዚህ ሰው ቀጭን ትዕዛዝ የተላኩ ነፍጠኞች በደረሱበት ሁሉ እልቂት ትርፋቸው ሆነ፡፡ ህፃን-አዋቂ፤ ሴት-ወንድ ሳይለዩ በክፋት በተገራው አዕምሮና በታዛዣቸው አፈሙዝ ብቻ እያሰቡ ህዝቡን ጨፈጨፉት፡፡ ገላጋዮች አርፍደው በደረሱበት በሁለተኛው የአለም ጦርነትም የሀገራት ድንበር ያለ ምንም ስስት በእነዚህ ወታደሮች ተጣሱ፡፡ ሂትለርና ጓዶቹ አለምን የፈጣሪ ያህል አዘዙባት፡፡ እስካልደረሰብን ምን ያገባናል ሲሉ የነበሩት ሀያላንም በመጀመሪያ ደንታቢስነትን ቢያሳዩም የኋላ ኋላ በሌሎች ላይ የተመዘዘው ሰይፍ ለነሱም እንደማይመለስ ሲገባቸው ማውገዝ ጀመሩ፡፡ በመጨረሻ ግን ወደ እልህ አስጨራሹ ጦርነት በጋራ ተቀላቀለው የናዚን ስርዓት ታሪክ አደረጉት፡፡ የሆነው ሁሉ ከሆነ በኋላ ከሞት የተረፉ ቁንጮ አመራሮች ለፍርድ ቀርበው ህግ ስለጥፋታቸው ተጠያቂ አደረጋቸው፡፡

ይህ ከሆነ ከሁለት አመት በኋላ ካርል ጃስፐርስ የተባለ ጀርመናዊ ፈላስፋ የመሪዎቹን ያህል ተመሪው ህዝብም የሞራል ተጠያቂ የሚሆንበትን ፅንሰ-ሀሳብ ይዞ ብቅ አለ፡፡ በሰው ልጆች ላይ ለተፈፀመው አሰቃቂ ወንጀል ተመሪው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ቅጥያጣውን የሂትለርን አምባ-ገነንነት በደንታቢስነትና በዝምታ ድጋፍ ሲሰጡ ለነበሩት ጀርመናዊያን የህግ ባይሆንም የሞራል ፍርድ እንደሚገባቸው ፈላስፋው ሞገተ፡፡ እ.አ.አ. በ1947ዓ.ም "The Question of German Guilt" ብሎ በሰየመው መጽሀፉ በጦርነቱና ከጦርነቱ በኋላ ሀገሪቱ ላስተናገደችው ድቀት ከላይ እስከታች ያለውን ዜጋ በመኮነን የህግ፣ የሞራልና የዲበ-አካል (meta-physical) ተጠያቂነት እንዳለባቸው በአመክንዮ አብራራ፡፡ በስርዓቱ ተገደውም ይሁን በፀጋ ተቀብለው መንግስቱን አበረታተዋል ያላቸውን ጀርመናዊያንን በሙሉ ከሞራል ተጠያቂነት እንደማያመልጡ የመከረበት ስራው አለም አቀፍ እውቅናን አላብሶታል፡፡ ለእንዲህ አይነቶቹ የህሊና ፍርደኞች መቀጫው ምን ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር ግን መልስ ያላገኘ ጥያቄ እንደሆነ እስካሁን አለ፡፡ አረመኔ መንግሥታትን ያበቀለ ማህበረሰብ፤ ጭካኔ ስጋ ለብሶና አይን አውጥቶ ገዢ ሲሆን እያየ አፉን ለጉሞ ያበረታታ ምን ቢቀጣ ስህተቱን ላይደግመው ይችላል? ራሱም እየተጎዳ ገዳዮችን የሚያፋፋስ በምን አይነት መንገድ ከተበዳዮች ጋር ገበታ ሊቀርብ ይገባዋል? የሂትለር ቡድን አለምን ወደ አዘቅት ሲሸኛት በአካል ያየው ጀርመናዊ ግን ገዢዎቹን ‹ኧረ በህግ› ብሎ ቢያስቆም ኖሮ ይሄ ሁሉ ተቀጥላ ስም ባልወጣለት ነበር፡፡

ከብሔር ልዩነት ይልቅ ጥልቅ ድህነት አንድ ያደረገን እኛ ኢትዮጵያዊያን በገዢዎቻችን ፊርማ ለደረሰው፣ እየደረሰ ላለውና ሊደርስ ካለው ጣጣ ከተጠያቂነት ለመዳን ምን እያደረግን እና ለሀገራዊ መከራውስ ምላሽ እንዲሆን የሰራነውስ በቂ ነው? ወይንስ ይቀረዋል? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ተጨማሪ ተከታዮችን እንጂ አዳዲስ መሪ ሀሳቦችንና ግለሰቦችን ለማፍራት ዝግጁ ያልሆነ ስርዓት ለሁለት አስርታት ራሱን ሲያደራጅ እንደነበር መናገር የረፈደበት ትርክት ነው የሚሆነው፡፡ የደንታቢስነታችንን መርገም ሰብረን ያገባኛል ልንል ስንል አገዛዙ ሊቀፈድደን በራችን ላይ እንዳለ ያስማማናል፡፡ እነርሱም ‹ፍፁም ሰላም› ብለው የሚያሞካሹት ‹‹መረጋጋት›› በዚህ ተግባራቸው የመጣ ነው፡፡ ሰልፋችንን በሰይፎቻቸው እንደሚበትኑትም ታሪክ አሳይቶናል፡፡ ስህተትና ወንጀል እየተሰራ እያዩ በዝምታ ማለፍ ያልቻሉት ቀዳሚዎቻችንም ዕጣ ፈንታቸው እስርና ሞት ነበር፡፡ ህልሞቻችን በግድየለሽነት ንፋስ እንደጉም ተበትነዋል፤ መማራችንም መከራችንን የሚያባብስ ሆኗል፡፡ መጪው ትውልድ ለመውጣት ወደሚከብድ የክህደት መቃብር እየተገፋ እንደሆነም ታዝበናል፡፡ ክፉ ግለሰቦች በአምላካዊ ክብር ሲሸለሙም እንድናይ ገዢዎች አስገድደውናል፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ሀገራዊ ኪሳራዎች መቆጠር ጥቂቶች የህግ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ራሳቸው ጥቂቶቹም ያውቁታል፡፡ እኛም አብዛኞቹ ከሚመጣው ትውልድ ‹‹ይሄ ሁሉ ሲሆን የት ነበራችሁ?›› ስንባል መልስ ለመስጠትና ከሞራል ተጠያቂነት ለማምለጥ ሳይረፍድብን ሰውን ከሌላው እንዲለይ ወዳደረገው ማንነታችን ተመልሰን መጠየቅ ለነገ የማንተወው የቤት ስራችን ነው፡፡

ኤሊ ቪይሰል የተባለ ከኦሽዊትዝ ማጎሪያ ቅጥር የተረፈ አይሁዳዊ ደንታ ቢስነትን ‹‹በብርሃንና ጨለማ፣ በአመሻሸና ንጋት በወንጀልና ቅጣት፣ በጭካኔና ርህራሄ፣ በክፉና ደግ መካከል ያሉ መስመሮች የደበዘዙበት እንግዳ እና ኢ-ተፈጥሮአዊ ኑባሬ ነው›› ይለዋል፡፡ አለም በዙሪያችን እንዲህ ስትታመስ እንደው የውስጥ ሰላምን ላለማጣት ያህል፣ መደበኛ ኑሮን ለመኖር ያህል፣ መልካም ምግብና ወይን ጠጅ ለማጣጣም ያህል ደንታቢስነትን መተግበር ግድ ነው ወይ? ብሎም ጠይቆ ነበር፡፡ የደንታቢስነት መጨረሻው የሰዋዊ ስሜት መሰለብና በዙሪያችን ለሚሆኑ ነገሮች ሁሉ ምላሽ አልባ መሆን ነው፡፡ ነጋዴው ትርፍ ከመሰብሰብ ውጪ ለሌሎች ሰዋዊ እሴቶች ግድ የማይሰጠው ከሆነና የማህበረሰቡ /የደንበኞቹ/ ሰብዓዊነት በመንግሥት አካላት ሲጣስ እያየ እንዳላየ ካለፈ ለገቢው ዘላቂነት መተማመኛው ምኑ ላይ ነው? ተማሪውስ? ‹‹ትምህርቴን ጨርሼ...›› ከሚለው መቋመጥ ባሻገር መፍትሄ የሚፈልጉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውዥንብሮችን ‹ይስተካከልልኝ› ብሎ ተፈጥሮአዊ መብቱን ባለመጠየቁ ምክንያት ብቻ የጓዶቹን ስራ ሲያጣው ከራሱ ውጪ ማንንም ተጠያቂ ለማድረግ የተሟላ ብቃት ሊኖረው አይችልም፡፡ ህይወት አቋራጭ መንገድ የላትም፡፡ ሊወገዱ ሲገባቸው ዘለን ያመለጥናቸው እንቅፋቶች ከኋላ ለሚከተሉን መሰናክሎች ናቸው፡፡ ጋዜጠኛውም ቢሆን ሀገር ስትፈርስ ተመልክቶ እንደ ሞያው ‹‹ሀገሪቷን አፈረሷት›› ከሚለው ሁተታ በኋላ እንደ ዜጋ ሀገሪቷን ለመታደግ ቢንጠራራ ዛሬ ከደረስንበት የሞራል ክስረት ላይ ባልተዘፈቅን ነበር፡፡ ምሁሩስ! እድሜውን ሁሉ ለእውቀት የባከነው ልጆቹ በሰላም እንዲያድጉ ሲል ለገዢዎች ሎሌ ለመሆን ነው? በችጋር እየረገፈ ላስተማረው ህዝብስ ምላሹ ለመከራው ጀርባውን መስጠት ነውን? ለዚህ እንዳልሆነ ራሱም ያውቀዋል፡፡ ብንወደውም ብንጠላውም ግን መሀል መንገድ ላይ ቆማ ወዴት ልሂድ ለምትለው ሀገር ፖለቲካዊ ህይወት ቀጣይነት ሁላችንም ተጠያቂዎች ከመሆን አንድንም፡፡ በተጨቆነ ማህበረሰብ መካከል እየኖሩ ግዴለሽ መሆን ጨቋኞችን የበለጠ አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡ ገዢዎች ደንታቢሶችን እንደአጋዥ ይቆጥሯቸዋል፡፡ የዜጎች ደንታቢስነት ሲስፋፋ ማህበረሰባዊ ድንዛዜን ይፈጥራል፡፡ ይህ ደግሞ ራስን ለበረታ አምባገነንነት አመቻችቶ መስጠት ይሆናል፡፡ የደነዘዘ ማህበረሰብስ ለመብቶቹ እንዴት ይገደዋል?

የአምባ-ገነን ስርዓት ለዴሞክራሲና ለመቻቻል ጊዜም ቦታም የለውም፡፡ ለማውራት እንጂ ለማዳመጥ ትሁት አይደለም፡፡ ለመዳንም ለማዳንም፤ ለማመንም ለማሳመንም አልበሰለም፡፡ እውቀት ጠላቱ ነው፡፡ ችሎት የኖረውን ህዝብ ማዋረድና ክብር ማሳጣት የተለምዶ ተግባሩ ነው፡፡ በወንበሩ ላይ የመቆየቱ ሚስጥር ከማህበረሰባዊ በጎ ፈቃደኝነት የተቸረው መሆኑን አያስተውልም፡፡ ከመወደድ ይልቅ ለመፈራት ይቸኩላል፡፡ ይሄ እንዲሆንለት ደግሞ ያፍናል፣ ያስራል፣ ያፈናቅላል፣ ይገድላል፡፡ በዓለማችን መጨቆን ብቸኛ የስልጣን መቆያ መፍትሔ የመሰላቸው መንግስታት ይሄንን ሲያደርጉ ኖረዋል፡፡ ግዴለሽ ተገዢዎች ግን ከጀርባቸው ነበሩ፡፡ ባይስማማንም እኛም የዚህን መሰል ስርዓት በጫንቃችን ደግፈን በኛው ላይ እንዲሰየጥን ፈቀደንለታል፡፡ የጋምቤላ ነዋሪዎች መግቢያ ሲጠፋቸው፣ የኦጋዴን ሰዎች ሲሰቃዩ፣ የጉራፈርዳ አርሶአደሮች ሲፈናቀሉና የኦሮሚያ ወጣቶች እስር ቤት መታጎራቸውን እየሰማን የተቀረነው ግን አሁንም በአርምሞ ውስጥ ነን፡፡ ሙስሊም ወዳጆቻችን መብቶቻቸውን ስለጠየቁ ሲታፈኑና በገፍ ሲታሰሩ የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ስለምን የአያገባኝም ደንታቢስነታችን ውስጥ ተሸሸግን? እርምጃው ትክክል ነበር ብለን ተስማምተን ይሆን? ነው ወይንስ ጉዳያችን አይደለም? ገዢዎቻችንስ ቢሆኑ በአለቃቸው በአቶ መለስ ሞት የነሱን ያህል (ምናልባትም ከነርሱ በላይ) አዝነን እንዲያ እንድንሆን ሲፈቅዱ (ሲያስገድዱን) ለአኛዋክ ብላቴኖች ሆነ በአዋሳ ጎዳናዎች ላይ ባለቁ የሲዳማ ወንድሞቻችን እንዳናለቅስ ስለምን ከለከሉን? ሆን ብለው ከሚኮረኩሙን ብዙ ባንጠብቅም ከመከራ አቻዎቻችን ግን ሰብዓዊነትን የተላበሰ የመቆርቆር ስሜት እንጂ ደንታ ቢስነትን አንጠብቅም፡፡ የፍትህ ጋዜጣና ባልደረቦች ለፕሬስ ነፃነትና ለዴሞክራሲያዊ ህላዌነት እንዲያ ሲዋትቱ ለደረሰባቸው እንግልት የሌሎች ጋዜጦች ቸልተኝነትስ ከአፋኞች ጋር መተባበርን አያመላክትም?

የተቃውሞ ኃይል ጎራዎችም ዜጎች የመከራ አጣብቂኝ ውስጥ መሆናቸውን ሲያውቁ ‹እንቃወማለን› ከሚለው የተለምዶ መግለጫ /መፈክር/ ባሻገር ባሉት ሰላማዊ ግፊቶች መንግስትን ከክፋት መንገዱ እንዲመለስ ያላስቻሉት በዚሁ በደንታቢስነት አባዜ ካልሆነ በቀር በሌላ በምን ሊሆን ይችላል፡፡ በጠንካራ መሰረት ላይ ሆነን እየሰራን ነው የሚሉን ፓርቲዎች የሀገሪቱ ህግና ነባራዊ ሁኔታዎች የተቃርኖ

ወደ ገፅ 26 ዞሯል



# መፈንቅለ-መንግስት ያሰጋናል?

*ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ*

ከሦስት ዓመታት በፊት በዝነኛው ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ የመፈንቅለ መንግስትን ጠቀሜታ አስመልክቶ ብዙዎቹ የጉዳዩ ተከታታዮች አስደንጋጭ ያሉት ፅሁፍ ታተመ፡፡ ርዕሰ ጉዳዩን ያጦዘው ከሌሎች ነገሮች በበለጠ የተፃፈው በፕ/ር ፖል ኮሊየር መሆኑ ነበር፡፡ ሰውዬው ከዛ በቀደሙ የተመራማሪነት ዘመናቸው እንደ ትጥግ ትግል ያሉ ሰላማዊ ያልሆኑ የስልጣን ሽግግሮች ምን ያህል አስከፊ ሀገራዊ ውጥንቅጦች፤ በተለይም በማህበር-ኢኮሚያዊው ስርዓት ላይ ሊያመጡ እንደሚችሉ ሲሟገቱ የከረሙ ናቸው፡፡ “Wars, Guns and Votes” እና “The Bottom Billion” የሚሉትን መጽሐፍቶቻቸውንም ሆነ ከእነ ሽንኪ ሆፍለር ጋር ያሳተሟቸውን ጥናቶች ያነበበ ፖለቲካዊ ዓመፅን ማሰብ አዳጋች ይሆንበታል፡፡ የኦክስፎርዱ የነገረ-ሀብት መምህር “let us now praise coups” በሚለው የጋዜጣው ፅሁፋቸው የዙምባቤውን ሮበርት ሙጋቤንም ሆነ የበርማ ጄኔራሎችን በመፈንቅለ መንግስት ማውረድ ይገባል፤ ለዚህም ምዕራባውያን እና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት መተባበር አለባቸው ብለዋል፡፡ እንደ መምህሩ ክርክር አምባገነን መንግስታት ዜጎቻቸውን እየቀጠቀጡ ሀገራቱን ሲያወድሙ ከመታገስ የሚያስከፍለው ዋጋ ቢኖርም መሪዎቹን በስዒረ-መንግሥት በመጣል ሀገራዊ አደጋውን መግታት ፖለቲካዊ ስህተት የለውም፡፡

እ.ኤ.አ ከ1945-2008 ዓ.ም. በአፍሪካ ውስጥ የተሞከሩትን 363 መፈንቅለ መንግስቶችን ያጠናቀረው በጆርጅ ሜሰን ዮንቨርሲቲ ውስጥ የሚገኘው የሲስተማቲክ ፒስ ማዕከል ለስዒረ-መንግሥት በሚሰጠው ብያኔ ከገዢው ቡድን አባላት ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚ የፖለቲካ ልሂቃንም የሚከወን ድርጊት አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ እንደተቋሙ፤ የተከፉ የወታደራዊው ክንፍ አባላትም ሆነ የፖለቲካው ተገዳዳሪ ልሂቃን ስልጣንን በጉልበት በመቀማት ከቀደመው ስርዓት መሰረታዊ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ማድረግ ከቻሉ፤ ሁነቱ በመፈንቅለ-መንግስትነት ለመሰየም በቂ ነው፡፡ ነገር ግን የተቋሙም ዘገባ እንደሚለው በአፍሪካ ውስጥ እየተደረጉ ያሉ መፈንቅለ-መንግስቶች እየቀነሱ መምጣት ለእነ ኮሊየር ዓይነት አጥኚዎች መልካም ዜና ባይመስልም፤ ሌሎች ፀሐፊዎች፣ የትኞቹም የስዒረ-መንግሥት ሙከራዎች ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሽግግሮችን ለማምጣት እንዳልቻሉ በመጥቀስ ፖለቲካዊ አመፅን ያወግዛሉ፡፡ ተቺዎቹ እንደሚሉት አማፂዎቹ አፋኙና ሙሰኛው የፖለቲካ ስርዓት ላይ ለመነሳት በቂ ምክንያት ቢኖራቸውም፣ ወደ አመፅ የሚመራቸው የማዕከላዊ መንግስቱን ስልጣን ለራሳቸው ጠቀሜታ ብቻ ለማዋል መሆኑ፣ ስልጣኑን ከያዙም በኋላ መሰረታዊ የፖለቲካ ማሻሻያዎችን ለመተግበር አቅም እና ፈቃድ አይኖራቸውም፡፡ አንድሪው ሚለር የተባሉ የነገሩ አጥኚ በበኩላቸው መፈንቅለ መንግስት በስኬት ተጠናቆባቸዋል የሚባልባቸውን ሴራሊዮን፣ ጋና እና ኒጀርን በመጥቀስ፤ በእነዚህ ሀገራት ተሞክረው የተሳኩት መፈንቅለ መንግስቶች ለጥቂት ጊዜያት ያህል ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማክበር ቢሞክሩም በመጨረሻ እነርሱም ካስወገዷቸው መንግስታት የባሱ እንደነበሩ ይናገራሉ፡፡ ፕ/ር ኮሊየርም ቢሆን ‹‹በርካሽ ባይመጣም›› ያሉትን መፈንቅለ-መንግስት ሲያብራሩ ኢኮኖሚያዊ መዘዙን በመጥቀስ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው በመጀመሪያው መጽሐፋቸው እንደሚያስረዱት፤ ዓመፁ በተካሄደ በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት የዜጎች የገቢ መጠን በየዓመቱ በ3.5 በመቶ ይቀንሳል፡፡ ይህ የገቢ መውረድ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ተመልሶ ማገገም ቢችልም በፖለቲካው ያለመረጋጋት የተነሳ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በከባድ መጠን ይቀዛቀዛል፡፡ ዶ/ር ሚለር ለነዚህም ሆነ ሀገራቸውን ወደ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሽግግር መውሰድ ስላልቻሉ የስዒረ-መንግስት ክሽፈቶች መሰረታዊ ያሏቸውን ጥቂት መገለጫዎች ያቀርባሉ፡፡ “Debunking the myth of the “Good” coup d’état in Africa” በሚለው ጥናታዊ ስራቸው፤ አማፂዎቹ ለአጭር ጊዜ ያህል ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ለመገንባት ቢሞክሩም በሂደቱ ለመግፋት ፍቃደኝነቱ የላቸውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አዲሶቹ መሪዎች ሀገራቸውን በቅጡ ለመምራት ህዝቡ በስፋት እንዲቀበላቸው ይሻሉ፡፡ ይህን የቅቡልነት መሻት ተቋማዊ ለማድረግ ሲታትሩ፣ በሌላ ጫፍ በመፈንቅለ መንግስት ወደ ስልጣን የመምጣት አካሄድንም በጎ ዕይታ ያለው አድርጎ ወደ ማስረፅ ይመራቸዋል፡፡ ይህ የአዲሱ ስርዓት ውስጣዊ ተቃርኖም፣ በተከታዮቹ ዓመታት ሌሎች የስዒረ-መንግስት ሙከራዎች እንዲደረጉ እድል ይሰጣል፡፡ ይህ ሁኔታም ሀገራቱን አጥኚዎች ‹‹የስዒረ-መንግስት አዙሪት›› (Coup trap) ብለው ወደሚጠሩት ስርዓታዊ ድቀት ውስጥ ይከታል፡፡

*መፈንቅለ-መንግስት መቼ?*

በአፍሪካም ሆነ በሌሎች ሀገራት የተደረጉ መፈንቅለ-መንግስቶችን ያጠኑ ፀሐፊዎች በመንስኤው ላይ ወደ አንድ ድምዳሜ ያዘነብላሉ፡፡ ማዕከላዊ መንግስቱ የሚተገብራቸው ፖሊሲዎች በውድቀት ሲደመደሙ እና ዜጎች በየትኛውም መስፈርት ለስርዓቱ የቅቡልነት መሰረት ሲነፍጉት ወታደራዊው ልሂቅ አመፅን ለመሞከር በቂ ገፊ ምክንያት ያገኛል፡፡ ክላውድ ዌልች “Soldiers and state in Africa” በሚለው ስራቸው እንደሚያወሱት ፖለቲካዊው ዓመፅ እንዲሳካ በመጀመሪያ ዜጎች ስርዓቱን ከመደገፍ ንፉግ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዌልች እንደሚጠቅሱት በዋጋ ንረት፣ በገቢ ኢ-እኩልነት እና በድህነት መበርከት መነሾነት የሚፈጠር የኢኮኖሚ መላሸቅ ዜጎችን ለብርቱ መከፋት ያጋልጣቸዋል፡፡ ነገር ግን ከዚህ በተፃራሪ ጠንካራ የኢኮኖሚ እድገት እና በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የሚሄድ የዜጎች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ባለበት ሁኔታ የሚሞከር ዓመፅ የመጀመሪያው ተግዳሮት ከአጠቃላይ የማህበረሰቡ ክፍል ይሆናል፡፡ ማህበረሰቡ ይህ የገቢ ምቾቱ እንዲታወክበት ስለማይፈልግ ሙከራውን ተቃውሞ ወደ አደባባይ ሊወጣ ይችላል፡፡ ሰላማዊ ሰልፎች፣ ረብሻዎች ወይም የፖለቲካ መሪዎች ግድያዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የመከሰት እድላቸው እየበዛ ከመጣ፤ ለመፈንቅለ-መንግስቱ አድራጊዎች የተመቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህ ሁነቶች ስርዓታዊ መናጋትን መፍጠራቸውን ወታደራዊው ቡድን ሲገነዘብ፣ የተሻለ አማራጭ አድርጎ ሊወስድ የሚችለው ይህን መናጋት በሚያባብሱ ነገሮች ላይ መጠመድን አልያም የሁከቶቹ ጡዘት ላይ ጣልቃ መግባትን እንደሆነ ስቴፈን ሊንደበርግ እና ጆን ክላርክ ይጠቅሳሉ፡፡ እንደ ሁለቱ ፀሐፊዎች ክርክር፣ በዚህ ዓይነት ስርዓታዊ መናጋት ውስጥ የገባ ገዢ ፓርቲ ዜጎችን ከተናወጠ ኑሯቸው መታደግ ስለማይቻለው፤ በመፈንቅለ-መንግስት ሊወርድ ቢችል ሁኔታውን የከፋ አያደርገውም፡፡ ለዚህ የኑሮ ውድነት ተጠያቂ የሚያደርጉት መንግስትን በመሆኑ፣ ጦር ኃይሉ ይህን ግዙፍ ቅሬታ በመጠቀም ስልጣንን በሃይል ለመንጠቅ ቢሄድ የሀገሪቱ ዜጎች ከመተባበር በመለስ ሌላ ፍላጎት እንደማይኖራቸው ክላውድ ዌልች ይናገራሉ፡፡ ሊንድበረግ እና ክላርክ “Does democratization reduce the risk of military in politics in Africa?” በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚደመድሙት በዚህ መሰል ክስተቶች በሚናወጥ ስርዓት ስር ዓመፁ ትክክል ቢሆንም፤ ከዚህ በተፃራሪው ዜጎች ዴሞክራሲያዊ አድርገው በሚያስቡት ስርዓት ላይ ሙከራው ከከባድ መዘዞች ጋር የመክሸፉ እድሉ ይበዛል፡፡ ፖል ኮሊየር እና አንኪ ሆፍለር በበኩላቸው የትጥቅ ትግልን የሚያነሳሱ ህዝባዊ ምክንያቶች ወደ መፈንቅለ-መንግስትም እንደሚወስዱ ይጠቅሳሉ፡፡ ፀሐፊዎቹ “Coup traps: why does Africa have so many coups d’état?” በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚሉት፤ ለትጥቅ ትግል መግፍኤ ተደርገው የሚቀርቡት ስልጣንን በመያዝ ለዓማፂው ሃይል አልያም ይወክለዋል ለሚባለው ማህበረሰባዊ ቡድን የተለያዩ ጥቅሞችን ለመስጠት ወይም በብሄር፣ ሃይማኖት እና መሰል የተለያዩ ማህበራዊ ተለዋጮች ወታደራዊ ኃይሉን ለማሳመፅ በቂ መነሾዎች ናቸው፡፡ እንደ አጥኚዎቹ ሙግት የዓመፁ ጠንሳሾች በጥንቃቄ መፈተሽ ያለባቸው እኒህን መሰል ስርዓታዊ ጉድለቶችን ነው፡፡

ሌሎች አጥኚዎች በሌላ ጫፍ እንደሚተነትኑት ለመፈንቅለ-መንግስት መሞከር በራሱ በሚሊተሪው መዋቅራዊ ስርዓት ውስጥ የሚፈጠሩ ቅሬታዎች ግዙፍ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያጠናው ዊሊያም ቶምፕሰን እኒህን መከፋቶች ‹‹ድርጅታዊ ቅሬታዎች›› (Corporate grievances) ሲል ይጠራቸዋል፡፡ በዚህ ሞዴል መሰረት፣ መፈንቅለ-መንግስት ሊከሰት የሚችለው ወታደራዊው ቡድን ተቋማዊ ፍላጎቱ እንደተነካበት ሲያስብ ነው፡፡ ፀሐፊው ለዚህ ማሳያ አድርገው የሚያቀርቡት የሞሪታኒያን እና የአይቬሪኮስትን ተሞክሮዎች ነው፡፡ እ.ኤ.አ. በ2008 ዓ.ም. በሞሪታኒያ የአራት ከፍተኛ ወታደራዊ ሹማምንቶችን ከስልጣን መነሳት መቀበል የተቸገሩ የወታደሩ ክፍሎች ስርዓቱን በአመፅ ጥለዋል፡፡ በሌላኛዋ ሀገር አይቬሪኮስት የሀገሪቱ ወታደሮች የደሞዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው ያነሱት ጥያቄ ባለመመለሱ መፈንቅለ-መንግስት ለመሞከር ተገድደዋል፡፡ ቶምፕሰን “Corporate coup-

maker grievances and types of regime targets" ብሎ በሰየመው ስራው፤ የወታደሩ ቅሬታ ሁልጊዜም በቀጥታ ከደሞዝ ጭማሪ ጋር ላይገናኝ ይችላል። የሙያ ዕድገት ሊገኝባቸው ይችሉ የነበሩባቸው እድሎች መዘጋት በተራዛሚውም የበታች ወታደሮች ሁልጊዜም እጅግ አደጋ በበዛበት ግን ደግሞ የማዕረግም ሆነ ሌሎች መሻሻሎች በሌሉበት ሁኔታ ለረዥም ጊዜ ሲቆዩ ስለ ስዒረ-መንግስት ለማሰላሰል ሊገደዱ ይችላሉ። እንደ ፀሐፊው መከራከሪያ፤ አናሳ የአካዳሚያዊና ወታደራዊ የሙያ አቅም ያላቸው ወታደሮች ለተለምዷዊው ወታደራዊም ሆነ ስርዓታዊ የአስተዳደር ዘዬ የተመቹ አይሆኑም። እነዚህ ሁነቶችም የበታች ወታደሮቹን አመፅን ለመሞከር እንዲደፋፈሩ ያደርጋቸዋል። ዊሊያም ቶምፕሰንም ሆነ ሌሎች አጥኚዎች እንደሚሉት ይህን መሰሉ ሙከራ ስኬታማ መሆን የሚችለው የተሻለ ልምድ ያላቸውን ወታደራዊ ልሂቃን ማቀፍ ሲችል ነው። እነዚህ ልሂቃን በበኩላቸው ወደዚህ ዓመፅ እንዲሳቡ ከሚገፏቸው ምክንያቶች አንደኛው ያገኙ የነበረው ጠቀሜታ አደጋ ውስጥ እንደገባባቸው ሲሰማቸው ነው። ብዙውን ጊዜ የዚህ መነሾ ሆኖ የሚቀርበው በሀገሪቱ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ አልያም በሚሊተሪው በጀት መቀነስ የሚፈጠረው ቀጥተኛ የጥቅም መጓደል ነው። በዚህ ወቅት ሁለቱም የወታደሩ ክፍሎች በጋራ የሚሞክሩት ያለመታዘዝ አልፎም ስልጣን የመንጠቅ አካሄድ ስኬታማነቱ የበዛ ይሆናል።

ለወታደራዊ ኃይሉ በሃይል ወደ ስልጣን መምጣት የነገሩ አጥኚዎች የሚሰጡት ምክንያት፤ በአፍሪካ ሀገራት ያሉት የፖለቲካ ስርዓቶች ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ያለማጠናከራቸው እና ሀገራቱ ወታደራዊ ክፍሉን የስልጣን መጠበቂያቸው ለማድረግ መሞከራቸው ነው የሚሉ ናቸው። ሚካኤል ብራቶን እና ኒኮላስ ቫንዲ ዋሌ ከረዥም ምርመራ በኋላ ያስቀመጧቸው መላምቶች ከዚህ አንፃር ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣቸዋል። እነ ዲዋሌ እንደሚሉት፤ ወታደራዊ ተቋሙ ዴሞክራሲያዊ ሂደቶችን ለማደናቀፍም ሆነ ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል። ተቋሙ ከዚህ ሂደት በተፃራሪ ከሄደ አደጋውም የበዛ ሊሆን እንደሚችለው ሁሉ፤ ስርዓቱን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግም ግዙፍ ሚና ይኖረዋል። የፖለቲካ መሪዎች የህግ የበላይነትን ለመሸራረፍ ከሞከሩ የሚጠብቃቸው በኃይል ከስልጣን መውረድ እንደሆነ ካወቁ የተሻለ ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚችሉ እነ ዋሌ ይናገራሉ። ምሁራኑ "Democratic experiments in Africa" በሚለው መድብላቸው እንደሚጠቅሱት ቡድኑ ወደዚህ አደገኛ ሙከራ የሚገፋው ተቋማዊ ጥቅሞቹ ሲነኩ ብቻ ነው።

አምባገነን መንግስታት ይህን ዓይነቱን የስዒረ-መንግስት ሙከራ አስቀድሞ ለመግታት የሚሞክሩት በአብዛኛው በሁለት መንገድ እንደሆነ ጥናት አድራጊዎቹ ይናገራሉ። የመጀመሪያው ወታደራዊ ልሂቃኑን በጥቅመኝነት ፖለቲካው ስር ማካተት ነው። በጉዳዩ ላይ የፃፉት ኮሊየርና ሆፍለር እንደሚሉት የስርዓቱ መሪዎች ጥቅመኝነትን ለማስፈን ሲሉ መጀመሪያ የሚያደርጉት የሚሊተሪ ባጀቱን በከፍተኛ ሁኔታ ማናር ይሆናል። ‹‹በዚህ መንገድ›› ይላሉ እነሆፍለር ከላይ በተጠቀሰው ስራቸው ‹‹ስርዓቱ ወደ ወታደራዊው ክፍል ከፍተኛ ቦታዎች የሚመለምላቸው ከሚቀርብላቸው ጥቅሞች አንፃር እጅጉን ታማኝ የሚሆኑትን ይሆናል።›› እነዚህ ጥቅመኛ ወታደራዊ ሹመኞችም ያገኙትን ጥቅም በማስላት መፈንቅለ-መንግስት ማድረግም ሆነ ለሙከራው መተባበር ይህን የጥቅመኝነት ሰንሰለት መበጠስ መስሎ ስለሚታያቸው ከነገሩ የተቆጠቡ ይሆናሉ።

ሁለተኛው የመሪዎቹ አካሄድ በዙሪያቸው የሚሰበሰቡና በእነርሱ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ብቻ የሚንቀሳቀሱ ልዩ ወታደራዊ ሃይሎችን ማቋቋም ይሆናል። ኤድዋርድ ሉትዋክ የተባሉ ፀሐፊ "Coup d'état: A practical handbook" በሚለው ስራቸው እንደሚጠቅሱት፤ የስርዓቱ መሪዎች እነዚህ ልዩ ሃይሎች ከወታደራዊው ክፍል ሊነሳ የሚችለውን የስልጣን ነጠቃ ለመግታት እንዲቻላቸው ወታደራዊ ክህሎታቸው ከጦር ሃይሉ ትይዩ የሚቆም እንዲሆን ያደርጋሉ። ሌሎቹ ፀሐፊዎች፣ ኢቫን ሾፈር እና አሮን በልኪን "Towards a structural understanding of coup risk" በሚለው ፅሁፋቸው የሚያነሱት ነጥብ፤ ዓመፁን ለማፈን መንግስታቱ ወታደራዊ ክፍሉን በተለያዩ ጠርዞች መከፋፈልን ይመለከታል። እንደ እነ በልኪን መከራከሪያ፤ ከልዩ ሃይሎቹ በተጨማሪ የሚሊተሪው ክፍል በተለያዩ እና እጅግ ተጣራሽ ፍላጎቶችን በሚገፉ ቡድኖች (የብሄር ወይም የሃይማኖት) ከተዋቀረ በጋራ መስራትን ግድ የሚለውን መፈንቅለ-መንግስት መሞከር የማይቻል ያደርገዋል።

እነሳሞራ እየመጡ ነው?

በአፍሪካ ውስጥየተሞከሩ መፈንቅለ መንግስቶችን ያጠኑ ፀሐፊዎች በብሔር ፖለቲካ እና በዓመፁ መሀከል ቀጥተኛ ተዛምዶ እንዳለ በተደጋጋሚ ያስነብባሉ። በተለይም ባለፉት ሃምሳ ዓመታት መቶ ሰማኒያ አንድ ሙከራዎችን ባስተናገደው ከሰሃራ በታች ባለው የአፍሪካ ክልል ብሄርተኝነት ቀዳሚ ተለዋጭ ሆኖ ይነሳል። ይህን ለማብራራትም ሶስት መከራከሪያዎች ተደጋግመው ይቀርባሉ። የመጀመሪያው የ‹‹ብሔር ብዙህነትን›› ሲንተራስ፤ ቁጥራቸው የበዛ ብሄሮች ባሉባቸው ሀገራት የመፈንቅለ-መንግስት ሙከራ ተደጋጋሚ ሁነት ስለመሆኑ ይጠቀሳል። ከብዙህነት ይልቅ በአንድ የብቻ ብሄር ፖለቲካዊ የበላይነት ሌሎች አቻዎችን ወደ ጠርዝ ስለሚገፋ፣ ይህ መገፋት ማህበረሰቡን ለዓመፅ ያመቻቻል የሚለው ሌላው ሙግት ሲሆን፤ የመጨረሻው መከራከሪያ ፖለቲካዊ የበላይነትን ለማግኘት በብሄሮች መሀከል የሚደረግን መገዳደር በምክንያትነት ያነሳል። በተለይም ቁጥራቸው ተመጣጣኝ በሆኑ ሁለት የብሄር ቡድኖች መሀከል የበላይነትን ለማግኘት የሚደረግ መተጋገል ስዒረ-መንግስትን አቋራጭ መንገድ አድርጎ ስለሚያሳስብ የዓመፅን ተደጋግሞ መከሰት ተጨባጭ ያደርገዋል።

በዚህ ጭብጥ ላይ የፃፉት ቦዩባካር ኒዲያ እንደሚሉት የሲቪል-ወታደራዊ ግንኙነትን የተረጋጋ ለማድረግ የአፍሪካ መንግስታት የሚመርጡት አካሄድ በሲቪል መንግስቱ መሪዎች እና በሚሊተሪው መሀከል የብሄር ተመሳስሎትን መፍጠር ነው። ይህ ሁለቱንም መዋቅሮች በአንድ ብሄር ልሂቃን መሙላት በተቋማቱ መሀከል የሚኖረውን ግንኙነት ሰላማዊ ስለሚያደርገው ዓመፅን ሩቅ ያደርገዋል። ፕ/ር ኒዲያ "The challenge of institutionalizing civilian control" ባሉት ጥናታቸው እንደሚያወሱት፤ ወታደራዊ ተቋሙን የሚመሩት ልሂቃን የብሄር ማንነት ከዚህ ቀደም ከነበረው የስርዓቱ መሪ ጋር አንድ ዓይነት የነበረ ከሆነ እና አዲሱ የስርዓቱ መሪ ከነርሱ ብሄር ውጪ ከመጣ ስልጣኑን ለመንጠቅ ማውጠንጠናቸው አይቀሬ ነው። ‹‹መሪው›› ይላሉ ኒዲያ ‹‹ዴሞክራሲያዊ በሆነም ሆነ ባልሆነ መንገድ ቢመጣ ወታደሮቹ የብሄር ማንነታቸውን የማይጋራውን መሪ ለመቀበል ይቸገራሉ።›› ክሪስተን ሃርከንስ የተባሉ ፀሐፊ "Dangers to democratization: military responses to constitutional leadership in Africa" በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚተነትኑት፤ ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚወለደው ሰው ወደ ስልጣን መምጣት በጥቅመኝነት ፖለቲካና በብሄር ማንነት ዙሪያ በተደራጀ ፖለቲካዊ ስርዓት ላይ አደገኛ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። በወታደራዊ ልሁቁ በኩል፣ አዲሱ መሪ ሌሎች የራሱን ብሄር ሰዎች ወደ ስርዓቱ ማምጣቱ አይቀርም የሚለው ቅድመ-ግምት፣ ይህ አካሄድም ከቀደመው መሪ ጋር በነበራቸው የአንድ ብሄር አባልነት ያገኟቸው ቀጥተኛ ጥቅሞች እና ስነ-ልቦናዊ ‹‹መደላደሎች›› እንደማይኖሩ ስለሚያምኑ፤ የቀድሞውን መሪ ወደ ስልጣን ለማምጣት አልያም ራሳቸው ስልጣኑን ለመያዝ ይሞክራሉ። እንደ አጥኚዎቹ በተለየ ሁኔታ ይህ የዓመፅ ሙከራ ሊከሰት የሚችለው መሪው የራሱን የብቻ የስልጣን የበላይነት ለማስጠበቅ አልያም የሃይል መሰረቱን ለማጠናከር ሲል የነበረውን ወታደራዊ ስርዓት እንደገና ለማዋቀር ሲሞክር ነው። በሌላ ጫፍ አዲሱ መሪ ወታደራዊ ኃይሉ ይህን ሊያደርግ እንደሚችል ከተጠራጠረ አስቀድሞ መከራውን ለማፈን ያስችሉኛል ያላቸውን አንዳንድ ድርጊቶችን ሊፈፅም ይችላል። ይህ በሁለቱም በኩል ሊደረጉ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችም በውጤታቸው ከስርዓታዊ መናጋት እስከ የእርስ በርስ ጦርነት ያሉ አደገኛ ክስተቶችን ሊቀሰቅሱ ይችላሉ።

በሌላ ጫፍ ሌሎች አጥኚዎች በብሄር ፖለቲካና በስዒረ-መንግስት መሀከል ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ፤ በመንግስታዊ መዋቅሩና በሚሊተሪው ውስጥ ያለውን የብሄሮችን ተዋፅኦ መመልከት ግድ እንደሚል ይናገራሉ። ከነዚህ አጥኚዎች አንዱ የሆኑት ስቴፈን ሊንደማን ሶስት መልኮች ላይ ያተኩራሉ። ፀሐፊው በመጀመሪያነት የሚያነሱት በመንግስታዊ ስርዓቱ ውስጥም ሆነ በወታደሩ ክፍል የሚስተዋለው የብሄር ተዋፅኦ ተመጣጣኝ እና ሁሉን አካታች

ወደ ገፅ 25 ዞሯል

*...በአፍሪካም ሆነ በሌሎች ሀገራት የተደረጉ መፈንቅለ-መንግስቶችን ያጠኑ ፀሐፊዎች በመንስኤው ላይ ወደ አንድ ድምዳሜ ያዘነብላሉ። ማዕከላዊ መንግስቱ የሚተገብራቸው ፖሊሲዎች በውድቀት ሲደመደሙ እና ዜጎች በየትኛውም መስፈርት ለስርዓቱ የቅቡልነት መሰረት ሲነፍጉት ወታደራዊው ልሂቅ አመፅን ለመሞከር በቂ ገፊ ምክንያት ያገኛል...*

ከኦሮሞ....

*(ከገፅ 3 የዞረ)*

ዲሞክራሲያዊ መስመር ነው›› ሲሉ እውነታውን በገደምዳሜ የነገሩን፡፡

## የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ምንድር ነው?

የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄን በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን፡፡ ፖለቲከኞቹ የሚያነሱት እና ብዙሃኑ የብሄሩ አባላት የሚያነሳው ብለን፡፡ የመጀመሪያውና በአብዛኛው አደገኛ ጎኑ የሚያመዝነው የኦሮሞ ‹‹የብሄር ፖለቲከኞች›› (Ethnic-nationalist elites) የሚያነሱት ነው፡፡ በዚህ ማእቀፍ ውስጥ የሚመደቡት የጥያቄያቸው መቼት ከአፄ ምንሊክ ‹‹የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ›› ጋር የሚተሳሰር ሲሆን፣ የእነዚህ ሊሂቃኖች ጥያቄ ብዙውን ጊዜ ‹‹ከጭቆና እና ከወረራ›› ጋር ተያይዞ ሲጎን ይታያል፡፡ እንደመጨረሻ መፍትሄ የሚያስቀምጡትም ‹‹ነፃ የኦሮሚያ ሪፐብሊክን›› መመስረት የሚል ነው፡፡ (በእርግጥ በቅርቡ የዳውድ ኢብሳ ኦነግ ‹‹የኦሮሚያ ህዝብ ይወስን›› ሲል፣ የከማል ገልቹ ኦነግ ደግሞ ‹‹መገንጠል የለብንም›› በሚል አቋማቸውን እንዳሻሻሉት ተናግረዋል)

በሁለተኛው መደብ የሚካተቱት ብዙሃኑ የብሄሩ አባላት ናቸው፡፡ የጥያቄያቸው ማዕቀፍም የኦሮሞ ባህሎች ተደፈጠጡ፣ በቋንቋችን መማር መቻል አለብን፣ በሀገሪቱ ፖለቲካ የቁመታችንን ያህል እንወክል፣ ፌደራሊዝም ያለጣልቃ ገብነት ይተግበር እና የመሳሰሉት የሚሉ ናቸው፡፡ (ይህ ክርክር መገንጠልን እንደአማራጭ አያስቀምጥም) እንግዲህ የኦሮሞ ህዝብን እንወክላለን በሚል የተመሰረቱ ድርጅቶች በሙሉ ‹‹የሚሸጥ ሃሳብ›› የሚያዘጋጁት ከእነዚህ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች አንፃር ነው፡፡ ሆኖም በብሄሩ ስም ከተመሰረቱ በርከታ ድርጅቶች መካከል ጥያቄዎቹን ለመመለስ በህወሓት/ብአዴን ድጋፍና እርዳታ ስልጣን በመያዝ በለስ የቀናው ኦህዴድ ቢሆንም በውስጣዊና ውጫዊ ድክመቶቹ የተነሳ ለጥያቄዎቹ መልስ ሲሰጥ ቀርቶ በግልባጩ በኦሮሚያ ላይ የስጋት ምንጭ በመሆኑ የኦሮሞን ብሄርተኝነት መምቻ ‹‹ዱላ›› ሆኗል፡፡

## የኦህዴድ ውስጣዊ ተግዳሮቶች

ኦህዴድ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን እንደድርጅት ተመስርቶ ለስልጣን ከበቃ በኋላ ራሱን የሚያጠናክርበት ወይም ከህወሓት ተፅእኖ ነፃ የሚወጣበት በርካታ አጋጣሚዎች ቢፈጠሩም ለመጠቀም አልቻለም፡፡ ለዚህ ክሽፈትም ጥቂት ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡

## ምክንያት አንድ

ኦህዴድ የተመሰረተው በኢህዴን ውስጥ ተራ ታጋይ በነበሩ (ምርኮኛ ወታደሮች) በመሆኑ ለስልጣን ከበቃ በኋላ በነበረው የበታችነት ስሜት የኦሮሞ ልሂቃኖችን ወደ ድርጅቱ እንዳይገቡ አግዶ መያዙ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው የስልጣን ሸሪኮቹ ህወሓት እና ብአዴን (ኢህዴን) ለቀድሞ መንግስት ያገለግሉ ከነበሩ ምሁራን ውስጥ የየብሔራቸውን ተወላጆች ወደ ድርጅታቸው ሲቀላቅሉ ኦህዴድ ከዚህ ትምህርት ወስዶ ፈለጋቸውን ከመከተል ይልቅ ‹‹ኢሠፓ፣ ኦነግ፣ ኢህአፓ...›› እያለ በማውገዝ በርካታ የኦሮሞ ምሁራኖችን ከፖለቲካው እንዲገለሉ አድርጓል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ተግባሩ ተገቢውን ዋጋ የከፈለ ይመስለኛል፤ ዛሬም ድረስ በድርጅታዊ አቅምና የፖለቲካ ቁመና መጠናከር ባለመቻሉ ማለቴ ነው፡፡

## ምክንያት ሁለት

የኦህዴድ አመራሮች በነበራቸው ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት ምክንያት ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ ከአስተዳደሪነት ይልቅ ‹‹አዲስ ገኘ ኦሮምኛ ተናጋሪ መደብ›› የመሆን ዝንባሌያቸው በተደራጁለት የኦሮሞ ተወላጆች ዘንድ ተቀባይነት እና ድጋፍ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል፡፡

## ምክንያት ሶስት

ኦህዴድ ኢህአዴግን ከመሰረቱት ከሌሎቹ ሶስቱ ድርጅቶች በተለየ መልኩ የአመራር አባላቱ በተለያየ ጊዜ ለቀው መውጣታቸው ለከፍተኛ ችግር አጋልጦታል፡፡ ሀሰን አሊ፣ ዮናታን ዲቢሳ፣ (ሁለቱም የስራ አስፈፃሚ አባላት ናቸው) ነጋሶ ጊዳዳ፣ አልማዝ መኮ፣ ዱባለ ጃሌ፣ ዲሪባ ሀርቆ እና ያሲን የተባሉ የአመራር አባላት እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ፡፡ (ዮናታን ዲቢሳ እና አልማዝ መኮ ኦነግን ተቀላቅለዋል)

## ምክንያት አራት

ኦህዴድ ከሌሎች የግንባሩ ፓርቲዎች በበለጠ መልኩ አብዛኛው ከፍተኛ ካድሬዎቹ በተለያዩ ጊዜያት ለሙስና መጋለጣቸው ደካማ ድርጅት ሆኖ እንዲዘልቅ አድርጎታል (በ1989 ዓ.ም. ብቻ ከነበሩት 10,300 ካድሬዎች ውስጥ/መካከል 10ሺውን በሙስና ማባረሩ ይታወቃል) እንዲያውም አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች በኦህዴድ ውስጥ ያለውን ሙስና እና የጥቅም ትስስር መነሻ በማድረግ ድርጅቱን ‹‹የጥቅመኝነት ፖለቲካ›› ምን እንደሚመስል ማሳያ አድርገው ሲያቀርቡት ይታያል፡፡

## ምክንያት አምስት

ኦህዴድ ከህወሓት/ብአዴን ተፅእኖ (ቁጥጥር) ነፃ ያለመሆኑ ነው፡፡ ቅድሚያም የሚሰጠው ለኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ሳይሆን ለሁለቱ ድርጅቶች ፍላጎት ነው፡፡

> ***...የኦህዴድ የአመራር አባላት ከላይ በተጠቀሰው ችግር ውስጥ የወደቁ ቢሆኑም በአሁኑ ወቅት በከፍተኛና የበታች ካድሬነት ኦህዴድን የተቀላ ቀለው አዲሱ ትውልድ ‹‹ጣልቃ ገብነትን›› ለመቀበል የተዘጋጀ አይመስለኝም፡፡ ይህም ሁኔታ የኦህ ዴድን አመራር አጣብቂኝ ውስጥ ከቶታል...***

## ምክንያት ስድስት

የኦህዴድ መስራቾችም ሆኑ በዚህ ወቅት ፓርቲውን የሚመሩት በየትኛውም መንግስት (ዘመን) የኦሮሞን ጥያቄ አንስተው የማያውቁ መሆናቸው በራሱ ጥያቄውን ከእነመልሱ እንዳያውቁት አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ድርጅቱ እንደድርጅት እንዳይቆም እንቅፋት ሆኖበታል፡፡

## የኦህዴድ የውጭ ተግዳሮቶች

ኦህዴድ ከምስረታው ጀምሮ በህወሓት ተፅዕኖ ስር የነበረ ሲሆን ካለፉት አስር አመታት ወዲህ ደግሞ ብአዴንም በኦህዴድ ላይ ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታን (ፖለቲካዊ ጉልበት) አዳብሮአል፡፡

ብአዴን እና ህወሓት ኦህዴድን በተለየ መልኩ ለመቆጣጠር ያላቸው ፍላጎት ‹‹ከፍራቻ የመነጨ›› እንደሆነ ይነገራል፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ የተመሰረተው በብሄር ፖለቲከኞች ከመሆኑ አኳያ የሚከተለው ፌደራላዊ አስተዳደር ቀመር ‹‹በህዝብ ብዛት፣ በሀብት ተመጣጣኝነት እና ከመልክዐ-ምድራዊ አስተዳደር አመችነት...›› ከመሆን ይልቅ ‹‹ቋንቋን›› መሰረት ያደረገ ሲሆን፤ ኦህዴድ ደግሞ ከአባል ፓርቲዎች በህዝብ ብዛት፣ በምጣኔ ሀብት፣ በቆዳ ስፋት እና በመሳሰሉት በእጅጉ የሚልቅ ሆኖ በግንባሩም ሆነ በመንግስት ውስጥ ያለው ስልጣን ከቁመቱ ጋር ያልተመጣጠነ መሆኑ ምን አልባት አንድ ቀን እንደአሳተ ጎመራ ሊፈነዳና ሊታረም የማይችል ጉዳት ሊያስከትል ይችላል የሚል የስጋት ቀጠና ስለሆነባቸው ነው፡፡ በተለይም በኢትዮጵያ ያለው ፌደራሊዝም ከመሰረታዊ ባህሪያቶቹ አንፃር በትክክል ቢተረጎም ኢህአዴግ ‹‹Ethnic Congress Party›› (የመድብለ-ዘውግ ስብስብ) ከመሆኑ አኳያ ኦህዴድ የሚያነሳው የስልጣን ጥያቄ ህገ-መንግስታዊ ድጋፍ እንዳለው እነህወሓት/ብአዴን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡

ከአራቱ የግንባሩ አባል ፓርቲዎች ውስጥ በፓርላማው የበለጠ መቀመጫ ያለውም ኦህዴድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ድርጅቱ የወከለውን ህዝብ ‹‹ታሪካዊ የስልጣን ጥያቄ›› ይዞ ቢነሳ እና በግንባሩ ፓርቲ አባላት መካከል ልዩነት ቢከሰት በቀላሉ የኦህዴድ ሊቀመንበር ጠቅላይ ሚኒስትር የመሆን እድሉ ይሰፋል፡፡

ህወሓት፣ ብአዴን እና ደኢህዴን በተለያየ ጊዜ የኢህአዴግ ሊቀመንበር እና የም/ሊቀመንበርነቱን ቦታ ሲፈራረቁበት ኦህዴድ አንድም ጊዜ ተራ ደርሶት አያውቅም፡፡ እዚህ ጋር ‹‹የህዝብ ብዛት›› የሚለውን መስፈርት ትተን ብዙውን ጊዜ ህወሓት እና ብአዴን ስኑ-አመክንዮ የሚያደርጉትን ‹‹የትግል ተሞክሮ›› እንኳ እንደመስፈርት ቢወሰድ፣ ኦህዴድ ቢያንስ ከደኢህዴን የተሻለ ‹‹የቆይታ ታሪክ›› ያለው ከመሆኑ አኳያ ኢህአዴግን በሊቀመንበርነት አለመምራቱ በኦሮሞ ተወላጆች ዘንድ እምነት እንዳይጣልበት አድርጎታል፡፡

የሆነ ሆኖ ለኦህዴድ ድክመት የህወሓት አመራሮች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ምክንያቱም ህወሓቶች ኦህዴድ በራሱ እንዳይቆም ከማድረጋቸውም ባሻገር በተለያዩ መድረኮች የአመራር አባላቱን በጋራ እና በተናጥል ሲያሸማቅቁት ይታያል፡፡ በተለይም ጠንካራ የኦሮሞ ብሄርተኛ የሆነ የኦህዴድ አመራር ሲመጣ ‹‹ኦነግ›› እያሉ ማሸማቀቅ የተለመደ የግንባሩ የፖለቲካ ጨዋታ ነው፡፡ ይህንን አይነት የማጠቃቀር ፖለቲካ በአብዛኛው ይጠቀም የነበረው የህወሓት አመራር ነው፡፡ አቶ መለስ ‹‹ህወሓት እና ብአዴን ንብ ሆነው ማር ሲሰሩ፤ ኦህዴድ ደግሞ ማሩን ሊልስ የመጣ ዝንብ ነው›› ሲሉ ድርጅቱን ከማጣጣላቸውም ባሻገር በትምህርት ዝግጅታቸውና በፖለቲካ ንቃታቸው የተሻሉ የሚባሉትን የአመራር አባላቱን በተናጥል ያሸማቅቁ ነበር፡፡ ለምሳሌ ግርማ ብሩን ‹‹ጎበዝ! ነገር ግን የሸዋ ፊውዳል ባህሪ የተጠናወተው›› ሲሏቸው፤ ዶ/ር ሙላቱ ተሾመን ደግሞ ‹‹ሙስና ውስጥ ባይገባም ሠነፍ ነው›› ያሉበትን አጋጣሚዎች ማንሳት ይቻላል፡፡ አቦይ ስብሃት ነጋም በአንድ ወቅት ‹‹ከሜዳ ሰብስበን አምጥተን ሚኒስትር አደረግናችሁ›› በማለት የኦህዴድ አመራርን የፖለቲካ ጉልበት ‹‹የለህም›› ሲሉ ☞

በግልፅ ተናግረዋል፡፡ የቀድሞ የኦህዴድ የአመራር አባል ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ‹‹አቶ መለስ የአሜሪካ አምባሳደር (በ1980ዎቹ አጋማሽ የነበረው) ‹የኦህዴድ አመራር አባላት ሆሊጋንሲቲክ ነው› ብሎኛል ብለው በተዘዋዋሪ ይሰድቡን ነበር›› ሲሉ ያስታውሳሉ፡፡

በእንዲህ አይነት ሁኔታም ኦህዴድ ውስጥ አቅም ያላቸው ሰዎች እየደበዘዙ እንደሄዱ ይነገራል፡፡ ነጋሶ ጊዳዳ፣ ሽፈራው ጃርሶ፣ ግርማ ብሩ፣ ሙላቱ ተሾመ... በተወሰነ ደረጃ የኦህዴድን ነፃነት ለማስመለስ የሞከሩ አመራሮቹም ‹‹በጠባብነት›› እና ‹‹የኦነግ አመለካከት ተሸካሚ›› በሚሉ ተቀጥያዎች ተወንጅለው ተገምግመዋል፡፡ እስከመጨረሻው የህወሓትን ጣልቃ ገብነት ከተቃወሙት ውስጥ ነጋሶ ጊዳዳ እና ሽፈራው ጃርሶ ይጠቀሳሉ፡፡ ነጋሶ በ93ቱ የኦህዴድ ግመገማ ላይ በታዛቢነት ለመገኘት የመጡትን የህወሓት የአመራር አባል ስብሃት ነጋን በይፋ ከመቃወምም አልፈው ‹‹እናንተ በዚህ አይነት መልኩ በእኛ ጉዳይ ጣልቃ እየገባችሁ የምትቀጥሉ ከሆነ አንፈቅድም፤ እኛ ሞተን ቢያንስ ለልጆቻችን ነፃነትን እንሰጣቸዋለን›› እስከማለት ደርሰው ነበር፡፡ ኦህዴድ የተጓዘው በዚህ መልክ በመሆኑ ተቆርቋሪ አባላቱን በየመንገዱ አራግፎአል፡፡

ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት ኦህዴድን ከሚመሩት ውስጥ አብዛኛው ከ1993 ዓ.ም በፊት የወረዳ ካድሬ የነበሩ እና በአስቸጋሪው ዘመን ያላለፉ በመሆናቸው ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን የህወሓት/ብአዴን አመራርን መገዳደር የማይችሉ የሆኑት፡፡ ለምሳሌም ሙክታር ከድር በወለጋ ጊንቢ የድልመጂ ወረዳ ካድሬ የነበሩ ሲሆኑ፣ አለማየሁ አቱምሳም እዛው ወለጋ የአንድ ወረዳ ኃላፊ ነበሩ፤ አስቴር ማሞ ደግሞ በጅማ ዞን የኦህዴድ ሴቶች ሀላፊ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከ93ቱ የኦህዴድ ‹‹ፈርሶ መሰራት›› በኋላ ሙክታር የጅማ ዞን ሀላፊ ተደርገው ተሾሙ፤ አለማየሁ አቱምሳ ደግሞ የምዕራብ ወለጋ የድርጅት ቢሮ ኃላፊ ለመሆን ቻሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት አለማየሁ አቱምሳ የኦህዴድ ሊቀመንበር እና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዘዳንት ናቸው፡፡ ሙክታር ከድር ደግሞ የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊ፡፡ ይህ ሁኔታ ከሌሎቹ የግንባሩ ፓርቲ አባል ድርጅቶች አንፃር ሲታይ የተለየና ጤናማ ያልሆነ መተካካት በመሆኑ ኦህዴድን ደካማ ከማድረጉም በላይ ልምድ በሌላቸው ወጣቶች መዳፍ ስር እንዲወድቅ አስገድዶታል፡፡

## የኦነግ ተፅእኖ

ኦህዴድ ከህወሓት/ብአዴን በተጨማሪ ከኦነግ የሚነሳበት ተፅእኖ ለድክመቱ የሚጠቀስ ነው፡፡ ኦነግ ከዚህ ቀደም በኦሮሚያ ላይ በነበረው ተፅዕኖ እና በብሄሩ ያለውን ተቀባይነት እየመነዘረ ኦህዴድ ላይ ያደርግ የነበረው ማጥላላት፣ ኦህዴድ ሊቋቋመው ያልቻለው ሌላኛው ተግዳሮት ነው፡፡

የኦነግን ጥቃት የከፋ የሚያደርገው ኦህዴድን የሚወነጅለው በሚከተለው ርዕዮተ አለም ሳይሆን በኦህዴድ የአመራር አባላት ማንነት ላይ መሆኑ ነው፡፡ ሁሉም የኦህዴድ መስራቾች በመደበኛ እና ብሔራዊ ወታደር ሆነው በኤርትራ ምድር ላይ በሻዕቢያ ተማርከው ኦህዴድን እንዲመሰርቱ መደረጉ ለኦነግ ትችት መደላድል ፈጥሯል፡፡ እናም ኦነግ ሁናቴውን ለበርካታ ዓመታት መጫወቻ ካርድ አድርጎታል፡፡ ከዚህም ባሻገርን ኦነግ ከመንግስታዊ ስልጣን የወጣሁት ‹‹አሻንጉሊት ለመሆን ባለመፍቀዴ ነው›› የሚለው ፕሮፓጋንዳው ኦህዴድን በብሔሩ እንዳይታመን አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ እንግዲህ ለደካማው ኦህዴድ ‹‹ባለበት መርገጥ›› የኦነግ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ መታመን የራሱ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ ኦነግ ይህንን ጉዳይ ለጥጦ የኦህዴድ መስራቾችን ‹‹ስማቸውን በኦሮሞ ስም የቀየሩ›› እስከማለት በመድረስ የኦህዴድ ሰዎች ኦሮሞ መሆናቸውንም ጭምር ጥርጣሬ ላይ የጣለበት ሁኔታ አለ፡፡ በእርግጥ ኦህዴድ ለዚህ ምላሽ ይሆን ዘንድ የኦነግን አካሄድ ‹‹የጠባቦች መንገድ›› ቢልም የሰማው አላገኘም፡፡ አልፎ ተርፎም በ1986 ዓ.ም ‹‹ፕሮግራሜ›› ሲል ባሰራጨው ሰነድ ላይ ‹‹ኦሮሞ በብሄሩ ውስጥም ሆነ በመላ ኢትዮጵያ ደረጃ የሚገኙትን መደባዊ ጠላቶቹን ለመምታት በሚያስችለው ዴሞክራሲያዊ አቋም ላይ የተገነባ ስልት ሊያካሄድ ይገባዋል›› ሲል የገለፀው ከኦነግ ፕሮግራም ጋር ፍቅር በወደቁ የኦሮሞ ተወላጆች ዘንድ እንደ‹‹መናፍቅ›› እንዲታይ አድርጎታል፡፡

## አዲሱ ትውልድ

የኦህዴድ የአመራር አባላት ከላይ በተጠቀሰው ችግር ውስጥ የወደቁ ቢሆኑም በአሁኑ ወቅት በከፍተኛና የበታች ካድሬነት ኦህዴድን የተቀላቀሉ አዲሱ ትውልድ ‹‹ጣልቃ ገብነትን›› ለመቀበል የተዘጋጀ አይመስልም፡፡ ይህም ሁኔታ የኦህዴድን አመራር አጣብቂኝ ውስጥ ከቶታል፤ ምክንያቱ ደግሞ ‹‹የብሄር ፌደራሊዝሙ በትክክል ከተተገበረ የጠቅላይ ሚንስትሩ ቦታ የኦህዴድ ነው›› የሚል ለህወሓት/ብአዴን አደገኛ የሆነ አዝማሚያ ያላቸው የኦሮሞ ወጣቶች ከቀን ወደቀን መበራከታቸው ነው፡፡ በአናቱም በኦነግ አንድም ተስፋ የቆረጡ፣ ሁለትም የኦነግ አቋም ፋሽኑ አል ፎበታል ወደሚል ድምዳሜ የተጠጉ ሆኖም ‹‹መንፈሱ››ን እንተ ገ ብራለን የሚሉ የብሄሩ ልሂቃኖችና በድህረ-97 ፓርቲውን የተቀላቀሉ ወጣቶች ‹‹ኦህዴድን ከውስጥ መቀየር ይቻላል›› በሚል ስሌት በድርጅቱ ዙሪያ መስፈራቸው ለአመራሩ ሌላ ራስ ምታት ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል፡፡

## የመስከረሙ ኦህዴድ

በዚህ በአዲሱ ዓመት ኦህዴድ በውስጣዊ አብዮት እየታመሰ ነው፡፡ ገና ከጅምሩም ከኃላፊነታቸው ዝቅ ያሉ አመራሮችን እያየን ነው፡፡ እንደአዲስ የካርታ ጨዋታ ‹‹የተገጠሙ››ም አሉ፤ የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዘዳንት አብዱልአዚዝ መሀመድ ወደፌደራል ሲመጡ፣ አስቴር ማሞ ደግሞ ከፌደራል ወደክልል ወርደዋል፡፡ (እዚህ ጋ የህወሃት/ብአዴን የቼዝ ጨዋታ ችሎታ ከደመርንበት ምንአልባት አስቴር ማሞ የክልሉ ፕሬዘዳንት ወይም ምክትል ፕሬዘዳንት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ንጉሱ አለማየሁ አቱምሳ ህመምተኛ ሆነዋል፤ አንስላሳዊው የቼዝ ተጫዋች በንግስቲቱ በሚገባ እየተጠቀመ ነው፡፡ ንጉሱንም እያሳደዷቸው ነው-በቼዝ ጨዋታ፡፡ አቶመለስ በህይወት በነበሩበት ጊዜ አስቴር ማሞን ለፕሬዘዳንትነት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ቦታ አጭተዋቸው ነበር፡፡) የማታ ማታም ወደእስር ቤት የሚላኩ የኦህዴድ አመራሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ እየተነገረ ነው፡፡ በእርግጥ በግሌ ይህ የአብዮት ሰይፍ የተመዘዘው ከኦህዴድ ጽ/ቤት ነው ብዬ አላምንም፡፡ አራት ኪሎ ከሚገኘው የኢህአዴግ ጽ/ቤት ነው ብል ግን ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ ይህንን የሚያረጋግጡ አንዳንድ ምክንያቶችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡


## የጁነዲን ጥፋት...

የቀድሞ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዘዳንት ጁነዲን ሳዶ ተገምግመው ተገኘባቸው በተባለ ጥፋት ከኦህዴድ የአመራር አባልነታቸው ተነስተው ተራ አባል ሆነው እንዲቀጥሉ ተወስኖባቸዋል፡፡ በእርግጥ የጥፋቱን አንድምታ ገምግመን በቀላሉ ከዚህ ውሳኔ ጀርባ ‹‹እነማን አሉ?›› የሚለውን ማየት ወይም መገመት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ መቼም የኦህዴድ ሊቀመንበር ተብለው በተሾሙ ማግስት ታማሚ የሆኑት ዓለማየሁ አቱምሳ እና እነሙክታር ከድር በዚህ ደረጃ ገፍተው ቀዳሚ አባል የነበሩትን ጁነዲንን ለማባረር በራሳቸው የሚቆሙ አይመስለኝም፡፡ በአናቱም በጁነዲን ላይ የቀረበው ክስ በቀጥታ የሚገናኘው ከኢህአዴግ እና ከመንግስት ጋር ነው፡፡ ምክንያቱም ጁነዲን በጋዜጣ የተቃወሙት ‹‹ባለቤቴን በግፍ አሰረብኝ›› ያሉትን መንግስት እንጂ የራሳቸውን ድርጅት ጓዶች አይደለም፡፡ (በነገራችን ላይ መንግስት ‹‹ዋሀቢያ›› እያለ የሚያሸማቅቃቸው ሠለፊዎች በሳውዲ አረቢያ እንደሚደገፉ ሲነገር፤ ከአህባሽ ጀርባ ደግሞ የአሜሪካ መንግስት እጅ አለ በሚባለው መላ-ምት ከተስማማን እና የጁነዲን ባለቤት የተያዙት ከሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ 50 ሺህ ብር ከበርካታ ቅዱስ ቁራን ጋር በዕርዳታ ተቀብለው መሆኑን ደምረን ቀላል ሂሳብ ካደረግነው፤ የኦህዴድ የመስከረም አብዮት በትክክልም ባለቤቱ ማን እንደሆነ ግልፅ ይሆናል)

ከአራቱ ድርጅቶች ‹‹በተከፋፈለ አመራር›› ስር በመውደቅ ኦህዴድ ሪከርዱን እንደያዘ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የተፈጠረው በኦህዴድ ውስጣዊ ድክመት ብቻ አይደለም፡፡ የህወሓት አመራር በሀገሪቱ ላይ ይከተለው የነበረው የማኪያቬሊ አስተምህሮት (ከፋፍለህ ግዛን) በኦህዴድ ላይም በመተግበሩም ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም ሌሎቹ ድርጅቶች በዚህ ችግር ውስጥ ሲገቡ አይታዩም፡፡ ህወሓት በ1993 ዓ.ም. ለሁለት ሲከፈል ከተፈጠረው ችግር ውጭ ማለቴ ነው፡፡ የብአዴን ወይም የደኢህዴን የአመራር አባላት አንድም ጊዜ እርስ በእርስ ሲወነጃጀሉ የታየበት አጋጣሚን አላስታውስም፡፡ ኦህዴድ ግን ብዙ ጊዜ በእንዲህ ዓይነት ማዕበል ተመቶ ሲንገላታ ተመልክተናል፡፡ የእርስ በእርስ ክፍፍሉ ምን ያህል በተናጥል ወይም በግለሰብ ደረጃ እንደወረደ የሚያሳየው ምሳሌ በ93ቱ ተሃድሶ የኦህዴድ የአመራር አባል የነበሩት አልማዝ መኮ በወቅቱ ከህወሓት ጋር ችግር ውስጥ ገብተው የነበሩትን ነጋሶ ጊዳዳን ‹‹ሂሳብህን አወራርድ!›› እያሉ ተችተው ሲያበቁ፣ በአንድ ወር ውስጥ ጥብቅና የቆሙለትን ስርአትም ሆነ ቀሪውን የኦህዴድ የአመራር አባላት ከድተው ከሀገር መኮብለላቸውን ስናስተውል ነው፡፡ በእርግጥም በርካታ አመክንዮችን እየጠቀስን የኦህዴድ አመራር ተመሳሳይ አቋም ኖሮት አያውቅም፣ ወይም ሆነ ተብሎ ጠንካራ አመራር እንዳይኖረው ተደርጓል ብለን መከራከር እንችላለን፡፡ በዚህ የእርስ በእርስ መጠላለፍም ዋነኛ ተጠቃሚው ህወሓት/ብአዴን መሆኑን መከራከር ጉንጭ አልፋ ነው፡፡

ኦህዴድ ብዙ ጊዜ ፈርሶ ተሰርቷል፡፡ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር አይጉና ናጫ እንደሆነም ነው ዛሬ ላይ የደረሰው፡፡ ኦነግ ከክልሉም ተባሮ ኦህዴድ የኦሮሞን ህዝብ መማረክ አልቻለም ነበርና በወቅቱ አቶ መለስ ‹‹ዝንብ›› እያሉ የሚያጣጥሉትን ኦህዴድ ጠንካራ መሆኑን ገልፀው ሲያበቁ የኦሮሞ ህዝብ ይቀበለው ዘንድ እንዲህ ሲሉ ማስታወቂያ ሰርተውለት ነበር ‹‹ማዕበሎች ከቀኝም ከግራም ተነስተው ነበር፡፡ በማዕበሉ የተናደደና የተሸረሸረ ባይጠፋም፡፡ ኦህዴድ ልክ እንደዋርካው ወደ መሬት ገብቶ ስለነበር አልተነቃነቀም›› ...ዛሬ ግን ይህን የሚል የለም፡፡ እናም የኦሮሞ ተወላጆች እየደረሰባቸው ያለው መከራ፣ መሰረታዊ ጥያቄያቸው፣ እንዲሁም የ‹‹ዋርካው›› ዕጣ ፈንታ ከመስከረሙ አብዮት ፊት ለፊት የቆሙ ይመስላል፡፡ ኦህዴድ ደግሞ ችግርህ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄን መመለስ አለመቻልህ ሳይሆን ‹‹መደባዊ›› ነው ተብሎ ስለተነገረው ‹‹ኪራይ ሰብሳቢ›› እና ‹‹ልማታዊ›› በሚሉ አጀንዳዎች ተጠምዷል፡፡

ሕግ



ጌታቸው ታምራት (LLB)

# ነፃነት ከሌለ ጥንካሬ ከወዴት?

"Our greatest security will be found on maintaing our freedom. We are not free because we are strong; on the contrary, we are strong because we are free. Our whole way of life rests upon the verity of this proposition." /የእኛ ትልቅ ደህንነት ያለው ነፃነታችንን ማስጠበቅ መቻላችን ላይ ነው፡፡ ጠንካራ ስለሆንን ነፃ አልሆንም በተቃራኒው ነፃ ስለሆንን ግን ጠንካራ ሆነናል፡፡ አኗኗራችን የተመሰረተው በዚሁ ብሂል እውነታ ላይ ነው፡፡/ የነፃነትን አስፈላጊነት በዚህ በነጠረ ቃል በጥሩ ሁኔታ የገለፁት ፕሮፌሰር ዴቪድ ፊልማንስ ‹‹The right of the accused›› /የተከሰሱ ሰዎች መብት/ በሚለው ፅሁፋቸው ነው፡፡ በእርግጥም የደህንነትና የጥንካሬ መሰረቱ ነፃነት ነው፡፡ የሃይማኖት ነፃነት፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት፣ የመሰብሰብ ነፃነት፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቤቱታን የማቅረብ ነፃነት፣ ወዘተ፡፡ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉ መብትና ነፃነቶች ተነፍገው ደህንነትና ጥንካሬ አይኖርም፤ መታሰብም የለብትም፡፡

እኛስ ነፃነት አለን? ጠንካሮችስ ነን? ነፃ ከሆንን የነፃነታችን መሰረቱ ምንድን ነው? ጥንካሬያችን ያለው የቱ ላይ ነው? ከላይ በጥቂቱ ለመግለፅ የሞከርኳቸው የነፃነት መገለጫዎች ሊሸራረፋና ሊቀናነሱ በማይችል መልኩ በመርህ ደረጃ ተቀምጠው መሬት ላይ መውረድ ከቻሉ አንድም ነፃነት የሚገኝበትን መንገድ አመቻችተናል በሌላ በኩል ደግሞ በነፃነታችን እየጠነከርን እንሄዳለን፡፡ የሀገራችን ህገ-መንግስት በበቂ ሁኔታ ባይሆንም አንዳንድ መብትና ነፃነቶችን በውስጡ ይዟል፡፡ እነዚህ ህግጋቶች በውዴታም ይሁን በግዴታ በዚህ ሰነድ ውስጥ መካተታቸው ለነፃነት መስፈን ከሚያስፈልጉት እርምጃዎች ጥቂት እንዳልን ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በህገ-መንግስቱ መብትና ነፃነት የሚለው ትርጉም የተሰጣቸው አብዛኞቹ እንዲያውም በአንዳንድ ሁኔታዎች ሁሉም ማለት በሚችል መልኩ በተግባር ሲታይ ተሸብበዋል፣ ለዜጐች አልተሰጡም ቢሰጡም ተነጥቀዋል፣ ነፃነታችንን አሳልፈን አንሰጥም ያሉ ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ንብረታቸውም ተወርሷል፡፡ በአደባባይም የግዴታ ‹ይቅርታ› አንገታቸውን እንዲደፉ ተደርገዋል፡፡ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነት፡፡ በህገ-መንግስቱ ተቀምጧል በተግባር ግን የለም፡፡ ሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ነፃ ጋዜጦች ተዘግተዋል፡፡ ታግደዋል አልያም በተዘዋዋሪ መንገድ ህዝቡ ጋር እንዳያደርሱ ተደርጓል፡፡ ለዚህ ምሳሌ ፍትህና ፍኖተ ነፃነትን መግለፅ ይቻላል፡፡ ይህ አካሄድ ለዜጐች ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ይገድባል ለመላው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ መረጃ የማግኘት ነፃነትን ያሳጣል፡፡ ያለ መረጃ ፍሰት መግባባት አይቻልም፣ በመተባበር መስራት ይከብዳል፣ የዜጐችን ንቃተ ህሊና ማዳበር አይቻልም፣ ወዘተ፡፡ ይህ ግን በአደባባይ ያለው እውነት ነው፡፡ በየመንግስት መስሪያ ቤቱ ህገ-ወጥ አሰራር መኖሩን እያወቁ፤ በሙስና የተጨማለቁ ግለሰቦች ለማውጣት በፍርሃት ቆፈን ተጨናንቀው ያሉ ሞልተዋል፡፡ ሀሳባቸውን በነፃነት መግለፅ የዕለት እንጀራቸውን መስዋዕትነት ያስከፍላቸዋል፡፡ የመንግስትን ፖሊሲዎችና የግለሰቦችን ብልሹና ህገወጥ አሰራር መተቸት ነፃነትን በተገቢው መንገድ መጠቀም ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ግን በእኛ ሀገር ባልተፃፈ ህግ ወንጀል ነው፡፡

የሃይማኖት ነፃነት በዚሁ ሕገ-መንግስት ውስጥ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ እንዲሆኑ፤ መንግስት በሃይማኖት ጉዳት ጣልቃ እንደማይገባ፣ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ እንዲሁም መንግስታዊ ሃይማኖት እንደሌለ በሀገሪቷ የበላይ የህግ ሰነድ በሆነው ህገ-መንግስቱ ውስጥ በነጭ መደብ ላይ በጥቁር ቀለም በደማቁ ተፅፏል፡፡ መሬት ላይ ያለው እውነታ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ መንግስት የሃይማኖትን ነፃነት እየተጋፋ ነው፡፡ በሃይማኖት ጉዳይ በገሃድ ጣልቃ እየገባ ነው፡፡ ይሄን የሃይማኖት መስመር ነው መከተል ያለባችሁ፤ ሃይማኖቱንም የሚመሩት ልሂቃን እኔ ካልኩት ውጭ አይሆኑም እያለ ነው፡፡ መንግስት የሃይማኖት መሪዎችን እየቀባና እየሾመ፤ የሃይማኖት አመለካከትን /Doctrine/ በፓርላማ ሳይቀር እየተነተነ የቱ ልክ እንደሆነ የትኛው የተሳሳተ መስመር ውስጥ እንዳለ ሰብኳል፡፡ ተከራክሯል፡፡ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ የማይገባው ሃይማኖቱ የእሱ ስላልሆነ ነው፡፡ በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ከገባ ወይ በማያገባው ገብቷል አልያም ሃይማኖቱ የመንግስት ነው፡፡ በሁለቱም መንገድ ግን ህገ-መንግስቱን ክዷል፤ ነፃነትን ተጋፍቷል፡፡ በህጉ እንደተቀመጠው መንግስት ሃይማኖት የለውም ቢባልም ሁሉም ሃይማኖቶች የመንግስት እስኪመስሉ ድረስ በቀጥታና በእጅ አዙር ሁሉንም ይነካካል፤ ይበረብራል፡፡ ታዲያ የሃይማኖት ነፃነት የት አለ?

የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት በህጉ ተቀምጧል ግን በአሁኑ ሰዓት መንግስትን በመቃወም መሰብሰብ አይቻልም፡፡ ህጉን መሰረት አድርገው በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ ፓርቲዎች ከደጋፊዎቻቸው ጋር በአደባባይ መገናኘት አይችሉም፡፡ ስብሰባዎቻቸውን የሚያደርጉት በስማ በለው ተጠራርተው ከመጡ ደጋፊዎቻቸው ጋር በየጓዳ ጐድጓዳው ውስጥ ነው፡፡ ሌላውም የህብረተሰብ ክፍልም ቢሆንም ተቃውሞውን ለመግለፅ አደባባይ አይወጣም፡፡ ቢጥመውም ባይጥመውም ዋጥ አድርጐ መቀመጥ አለበት፡፡ አደባባይ ወጥቶ መሰብሰብ የሚቻለው የገዢው ፓርቲ ዓመታዊ በዓላትን ለማክበር፣ መንግስት የሚጠራቸውን ስብሰባዎች ለማድመቅና ‹ታላቁ› መሪያችን ለማለት ብቻ ነው፡፡ በአደባባይ መሰባሰብ ከምርጫ 97 ወዲህ በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር በግልፅ ከታገደ በኋላ ይህ ነው የሚባል የተቃውሞ ሰልፍ ተደርጐ አያውቅም፡፡ ህዝቡ በጋራ የሚሰበሰብበት ጉዳይ አጥቶ ሳይሆን ነፃነቱን ተነፍጐ ነው፡፡ ለነገሩማ መሰብሰብ አትችልም የሚለውን እገዳ ለማስመለስ ራሱ መሰብሰብ ይገባው ነበር፡፡ ታዲያ የመሰብሰብ ነፃነት የታል?

ዜጐች የፈለጉትን ንብረት የማፍራት እና ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብታቸው በህግ ደረጃ ተቀምጧል፡፡ መንግስትም እነዚህን መብትና ነፃነቶች በህጉ ማካተቱ ያኩራራዋል፡፡ በተግባር ያለው ግን ከዚህ በእጅጉ የራቀ ነው፡፡ ነፃነታቸውን የሚጠይቁ፣ እውነታውን ለህዝቡ ይፋ የሚያደርጉ፣ ህጉ መከበር እንዳለበት የሚከራከሩ ግለሰቦች ከቤታቸው ደጃፍ እስከ መድረሻቸው ድረስ የመዘዋወርና የመኖር ነፃነታቸውን በሚጋፉ የደህንነት ሃይሎች እርምጃቸው እየተቆጠረ ክትትል ይደረግባቸዋል፤ ዜጐችን ለማፈን በወጡ ሕጐች ከለላነት ክስ ይመሰረትባቸዋል፡፡ ክስ ከተመሰረተባቸው ደግሞ በየትኛውም ደረጃ ማስረጃ አቅርበው ቢከራከሩም ጥፋተኛ መባላቸው አይቀርም፡፡ በህጉ ለተከሰሱ ግለሰቦች የተሰጠው መብታቸው አይከበርላቸውም፡፡ በነፃነት ከህግ አማካሪዎቻቸው ጋር መገናኘት አይችሉም፡፡ የተከሰሱት ጥፋተኛ ለመባል እንጂ ለመከራከር አይደለም፡፡ በእስር ላይ ሆነው እንጂ የዋስትና መብታቸው ተከብሮ ውጭ ሆነው መከራከር አይችሉም፡፡ የኑሮ አቅማቸው እንዲዳከም ላባቸውን ጠፍ አድርገው ያፈሩት ንብረታቸው እነሱን ታሳቢ አድርገው በወጡ ህጐች አማካኝነት ይወረሳል፡፡ በተቃራኒው የእነሱን ነፃነት አፍነው በህገ ወጥ መንገድ ሀብትና ንብረት ያፈሩ ግለሰቦች እንደ አንበሳ ጥጃ ይፈነድቃሉ፡፡

እነዚህን ለአብነት ያህል አነሳን እንጂ ብዙ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ነፃነት ከሌለ በሙስና የተጨማለቁ ባለስልጣናትን ማጋለጥ የምጥ ያህል ይከብዳል፡፡ ተሰብስቦ፣ በጋራ ጉዳይ ላይ ተመካክሮ የለውጥ አማራጭ መጠቆም ካልተቻለ የተበታተነ ሀሳብ በፍርሃት አኮፋዳ ውስጥ ከተን መጠንከር አንችልም፡፡ በቀን አንዴ ብንጐርስ እንጂ ሁለት ሶስቴ ይቸግረናል፡፡ የጥይት ድምፅ ስላልሰማን ደህንነት አለ ማለት አይደለም፡፡ ዜጐች እየታፈኑ፣ እየተዋከቡ፣ አፋቸውን ተለጉመው እንዲፈሩ እየተደረገ፣ እየታሰሩ፣ ንብረታቸው በአደባባይ እየተወረሰ፣ በማይናገረው ልቦናቸው ውስጥ የነፃነት ፍላጐት አብጦ እያለ ስለነፃነት ማውራት አይቻልም፡፡ ስላልወደቅን ጠንካራ ነን ማለት አንችልም ግን ልፍስፍሶች ነን፡፡ ምክንያቱም ነፃነት የለንም፡፡ አንድም ነፃነታችንን አሳልፈን ሰጥተናል አልያም ደግሞ ማስመለስ አቅቶናል፡፡ ከላይ መነሻዬ ላይ እንደገለፅኩት የጥንካሬ መሰረት ሊሆን የሚችለው ነፃነት ነው፡፡ ነፃነት ከሌለ መጠንከር አይቻልም፡፡ ካልጠነከርን ደግሞ እድገትና ብልፅግና አይኖርም አለ ብለን የምናወራ ከሆነ ተሳስተናል፡፡ ያለ ነፃነት ቀጣይነት ያለው ደህንነት መገንባት አይቻልም፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ ችግር ባለበት ሀገር ስለምን ስለነፃነት፣ እድገት፣ በምግብ እህል ራስን ስለመቻል፣ ስለደህንነትና ሌሎች ጉዳዮች ለማውራት እንደፍራለን ስለ ነፃነት የምናደርገው ማናቸውም ትግል ለአንድ ሰከንድ እንኳ መስተጓጎል የለበትም፡፡ ነፃነታችን በገዥዎች ቁና እየተሰፈረ የሚሰጠን የኑሮ ራሽን ሳይሆን በተፈጥሮ የተቸረን፣ ብዙሃን የሞቱለት፣ በህግ ተደንግጎ ያለ ከሆነ መከበር ያለበት ከሌለ ደግሞ ህግ የሚያስፈልገው፤ ከሁሉም በላይ የጥንካሬያችን መሰረት ሊሆን የሚገባው ነው፡፡ ነፃነታችንን እናስመልስ ጥንካሬያችንም ይመጣል ከዚያ ሁሉንም ለማድረግ ይቻለናል፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡



# ተባብረዋል አርበኞችሽ፣ አይነካም ከቶ ነፃነትሽ፡፡

## ከቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር የተወሰደ

ታዴዎስ ታንቱ

በአቅርቦት ዘርፍ ትጋት ስሟ አሻቅቧል፡፡ አቀባብሎ በማነጣጠር ዒላማ የመምታት ችሎታ ግን አልነበራትም፡፡ ለምክንያቱ ደግሞ ምክንያት ተመዝግቧል፡፡ የባህል ተፅዕኖ ውጤት ይጠቀሳል፡፡ ከዒላማ ተኩስ ልምምድ በሩቅ ርቀት ማደን ዐቢይ ሰበብ ሆኖ ይወሰዳል፡፡ በባህላዊ እሳቤ ጠብመንጃ ለወንድ ጀብዱ ብቻ ተፈቅዷል፡፡ ዛሬ ግን ቀውጢ ቀን መጥቷል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከኢትዮጵያ መሬት ገብቷል፡፡ ድም! ም! ም! ም! ድም! ም! ም! ም! ይህ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የመድፍ ተኩስ ድምፅ ነው፡፡ ባሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ልዕልት በባሌ መስመር በውጊያ ወረዳ በተጨባጭ የተጋድሎ አስተዋፅኦ ትስተዋላለች፡፡ የቀድሞ ዘመን የድሎት ኑሮ ቀርቷል፡፡ ሀገር ተደፍራ መልካም ኑሮ ከግንዛቤ ማህደር ውስጥ እንዲገባ አይታሰብም፡፡ ልዕልቷ ሥራ በዝቶባታል፡፡ በጣም በዝቶባታል፡፡ ጥይቶችን በዓይነት በዓይነቱ መድባ በየአቅጣጫው ለአርበኞች ትሰድዳለች፡፡ በተጨባጭ በተግባር አስመስክራለች፡፡ የቁስለኞች እንክብካቤ በኃላፊነቷ ሥር ወድቋል፡፡ አቅም በፈቀደ መጠን ለአርበኞች ቀለብ የማቅረብ ስራም የልዕልቷን የቅርብ ክትትል ጠይቋል፡፡ መድፍ ሲያጓራና መትረየስ ሲንጣጣ ከድንጋጤ ፀድታ ትቆማለች፡፡ በተግባር ልበ ሙሉ ሴት መሆኗ ተረጋግጧል፡፡ ማን ይፈራል ሞት? በአጠገቧ ብዙ ጊዜ ጀግኖች ወድቀዋል፡፡

የግል ህይወቷ ተመሰቃቅሏል፡፡ ግዳጇን ግን በፀጋ ተቀብላለች፡፡ አሸዋ ለብሳ ድንጋይ ተንተርሳለች፡፡ አንድ ዓመት ሙሉ በረሐ ለበረሐ ተንከራትታለች፡፡ ቆራጧ ልዕልት ቆርጣለች፡፡ ፈሪ በዋለበት አትውልም፡፡ ጦርነቱ ህይወት እየበላና ነፍስ እያጨደ ቀጥሏል፡፡ ከወገን የመከላከል አቅም በላይ አሻቅቧል፡፡ ጀግናዋ ልዕልት ከውጊያ ወረዳ ላይ መሆኗን አንዘንጋ! የኢትዮጵያ አርበኞች ሕይወታቸውን ገብረዋል፡፡ በጀግንነት ሳይሆን በጦር መሣሪያ ብዛትና ጥራት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የበላይነትን ይዟል!

አሁን ሚያዝያ ወር ውስጥ እንገኛለን! ታሪክ በታሪክ ይናገራል! 1929 ዓ.ም. እንደ ነበር መዝግበናል፡፡ ድም! ም! ም! ም! ድም! ም! ም! ም! ቡም! ቡም! ቡም! የመድፍ ተኩስ አሻቅቧል! የቦምብ ውርወራ በቡምታ ድምፀት ምድርን ያናውጣል! ልዕልቷ ከውጊያ ወረዳ መኻል ትገኛለች! ሀገሯንና ሐይማኖቷን ለማዳን ትታገላለች! ሳታቅማማ ወደ ፊት ታመራለች! ሳታመነታ ዘለቀች! ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሳትንበረከክ ትጓዛለች! በአኩሪ ተግባሯ ስሟን አስመዘገበች! ሀገሯን እንደምትወድድ በድርጊት አመለከተች! የወርቃማ ታሪክ ባለቤት ትሆናለች! በታማኝነት ዘለቀች! በየዕለቱ ታሪክ ታስመዘግባለች! የጥይት ጩኸት ለሷ ጣዕመ-ዜማ ነው! ድም! ም! ም! ም! ድም! ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! በጣም ያሳዝናል! ለአንድ ዓመት ሙሉ በረሐ ለበረሐ የተንከራተተችው ልዕልት በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጥይት ተመትታ ወደቀች! ነገር ግን ነፍሷ ከስጋዋ አልተለየችም! በህይወት አለች! ጉዳቷ ግን ከባድ ነው! ውድ የኢትዮጵያ ልጅ በዓላማዋ ፀንታ ራሷን ሆና ዘለቀች፡፡

ባሁኑ ሰዓት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ ልዕልቷ እየተጠጋ ነው፡፡ በሕይወት እንደ ነበረች ከቅርብ ርቀት አይተዋታል፡፡ የኢትዮጵያ ጀግኖችን አስክሬን እየረገጠ ያልፋል፡፡ ልዕልቷ በውጊያ ወረዳ ላይ በፅናት እንደ ነበረች ከአስተማማኝ ምንጭ መረጃ ታጥቋል፡፡ ተጠግቷል፡፡ የልዕልቷ ባለቤት ጀግናው ደጃዝማች በየነ መርዕድ በታላቅ ጀግንነት ተሰውቷል፡፡ አስክሬኑ ተዘርሮ ይስተዋላል፡፡ ወራሪው ኃይል የጀግናውን የበየነ መርዕድን አስክሬን በአድናቆት ይመለከተዋል፡፡ ጥቂት ሄድ አለ፡፡ ልዕልቷን ከወደቀችበት አነሳት፡፡ ከአማርኛ በስተቀር ሌላ ቋንቋ አታውቅም፡፡ ደም ይፈስሳት ነበር፡፡ ፋሽስቱ መስመራዊ መኮንን መልእክት ሊነግራት ፈልጓል፡፡ አስተርጓሚ የግድ ብሏል፡፡ ነገር ግን ‹‹አስካሪስ›› እየተባሉ የሚጠሩት ባንዳዎች ራሳቸው አማርኛ የማያውቁ ነበሩ፡፡ ሌሎች ባንዳዎች ደግሞ ጆሮአቸውን ቢቆርጡት ኢጣሊያንኛ አይሰሙም፡፡ የግድ ሁለቱን ቋንቋዎች የሚያውቅ መገኘት ነበረበት፡፡ መገኘቱም አልቀረም፡፡ የፋሽስቱ መስመራዊ መኰንን በድል ስሜት አፉን ከፈተ፡፡ በኩራት መንፈስ ገናናው የኢጣሊያ መንግስት ሊሸነፍ እንደማይችል ተናገረ፡፡ ንግግሩን ሳያቋርጥ ቀጠለ፡፡ አሁንም ቀጠለ፡፡ በተለይ ልዕልቷን አስመልክቶ የተስፋ ቃል አወረደ፡፡ በእንክብካቤ እንደምትያዝ ገለፀላት፡፡ የልጆቿ ዕጣ ፈንታስ ምን ሊሆን ይችላል? ራሷን በራሷ ጠየቀች፡፡ በእጅጉ አሳስቧታል፡፡ የሆነውን ማንም ያውቃል፡፡ ወደ ፊት ምን ሊሆን ይችላል? መተንበይ ይከብዳል፡፡

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ልዕልቷን ወደ አዲስ አበባ አመጣት፡፡ ውላ አላደረችም፡፡ ቁስሏ አልዳነም፡፡ የበረሐ ልብሷን እንኳን አልቀየረችውም፡፡ ከግል ንብረቷ ምንም ነገር አልያዘችም፡፡ በግንቦት ወር 1929 ዓ.ም. ወደ አዚናራ ተጠረዘች፡፡ ከሕፃናት ልጆቿ ጋር ታሰረች፡፡ ልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለሥላሴ! ጀግናዋ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ልጅ!

ልዕልቷን ከእስራቷ በበለጠ ብቸኝነቱ ጎድቷታል፡፡ አዚናራ ወህኒ ቤት ውስጥ ማንም አፅናኝ አልነበራትም፡፡ ከልጆቿ ጋር ተኮማትራ ትውላለች፡፡ ሌሎች እስረኞች ሊያናግሯት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ልጅ በመሆኗ ብቻ ራቁዋት፡፡ ከሷ ጋር መነጋገር ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነትን የመግለፅ ያህል ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ሁሉም ፈርተዋታል፡፡ ይህች ምስኪን ልዕልት ወገን አጣች፡፡

ልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለሥላሴ በብቸኝነት ተኮማትራ ስትኖር በድንገት በሳምባ ምች ተጠቃች፡፡ ሕመሟ ደግሞ እየባሰ ሄደ፡፡ ክፉኛ ተሰቃየች፡፡ ስለዚህ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሹማምንት ተሰብስበው ከአንድ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የግድ ነበር፡፡ ወደ ሮማ ተላከች፡፡ ሕክምና ተደረገላት፡፡ ነገር ግን ምንም አልተሻላትም፡፡ እንዲያውም ሕመሟ እየፀና ሄደ፡፡ ስለዚህ በሰኔ ወር 1932 ዓ.ም ለአየር ለውጥ ታስቦ ቶሪኖ ወደ ተባለ ስፍራ ተወሰደች፡፡ ጀግናዋ የኢትዮጵያ ልጅ ግን አልተሻላትም፡፡ ጥቅምት 4 ቀን 1933 ዓ.ም. በሰላሳ አንድ ዓመቷ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች፡፡ ተንከራታቿ፤ አጋር ከጎኗ ያልነበራት ምስኪኗ ልዕልት አረፈች፡፡

አርበኛዋ ልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለሥላሴ ሶስት ህፃናት ልጆቿን በባዕድ ሀገር ትታ ለአንዴና ለሁልጊዜ አሸለበች፡፡ በ1934 ዓ.ም ጌታቸው በየነ ዕድሜው 9 ዓመት እንደነበረ ዋቢ ሰነድ ይዘናል፡፡ መርዕድ በየነ 8 ዓመቱ እንደ ነበር ተመልክቷል፡፡ ሳምሶን በየነ ደግሞ 7 ዓመቱ እንደ ነበር ታውቋል፡፡ እናታቸው ከሞተች በኋላ ህፃናቱ ከቶሪኖ ወደ ሊጎሪያ ሪቪራ ተወሰዱ፡፡ ኮንሶላታ የተባለ ማህበር በጊዜው በእንክብካቤ ይዟቸው እንደ ነበር ታውቋል፡፡ ልጆቹ አድገዋል ወይስ ሞተዋል? ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል ወይስ እዚያው ቀርተዋል? ከመካከላቸው ዛሬ በህይወት የሚገኝ አለ ይሆን?


ልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ንጉሰ ነገስቱ እቴጌ መነንን ከማግባታቸው በፊት የወሎ ተወላጅ ከሆኑት ከወይዘሮ ወይኒቱ ዐመዴ በ1902 ዓ.ም. እንደተወለደች በታሪክ ተመልክቷል፡፡ ልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ በልጅነት እድሜዋ ከተማሪ ቤት ገብታ ንባብና ጽሕፈት ከእጅ ሥራ ጋር ተምራለች፡፡ ከርታታዋ ልዕልት ሃይማኖት አጥባቂም እንደ ነበረች ተመልክቷል፡፡

የልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለሥላሴ አፅም ወደ ሀገር ቤት እንዲመጣ ሐሳብ ቀርቦ ነበር፡፡ ለማስረጃም፤ ባንድ ወቅት በቫቲካን የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን ሚኒስትር ማርቆስ አጋጅ የለው ይህን ሐሳብ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አቅርቦ እንደነበር ተመልክቷል፡፡ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግን ሐሳቡን ውድቅ አድርገዋል፡፡ ምናልባት ንጉሠ ነገሥቱ ከባለቤታቸው ከእቴጌ መነን ውጭ ከሌላ ሴት መውለዳቸው ጎልቶ እንዲታወቅ አልፈለጉም፡፡ ወይም በማናውቀው መንገድ የተሰማቸው ነገር ሊኖር ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ ለእሳቸው ክብር ተብሎ ይህች የሀገር ባለውለታ መረሳት የለባትም፡፡ አሁንም ቢሆን አፅሟን ከሮም በማምጣት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅጥር ግቢ ውስጥ ለማሳረፍ በጥብቅ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ልጆቿ ሞተው ከሆነ የልጅ ልጆቿ ያስቡበት፤ የሀገር ባለውለታዎች ከየትኛውም መደብ ቢወለዱ ልዩ ክብር ይገባቸዋል፡፡ የሞተችበት ቀን ይታወቃል፡፡ መቃብሯ ያለበትም ስፍራ ግልፅ ነው፡፡ መቃብሯ ምናልባት ቁጥር ሊኖረውም ይችላል፡፡ በዘመኑ ጣሊያን የሰለጠነች እንደነበር አንርሳ! ሁሉም ድርጊት በሰነድ ይሰፍራል፡፡ ትምህርት ቤቶችና መንገዶችም በስሟ ሊሰየሙ ይገባል፡፡ ዘለዓለማዊ ክብር ለአርበኛዋ ልዕልት ለሮማነወርቅ ኃይለሥላሴ!

አሁን ደግሞ ከልዕልት ሮማነወርቅ ኃይለሥላሴ ወደ ሸዋረገድ ገድሌ ተንደርድረናል፡፡ ሸዋረገድ ገድሌ በኢትዮጵያ የአርበኞች ታሪክ የላቀ ስፍራ ይዛለች፡፡ ይህች አርበኛ ከተጻፈላትና ከተነገረላት የበለጠ የጀግንነት ውሎ ሁነት ቅርስ ለትውልድ አውርሳለች፡፡ ይህ ደግሞ በቅብብሎሽ ለወረደው ለቀደምት ኢትዮጵያውያን አትንኩኝ ባይነትና አይበገሬነት አጠናካሪ ነቃሽ ሆኖ ይወሰዳል፡፡ የሀገር መኩሪያ የወገን መመኪያ ናት፡፡ የጀግና ዘር በጀግንነት ታሪክ ማህደር ስሟን በወርቅ ቀለም ተከለች፡፡ ሸዋረገድ ገድሌ!

ዛሬ ግን የጅግንነት እሳቦት ትርጉሙ ከነባሩ ፅንስ-ሓሳብ ወጥቶ ለእርካሽ ግለሰባዊ አመልኮና ለጎጥ

ወደ ገፅ 27 ዞሯል



# ሃሣብ...ማሠብ ... አሳቢነት...

ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

ወድቋል ማለት ይቀላል፡፡ አልጋው ላይ የተጣለ እንጂ የተኛ አይመስልም፡፡ ጥልቅ መጥፋት ውስጥ ነበር፡፡ ሕልምም ቅዠትም አላየም፡፡ ተኝቶ ብቻ ነው የተነሳው (ይቅርታ ተኝቶ ነው የነቃው)፡፡ አልጋው ላይ ወድቆ ነበረ የተነሳው፡፡

ዓይኖቹን ገለጠ በሥተግራ በኩል ካለችው ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ከኮንዶም አጠገብ የተቀመጠ አንድ የሮዝማን ሲጋራ አንሥቶ ለኮሠ፡፡ አሠበ፡፡ ማሰብ ማፍጠጥ ከሆነ እያሰበ ነው (እዚህ ላይ አሰበ ያልኩት እኔ ነኝ ወይስ እርሱ እያሰብኩ ነው አለ) መልካም አለም አላለም... እያሰበ ነው፡፡ ...እኔም ካልኩኝ እያሳሰብኩት ነው፡፡

በሌላ ሁኔታ ውስጥ በማናሰላስላት ነጥብ ላይ መብሰልሰል ማሰብ ከሆነ (በትላንቱ ሁኔታ ውስጥ መፀፀት ወይ መደነቅ) ማሰብ ከሆነ አፍጥጧል፡፡ ማፍጠጥ ማሰብ ተደርጎ ስለሚወሰድ፡፡ ምን አልባት ማሰብ ከመፃዒ ጊዜ ጋር ቁርኝት ሊኖራት ይችላል፡፡ ወደኋላ ማሰብ ግን ስላልታሰበበት የማሰብ ያህል ነው፡፡ ማስታወስ የተሆነውን ወደኋላ የመተርተር ውጤት እንጂ በራሱ የአሁንታ ሁኔታ አይመስለኝም፡፡

ሲጋራውን በረዥሙ ሳበ፡፡ በረዢሙ ተነፈሰ፡፡ ጢሱ ተበተነ ...የጢሱ ሽታ ትላንት ያሳለፈውን ሁኔታ መሰለው ትላንትን እያስታወሰ (እያሰበ) ሌላ ሀሳብ ታሰበው ...ከአንዱ ወደ ሌላው ሲሸጋገር የሚያውቀው ነገር አልነበረውም፡፡ ... (ካላወቀ እነዴት እያሰበ ነው) ማለት እንችላለን... ቢሆንም አያሰበ ነው...

*

ለመተኛት ማንቀላፋት ያስፈልጋል፡፡ ካንቀላፉ መውደቅ አለ፡፡ መውደቅ!!! ከወደቁ በኋላ የሞት ልምምድ (እንቅልፍ) አለ፡፡ ...እንግዲህ በእንቅልፍ መሃል ነው... ሕልም የሚታለመው ሕልም ከሌለ ቅዠት ከምንም ግን መቃዠት በራሱ ተመራጭ ነው፡፡ ...ብዙ ጊዜ ግን የሚሆነው ምንም ነው፡፡ ተኝቶ መንቃት ወድቆ መነሳት ብቻ፡፡ ያለሕልም ያለ ቅዠት... ከወደቀበት ተነሣ፡፡

ወጣ፡፡

የሆቴሉን ደረጃ እየቆጠረ ወረደ፡፡ ሰባት ደረጃ፡፡ ሥምንተኛው ወለል፡፡ ሰባት ነው አለ፡፡ ለራሱ ስምንተኛውንም አልቆጥርም ብሎ በልቡ አሰበ፡፡ ሰባትን ስለሚወድ የእድል ቁጥሬ ሰባት ነው ይላል.. ሥላሴ በሰባት ናቸው፡፡ ሰው የሰባት ነገሮች ውጤት ነው... የስጋው ክፍል አራት፡፡ ስጋ ጎደሎ የሚሆነው ደካማ የሆነው ሙሉ ስለሆነ ነው፡፡ ነፍስ የሶስት ባህርያት ውጤት ናት የማሰብ የመናገር የሕያውነት እኔ ከነፍስ ወገን ስለሆንኩ በሰባት አምናለሁ አለ... ሰባት ራሱ በራሱ ለራሱ የታመነለት ቁጥር ነው፡፡ ሲወጣ በልቡ እንዲህ ተናገረ...

‹‹ወለሉ ሳይቆጠር ደረጃው ሰባት ነው›› ሲል፡፡

ከተማይቱ በብዙ የተጨነቁ መንፈሶች የተሞላች ናት፡፡ በከተማይቱ የሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም ከሕይወትና ከፊደል የተማሩ አዛውንቶች ሳይቀሩ... ሕይወታቸው በዕንባና በሀዘን ማህበረሰብንም በማማረር የተሞላ ነው፡፡ ለከተማይቱ ነዋሪዎች ሕላዌ በጣራና በግድግዳ ላይ የተመሰረተ ሆኗል... ከዚህ ከፍ እንዳይሉ ግራና ቀኙን አይተው እንዳያስተውሉ እንዳይጠይቁ... የከተማዋ ድምፅ አልባ ሕግ አይፈቅድም፡፡ በዚ ትንሽ እድሜ ጠገብ ከተማ ውስጥ ሕይወት በንድፍነት ደረጃ የተቀመጠ ሲሆን ቀለም አልተቀባም፡፡ የትኛውም ነዋሪ የሚኳዝበትን ያለበትን አያውቀውም... እዚች ድሃ ነገር ግን ውብ ከተማ ውስጥ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች በድንገተኝነት ላይ የተመሰረቱ ናቸውና የዚች ከተማ የሕግ መፅሐፍ ‹‹ድንገትና ምናልባት›› የሚል ነው፡፡

አየ፡፡

ሰማዩን ምድሩን የፊቱን የኋላውን ሁሉንም አየ፡፡ ዓለም እንደከዚህ በፊቱ ናት፡፡ ወያላዎች ይጠራሉ... ሴቶች አጊጠዋል ... ካፌዎች ቡና መቁላት ጀምረዋል፡፡ እርሱም እንደትላንት ጠዋቱ የመጀመሪያውን ቡና ለመጠጣት ካፍቴሪያ ሊቀመጥ ነው ...ዛሬ ጠዋት ደግሞ የትላንትናው ምሽት ይወራል ስለድራፍት ስለቢራ ስለውስኪ ስለፐብ ስለክለብ መጨረሻ መሐል መጀመሪያ ደግሞ ሴት ስለ ሴት ስለ ሴት...ስለ ሴት...የአንድ ቀለም ወግ፡፡ ተራ ወሬ ሕይወት አልባ ድምፅ ...ለነገሩ ምርጥ ሀሳብ ራሱ ወረቀት ላይ ካልሰፈረ ተራ የአይን ደመና ነው፡፡ ደመናው በቀለም ረጥቦ ወረቀት ሜዳ ላይ ከዘነበ ተራና መናኛው ወሬ ትንሽ ሃሳብ መሆን ይችላል፡፡ ከወሬ ከፍ ያለ፡፡

አለም አሁንም በዓይኑ ፊት እንደትላንቱ ናት፡፡

ጠየቀ፡፡...

ትላንት የሞቱ ምን አመለጣቸው፡፡ በዛሬውና በትላንቱ እንቅስቃሴ መሃል ምን ለውጥ አለ? የዛሬው ሰው ከትላንቱ በምን ከፍ ይላል? የአምናው ጣዕም ከዘንድሮው በሚሻልበት አለም ...የዛሬ ምርጥነት ምኑ ላይ ነው፡፡ እየቀነሰ ...እየወረደና እየተዋረደ በሚገኝ ሁኔታ ውስጥ ከትላንት ወደ ዛሬ የመገኘት በረከትነት ምኑ ላይ ነው? በሕይወት ያሉት ከሞቱት ዝቅ ካሉ... በሙታን ቀናቶች ላይ ሕያዋን ቀናተኞች ከሆኑ የዛሬ ዛሬነት ምኑ ላይ ነው? እናንተ አምና... ካቻምና... የዛሬ ሃያ አመት የሞታችሁ ሆይ... ቀናቶቻችሁን መልሱልን... ቀኖቻችን ከእናንተ ይልቅ ብርሃናማ አይደሉምና፡፡

የሚያየውን ሰው ሁሉ ተፀየፈ፡፡ ...ሰው ሁሉ አንድያይነት ቀለም የተቀባ ብራና መሰለው ያውም ከባድ ቀይ የተቀባ...

አስተናጋጇ መጣች፡፡

ቡና አላት እንደወረደ፡፡...

ቡና ሲያዝ አፉ በምራቅ ልቡ እንዲህ በማይለው ሐሤት ይሞላል...

ቡና ሊጠጣ ነውና ደስተኛ ነው፡፡

*

ቅድም ስለማሰብ ያሰበው ትዝ አለው፡፡ ማሰብ... ምንድን ነው? ሰው በማሰቡ ከእንስሳት ይለያል ሲባልስ እንዴት ነው?... የሰው ልጅ ምንን ስላሰበ ነው ከእንስሳት የሚነጠለው? ወይስ እያሰበ መሆኑን (ማሰብ መቻሉን ማወቁ) ነው? ከእንስሳት ልዩ የሚያደርገው፡፡ እንስሳት ወደ ማይሆን አቅጣጫ ሲኳዙ እረኛቸው እንደሚያግዳቸው ሁሉ ማሰብ እረኛችን ትሆን? እንዲህ ከሆነ የሰው ልጅ መች እረኛውን ሰማ?... ከኔ ጀምሮ፡፡ አሁን እኔ ውስጥ እዚህ ካፍቴሪያ የተሰበሰቡ ሰዎች የሉምን?... ምክንያቱም ስለ ራሱ ሙሉ የሆነ ስለእነርሱ አይሳሳትም፡፡ PARADE

ውሸት???

ማሰብ ከእንስሳት የተለየንበት ሳይሆን ከአራዊት ይልቅ አውሬነታችን የተገለጠበት ከትንኛም በታች ቅንጣት ያከልንበት ሁኔታ ነው፡፡ ማሰብ ነውራችንን አደባባይ ያሰጣብን ከእኔነታችን ያጣላን ከእንስሳት ዝቅ ያደረገን ነገር ነው፡፡ ቡናው እስኪቀርብ እነዚህን እያሰበ ነበረ...

ቡና ቀረበለት፡፡

የመጀመሪያው ቡና፡፡ ...ቡናውን እየጠጣ... ስራውን በእጅጉ እንደያዘ ከደረሰበት ቀጠለ...

‹‹ዘሎ ገደል የገባ እንስሳ የትኛው ነው?... የሰው ልጅ ብቻ፡፡ መውደቅ አውቆ ማጥፋት አስቦ ማጥቃት... አስቦ መጥፋት የሰው ልጅ ብቸኛ መለያ ነው... የማያስብ እንስሳ ጥፋት ከሚያስብ የሰው ልጅ አጥፊነት አናሳ ከሆነ የሚያስብ የሰው ልጅ ጥፋት በማያስብ እንስሳ ካልተደረገ ከሁለቱ አናሳው ማን ነው፡፡ ...ያሰበውስ? የደመ-ነፍስ እውቀት ከነፍሳዊ እውቀት ከተሻለ ሰው ክብሩን ለእንስሳ ሊለቅ ይገባዋል፡፡ በርሱ የተደረገው ጥፋት በእሪያዎች የለምና...››

ወደ ራሱ ተመለሰ የቡናውን ስኒ አነሳ... አልቋል ስኒው ውስጥ የዕድፍ መስመር አየ ...የአቧራ መንገድ የሚመስል ብዙ አቋራጭ መንገድ መሳይ ነገር ከንፈሩ በነካበት የስኒው የውስጠኛ ክፍል ደግሞ ሰፊ የአቧራ ሜዳ ወይም የሸርተቴ መጫወቻ መሳይ... ነገር ይታያል...

ራሱን ወቀሰ ‹‹ወደማልኩበት እንዴት ተመለስኩ?›› ትላንት ዕርሜን ስጒርስ ለምን አላፈርኩኝም? ሐፍረቴን ለመግለፅ የማይራራልኝ ‹‹የሰው ልጅ ያስባል›› የሚል ማፈርያዬን እንዴት እመካበታለሁ? አለማሰብ ባይቻልም ማሰብን መመኪያ ለማድረግ የሰው ልጅ እጅግ ብዙ ይቀረዋል፡፡ ይህች ውብ ዓለም እናስባለን በሚሉ ደናቁርቶች ጠፍታለች፡፡ ረሃብ የሰው ልጆች የተንኮል ቀመር ነው፡፡ ጦርነት የሰው ልጆች ያለማሰብ ውጤት ነው በሽታ በሰው ልጆችች ተቦክቶ ይጋገራል... የዋሆች ይመገቡታል ፈጥነው ይሞታሉ፡፡ ይህ የሰው ልጅ የማሰብ ውጤት ነው ግን ይህ ዓይነት ጭካኔ በእንስሳት አልተደረገም... ስለዚህ ከሚያስበው የሰው ልጅ እንስሳቶች በለጡ፡፡... የተበለጠ ጎበዝ የሰው ልጅ ብቻ ነው፡፡ ያሸነፈ ተሸናፊ፡፡...

> ...ከአራዊት ይልቅ አውሬነታችን የተገለጠበት ከትንኛም በታች ቅንጣት ያከልንበት ሁኔታ ነው፡፡ ማሰብ ነውራችንን አደባባይ ያሰጣብን ከእኔነታችን ያጣላን ከእንስሳት ዝቅ ያደረገን ነገር ነው...

ድጋሚ ካዘዘው ቡና ለመጀመርያ ጊዜ ፉት አለ

ጥቁረቱ ደስ ይላል፡፡...

ቡና ባይኖር ዓለም ምን ትመስል ነበር? አለ በውስጡ

ራሱን ቡናን ትመስል ነበር፡፡

በቡና ጥቁረት ስር የሃሳባዊነት ብርሃን ተሸሽጓል፡፡

እዚህ ቤት ያለው የቡና ጣዕም የሚወደው ዓይነት የቡና ጣዕም ነው፡፡

ምላሱ ላይ ያለውን ቡና እያሰበ ቀና አለ የቤቱ መግቢያ ላይ በቢጫ ፕላስቲክ ላይ የተለጠፈ ጥቅስ አየ… ስለቡና ይህንን ጥቅስ እልፍ ጊዜ አንብቦታል የሚካኤል ባዛክ “When you drink a cup of coffee, an Ideas comes Marching in your brain”

የመጨረሻውን የቡና ጨመቅ ወሰደ ቡናውን ምላሱ ላይ አሽከረከረ፡፡ አሁን አንተ ምን ታስባለህ? አለ ራሱን፡፡ የቡና ጣዕምን ለመለየት ከማሰብ ምላስ በቂ ነው የቡና ጣዕምን ለማወቅ ምላስ ያስፈልጋል፡፡ ያለምላስ በማሰብ ብቻ መልካም ወይም መጥፎ ጣዕም ሊታወቅ አይችልም፡፡ ስለዚህ አሁን ማሰብ በጣዕም ላይ የምትደረግ ትኩረት ናት እንጂ ሌላ ጨዋታ አይደለችም…

ለምሳሌ…

ሰው ያስባል በማሰቡም ተዋርዷል እያልኩ እያሰብኩ ነው እንበል (አሁን) እንስሳው ደግሞ ስለ አለማሰቡ ምንም አያስብም አያውቅምም፡፡…

እኔ ስላሰብኩት ምን ይፈጠር? … ይህ ምላሽ ትንሽ ቀላል ሊመስል ይችላል ነገር ግን ‹‹እኔ ስላሰብኩ ምን ይፈጠር?... የሚለው ምላሽ የጥያቄው ምላሽ ብቻ አይመስለኝም ከጥያቄው በኋላ የመጣ አንድ የሀሳብ መስመር ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ ‹‹ሰው ያስባል ነገር ግን በማሰቡ ተዋርዷል›› እንዲህ ከሆነ ደግሞ አልታሰበም ማለት ነው(ራሱን)፡፡ …ምክንያቱም ከዛ በኋላ የታሰበው ‹‹እኔ ስላሰብኩኝ ምን ይፈጠር ስለሆነ፡፡››

ሁለት፡፡..

እንስሳው ስለ አላሰበ አይደለም ያላጠፋው፡፡

እንዳያስብ ሆኖ በሆነ (በተፈጠረ) ነገር ላይ፡፡… እሻላለሁ… ይሻላል፡፡ እበልጣለሁ ይበልጣል፡፡ ብሎ መነፃፀር አለመሻል ይመስላል፡፡ ምክንያቱም አልሻልም አልችልም አይደለሁም ማለት የማይችል እንደሆነ ከሚኖር ነገር ጋር መሆንን ሲሻ ከማይሆን ከአለመሆን ጋር የሚስማማ የሰው ልጅ ሁኔታውን ከሚኖር እንስሳ ጋር በምን ይለያል? ምክንያቱም እንስሳው የማያጠፋው ስለማያስብ ሳይሆን ሁኔታውን ስለሆነ ነው፡፡ የሚያጠፋውም እንዲያ ስለሆነ ነው፡፡

ማሰብ የመሆን ምክንያት አይደለም፡፡ መሆን ግን አብዛኛውን ጊዜ የማሰብ ሳይሆን የመፈለግ ውጤት ናት… አስበን አንፈልግም የፈለግነውን እናስባለን እንጂ፡፡ እውነት ነው የቃላት ጨዋታ ሊመስል ይችላል ግን

የምናወራው (የምፅፈው) (*የምታነበው) ስለ ማሰብ የምትታሰብ የወረቀት ወሬ ናት፡፡… ቅድም እንዳወራነው ወደ ኋላ ልተርትና የአፍ ደመና ዝናብ መሆን ባትችል እንኳ ካፍያ እናድርጋት ትንሽ ወሬ፡፡ በብራና ላይ ቅንጣት ብርሃን መሆን ስለምትችል የምናስበው በቃል ስለሆነ የቃል ጨዋታ ብሎ ነገር የለም፡፡ ቅድም ከተናገርኩት ጋር በመጠን የተቃረንኩ ይመስላል… ከዚያ ምልከታ በኋላ ይሄኛውን ከተቀበልኩስ የቃላት ወንዝ በሃሳብ እዚህ ካደረሰኝስ የቃል ጨዋታ ያልሆነ ስለሌለ ሁሉም ‹‹ንድፍ›› የቃል ውጤት ነው፡፡ መስመር ራሱ ሳይቀር….፡፡

*

ጠረጴዛ ላይ ባዶ ሲኒ… ሲኒው ዜሮ መሳይ የቡና ስኒ ማስቀመጫ ላይ የስኒ ማስቀመጫው ስኒውን ተሸክሞ ዜሮ ቅርፅ ጠረጴዛ ላይ ይታያል፡፡

አስተናጋጇ መጣች፡፡

ስኒውን ልታነሳው መስሎኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ከአጠገቤ ካለው ጠረጴዛ ላይ ያሉትን ጥንዶች ለመታዘዝ ነበር፡፡ አመጣጧ፡፡ ለካ የምትንጎራደደው ስራዋ ስለሆነ ነው፡፡ መንጎራደድ ከጠረጴዛ ጠረጴዛ እዚህ ቤት ብዙ ደስ የሚሉ ዜሮ ነገሮች ይበዛሉ… ይህንን ያልኩት የአስተናጋጇ ዳሌ ስለሚያምር ነው ምርጥ ቅንፍ አላት ()

እዚህ ቤት ስገባ ይህን ሐሳብ እፅፈዋለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር፡፡ አንዳንዴ ሐሳብ ራሱ ሳያስበኝ አይቀርም፡፡ እንደ ምርጥ ባለ ቅኔ ውብ ስንኞች፡፡ ሳይታሰቡ እንደሚፈሱ ግጥሞች፡፡ …እንደ ባለተሰጥዖ ቀልደኛ ቀልዶች፡፡ …ተፃፈ፡፡ በድንገት እኔ የዚች ፈገግታ የተለያት የተወዳጇ ኑሮ ወደ ጎን ያዘመማት ከተማ ነዋሪ ነኝ በከተማችን እንብርት ላይ የተፃፈው ሕግም ተገዢ ነኝ… የከተማዋ ቁልፍ ሕግም ‹‹ድንገትና ምናልባት›› የሚል ነው… ይህ ሕግ የህዝቡን ሕይወትና ኑሮ አማክሎ የወጣ እንደሆነ የከተማዋ ‹ጭቃ ሹሞች› ይናገራሉ… እንዲህ ሲሉ… ‹‹የሕዝቡ ሕይወት የሚመራው በምናልባት ነው… ድንገት ተነስቶ… የሚኖር ሕዝብ ስለሆነ በድንገት ለሚመራ ሕዝብ የምናልባት ስርዓት ሊጨመርበት (ለት) ይገባል… ምናልባት ለሚሆነው ነገርም… የድንገት ሕግ ያስፈልጋል… ስለዚህ እኔም የዚህ ከተማ ሕግ ተገልጋይ ነኝና እዚህ cafeteria ይህን ፅሑፍ ፃፍኩት ድንገት

*

መፍሰስ መልካም ነው፡፡ ወደ ሐሳብ ወንዞች ወደ ፍላጎት ውቅያኖስ የመሆንን ተራራ ባያቅፉትም እየዳሰሱ፡፡ …በእውነት ሽለቆ ባይኖሩም እየተሽሎከሎኩ፡፡ ወንዙ ወደ ሚያደርሰን እየታጠፍንም ቁልቁል እየተወረወርንም በፀጥተኛው ሜዳ ላይ እንደማይጓዝ ለጥ ብለን እንደ አሸዋ በልባችን… እየተሳብን … አንዳንዴም በአሸዋማ ሜዳዎች ላይ ውለታ ቢስ ለመሆን ቁልቁል እያረግን መፍሰስ እስከመድረሻችን… ለመተኛት መውደቅ ለመውደቅ ማንቀላፋት… ለሕልም …ለቅዠት ምንምንም ላለማየት ተኝቶ ለመንቃት፡፡ ወድቆ ለመነሳት መውደቅ… መውደቅ… መውደቅ…

ቅድም ሆቴሉ ውስጥ ወድቆ ሲነሳ… አንቀላፍቶ ሲነቃ ያሰበውን አሁንም አሰበ፡፡ አንድ አንድ ሐሳቦች እንዲህ ናቸው… አይለቁም…. ይኖራልሉ…ብቅ…ያላሉ…ድንገት

## መፈንቅለ መንግስት….

(ከገፅ 15 የዞረ)

ሲሆን መፈንቅለ-መንግስት የመሞከር እድሉም በዛው ልክ አነስተኛ ይሆናል፡፡ ለዚህ በምክንያትነት የሚጠቀሰው፤ መፈንቅለ-መንግስቱን ለመሞከር የሚያስቡ ልሂቃን ከራሳቸው ወታደራዊ ቡድንም ሆነ ከስርዓቱ የሚገጥማቸው ብሄርን ማዕከል ያደረገ ተግዳሮት ነው፡፡ ሚሊተሪው ብዙሃኑ የተወከሉበት መሆኑ አንዱ ምክንያት ሲሆን፤ ሌላኛው ተግዳሮት መንግስታዊ ስርዓቱ የብዙሃኑ ውክልና እንዳለው ስለሚታሰብ የተሻለ ቅቡልነት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አማፂዎቹ የሌላ ብሔር አባላትን ወደ አመፁ እስካልቀላቀሉ ድረስ ሙከራቸው አዳጋች ይሆናል፡፡ ሊንድማን “The ethnic politics of coup avoidance: evidence from Zambia and Uganda” በሚለው ስራቸው በሁለተኝነት የሚጠቅሱት ወታደሩ እና መስተዳድሩ በተመሳሳይ ብሄር አባላት ሲሞላ ስዒረ-መንግስት አዳጋች መሆኑን ነው፡፡ የዚህ ምክንያቱ ግልፅ ነው፡፡ ሁለቱንም መንግስታዊ መዋቅሮች የሚመሩት የአንድ ብሄር ተወላጆች ከሆኑ የፍላጎት ግጭት ሊፈጥሩባቸው የሚችሉባቸው ዕድሎች አነስተኛ ስለሚሆኑ አልፎም የሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ስርዓቱ ላይ ለማመፅ ተቋማዊ አቅማቸው ስርዓቱን በሚመሩት የአንድ ብሄር ልሂቃን ስለሚዳከም ለማመፅ ይቸገራሉ፡፡ የመጨረሻው የአጥኚው ትንታኔ ሁለቱም ተቋሞች በዋናነት በሁለት ግዙፍ ብሄሮች የሚመሩ ሲሆኑ ፖለቲካዊ ዓመፅን መጥራታቸው ላይ ያተኩራል፡፡ እንደ ሊንድማን መከራከሪያ፤ ማዕከላዊ መንግስቱን በተገዳዳሪ አቅም የሚመሩት የሁለቱ ብሄሮች ልሂቃን፤ የየራሳቸውን ብሄር አባላት ከወታደሩ ክፍል ለማሰባሰብ ይሞክራሉ፡፡ ይህኛው አማራጭ ሚሊተሪውን የመፎካከሪያ ሜዳ ስለሚያደገው የመፈንቅለ-መንግስትን አማራጭ የማይቀር ያደርገዋል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ካላቸው የእርስ በእርስ አለመተማመን አንፃር ቢያንስ ሊሞከር የታሰበን ዓመፅ ለማክሸፍ በሚል ዓመፅ ሊቀሰቅስ እንደሚችል ሊንድማን ይናገራሉ፡፡ ሌላኛው ፀሐፊ ዴቪድ ሳልድስ ዎርዝ በበኩላቸው ማዕከላዊ መንግሥቱ የብዙ ብሄሮች ውክልና ቢኖረውም ሚሊተሪው በሁለት ብሄሮች ተመጣጣኝ ውክልና የተዋቀረ ከሆነ ወታደራዊ ዓመፅ የመከሰት ዕድሉ ይበዛል፡፡ ዴቪድ “Civilian control of the military in black Africa” በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚናገሩት የአንዱ ብሄር ልሂቃን ከሌላ አቻቸው የተለዩ ጥቅሞችን እና የበላይነትን መፈለጋቸው፤ አንዳቸው ዓመፁን ቀድመው እንዲሞክሩት ያስገድዳል፡፡ ፀሐፊው የሚያነሱት ሌላው ነጥብ ቀድሞ ከፍተኛውን የፖለቲካ ስልጣን ይዘው የነበሩ የአንድ ብሄር ተወላጆች ከዚህ የስልጣን ክበብ ሲገፉ፤ ወታደሩ ውስጥ ወዳሉት የብሄር መሰሎቻቸው ወደ መመልከት ያዘነብላሉ፡፡ በዚህ መልኩም ስልጣንን በሃይል በመንጠቅ ወደ ነበራቸው የመሪነት ቦታ ለመመለስ ይሞክራሉ፡፡

እነዚህን ከላይ የቀረቡ የጉዳዩን መተንተኛ ማዕቀፎች አሁን ባለው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ አውድ ለመመልከት ብንሞክር የሚሰጡን ጥቂት ዕይታዎች ይኖራሉ፡፡ በ1985 ዓ.ም. የታተመ አንድ የኢህአዴግ ድርሳን ‹‹የኢትዮጵያ ሰራዊት ከምዕራባውያን ቁጣ ለመዳን ገለልተኛ እንዲመስል ቢደረግም፤ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስፈፃሚ መሆኑ ግን የግድ ነው›› ቢልም፤ በእነ ኮሊየር ሙግት መሰረት ብረታዊ ትግልን የሚያስነሱ ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቅሬታዎች ስዒረ-መንግስትንም ለመቀስቀስ በቂ ናቸው፡፡ ከኦብነግ እስከ ኦነግ፤ ከአርበኞች ግንባር እስከ ጋምቤላ ነፃ አውጪ ያሉ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ብረት ካነሱ ሰንብተዋል፡፡ እነዚህ በአሸባሪነት የሚከሰሱ ሃይሎች እንደቆሙበት አውድ የድጋፍ መሰረት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ እነዚህን ሃይሎች ያነሳሱ ቅሬታዎች፤ ከየቡድኖቹ የብሄር ገፅታ አንፃር ወታደራዊው ክፍል ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚዘለል አይሆንም፡፡ በተለየ ሁኔታም ባለፉት አስርት ዓመታት የአማርኛ እና የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ከፍተኛ ወታደራዊ ሹማምንቶች ስርዓቱን እየከዱ ወደነዚህ ሃይሎች መቀላቀላቸው ስቴፈን ሊንድማን እንደሚሉት መፈንቅለ-መንግስት ያልተሞከረበት ምክንያት በሚሊተሪው ውስጥ ያሉት የትግሪኛ ቋንቋ ተናጋሪ አባላት ጥቅመኝነታቸውን ለመሰዋት ፍቃደኛ አለመሆናቸው ይመስላል፡፡ ሟቹ አቶ መለስም ለመጨረሻ ጊዜ ቃለ-መጠይቅ ሳደረገላቸው ሪቻርድ ዳውደን ሚሊተሪው የአንድ ብሄር አባላት የብቻ የበላይነት እንደሚታይበት ተናግረዋል፡፡ እነዚህ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከአንድ የተወሰነ ማህበራዊ ቡድን መምጣታቸው፣ በሃሜት ኮሪደሮች እንደሚነገረው በተለያዩ ቀጥተኛ ባልሆኑ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ከስርዓቱ ጋር መተሳሰራቸው አልፎም እንደ እነ ዶ/ር መረራ ጉዲና ያሉ አጥኚዎች ‹‹የአንድ ብሄር መንግስት›› /ethniocratic state/ ሲሉ መንግስታዊ መዋቅሩን የመጠራታቸው ተሳስሮሺያዊ ሁነት፤ ለወታደራዊ ልሂቃኑ ዓመፅን ማሰብ አትራፊነቱ እንዳይታይ አድርጎታል፡፡

የቀደሙ ጊዜያቶች በዚህ መንገድ ቢያልፉም ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን እንዳነሱት የብሄር ፖለቲካ በከረረበት የኢትዮጵያ ሁኔታ፤ ወታደራዊ ክፍሉን በበላይነት የያዙት ቡድኖች ከነርሱ ከተለየ ብሄር የሚመጣን መሪ መቀበል አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ የህወሓት መሪዎችም በአዲሱ የኃይለማርያም ደሳለኝ አስተዳደር ውስጥ ‹‹እያጣነው ነው›› የሚሉትን ፖለቲካዊ ስልጣን ለማግኘት ስዒረ-መንግስት የመጨረሻ ምርጫቸው ሊሆን ይችላል፡፡

## የአፃፃፍ....

(ከገፅ 15 የዞረ)

በቅጥያ ነው። የካህሮስቲ አፃፃፍ እጅግ ጥንታዊና ከኢትዮጵያው ፊደል የቀደመ በመሆኑ የኢትዮጵያው አጻጻፍ በህንድ ፊደል ተፅእኖ የተገኘ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

የኢትዮጵያን አፃፃፍ ከሌሎች የሴም የአፃፃፍ ስልቶች ሁሉ የሚለየው ሌላው ባህርይ ከግራ ወደቀኝ መፃፉ ነው። በአብዛኛው በኢትዮጵያ ፊደል የመፃፍ ስልት ደንብ በመጀመሪያ በዚህ ፊደል ይፃፍ ከነበረው ከግዕዝ ቋንቋ የተወረሰ ነው።

በደምሳሳው ስለ ኢትዮጵያ ፊደል ይህን ያህል ብለን ወደ መሰረታዊ ነጥባችን እንመለስ። የአማርኛን የአፃፃፍ ስርዓት ስለማሻሻል። ይህ ጉዳይ (የአማርኛን አፃፃፍ ማሻሻል) አዲስ የውይይት ነጥብ አይደለም። ለረዥም ጊዜ ብልጭ ድርግም እያለ የመስኩን ባለሙያዎች ለውይይት አንዳንዴም ለንትርክ ጋብዟል። ፕ/ር ባዬ ይማም በቅርብ ጊዜ በዚህ ላይ የሰራው ስራ አለ። ታላቁ ደራሲ ሀዲስ አለማየሁም "በፍቅር እስከመቃብር" የረዥም ልቦለዶች ውስጥ ከሞክሼ ፊደላት መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ በወጥነት ተጠቅመዋል። ከዚህም ባሻገር ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የተለያየ ትርጉም የሚሰጡትን እንደ ዋና፣ ገና የመሳሰሉትን ለመለየት ረዥም አናባቢ በያዘው ፊደል አናት ላይ የነቁጥ ምልክት በማስቀመጥ ለችግሩ መፍትሄ ጠቁመዋል። ሌሎችም በጣት የሚቆጠሩ ደራሲያንንና ምሁራን የአማርኛ ቋንቋ የኢትዮጵያ ፊደላትን ተጠቅሞ በሚፅፍበት ጊዜ የሚታየውን የሞክሼ ፊደላትና የሚጠብቁና የማይጠብቁ ፊደላት ችግር ባጋጠማቸው አጋጣሚ ሁሉ ሲያነሱ ቆይተዋል፤ እና ጉዳዩ አዲስ አይደለም።

የአማርኛን የሞክሼ ፊደላት ችግር አስመልክቶ ለሚሰነዘሩ አስተያየቶች በተቃርኖ የሚቀርቡ ሀሳቦችም በርካታ ናቸው። እነዚህ አስተያየቶች በአብዛኛው የችግሩን ምንጭ ሳይሆን ብሔራዊ ማንነትንና ስር-ሰደድ ታሪክን እማኝ እየጠቀሱ የሚሟገቱ ናቸው። በርግጥ የኢትዮጵያን ፊደል ከግዕዝ ቀጥሎ የተጠቀመው አማርኛ ነው። ከአማርኛ ብሔራዊ ቋንቋነት ጋር ተያይዞም ፊደሉን አንዱ የማንነታችን መገለጫ አድርገን እንወስደዋለን። ግፋ ሲልም የምንኮራበት ብዙዎች ነን። ለዚህ ነው "ጽህፈቱ ይሻሻል፣ ሞክሼ ፊደላት መላ ይበጅላቸው" የሚለው ሀሳብ ከዚህ ብሔራዊ ማንነት ላይ ትንሽ ጉድፍ እንደማንሳትና የአፃፃፍ ስርዓቱን የበለጠ የሚያኮራ ለማድረግ የቀረበ እንጂ፣ ከጥላቻና አፃፃፉን ለማጉደል ተደርጎ መታሰብ አይገባውም።

የአንድን ቋንቋ የአፃፃፍ ስርዓት ለማሻሻል የሚነደፉ ፕሮጀክቶች ሁለት ደረጃዎች አሏቸው። የመጀመሪያው የአፃፃፍ ስርዓቱ ችግር አለበት ወይ? የሚለው ነጥብ ነው። አጻጻፉ ችግር ከሌለበት ፕሮጀክቱ እዚሁ ላይ ይጨነግፋል። ችግር እንዳለበት ስምምነት ላይ ከተደረሰ ደግሞ የፕሮጀክቱ ሁለተኛው ደረጃ ይቀጥላል። ችግሩ ይስተካከል ወይስ እንዳለ ይቀጥል? የሚለው ነው።

ይህ ጥያቄ የሚያሳየው የአፃፃፍ ስርዓቶች ችግር ቢኖርባቸውም ሳይሻሻሉ እስከ ችግራቸው ሊዘልቁ እንደሚችሉ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ የላቲንን ፊደል ይጠቀማል። በእንግሊዘኛ አፃፃፍ እንደሚናገሩት የማይፃፉ ቃላት በርካታ ናቸው፤ እንደ ‹‹Knowledge, knife, write›› ያሉትን ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ታዲያ ይህ ሁኔታ በእንግሊዝ ቋንቋ ምሁራንና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ወገኖች ችግርነቱ ሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል። "ይሻሻል ወይስ አይሻሻል?" የሚለውን በተመለከተ ግን፣ ችግሩን ለማሻሻል መሞከር ከችግሩ የበለጠ ችግር ፈጣሪ ሆኖ ስለተገኘ እንዳለ መቀጠሉ ተመርጧል።

የአማርኛም ሁኔታ ከዚህ ያፈነገጠ መሆን የለበትም። በመጀመሪያ በጉዳዩ ላይ የሚሰሩ አካላትና ምሁራን ችግር መኖር ያለመኖሩ ላይ መግባባት ይጠበቅባቸዋል። አብዛኛውን ጊዜ በጉዳዩ ላይ የሚነሱ ውይይቶችና ክርክሮች በቀጥታ ዘለው ሁለተኛው ደረጃ ላይ (ይቀነስ አለ፣ ይለወጥ አለ) የሚለው ላይ የሚሄዱ ናቸው።

ለመሆኑ የአማርኛ አፃፃፍ ችግር አለበት? ካለበትስ ችግሩ ምንድ ነው? በተደጋጋሚ እንደሚነሳው የአማርኛ አፃፃፍ ችግር አለበት፤ ችግሩ ደግሞ የሞክሼ ፊደላት መኖርና ጠብቀውና ላልተው የሚነበቡ ድምጾችን አለመለየቱ ነው። እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው አፃፃፉ ከጽህፈት ስርዓት መመዘኛዎች አንፃር ችግሩ አለበት ተባለ እንጂ፣ በዚህ ችግር የተነሳ የአማርኛ ጽህፈት መልእክት ማስተላለፍ ተሳነው አለመባሉን ነው።

የአማርኛ አፃፃፍ በሚጠቀምበት የፊደል ገበታ ላይ አንድ ድምጽ ከአንድ በላይ ምልክት ተሰጥቶታል። እነዚህ ከአንድ በላይ ምልክት የተሰጣቸው ድምጾች ሀ፣ ጸ፣ አ እና ሰ ናቸው። በዚህም የተነሳ አማርኛ መደበኛ የሆነ የአፃፃፍ ስርዓት እንዳይኖረው ሆኗል። አንዱ በሰበሰ ሲል ሌላው በሠበሠ ብሎ ይጽፋል። ውሃ፣ ውሀ፣ ውኃ፣ ውሐ የሚሉት የአንድ ንግግራዊ ቃል ወካይ አራት የአፃፃፍ መንገዶች ናቸው። ብዙዎች ለዚህ ሀሳብ የሚያቀርቡት መቃወሚያ አይ አይሆንም፤ ይህኛው አፃፃፍ አልተለመደም፤ ወይም በግዕዝ ቋንቋ እንዲህ አይፃፍም፤ የሚል ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ግዕዝና አማርኛ ሁለት ቋንቋዎች ናቸው። በየትኛውም መንገድ ግዕዝን እያሰብን አማርኛን መፃፍና ማንበብ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። "አልተለመደም" የሚለውን በተመለከተ ግን ብዙ ትክክለኛ አማራጮች አስቀምጦ "የተለመደውን ብቻ ምረጥ" ከማለት ለምንድነው አንዱን መርጠን የማናስቀምጠው? እውቃለሁ "ውሐ" ብሎ መፃፍ አልተለመደም፤ ግን ትክክል ነው። ሁለቱ ፊደላት ተገጣጥመው ሲነበቡ "ውኃ" የሚለው ቅንብር የሚሰጠውን ትርጉም ይሰጣሉ። ጽህፈት የድምፅ ውክልና እስከሆነ ድረስ አራቱም አፃፃፎች ትክክል ናቸው።

የሞክሼ ሆሄያት ችግር የተከሰተው የአማርኛ ቋንቋ የግዕዙን የፊደል ገበታ እንዳለ በመውሰዱ የተነሳ ነው። በአማርኛው የፊደል ገበታ ላይ ሞክሼ ሆነው የተከሰቱት ፊደላት በግዕዝ ቋንቋ የተለያዩ ድምፆች ወካይ እንደነበሩ ለማሳየት ማስረጃ ማቅረብ አይገድም። ለምሳሌ በግዕዝ ቋንቋ፡-

መሀረ "አስተማረ"

ሰረቀ "ሳይሰጠው ወሰደ"

መሐረ "ምህረት አደረገ "

ሠረቀ "ፀሐይ ወጣ"

የሚሉትን የተለያየ ፍቺዎች ይሰጣሉ። በመሆኑም በግዕዝ "ሀ" እና "ሐ" በአማርኛ "ወለደ" እና "ወሰደ" ውስጥ የትርጉም ለውጥ እንደሚያመጡት "ለ" እና "ሰ" ይቆጠራሉ።

አማርኛ የግዕዝን የፊደል ገበታ ሲወስድ እነዚህን የማያስፈልጉትን ፊደላት መተው ነበረበት። ምክንያቱም አንድ ቋንቋ ጽህፈት ሲያበጅ መሰረት ካደረገው የፊደል ገበታ ውስጥ ቋንቋው ላሉት ድምፆች ወካይ የሆኑትን ወስዶ ትርፎቹን/ ቋንቋው የሌሉት" ድምጾች የሚወክሉትን/ መተው አለበት። በአንፃሩ ደግሞ መሰረት ባደረገው የፊደል ገበታ ውስጥ የማይወከሉ ድምፆች ካሉት አዲስ ፊደል መፍጠር ይጠበቅበታል። ለምሳሌ የኦሮምኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ፊደል ይፃፍ በነበረበት ዘመን አንድ ፊደል ጨምሯል፤ ከአንገትዋ በላይ በላይ ባለው ክብ ውስጥ ሰረዝ ያላት ‹‹ጰ››።

የመጥበቅና የመላላት ጉዳይ ደግሞ ከሞክሼ ፊደላት በተቃራኒው ሂደት የተፈጠረ ነው። የሞክሼ ፊደላት ችግር ለአንድ የንግግር ድምጽ ከአንድ በላይ ምልክት በመስጠቱ የተፈጠረ ሲሆን፣ የመጥበቅና የመላላት አፃፃፍ ችግር ደግሞ አንድ ፊደል ሁለት የድምፅ ቅንብሮችን በመወከሉ የመጣ ነው። ለምሳሌ ዋና "አብይ" እና ዋና "መዋኘት" የሚሉት አፃፃፎች ውስጥ "ና" የተባለ ፊደል በመጀመሪያው ውስጥ /ውአአ/ ን ሲወክል፣ በሁለተኛው ውስጥ /ውአ/ ይወክላል። ስለዚህ ችግሩ ሁለቱ የድምጽ ቅንብሮች በተመሳሳይ ፊደል መወከላቸው ነው። ለዚህ ብዙዎች የሚያቀርቡት መከራከሪያ፣ "በአረፍተ ነገር ውስጥ ስንጠቀምበት የትኛውን ፍቺ ማለት እንደሆነ ግልፅ ይሆናል" የሚል ነው። እርግጥ ነው በአገባቡ ግልፅ ይሆናል። ግን በቁሙ፣ የትኛውም አውድ ውስጥ ሳይገባ የትኛውን ፍች ለማለት እንደተፈለገ ግልጽ ቢደረግ የበለጠ ጥሩ አይሆንም? ይህ አጠቃቀሙን አያቀለውም? ለዚህ እኮ ነው ሀዲስ አለማየሁ ጠብቆ መነበብ በሚገባው ላይ ነቁጥ ያስቀመጡት። አንድ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ "በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገር ስሩ/ሪ" ተብሎ ገና እና ዋና የሚሉት ቃላት ቢገኙ ተማሪው በሚጠብቀው ነው ወይስ በሚላላው ፍቺ የሚሰራው? እና ይህ ችግር አይደለም?

እንግዲህ "የአማርኛ ቋንቋ አፃፃፍ ችግር አለበት" ሲባል፣ በዋናነት እነዚህን ሁለቱን ጉዳዮች ማለት ነው። እናም የሚያስከትለው ጉዳትና የሚያመጣው ጥቅም በጥናት ታይቶ ጥቅሙ የሚያመዝን ከሆነ ችግሩ ቢወገድ ምን ክፋት አለበት?

ወደር የለሽ ጥንታዊ ስልጣኔያችን በእጃችን ያለ ዛሬያችንን አኮስሶነ አስተሳሰባችንን ያለ ልክ ተጭኖታል። ማንነታችንን የምንገልጸው በሱ ነው፤ የምንኮራው በሱ ነው። ይህ ባልከፋ፤ ክፋቱ ጉድፉን ልንነቅስለት አለመድፈራችን ነው። ጉድፉን ነቅሰን ለመታደግ ይቅርና ስለ ጉድፉ ማውራት የሚያስቀስፍ ይመስለናል።

## ደንታቢስነታችን....

(ከገፅ 15 የዞረ)

እንቅስቃሴዎችን እንደማይኮንኑ እያወቁ ባለመጠቀማቸው ብቻ ስርዓቱን ዴሞክራሲያዊ /የመድብለ-ፓርቲ/ በማስመሰል ላበረከቱት አስተዋጽኦ ኃላፊነታቸውን ከሁሉ አደገኛ ያደርገዋል። አመራሮቻቸው በማይገባ ምክንያት ሲታሰሩ በአደባባይ ወጥቶ እስከመጮህ የሚደርስ ህጋዊ ፈቃድ የተቸራቸው ቢሆንም አጥጋቢ ያልሆኑ ሰበቦችን በመደርደር ለሚያሳዩት ቸልተኝነት ግን የሞራል ተጠያቂነቱን ሸክም በግላቸው ይወስዱታል። በህይወት ስለመኖራቸው ማሳያ የሚሆነው ከዚህ ድንዛዜ በመንቃት የእውቀትና የጥበብ መስመሮችን ለመከተል ሲሞክሩ ብቻ ነው።

መልካም ስማችንንና ታሪካችንን ከግድፈት ለመታደግ ከግል ምልከታችን ፈቅ ማለት ጊዜው ያስቀመጠልን ዕዳ ነው። አንድን ህፃን በውሃ ከመስጠም ለማዳን እጃችንን መዘርጋት ብቻ በቂ እኮ ነው። ምነው ከህፃኑ ነፍስ ይልቅ ለልብሳችን መጨቅየት አሰብን?

በቪየትናም ጦርነት ወቅት የተከሰተው የማይ ላይ ጭፍጨፋ የወቅቱ ተጠቃሽ ክስተት ነው። በዘመኑ የአሜሪካን ወታደሮች መረን ባጣ ቅጣት ሴትና ህፃናትን ሳይለዩ ይረሽኑ ነበር። ኸግ ቶምሰን የተባለ አሜሪካዊ የሄሊኮፕተር አብራሪ ግዳጅ ተሰጥቶት ቅኝት ላይ እያለ አሰቃቂውን ኩነት ተመለከተ። ወዲያውም በገዳይ ጓዶቹና በተገዳይ ንፁሃን መካከል ሄሊኮፕተሯን አሳርፎ መሀል ሜዳው ላይ በመቆም ‹‹ወይ እኔ ላይ ተኩሱ ወይንም እነሱ ላይ መተኮስ አቁሙ›› በማለት እጆቹን ወደ ላይ ዘረጋ። ከመቅስፈት ግድያው ቆመ። ቶምሰን አደጋው የማይደርስበት ቢሆንም ሌሎችን ለመታደግ ሲል በራሱ ህይወት ቆመረ። ለሀገሩና ለዜጎቹ ደህንነት ቢያስብም ሰብአዊነት ግን ወደ ንፁሀን አደላ። የእርሱ አይነት ጥቂቶች በጦሩ ውስጥ ቢኖሩ ኖሮ የቪየትናም ጦርነት ለታላቋ አሜሪካ በደም የተፃፈ ታሪክ ግድፈት ባልሆነ ነበር። የማይ ላይ ታሪክ የትም ሊፈጠር ይችላል። መልኩ ይቀየር እንጂ እኛም ጋር በእለት ተዕለት ኑሮአችን የምናስተውለው ነው። ታዲያ ይህን መሰሉን ክስተት እየተመለከትን ምላሻችን ምንድን ሆነ? አስቀድሞ ስለመብቶቻቸው የጠየቁ ዜጎችን በግድያ፣ በእስርና በስደት ከአደባባዩ የሚያርቅ የዚህ አይነቱ ሥርዓት በመጨረሻም የአፈና እጆቹ ስለሌሎች መከራ ደንታቢስ ወደነበሩት ያዞራል።

## ወልደጊዮርጊስ....

(ከገፅ 15 የዞረ)

ከሶስት በላይ፤ ወልደጊዮርጊስ እንደሆኑት፤ ከጣሊያን ወረራ በፊት አንድ - ጠላት መጣብህ አሳድደህ ያዘው እንላለን፤ ጣሊያን ሰተት ብሎ ገብቶ ዙፋኑን ሲቆጣጠረው - ማንም የለ እንዳንተ እንላለን፤ ተሸንፎ ወዳገሩ ሲገባ- ድሮስ አለአቅሙ ተንጠራርቶ፤ መስሎታል በቀላሉ የምንሸነፍ እንላለን።

እኛወልደጊዮርጊስወልደዮሐንሶች፤ በጥቂት አመታት ውስጥ ሶስት መልክ ይዘን ብንንቀሳቀስም፤ ነገር በሆድ የማሳደርና ቂም የመቋጠር ልምድ ያካበተው ሃበሻ በቅኔና በአግቦ መውጪያ መግቢያ ቢያሳጣንም፤ ‹ንጉሱ እስካሉ ድረስ ችግር የለውም› የምንል ነው የምንመስለው፤ የመጣ ሁሉ ይነዳናል፤ የመጣ ሁሉ ይጋልበናል፤ የተሾመ ሁሉ ወደ ፈለገው አቅጣጫ ይወስደናል፤ ‹እሺ› ብለን መታዘዝ ብቻ አይበቃንም፤ ሌሎች እንዲታዘዙ በኪነጥበብ ተሰጥኦዋችን የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ኃላፊነታችንን እንወጣለን - በየባህርያችሁ ተሰለፉ፤ የሰልፋችሁን ፊታውራሪ ምረጡ ብንባልም እንደ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ ያሉትን ነው የምናስቀድመው!

ሐ) ሰለሞን ተካልኞች

ካፎቱ ይውጣ ጕራዴ ሣንጃው
ደም በደም ይሁን መረማመጃው
እሪ በል መርኬ እሪ በል ፒያሣ
ይጭስ ይጫጫስ አንጄ ተነሣ...

...ታውቁታላችሁ፤ ኢሕአዴግ ከመግባቱ በፊትና ከገባ በኋላ፤ የኢህአዴግን ስርዓት በማጥላላት፤ አገዛዙን በመቃወም፤ ባልተለመደ ሁኔታ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ግጥሞችን በማዜም፤ የተቃዋሚዎች ድምፅ የሆነ ሰው ነበር - ነበር - ሰለሞን ተካልኝ።

በቅርቡ፤ ለረዥም አመታት ከቆየበት አሜሪካን ሀገር ተለይቶ፤ የኢትዮጵያን ምድር ለመርገጥ ሲገባ፤ ከመምጣቱ ጋር አንድ ዜና ተያይዞ ተሰማ፤ ሹክሹክታው ቀጠለ፤ ኢህአዴግን የረገመበት አንደበት መልሶ ለማመስገን ተጠቀመበት፤ ይህንን ‹ሹክሹክታ› ይዞ፤ ቴዎድሮስ ተክለአረጋይ፤ ሰለሞን ተካልኝን ‹ለቁም ነገር መጽሔት - ሐምሌ 99 ዓ.ም› ዕትም ጋበዘው። እንዲህም አለ...

‹...ባለፈው 10 ዓመት ያመንኩበትን ሰርቻለሁ። አልፏል። ያ ያመንኩበትን ነገር ግን አሁን ተቀምጬ ሳስበው ጥፋት እንደነበር አምኜበታለሁ። በፍርድ ቤት የተከፈተብኝ ክስ ሲነሳልኝ ሕዝብንና መንግስትን ለማራራቅ ሳይሆን ለማቀራረብ ነው የምዘፍነው...

‹... የኢትዮጵያን መንግስት ሳልነቅፍ፣ ሕዝቡ ለተቃውሞ ቢወጣም ሳልደግፍ፣ ሕዝብንና መንግስትን የሚያስታርቁ ሰላማዊ የሆኑ (ስለፍቅርና ስለሰላም የሚሰብኩ ዘፈኖች) የምዘፍን አርቲስት ነኝ...›

ሰለሞን፤ ያኔ የተጫወታቸውን ዘፈኖች የሚያፍርባቸው ይመስላል- ቃለ ምልልሱን ሳነበበ፡፡ የእብደት መን ነው የሚለው፤ ሲቃወም መቆየቱ ልክ እንዳልነበር ለመናገር በብዙ ይደክማል፤ አለቦታዬ ነበርኩ፤ አሁን ግን ተመልሻለሁ ባይ ነው፤ በትላንት ማንነቱ አፍሯል፤ ፀፀቱ ሊያባራለት የቻለ አይመስልም፤ ኢሕአዴግን እንደ ንስሃ አባቱ ቆጥሮ፤ ስምህን አጥፍቻለሁና ይቅርበለኝ ለማለት ከወደቀበት ቦታ ጉልበቱ እንጂ ልቡ የተነሳ አይመስልም፤ ልቡ አሁንም እዚያው መንግስት እግር ስር ነው - ብትረግጡኝም ይገባኛል ብሎ፤ ‹አይደለም እናንተን ለመቃወምና ለማዋረድ ቀርቶ ለማመስገንስ ክብሬና ሞራሌ ይፈቅድልኛል ወይ?› የሚል መስሎ።

ሰለሞን፤ ከመንግስት ተጣልቶ፤ ከባዕዳን ጋር ተጠግቶ፤ በቆየባቸው ዓመታት ውስጥ፤ ብዙ ነገር በህይወቱ እንደጐደለበት ሆኖ ይሰማዋል፤ በእናቱ ቀብር ላይ አልተገኘም፤ አባቱንም ያገኛቸው በእርጅና ምክንያት አንድ ዓይኗቸውን አጥተው ነው - ይህ ሁሉ የሆነው፤ ‹ውጣ! ተቃወም! ድንጋይ ወርውር! ጠመንጃ አንሣ› በማለቱ ነው ይላል-

...እንዲህ ነን - ሰለሞን ተካልኞች፤ ፊት ለፊት ስንቃወም እንቆይና፤ ይሄ መንግስት በዘር ከፋፈለን፤ ባንዲራችንን ጨርቅ አለብን፤ ገነጠለን፤ አስገነጠለን ስንል እንቆይና፤ ለትምህርት ስርዓት መውደቅ ተጠያቂው እሱ ነው፤ ለስግብግብ ነጋዴዎች አሳልፎ የሰጠን እሱ ነው፤ ፍትሐዊ ላልሆነ የሀብት ክፍፍል ተጠያቂው እሱ ነው ስንል እንቆይና፤ ይህንን በማለታችን በሀገራችን መንግስት በጥብቅ እንደምንፈለግ ይሰማንና፤ ሕዝቡ በራሱ ፍቃድ የብሔራዊ ጀግንነት ሜዳሊያ እንዳጠለቀልን ሆኖ ይሰማንና፤ ተሰድደን፤ ከተቃዋሚዎች ጐራ ተሰልፈን፤ የሰልፋቸው አስተባባሪና መፈክር ያዥ ሆነን፤ በድምጻችን በዘፈናችንና እልሃችን ብዛት ኢህአዴግ የሚወድቅ ይመስለንና... እያየነው ስንሄድ የመሰለን ሳይሳካ ሲቀር፤ አካሄድና አገባቡ በቅጡ አልዋሃደን ሲል፤ ድሮም አለቦታዬ፤ አለ ጀግንነቴ አለ ፖለቲከኝነቴ ነበር የተገኘሁበት ብለን ፊታችንን እናዞራለን - ወደነቀፍነው ቤተ መንግስት።

‹ማረኝ ብዬሃለሁ እሞትብሃለሁ - › እንለዋለን መንግስትን፤ ‹ወሬኛም ያውራ ሆሜት ይደርደር/ እኛስ ሆነናል ፍቅር በፍቅር› እንለዋለን ኢህአዴግን።

ወደዚህ አቋም የምንመለሰው፤ እንደኔ እንደኔ፤ መስለን ለማደር ነው ብዬ አምኜ ለመቀበል እቸገራለሁ፤ ብዙዎቻችን ድጋፋችንም ተቃውሞአችንም መሰረቱን አሸዋ ላይ እንዳሳረፈ ቤት ነው፤ ፅኑ ማረፊያ ያለው ፖለቲካዊ አቋም የለንም፤ ስለምንቃወመው ርዕዮተ ዓለም በቂ ዕውቀት የለንም፤ ያለን ስሜት ነው፤ ስሜታችን ደግሞ ዙሪያችን ካለው መንፈስ ላለመለየት ይሆናል፤ ዙሪያችን ካለው ሰው ሙቀት ተጋብቶብን፤ ተነጥለን ብንወጣ፤ በመለየት እና በብቸኝነት ብርድ የምንቀጣ ይመስለናል፤ አብረውን ካሉ ሰዎች በተሻለ መንገድ ያፈራነው ‹ስም› ካለ ደግሞ፤ እኛ ነን ፊት ለፊት መንገድ መሪ፤ የተቃዋሚ ሰልፈኞች አስተባባሪ፤ ከርቀት ለሚያዩን በሀገር ፍቅር ልባችን የነደደ፤ በኢህአዴግ አመራር ቆሽታችን ያረረ መስለን እንታያለን፤ ውስጣችን ሲከፈት ግን በውስጣችን የሚመላለሰው ሀሳብ ሌላ ነው - እስከመቼ ድረስ ነው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድምፅ ማጉያ የምሆነው? እስከመቼ ድረስ ነው በተቃዋሚነት ተፈርጄ ሀገሬ ሳልገባ፤ እናቴን ለመቀበር ሳልታደል፤ ሽማግሌ አባቴን ለማየት ሳልበቃ፤ የናፈቀኝን ሽሮ ሳልበላ፤ እንደ ልቤ ሀገሬን ሳልዞራት ባክኜ የምቀረው? የሚል ጥያቄ ሽው ይልብናል-

ብዙዎቻችን - ሰለሞን ተካልኞች - ግን የአወጣጣችን ያህል አመጣጣችን ስለሚያስደነግጥ ነው ሕዝቡ ግር እና ቅር የሚሰኘው፤ ሁለት አፍ የሚለን፤ በሁለት ቢላዋ በሉ የሚለን፤ አስብተው ሊያርዱን እና ሊያሳርዱን ነው ከተሰደዱበት ቀዬ ከተሸሸጉበት ጥግ ብቅ ያሉት የሚለን፤ አፋችን አለቅጥ ስለሚለፈልፍ ነው፤ ከልክ ስለምናልፍ፤ መንግስት ፊት ቀርበን ከበሮ እሆንልሃለሁ፤ ባሻህ ሰዓት እንደልብህ ብትደበድበኝ አለቅጥ እጮህልሃለሁ፤ ያኔ ጩኸቴን የሰሙ ሰዎች ሲሰበሰቡ ፕሮፓጋንዳህን ትነዛለህ ስለምንል ነው። አንዳንዶቻችን እንዲህ ነን፤ አንዳንዶቻችን ደግሞ ወደፊት እንደምናነሳቸው ቴዲ አፍሮ እና ተመስገን ገብሬ...

## ተባብረው....

(ከገፅ 23 የዞረ)

ሥርዓት አገዛዝ እድሜ ማራዘሚያ ፍቱን እንክብል እንዲሆን ገገርዎች ሳያሰልሱ ይሰራሉ። በተለይም ወጣቱን ትውልድ ከኢትዮጵያዊ የሞራል ውርስ ለማራቅና ብሔራዊ ስሜቱን ጨርሶ ለማጥፋት በዘረጉት መርሐ-ግብር አኳያ ሥነ-ልቦናውን በቅጥፈት ጋጋታ ይፈታትኑታል። በዚህ ሒደት ከተራ የመግባቢያ ቃላት አንስቶ ክቡር ዕንስ ሀሳቦችን በስፋት ያመቁ አባባሎችን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ገበያ ላይ አውለዋል።

ጀግንነት እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ከጦር ሜዳ ጀብዱ ጋር ይቆራኛል። አጼ ቴዎድሮስ፤ ደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማዕት፤ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፤ ልጅ ኃይለማርያም ማሞና ፊታውራሪ ሺመልስ ሀብቴ ከቀደምት የኢትዮጵያ ጀግኖች በጥቂቱ ይጠቀሳሉ። ጀግና መርህ ታጥቋል! ጀግና ርዕዮተ ዓለም አለው! ጀግና ዓላማ አንግቧል! ጀግና በጦር ሜዳ ቆስሎ እንኳን ከሰራዊቱ ለመለየት ፈቃደኛ አይሆንም! ወጣት የነብር ጣት! መሠሪን ከጀግና ለይ! ተነሣ ተራመድ!

ሸዋረገድ ገድሌ ለኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ትግሉ የጠየቀውን አስተዋፅኦ ሁሉ አድርጋለች። ይህች ጀግና ሀገር ወዳድ ሴት የገዛ ርስቷን በመሸጥ መትረየስና በርካታ ጠብመንጃዎችን ገዝታ ለአርበኞች አድላለች። እንዲሁም በግል ገንዘቧ ልብሶችንና መድኃኒቶችን አቅርባለች። በተመሳሳይ መልኩ የገዛ ቀሚሷንና ኩታዋን በመቅደድ ለቁስለኛ አርበኞች የቁስል ማሰሪያ ማድረጓ ተመልክቷል።

ሸዋረገድ ገድሌ ውስጥ ውስጡን ከፍተኛ የመሳሪያ አቅርቦት እንደምትፈፅም የባንዳ መረጃ ለወራሪው ኃይል ሳይውል ሳያድር ደርሶታል። ወራሪው ኃይል ይህ መረጃ እንደ ደረሰው በቀጥታ ይዟት ወደ ሜዲትራኒያን ባሕር ጠረዛት። ጀግናዋ ሸዋረገድ ገድሌ በሜዴትራኒያን ውስጥ በሚገኝ ደሴት ለሁለት ዓመታት በእሥራት ማቃ ተፈታች። ሸዋረገድ ገድሌ አሁንም አላረፈችም። ሕዝቡን ለጦርነት የሚያነሳሱ በርካታ ግጥሞችን እያደራጀች ትበትን ገባች። ስለሀገር ፍቅር በተከታታይ አስተማረች። አርበኛዋ አሁንም እንደገና ተያዘች። ብዙ ሰው እንደምትገደል ጠብቆ ነበር። እሷም ለሀገሯ ነፃነትና አንድነት ሲባል ብትገደልም ደንታ አልሰጣትም። ነገር ግን ወራሪው ኃይል ባንድ ወይም በሌላ ምክንያት አልገደላትም። በቀጥታ ወደ ወህኒ ቤት ላካት። ነገር ግን እንዳለፈው ጊዜ ወደ ሜዲትራኒያን ደሴት አልተጫነችም። አሁን በቀጥታ ወደ አዝናራ ተጠረዘች። አዝናራ ዓመት ተመንፈቅ ታሰረች። ሸዋረገድ ገድሌ በአዲስ ዓለም የነበረውን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ምሽግ ለማፍረስ በተደረገው ዕቅድ ትልቅ ሚና ተጫውታለች። ምሽጉን ለማፍረስ በተካሄደው ጦርነት ከአንድ መቶ በላይ የወራሪው ኃይል ተዋጊዎች ተገድለዋል። በተጨማሪም በርካታ የጦር መሳሪያ ከአርበኞች እጅ ገብቷል። አርበኛዋ ሸዋረገድ ገድሌ እንደ ገና ተማረከች። በዚህን ጊዜ ግን የትም አልተላከችም። ተይዛ ወደ ዓለም በቃኝ ተወረወረች። ከዚያም ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሹማምንት ፊት አቀረቧት። ቀደም ሲል የሰሯችው ጥፋቶችና የተደረገላት ይቅርታ በዝርዝር ተነገራት። አሁን ግን ምንም ይቅርታ እንደማይደረግላት አረጋገጡላት። ከዚያም በሞት እንድትቀጣ ወሰኑባት። ነገር ግን አሟሟቷ ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚገባው አልገለፁላትም። በዚህ ምክንያት ትሰቀል ወይም ትረሸን እንደሆነ አላወቀችም። ሆኖም የሞትን ፅዋ በፀጋ ለመጨለጥ ተዘጋጅታ ትጠብቅ ገባች።

ቆራጢ የኢትዮጵያ ልጅ ሸዋረገድ ገድሌ በዓለም በቃኝ ታስራ ሞቷን በመጠባበቅ ላይ ሳለች የእንግሊዝ ሰራዊት ወደ ኢትዮጵያ የመግባቱ ወሬ ተሰማ። በተቃራኒው ደግሞ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እየተፍረከረከ ሔደ። አርበኞች ደግሞ በከፍተኛ መነቃቃት ተነሳሱ። በማያጠራጥር መልኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል አድራጊነት ተረጋገጠ። በዚህን ጊዜ ሞት ተፈርዶባት የምትገደልባትን ቀን በመጠባበቅ ላይ የነበረችው አርበኛዋ ሸዋረገድ ገድሌ ተለቀቀች። አርበኛዋ ሸዋረገድ ገድሌ የኢትዮጵያ ባንዲራ ወርዶ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀል አይታ ስቅስቅ ብላ አልቅሳለች። ክብርና ሞገስ ለሸዋረገድ ገድሌ! ክብርና ሞገስ መተኪያ የሌለውን ሕይወታቸው ለሉዓላዊነታችንና ለአንድነታችን መጠበቅ ገፀ በረከት አድርገው ለሰጡ የኢትዮጵያ ጀግኖች ሁሉ!



አስራት አብርሃም

# የህወሓት ነገር

ህወሓት ከምስረታው ጀምሮ ከበርካታ ግራ አጋቢ ነገሮች ጋር የተወሳሰበ ፓርቲ ቢሆንም ከአቶ መለስ ሞት በኋላ ደግሞ ግራ አጋቢነቱ ይበልጥ ጨምሯል። በእርግጥ ህወሓት በአቶ መለስ ሞት የደረሰበት ጉዳት ቀላል ባለመሆኑ በሆነ ባልሆነው (ያለ አላማ) መወራጨቱ የሚጠበቅ ነው። እናም በአጠቃላይ ነገረ ስራው ሲታይ መሪው መንገድ ላይ ጥሎት የሄደ ዓይነ ስውርን መስሏል። በዚህም የተነሳ የእውር ድንብር እርምጃ እየወሰደ ነው። ከሁሉም ከሁሉም የከፋው ግን ዓረና ላይ በተለይ ደግሞ ከፓርቲው ተለይተው በተለያዩ የተቃውሞ ጎራዎች የተሰለፉቱን ቱባ ቱባ የቀድሞ አባላቱ ላይ "ሳልሳይ ወያኔ" የሚል ስም ሰጥቶ የጀመረው አፍራሽ ዘመቻ ነው። የዛሬው ፅሁፌም በዚህ ላይ የሚያተኩር ነው።

"መቓልሕ" በሚባለው የክልሉ መንግስት ወርሐዊ መፅሔት የመስከረም 2005 ዓ.ም እትሙ በርዕሰ አንቀፁ ላይ "ኣብ ዝባን መቓብር በዓል ራኢ መራሒና ልምዓት፣ ዴሞክራሲን ሰናይ ምምሕዳርን ይዕምበብ እምበር ኳኸቶ አይበቕሎን" በሚል ርዕስ ይጀምራል። ('በባለራዕዩ መሪያችን መቃብር ላይ ልማት፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ያብብበታል እንጂ እሾህ አይበቅልበትም' እንደማለት ነው።) በመቀጠል አቶ መለስ ለሚቀጥሉት ሃምሳ ዓመታት ሊያሰሩ የሚችሉ ዕቅዶችና አቅጣጫዎች እንዳስቀመጡላቸውና ወ/ሮ አዜብ መስፍን እንዳሉት ሳይበረዝ፣ ሳይከለስ በዚያ ቀጥ ብለው እንደሚጓዙ ይዘረዝራል።

የርዕሰ አንቀፁ ፅሁፍ "እቲ ኽልቢ ይንባሕ እቲ ጭራ ነብሪ ዝሓዘ ህዝቢን መንግስቲን ግና ጉዕዝኡ ክቕፅል እዩ" በሚል ሌላ መፈክር ነው የሚዘጋው። ይህም "ውሾቹ ይጩኹ የነብር ጭራ የያዘው መንግስትና ህዝብ ግን ጉዞውን ይቀጥላል" የሚል ነው። የዛሬን አያድርገውና ይህንን ተረት አቶ መለስ ነበሩ ደጋግመው የሚተርቱት። በፊት "ውሾቹ ይጮኻሉ ግመሉ ግን ጉዞውን ቀጥሏል" የሚል ነበር። ተረቱን ህወሓት ከዓረቡ ዓለም ከእርዳታ ጋር እንዳለ የወረሰው መሆኑ ይታወቃል። አሁን ግን ግመሉ የነብር ጭራ ወደያዘ የተጨነቀ መንግስት ባህሪይ እንደተቀየረ ከመፈክሩ ፍሬ ነገር መረዳት ይቻላል። ህወሓት ለምን ይሆን የአቶ መለስ ተረቶች ሳይበረዙና ሳይከለሱ መጠቀም የተሳነው?! ተረትማ እንዲያውም በተፈጥሮው 'አይከለስ አይበረዝ' ነው የሚባለው። መቼም የእነርሱ ነገር ከድሮም ጀምሮ አይሆንም የሚባለው እንዲሆን፣ ይሆናል የሚባለው ደግሞ እንዳይሆን ማድረግ ነው።

የአቶ መለስን ሞት አስመልክቶ ህወሓት ወዳወጣው ድርጅታዊ መግለጫ ስንሻገር ደግሞ እንዲህ የሚል እናገኛለን፤

*ዝኽበርካ ህዝቢ ትግራይ፣*

*ዝኽበርኩም አባላት ውድብን ፈተውትን፣*

*መለስ ሓደ ሻዕ ብቐትሪ ሓደ ሻዕ ብፀልማት እናተፋሕኾ ናብ ደንበ ክራይ አካብነት ክኣትዉ እዮም ኢሉ ዝነገረና፣ ምንቅስቓስ ተሃድሶና ናብ ጓሓፍ ዝደርበዮም ኣብ ደንበ ፀላእትና ዝወገኑን ካልኦት ፀላእትናን ኣብ መንገዲ ልምዓት፣ ዴሞክራሲን ሰላምን መለስ ኳኾቶ ኮይኖም ትልኽ እናበሉ ከሕንኩሉና ምፍታኖም አይተርፍን። ድሮ እኳ ሓዘንትን ሓለይትን መሲሎም ክተዓረቑ ዘይክእል ደንበ ልምዓትን ደንበ ክራይ አካብነት ክሓዋውሱ፣ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ዘለዋ ሃገር ምኳና ከም ወትሮኦም እናረስዑ ሓደ ሻዕ ንተዓረቑ፣ ካሊእ ግዜ ንበይንኹም ከይትደኽሙታስ ክንሕግዝ፣ ወጃዕ እንትብሎም ድማ ካብቲ ናይ ቃልሲ ወነና፣ ብስም ስውእ መራሒና ዝኣተናዮ ቃል፣ ካብ ናይ ተግባራዊ ርብርብናን ተበግሶታትና ዘመዛብሉና መሲልዎም ናይ በለካን ለኽዓካን ብዕራይ ወለደ ልሙድ ናይ ውድቀት ዜናታቶም ክፍንዉ ጀሚሮም ኣለዉ።"*

ይህ ከላይ ዘለግ ብሎ በትግርኛ የቀረበው ሀሳብ ወደ ወደ አማርኛ እንዲህ መልሸዋለሁ፤

"የተከበርከው የትግራይ ህዝብ፣

የተከበራችሁ የድርጅታችን አባላትና ወዳጆች፣

መለስ 'አንድ ጊዜ በጨለማ ሌላ ጊዜ በብርሃን ወደ ኪራይ ሰብሳቢነት ጎራ ይገባሉ' ብሎ እንደነገረን፣ የተሃድሶ እንቅስቃሴያችን ወደ ቆሻሻ መጣያ የወረወራቸው፣ ከጠላቶቻችን ጎራ የወገኑና ሌሎች ጠላቶቻችን ከልማት፣ ከዴሞክራሲና ከሰላም መንገድ ሊለዩን እሾህ ሆነው ሊያደናቅፉን መሞከራቸው አይቀርም። ይሄው አሁን አዛኝና አሳቢ መስለው፣ ፈፅሞ ሊታረቅ የማይችለውን የልማት እና የኪራይ ሰብሳቢነት ጎራ ለማደባለቅ፣ ሕገመንግሰታዊ ስርዓት ያላት አገር መሆኗን እንደ ሁልጊዜው እየረሱ አንድ ጊዜ እንታረቅ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ለብቻችሁ ሆናችሁ አትችሉትም እናግዛችሁ፣ በተቃራኒው ደግሞ ለመሪያችን የገባነው ቃል እንዳንፈፅም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዳንገባ የሚያዘናጉን መስሏቸው፣ በሬ ወለደ ዓይነት ወሬ እና ሌሎች በርካታ የውድቀት ዜናዎች ማሰራጨት ጀምሯል" ነው የሚለው።

እዚህ ላይ ብዙ መነሳት ያለባቸው ጉዳዮች ይኖራሉ። ለምሳሌ ህወሓት ከቀድሞ የአመራር አባላቱ ጋር በሚስጥር እየተነጋገረ ነው የሚል ወሬ ይነዛ የነበረው ከዚያው ከራሳቸው ከህወሓት መንደር ነው። ከዚያም አልፎ ተርፎ ይህን ነገር የሚያስተባብሩት አቶ ስብሓት ነጋ ናቸው የሚል ወሬ ሆን ተብሎ ቀንደኛ በሆኑ የህወሓት ወሬ አራጋቢዎች በየካፌውና በየቡና ቤቱ ይራገብ ነበር። እንግዲህ ህወሓት አቦይ ስብሀትን ማውገዝ ከፈለገ በግልፅ ያውግዛቸው። እርሳቸው ድሮም የአቶ መለስ ወገን እንጂ የአንጃው ወገን አልነበሩም። ከወጡት ጋር ለመወገን መሰረታዊ ባህሪያቸው አይፈቅድላቸውም። አህያውን ፈርቶ... እንዲሉ በዓረና ላይ ማሳበብ የተፈለገበት ምክንያት በራሱ በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን መከፋፈሎችና ችግሮች በውጭ ጣልቃ ገብነት የተፈጠረ ለማስመሰልና ምንም የማያውቁትን በተለይ ከድል በኋላ እውነት መስሏቸው ድርጅቱን የተቀላቀሉ ወጣቶችና ምሁራን ለማታለል ወይም አጀንዳ ለማስቀየር የአባይ ወልዱ አመራር የወሰደው ርካሽ የማታለል ተግባር ነው ሊሆን የሚችለው።

እኔ በግሌ ይህ ነገር ውሸት መሆኑ አውቅ ነበር። ምንም ዓይነት የተጀመረ ድርድር ሆነ እርቅ አልነበረም። ስጠረጥር ግን ህወሀት ሆን ብሎ እነስዬ እና እነገብሩ በተቃዋሚው ጎራ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ታስቦ የተወጠነ ሴራ ነው የሚመስለኝ። የሚገርመው ደግሞ ይህን አጀንዳ ከሚገባው በላይ ለማጮህ በመፈለግ "በእርቅ ሰበብ ውስጣችን ገብተው ሊበትኑን ነበር" የሚል መግለጫ መስጠታቸው ነው። "ከማንኛውም ወገን ጋር እርቅ እንደማናደርግ ህዝቡ እንዲያውቅልን እንፈልጋለን። እርቅ የሚኖረው በመቃብራችን ላይ ብቻ ነው" ብሏል መግለጫው። ለምን ሁልጊዜ ጠላት አለን ብለው እንደሚያስቡ ግራ ይገባኛል። በሌላ በኩል አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከሻዕቢያ ጋር ለመነጋገር እንደሚፈልጉ ግልፅ አድርጓል። ስልጣናቸው ትግራይ ላይ ያለውን አስተዳደር አያጠቃልል ይሆን?! የህወሓት መግለጫ መሪው አሁንም ጓድ መለስ እንደሆኑ አቋሙን ግልፅ አድርጓል። ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ እንዳሉት አይዟችሁ እርቅ የሚባል ነገር አይኖርም ተብሎ ለህዝብ እንዴት ይነገራል?

የተደናበረው የህወሓት መግለጫ ጥሪ ያላደረገለት የህብረተሰብ ክፍል የለም ማለት ይቻላል።

የተከበርከው የትግራይ ህዝብ፣ የተከበራችሁ የድርጅታችን አባላት፣ የተከበርከው ታጋዩ የትግራይ ህዝብ፣ የተከበራችሁ የድርጅቱና አባላትና ወዳጆች፣ የተከበርከው የገጠር ታጋዩ ህዝባችን፣ የተከበርከው የከተማ ታጋዩ ህዝባችን፣ የተከበራችሁ የመንግስት ሰራተኞች፣ የተከበራችሁ የድርጅታችን አባላትና ደጋፊዎች...! በመግለጫው በእያንዳንዱ አንቀፅ መግቢያ ላይ እነዚህና መሰል አገላለፆች ታገኛላችሁ። ዝገርም ነገር! ይህ ሁሉ የውዳሴ ጋጋታ የገባበትን ውጥረትና ፍራቻ ወለል አድርጎ የሚያሳይ ነው።

ከሁሉም በጣም የሚያስገርመው ደግሞ በመግለጫው ማብቂያ ላይ የሚገኘው ዐረፍተ ነገር ነው። "ናይ መለስ ሓሳብ፣ መስመርን አንፈታት ግዝ ሰጊሩን ነዊሕ ኣሚቱ ዝጓዓዝ ስለዝኾነ መለስ ብኣካል ዝተፈለየና እንተኾነ እውን ብሓሳባቱ፣ ብመስመሩ፣ ብራእዩን ክመርሓና እዩ። ሕዚ እውን መራሒና እዩ።"

"የመለስ ሀሳብ፣ አቅጣጫና ራእይ ጊዜን ተሻግሮ የሚጓዝ ስለሆነ፣ መለስ በአካል ቢለየንም በሀሳቦቹ በያዘው መስመርና በራእዩ ይመራናል። አሁንም መሪያችን ነው።" በዚህ አባባል የሄድን እንደሆነ ህወሓት በዓለማችን በሙት መንፈስ የሚመራ ብቸኛ ፓርቲ ያደርገዋል። በተግባር ደግሞ ህወሀት ሀሳብ የሚያመነጭለትና የሚመራው ሰው ስለተለየው አሰራሩ ሁሉ ዶግማዊ ይሆናል ማለት ነው። በዶግማ የሚመራ ደግሞ የኃይማኖት ተቋም እንጂ የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም። አቶ መለስ የሁሉም ነገር መሃንዲስ ነበሩ ሲባል የሰማ ቀልደኛ "መሃንዲሱ ከሌለ ግንበኞቹ ምን ያደርጋሉ!" ሲል ቀልዷል። እውነቱነ እኮ ነው፤ መሀንዲሱ ከሌለ ግንበኞቹ ምን ያደርጋሉ!

የክልሉ ፕሬዚደንትና አዲሱ የህወሓት ሊቀመንበር አቶ አባይ ወልዱ ያወጡት መግለጫ ደግሞ የሞኝ ብልጠት ያለበት ይመስላል።

"ዝኽበርካ ህዝቢ ትግራይ

ዝኽበርኩም አባላት ምክልኻል ሃገርን አባላት ውድብን" ብሎ ይጀምርና ብዙ ብዙ ነገር ይደሰኩራል። እርሱ የክልሉ ፕሬዝደንት ሆኖ ሳለ ለመከላከያ አባላት ጥሪ ማቅረቡ ሌላው

አስገራሚ ነገር ነው። መከላከያው አሁንም የእኛ ነው ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም። ያለበት ኃላፊነት ግን እንዲያ እንዲል የሚፈቅድለት አይደለም። አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ይታዘቡናል አይባልም እንዴ! የሾሙትን ሰው መናቅማ ደግ አይደለም! ያም ሆነ ይህ አባይ ወልዱን እንደ መሪው አድርጎ የሚቀበል የመከላከያ አባል ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም። ያው አሁን እንደጀመረው የአቶ በረከት ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ ይቀጥሉ እንደሆነ እንጂ ህወሓት በአቶ መለስ ጊዜ የነበረውን ያህል ተሰሚነት በአባይ ወልዱ ጊዜ ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም።

ለነገሩ አቶ አባይ ወልዱ ከትግሉ ወቅት አንስቶ እስካሁን ያላቸው ታሪክ እንደሚያሳየው ተከታይ እንጂ መሪ አልነበሩም። የተሰጣቸውን የስራ መደብ በመፈፀም ከአለቆቻቸው ስር ሆነው እስከዛሬ ተጉዘዋል። ሀሳብ አመንጪም አልነበሩም። በታሪክ አጋጣሚ ዛሬ አዲስ ሀሳብ ማመንጨት ግድ በሚልበት ቦታ ላይ ተቀምጠዋል። ነገር ግን በመለስ ሀሳብ እንጂ በራሳቸው ሀሳብ ክልሉን እንደማይመሩት ግልፅ አድርገዋል። “ጓድ መለስ በአካል ቢለየንም አሁንም መሪያችን ነው” ብለዋልና። በዚህ ነገር ከአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር የሚመሳሰሉ ይመስላሉ። በብቃት አቶ ኃይለማርያም እንደሚሻሉ ግን በጣም ግልፅ ነው። ለዚህ ነው አቶ አባይ ወልዱ የህወሀትን ጥንካሬ ያስጠብቃሉ ተብሎ የማይታሰበው።

በድሮ ጊዜ ራስ ስዩም የትግራይ ህዝብ ሲበድል፣ ፍትህ ሲያጣ እያዩ ለሸዋው መንግስት ታማኝ ሆነው በመገዛታቸው ይወቀሱ ነበርና አንዲት ሴት እንዲህ ስትል ገጠመችላቸው ይባላል፤

“አባ ይርጋ፣ ስዩም አባ ይርጋ
መውደልደላይ፣ ከም በቅሊ ዕዳጋ
ሽንኳይ ተዋጊእካ፣ ክተምልስ አልጋ
ተሸይጥካ እኳ፣ ዘይተውፅእ ዋጋ።”

ግጥሙን ወደ አማርኛ ስመልሰው ብዙም ለውጥ የለውም። አማርኛ እና ትግርኛ ይህን ያህል ይመሳሰላል እንዴ እስክል ድረስ አስገርሞኛል። ይሄው ማነፃፀር ትችላችሁ፤ የራስ ስዩም የፈረስ ስማቸው “አባ ይርጋ” ነበር።

“አባ ይርጋ፣ ስዩም አባ ይርጋ
አውደልዳይ፣ እንደ በቅሎ መሰጋ
እንኳንስ ተዋግተህ፣ ልታስመልስ አልጋ
ተሸጠህም፣ አታዋጣም ዋጋ።”

ይህ ግጥም ምንም እንኳ የተገጠመበት አውድና ዘመን ፍፁም የተለየ ቢሆንም አቶ አባይ ወልዱን በትክክል የሚገልፅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በአባይ ወልዱ የሚመራው አሮጌው የህወሀት አመራር ስልጣኑን ለማስጠበቅ ሲል ፓርቲውን ለበረከት ስምኦን በገፀ በረከትነት አስረክቦ ሰልፉን አሳምሯል። አቶ አባይ ወልዱ ቀድሞ ለመለስ ያደሩ ነበሩ፤ አሁን ድግሞ ለበረከት። የራሱ የሆነ አቋምና ሀሳብ የሌለው፣ በራሱም የማይተማመን ሰው ሉሌ ከመሆን ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም። ህወሀት አሁን በትክክል አርጅቷል። ማርጀት ብቻ አይደለም ጃጅተዋል ቢባል የተሻለ ይገልጸዋል። ለህወሀት እውነተኛ ተሃድሶ የሚያስፈልገው ጊዜም አሁን ይመስላል።

በህወሀት ውስጥ በውድም በግድ አባል ሆኖ ያለው ወጣትና ምሁር በቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ይታወቃል። ይህ ወጣት የበረከት አገልጋይ መሆን አለበት ብዬ አላስብም። በፓርቲው ውስጥ ከታች የለውጥና የእርምት እንቅስቃሴ መጀመር አለበት። ለኤርትራ ጥቅም የቆመውን አሮጌውን አመራር በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመቀየር የአገሩን ጥቅምና ሉኣላዊነት የሚያስገብር አቋም በመያዝ፣ የባህር በራችንን ለማስመለስ የሚደረገውን ትግል በመቀበል መታገልና የራሱን ታሪክ በወርቅ ቀለም መፃፍ ይችላል። የአቶ መለስን ታሪክ መድገም ቁም ነገር የለውም። በህወሀት ውስጥ ያለው የትግራይ አዲሱ ትውልድ ፈፅሞ የማንም ሉሌ መሆን የለበትም። እኛ ጠባችን የአገራችን ሉኣላዊነት አሳልፎ ከሰጠው አሮጌው የህወሀት አመራር እንጂ በተለያየ ምክንያት የህወሀት አባል ሆኖ ከሚገኘው ወገናችን ጋር አይደለም። ቢኖረን ልዩነት እንጂ ጠላትነት አይደለም። በኢህአዴግ ውስጥ ያሉ ሌሎች ፓርቲዎች ውስጣዊ አቅማቸውን በወጣት ምሁራን ሲገነቡ ህወሀት ግን ፓርቲውና ክልሉን የድሮ ካድሬዎች መጦሪያ አድርጎታል። በፓርቲው ውስጥ ያለው ወጣትና ምሁር ተላላኪና አገልጋይ እንጂ በራሱ ሀሳብ የሚጓዝ፣ የራሱን ራዕይ ያለው መሪ ሆኖ እንዲወጣ የሚፈለግ አይደለም። ከአቶ መለስ እልፍ ጊዜ የሚሻል ራዕይ ያለው ወጣት ሊኖር እንደሚችል ግን መገመት ይቻላል።


ስለዚህ “ለቀጣዮቹ አርባ እና አምሳ አመታት በአቶ መለስ ራዕይ ነው የምንመራው” የሚለው አቋም በህወሓትና በኢህአዴግ ውስጥ ላለው ምሁርና ወጣት ስድብ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። አቶ መለስ ለቆሙለት አላማ ትክክልም ሆነ አልሆነ በፅናት መቆም መቻላቸው የሚደነቅ ነው። ይህን ፅናታቸውን መውረስ ይቻል ይሆናል። ራዕያቸውና አላማቸው ላይ ግን ሊወረሱ የሚገባቸው መውረስ፣ መወገድ የሚገባቸው ደግሞ ማስወገድ ያሻል። ለምሳሌ በባህር በር ላይ የነበራው አቋም ፈፅሞ ሊወረስ የሚገባ ነገር አይደለም። አባይን ለመገደብ ቆርጠው የገቡበት ጉዳይ ግን ጥሩና ጠቃሚ ነገር በመሆኑ ከግብ ማድረስ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ወንዞቻችን እስከመገደብ ድረስ የሚጓዝ ራዕይ ሊኖረን ይገባል።

ያም ተባለ ይህ በየትኛውም ፖለቲካዊ አደረጃጀት ውስጥ የታቀፈ አዲሱ የኢትዮጵያ ትውልድ የራሱ የሆነ ራዕይና አላማ ሊኖረው ይገባል። በራሱ ሀሳብና እምነት መጓዝ፣ በራሱ ርዕዮተ ዓላማዊ እይታ መራመድና መታገል አለበት። ህይወት አንድ ጊዜ ብቻ የሚኖሩት ብርቅ ነገር ነውና። ለጊዜያዊ ጥቅም፣ ለሆዳችን ስንል አገልጋይና ተላላኪ በመሆን ይህን ዳግም የማይገኘውን ህይወት እንኖረው ዘንድ የተገባ አይደለም።

ማስታወቂያ

ማስታወቂያ

አዲስ መፅሐፍ በገበያ ላይ




## በዚች ምድር የሰው ልጆች ቀንደኛ ጠላቶች

ሌብነት፣ ውሸት፣ አሸሙርና ውንጀላ
ምቀኝነት፣ ተንኮል፣ ክህደትና ብቀላ
ወሬኛነት፣ ትዕቢት፣ አስመሳይነትና ጉራ
ግብዝነት፣ ጥላቻ፣ ትምክህትና አመንዝራ።
ከነስማቸው ውጉዝ - ምግባረ አሳፋሪ
የፍቅር ፀር - ግንኙነት አሻካሪ
ሰላም አደፍራሽ - ነቋሪ አደንቋሪ
የጤና ጠንቅ - ሕይወት አጨላሚ።

ከእነዚህ መካከል አንዱ የተቆራኘበት
ሰላም አይሰጥ፣ ለራሱም ሰላም የለበት
በጌታም አምላክ ዘንድ - ፅዩፍ ተወጋኘ
በሰው ልጆች መሃል - ቀላይ ተዋራጅ።

ይህ ዓይነቱ ሰው ዝቃጭ ነው የሕይወት አተላ
ልቡ ከቶም የማይገኝ መሰሪ እሾኽ አሜኬላ
በአምሳለ እግዚአብሔር
ከማንም በላይ በክብር ተፈጥሮ
በላቡ በወዙ መኖር ሲገባው ለፍቶ
ጥሮ ግሮ
የሰው ሕይወት ይበጠብጣል
በምቀኝነት ታውሮ።
ፈጣሪ አምላካችን ለእኛ ሲል ተሰቅሎ
ክቡር ሕይወቱ ሰጥቶን
ሥጋዬ የበላ ደሜ የጠጣ
ዘላለማዊ ሕይወት ያገኛል ብሎ
በደሙ ዋኽቶን
አይከብድም ወይ በክህደት ውንጀላ
እርስ በርስ መበላላቱ
ከፈጣሪ ትዕዛዝ ከአምሳለ ፍጥረት
ወርዶ አንሶ መገኘቱ።
ሰላም፣ ዕድገት፣ ደስታ የማግኛው ምስጢር
ቅንነት፣ ደግነት ሆኖ ሳለ መተሳሰብ ፍቅር
ምን ይገኛል ከውሸት አስመሳይነት?
ቀሎ አፍሮ ወድቆ ከመገኘት
ምንድ ነው ጥቅሙ በጥላቻ ብቀላ መጠላለፍ?
በጥፋት ጎዳና ጠልፎ ለመጣል መክለፍለፍ
ምን ይጠቅማል የብጥብጥ ምንጭ
መሆን የሐጥያት ጎተራ?
የዘሩትን ማጨድ ላይቀር ክፋት
ተንኮል ዘርተን ባናፈራ
ስለዚህ እባካችሁ ሰዎች!
ንፁህ እንቅልፍ የሚተኛው
ሰላም ደስታ የሚመጣው
የህሊና እርካታ የሚገኘው
ፍተው ደክመው ሲተኙ ብቻ ነው።

*ወ/ሮ አስቴር ሠይፈ (አስቴር ጠጅ)*
*የፈተና መጽሐፍ ደራሲ*

## የልማታዊ.... (ከገፅ 12 የዞረ)

ተቋማት በሚያፈሯቸው የተማሩ ባለሙያዎች ላቅ ወዳለ ከፍታ ማሸጋገር የሚለው ከፍታና ሽግግር ማለት ግን፣ባገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለማስረገጥ ያህል፤ ኢቲቪ አንጀት ላይ ጠብ በማይለው ባለፈው ሰሞን አየር ላይ ባዋለው ዶክመንተሪው ከሺ አመታት በፊት ይኖሩ የነበሩ የድንጋይ ዘመን አባቶታቸው ይሰሩት የነበረውን የድንጋይ መጥረብ ስራ ከ15 እና ከ16 ዓመታት በላይ በትምህርት ገበታ ያሳለፉ "ባለራዕዮች" "ምሩቃን" የተሰማሩበት የድንጋይ መጥረብ "ኢንዱስትሪው" "ከፍታና ሽግግር" አይነት በፍፁም አይደለም፡፡ ምናልባትም ይህ "ባለራዕዮቹ" የተሰማሩበት የድንጋይ መጥረብ ስራ ወደኛ ሀገር ሲመጣ የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ የሚያስገኘው ፍሬ ይህንን አይነት "ቁመና" ኖሮት ከሆነ አላውቅም፤ ተፅፎ ግን አላነበብሁም፡፡ ባንዳንድ ሰዎች ዘንድ ምሩቃን ድንጋይ ጠራቢዎችን በሚመለከት ተሳታፊዎቹ ስራ ፈጣሪዎች ናቸው ሲሉ እሰማለሁ፡፡ ይህ አረዳድ ግን ትክክል አይመስለኝም፡፡ "ለምሩቃኑ" የራሳቸውን ስራ ፈጠሩ የሚባለው በተማሩት ዘርፍ በግላቸው ሲሰማሩ ነው፡፡ ለምሳሌ የህክምና ምሩቅ የግሉን ክሊኒክ ወይንም ሆስፒታል የከፈተ እንደሆነና በግሉ የህክምና አገልግሎት መስጠት የጀመረ ጊዜ የራሱን ስራ ፈጠረ እንልዋለን እንጂ ሃኪም ድንጋይ ጠራቢውን የራሱን ስራ ፈጠረ ልንለው አንችልም፤ ምስኪኑ ላብ አደር እንጂ፡፡

ለማንኛውም፣ የተማሩ ሰዎች የራሳቸውን ስራ በተማሩበት የትምህርት መስክ አለመፍጠራቸው በራሱ የትምህርት ፖሊሲው ሳይውል ሳያድር ፍተሻና ለውጥ እንደሚያስፈልገው የመጠቀ ምርምር ሳይካሄድ በራሱ አመላካች ነው፤ ውድቀት ለሚያነበው ሰው ትልቅ መፅሃፍ ነው አይደል የሚባለው፡፡

2. ለልማታዊ መንግስት የእድገት ፍኖትነት ቀጣዩ ወሳኝ ጉዳይ ርዕዮቱ ታሳቢ የሚያደርገው የሃብት ምንጭ(Resource) ነው፡፡ በልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ለአንድ አገር ትልቁ የሃብት ምንጭ ነዳጅ፣ የከበሩ ማዕድናት ወይንም የተፈጥሮ ሃብት አይደለም፤ ይልቁንም መተኪያ የሌለው ህዝቧ እንጂ፡፡ በዚህ መሰረት ለኢትዮጵያ ሃገራችንም ትልቁ ሃብቷ ኢትዮጵያውያን ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ነዳጅ ወይንም ሌላ የተፈጥሮ ሃብት ጠቃሚ አይደለም ማለት አይደለም፤ ለኢትዮጵያ ከኢትዮጵያውያን በላይ ጠቃሚ ግን ለአሳር ለማለት እንጂ፡፡ ሆኖም ግን ይህንን ለኢትዮጵያ "ህዳሴ" እውን መሆን የማይተካ ሚና የሚጫወተውን የሃገር ሃይል በጎሳ በተጠነፈረ አስተሳሰብ ስንከፍለውና ስናባትለው፣ በሃገር ላይ ትልቅ ወንጀልና ደባ እንደመፍፀም ይቆጠራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌላ መሆንና መደረግ የሚገባው ጉዳይ ምንድን ነው፣ ዜጎች የተሻለ መፍጠር እንዲችሉ፣ በልበ ሙሉነት ማሰብ እንዲጀምሩ፤ ማንኛውንም ነገር የሚፈጥረው ሰው ነውና፣ ነፃነት እጅግ አስፈላጊና ሊሰፍን የሚገባው አብይ ጉዳይ ነው፤ እጅግ አስፈላጊ የልማት ሞተር ነውና፡፡ ከዚህ ውጭ ልበ ሙሉ ዜጎች በሌሉበት፣ ዜጎች ብንናገር እንዲህ ልንሆን እንችላልን እያሉ ተሳቀው በሚኖሩበት ሁኔታ፣ የእውቀት ባለቤቶች በሰፊው ባልተሳተፉበት አካሄድ ምንም ርዕዮተ-ዓለም እንከተል ምን፣ ትርፉ ድካም ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው ከልማት በፊት ነፃነት አስፈላጊ ነው፤ ነፃነት የሌለው ሰው የሚያስበው ትክክል አይደልም፣ ነፃ የሆነ ትውልድ መፍጠርም አይችልም በሚል ክርክርና ሙገት የሚከፈተው፡፡

ከላይ ከቀረበው የምንረዳው ምንድን ነው፤ አሁን በአገራችን ያለው ብሄርን ብቻ መሰረት ያደረገ አስተዳደራዊ መዋቅር ከልማታዊ መንግስት አስትሳሰብና አስተምህሮ ጋር አብሮ እንደማይሄድ ነው፡፡ ስለዚህ አቅምንና ችሎታን መሰረት ያደረጉ አሰራሮች ቢሰፍኑ፣ የእውቀት ባለቤቶች በሰፊው በአገር ግንባታና አስተዳደር ረገድ ቢሳተፉ፣ የጎጥ ድስት ወጥቶ የአቀምና የችሎታ ድስት ቢገባ ድህነትን በልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ አንደባለን መጣል እንችላልን፡፡

3. ሶስተኛው ቁም ነገር ደግሞ የአለማቀፋዊ ተወዳዳሪነት መዳበርን የሚመለከት ነው፡፡ አለማቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሱት እርምጃዎችን መውሰድ ጠቃሚ እንደሆነ ቻንግ በመፅሃፋቸው ይመከራሉ፡፡

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ የትነው ያለችው ብሎ መጠየቅ ተገቢም አስፈላጊም ሆኖ ይታየኛል፡፡ በቅርቡ የአለም አገራት ደረጃዎች በመመደብ ታዋቂ የሆነው የአለም የኢኮኖሚ ፎረም (World Economic Forum) የአለም አገሮችን የ2012 የተወዳዳሪነት ደረጃ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ኢትዮጵያም በሪፖርቱ ከዚህ በፊት ታሽቆለቁልበት ከነበረው ፍጥነት ጨምራ 144ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፤ በ 2009/2010-106ኛ ደረጃ ስትይዝ፣ በ2010/2011 ደግሞ 119ኛ ተርታን ይዛ ነበር፡፡ ይህ ማሽቆልቆላችን፣ ተወዳዳሪነት ከሚያጎለብተው የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኗል፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ ይህ የአለም የኢኮኖሚ ፎረም ሪፖርት የኢትዮጵያ የተወዳዳሪነት ደረጃ በልዩ ሁኔታ ማሽቆልቆል በራሱ አንድ ነገር ጠቋሚ ነው፤ ያልፈታናቸው ቁልፍ ችግሮች እንዳሉን፤ ለውጦች እንደሚሹ፤ አዳዲስ የማነቃቂያና የማገገሚያ እርምጃዎች አስፈላጊ እንደሆኑ፤ ያለበዚያ ግን የልማታዊ መንግስት አስትሳሰብ መከተላችን ተወዳዳሪነታችንን ካላጎለበተ ጠቀሜታ እንደሌለው ያሳያል፡፡

4. በመጨረሻ ላይ የማቀርበው የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ማጠንጠኛ የሆነው ቁልፍ ነገር፤ የአንድ አገር መሪ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሲሆን፣ ይህም ትኩረቱ ከባህላዊና አነስተኛ አርሶ አደርን ማዕከል ካደረገ የእርሻ መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ወደ ዘመናዊ አምራች (manufacturing) የኢንዱስትሪ መር ፖሊሲን ማተኮርን የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን መሰረታዊ የአገር የኢኮኖሚ ፖሊሲ በተጠናከረና በሰፊ መሰረት ለማስኬድ ለአምራች ኢንዱስትሪው እድገት ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው የገጠር ልማትና የእርሻ ፖሊሲዎች የደጋፊነት ሚና እንዲኖራቸው ተደርገው መቀረፅ ይኖርባቸዋል፡፡

ወደ ሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ስንመጣ በተለይ ባለፉት ሁለት አስርት አመታትና ከዚያ በላይ በላይ ባህላዊ አነስተኛ አርሶ አደርን ማዕከል ያደረገ፣ ምንም መሻሻል ያልታየበት ግብርናን ቅድሚያ ሰጥተን ቆይተናል፡፡ የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብን ከተከተልን ግን ይህ የነበረውና አሁንም ያለው የትኩረት አቅጣጫችን መቀየር ነበረበት፣ አሁንም ይኖርበታል፡፡ የኢንዱስትሪ ሴክተሩም ቢሆን እዚህ ግባ የሚባል መሻሻል አልታየበትም፡፡ ለዚህም ይመስላል፣ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ በሃገራችን በቤተሰብ ደረጃ በዘላቂ ሁኔታ የገቢ ምንጭ መጨመርና ስብጥር መፍጠር፣ ብሎም ሰፊና ደሀ-ተኮር የሆነ ቋሚ የስራ እድል ማስገኘት ዳገት የመውጣት ያህል ከብዶን እያለከለክን ያለው፡፡ የምንሰራቸው "ልማታዊ" ስራዎቻችን በቤተሰብ ደረጃ የገቢ ምንጭ መፍጠር ካልቻሉና የስራ እድል ካላስገኙ፤ መንገድ መስራት፣ ህንፃ ማቆም፣ "ንፁህ" የመጠጥ ውሃ ማቅረብ፣ ወዘተ... ዜጎች ስራ ሳይኖራቸውና በቤተሰብ ደረጃ ገቢያቸው ሳይሻሻል ድህነትን በዘላቂነት እንቀርፋለን ብዬ አላስብም፡፡ ስለዚህ ባህላዊ ትናንሽ አርሶ አደሮችን ተኮር የሆነው ግብርናችንና እያዘገመ (stagnated) ያለውን የአምራች ኢንዱስትሪው እድገት ከላይ በቀረበው የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ተቃኝቶ ማስተካከያዎችን ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ማስተካከያዎችም አሁን ካለንበት ሁኔታ አኳያ ሙሉ በሙሉ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የርዕዮት ለውጦችን ጭምር ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

ባጠቃላይ የልማታዊ መንግስት ፍልስፋናን በመሪ ሃሳብነት ተቀብለን እስከተገዝን ድረስ፣ ሃሳቡን ተከትለን የሚያዝናና የልማት ድል እንድናገኝ ከላይ የተብራሩትን ጉድለቶቻችንን ማስተካከል ይኖርብናል፡፡ በሂደትም የሚከሰቱ ተግዳሮቶች ተነቅሰው እየወጡ በይደር ሳይተው መስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም "የታላቁን መሪያችንን ራዕዮችና ህልሞች" ከግብ ለማድረስ ከላይ ለመዘርዘር የሞከርኳቸው ለውጦችንና ማሻሻያዎችን መተግበር እጅግ አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ አለበዚያ ግን ለአመታትም ቢሆን የኤሊ ጉዞ መጓዛችን አይቀሬ ነው፡፡ 'አዲሱ' አመራርና ምልምልም በድህነት ለተደቆሰችው አገራችን 'የለውጥ ሃዋርያና የተስፋ አርዓያ' መሆን ይጠበቅበታልና ስራውን ሲጀምር ማሻሻያዎችንና ለውጦችን በቅድሚያ የሚከውናቸው የቤት ስራውና አገር አድን ተግባሮቹ ቢሆኑ መልካም ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ጤና ይስጥልኝ! ቸር ይግጠመን!

• • • • • • • • • • • • •

## ኬኒያን.... (ከገፅ 13 የዞረ)

ጊዜ አረ እንደውም ሁልጊዜ ገንዘብ የተቀበለ ኬኒያዊ ይኖራል።

ታድያ አንድ ቦታ ፍንዳታ ሲሰማ የአበሻ ቤት በፍተሻ ቁምስቅሉን ያያል። ነገሩ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነው። "ግርግር ለሌባ ይመቻል"እንዲሉ፤ በኬኒያ ደግሞ ፍንዳታ ለፖሊስ ይመቻል ነው። ፍንዳታውን ያደረሱ ተጠርጣሪዎችን ለማደን "አሰሳ ይደረግ" የሚል መመሪያ ይወጣል። ይሄኔ ፖሊስ ሆዬ በየሀ በሻው ቤት እኩለ ሌሊት ሁላ እየሄደ ሻንጣ ይበረብራል። ወንጀሉን የሚፈልግ አይምሰልዎ... "ፔሳ" ነው የሚፈለገው። የፈረደበት አበሻ ቤቱ የመጣውን ፖሊስ ሁላ በሽልንግ እያበሰ ይሸኛል።

ለዚህ ለዚህ መድሃኒቱ ሱማሌ ነው። ፖሊሶች በሆነ ባልሆነው ፍተሻ እያሉ ሲያስቸግሩ ከያሉበት ተጠራርተው መሳሪያ የታጠቀውን ፖሊስ ሱማሌ ነብሴ ቀበቶ እንኳ ሳይታጠቅ ከበባ አድርጎ ሊደበድባቸው ይችላል። ስለዚህ ነው መሰል የኬኒያ ፖሊሶች አበሻን ይበልጥ ይደፍራሉ። አበሻ ፖሊስ ሲመጣበት ካለው በእጁ "ፔሳ" አስጨብጦ፤ ከሌለው በእግሩ ሮጦ ነው የሚያመልጠው።

ኬኒያ በነበርኩበት ጊዜ በጣም ሲያንገበግበኝ የነበረው ነገር በሄድንበት ሁሉ መደፈራችን ነበር። በሀገራችን የገዛ መንግስታችን ይደፍረናል። በሰዉ ሀገር ደግሞ የጠገበ ፖሊስ አበሳችንን ያበላናል። ይሄ በጣም ያበሳጫል። በእውኑ ኢትዮጵያዊ ተፈጥሮው እንዲህ ነውን!?

በመጨረሻም

ኬኒያውያን ለስጋ ያላቸው ፍቅር ተነግሮ አያልቅም። ወዳጆቼ እንዳሉኝ ከሆነ በኬኒያ የሆነ አለመረጋጋት ነገር ቢከሰት እና ዘረፋ ቢጀመር ዘራፊው መጀመሪያ የሚሄደው ወደ ወርቅ ቤት ሳይሆን ወደ ስጋ ቤት ነው ብለውኛል። የኬኒያ ጎረምሳ ላፈቀራት ልጅ የፍቅሩን ልክ ሲገልፅ እንዲህ ብሎ ነው አሉ፤ "ናኩፔንዳ ዌዌ ከማ ኛማ ቾማ!" ይላታል። ወደ አማርኛ ሲመለስ "ልክ እንደተጠበሰ ስጋ ነው የምወድሽ"

እኔ የምለው እኛም ዘንድ ስጋ ኪሎው 180 ብር ገባ ብሎ የፒያሳው አራዳ ጋሽ ፍቅሩ ኪዳኔ ነገረኝ! እኛም ወደፊት ቆነጃጅቶቻችንን "እንደ ቁርጥ ስጋ የተወደድሽው ፍቅሬ!" ማለት ሳንጀምር አንቀርም።

ወዳጄ ለዛሬ ኬኒያን በድርበቡ ለማሳየት ሙከራ አድርጌያለሁ። ወደፊት ብዙ የምናወጋው ይኖረናል። እድሜ ይስጠን ብቻ!

አማን ያሰንብተን!

## ቃሊቲን.... *(ከገፅ 36 የዞረ)*

ኮማንደር በያዝኩት ቲ-ሸርት ላይ ‹‹ስሜ ተጠቅሶ እረገማለሁ›› ወይም ‹‹እወገዛለሁ›› ብሎ እንደማያስብ ስለማውቅ ምን አይነት መልዕክት ያለው ፅሁፍ ከቲሸርቶቼ ላይ እየፈለገ እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም። ፍተሻው እንዳለቀ ‹‹ዕቃህን ሰብስብና ተከተለኝ!›› አለ-ከመሬት ተነስቶ የጠላኝ ኮማንደር። ጓዜን እንደምንም ሸካክፌ ተከተልኩት። ከላይ የጥበቃ ማማ ያለበት ከሲሚንቶ የተሰራ ቤት ጋ ስንደርስ ቆመና ከኪሱ ቁልፍ አውጥቶ ከፈተው። ሶስት በሶስት የምትሆን ኦና ቤት። ‹‹ግባ!›› ከአስደንጋጭ ቁጣ ጋር ተያይዞ የመጣው የኮማንደር ትዕዛዝ።

ባዶዋ ክፍል ከገባሁባት በኋላ በሯ ከውጭ ሲዘጋ ሙሉ በሙሉ አይንን በሚወጋ ጨለማ ተዋጠች። ከጨለማው በተጨማሪም ክፍሏ አንዳች ክፉ ሽታ አውዷታል። ‹‹ምንድር ነው የሚሸተው? እነዚህ ሰዎች እንደደርግ ዘመን ሰው እየገደሉ ይቀብራሉ እንዴ?›› በውስጤ አሰብኩ። በእርግጥ ደርግ የአፄ ሃይለሥላሴ ባለሥልጣናትን እና ‹‹ፀረ አብዮተኛ›› ያላቸውን ወጣቶች ከርቸሌ ግቢ ውስጥ ገሎ እንደቀበረና ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ አፅማቸው በቁፋሮ እንደወጣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሰማሁት ወሬ ድንገት ትዝ ብሎኛል። ሆኖም ምንም አማራጭ ስላልነበረኝ ፍራሼን አንጥፌ ጋደም አልኩ። ከግማሽ ሰአት በኋላ ሽታውንም ጨለማውንም ለመድኩት። ከውጭ የዘቦቹ ኮቴ ይሰማል-የጥበቃ ማማው ላይ ሲወጡና ሲወርዱ። የመፅሀፍ ቅዱሱ ያዕቆብ በበረሃ ተኝቶ መልአክት ሲወጡና ሲወርዱ አየበት የተባለው መሰላል ትዝ አለኝ። በዚህ አይነት ሁኔታ በግምት ለሰአታት ከቆየሁ በኋላ ቀን ፍርድ ቤት ከአንበሳ ቤት የእስር ጓደኛዬ ጋር ተካፍዬ ከበላሁት በርገር ውጭ ምንም እንዳልበላሁ ትዝ ሲለኝ ረሃብ ሞረሞረኝ። እናም በያዝኩት ፌስታል አንዳች የሚበላ ነገር እንዳለ ስለማውቅ ከተጋደምኩበት ተነስቼ ፈታተሽኩ፤ በርገር አገኘሁ። አወጣሁት፤ ሁለቴ እንደገመጥኩለት በጨለማ መብላቱ እንደአንዳች ነገር ስለቀፈፈኝ፣ የታሰርኩበትን ክፍል በር መደብደብ ጀመርኩ። ከውጭ ያለ ፖሊስ

‹‹ምን ፈለክ?›› አለ በአስገምጋሚ ድምፅ፤

‹‹በሩን ክፈትልኝ››

‹‹ለምን?››

‹‹በጨለማ ራት መብላት አልቻልኩም››

‹‹ተወውና ተኛ! አይከፈትም››

ይህን ግዜ አእምሮዬ ወደህንድ ይዞኝ ነጎደ። መፃህፉን ባላስታውሰውም አንድ ያነበብኩት ነገር ትዝ አለኝ። በሒንዱ ኃይማኖት ጀንበር ካዘቀዘቀች በኋላ ምግብ አይበላም። ይህ ከእምነቱ ትዕዛዛት አንዱ ነው። ምክንያቱ ደግሞ በጨለማ ሲበላ ነፍስ ያለው ነገር ከምግቡ ጋር ተደባልቆ ነፍስ እንዳይጠፋ ለኃይማኖታዊ ጥንቃቄ ነው። እኔ ግን እንደው ምክንያቱን ሳላውቀው በጨለማ መብላቱን ጠላሁት። እናም ፖሊሱ እንዳለው ትቼው እንደራበኝ ተኛሁ። ... የሚያነጋግሩት ሰው ሳይኖር፣ ያውም በጨለማ የተዋጠ ክፍል ውስጥ ለብቻ መሆን እንዴት ይጨንቃል?

መቼና እንዴት እንቅልፍ እንደወሰደኝ አላወኩም። ብቻ የጭለማ ቤቷ በር ተንኳኩቶ ተከፈተና ለሽንት እንድወጣ ተነገረኝ፤ በማረሚያ ቤቱ ደንብ የእስረኞች ክፍል የሚከፈተው ከጥዋቱ አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን፣ የሚዘጋው ደግሞ ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰአት ነው። የጨለማው ክፍል እስረኞች ግን ሌላው እስረኛ ከመውጣቱ አስቀድሞ ከሌሊቱ አስራአንድ ሰአት ለሽንት እንወጣለን። እኔ በዚህ ሰአት ለሽንት እንድወጣ የተፈለገው እስረኞች ከክፍላቸው ሳይወጡ ነው፤ ነገርየው ማንም እስረኛ እንዳያየኝ ለማድረግ ነው፤ ማታም ለሽንት የሚከፍቱልኝ እስረኞች በየክፍላቸው ከገቡና በር ከተዘጋ በኋላ ነው። እናም ለጥቂት ደቂቃ መፀዳጃ ቤት ተጠቅሜ፣ ፊቴንም እንደነገሩ ውሃ አስነክቼ ወደ ክፍሌ ተመለስኩ፤ በሩ ከውስጥ ወደ ውጭ ተስቦ ተዘጋ፤ ጭለማውም ተመልሶ በእኔ ላይ ነገሰ።

የሆነ ሆኖ ብዙም ሳይቆይ በአንደኛው መስኮት በኩል በምስማር በተበሳች ቀጭን ቀዳዳ ብርሃን ሲገባ አየሁ። አይኔን ወደቀዳዳዋ አስጠግቼ ወደውጭ ለማየት ሞከርኩ። ብዙም አልተሳካልኝም። ተውኩትና ክፍል ውስጥ ‹‹ወክ›› ማድረግ ጀመርኩ፤ ጥቂት ከተንቀሳቀስኩ በኋላ ጨለማው አይኔን ስለወጋኝ ፍራሼ ላይ ተጋደምኩ። ጨለማ ቤት የመታሰር ቅጣቱ በጨለማ የመከበብ ዕዳ ብቻ አይደለም። ጨለማው ከመግዘፉ የተነሳ አይንህ መስራትና አለመስራቱን ማረጋገጥ ይሳንሃል። እንዲሁ ተዳፍኖ የሚቀር፣ ሲከፈትም የማታይ እስኪመስልህ ድረስ የአይንህን ብርሃናማነት ትጠራጠራለህ። ማረጋገጫህ ምንድን ነው? ምንም! አንዲትም የብርሃን ሰበዝ ተሰርቆ በማይገባበት ልስን ጨለማ ማረጋገጫህ ምንድን ነው? በተስፋ መቁረጥ እንቅልፍ ይዞኝ ሄደ፤ ምን ያህል ሰአት እንደተኛሁ ሳላውቅ በሩ ተከፈተና አንድ ፖሊስ ከቤተሰቦቼ የተላከ የምሳ ሳህን ሰጥቶኝ በሩን መልሶ ዘግቶ ሄደ። ጥቂት ቆይቼ በሩን ደበደብኩ

‹‹ምንድን ነው?››

‹‹ሰአት ስንት ነው?››

‹‹ሃያ ጉዳይ››

‹‹ለስንት?››

‹‹ለስድስት››

ሳሃኑን ፈትቼ ለመመገብ ሞከርኩ፤ ግን አሁንም አልቻልኩም፤ ከዚህ በፊት ተሞክሮው ስላልነበረኝ በጭለማ መመገብ እንደሚከብድ አላውቅም ነበር። ጥቂት ጉርሻዎችን በውሃ አምጌ ከጎረስኩ በኋላ የበረሮ ድምፅ ስለሰማሁ ተውኩትና እስከአሁን ምን ያህል በረሮ ከምግቡ ጋር ቀላቅዬ እንደጎረስኩ ማሰብ ጀመርኩ። ከአሳቤ ሳልላቀቀ እንቅልፍ አሸነፈኝ። ስነቃ በጣም ብዙ ሰአት እንደተኛሁ እርግጠኛ ስለሆንኩ አሁንም በሩን ከውስጥ ወደውጭ ደበደብኩ

‹‹ምን ፈለክ?›› አለኝ የቅድሙ ድምፅ።

‹‹ሰአት ስንት ነው?››

‹‹ጤና የለህም! አሁን ጠይቀህኝ ነግሬ የለህ እንዴ?››

‹‹አሁን አይደለም የጠየኩህ። ለስድስት ሃያ ጉዳይ ላይ ነው››

‹‹ታዲያ አሁን ስድስት ተኩል እኮ ነው››

‹‹ይቅርታ እንቅልፍ ወስዶኝ ስለነበር ብዙ ሰአት የተኛሁ መስሎኝ ነው››

መልስ የለም፤ ለራሴ ፈገግ አልኩ። ለካስ ሀምሳ ደቂቃ ተኝቼ ነው እንዲህ ብዙ ጊዜ ያለፈ የመሰለኝ። ... የሚነበብ ነገር አልያዝኩም፤ ብቸኝነቱ ደግሞ ሊውጠኝ ደርሷል፤ ክስ ቻርጄን አነሳሁና ሚስማር ወደበሳት ቀዳዳ አስጠግቼ አንድ አንድ ፊደል ላይ እያነጣጠርኩ ማንበብ ጀመርኩ፤ በዚህ አይነት መልኩ አንድ አራቴ ደጋግሜ ካነበብኩ በኋላ ግን ጨለማው ብዥ አለብኝና ምንም ነገር ማየት ተሳነኝ። በጣም ደነገጥኩ፤ እንደምንም በዳበሳ ፍራሼ ላይ ሄጄ ተኛሁ። ያ የአይኔ ብርሃን ጥርጣሬ መልሶ ተቆጣጠረኝ። ሥጋት! አይን ያለ ቅንጣት ብርሃን ተራ ብልቃጥ መሆኑን ተረዳሁ። ከተጋደምኩበት ተነሳሁ። መልሼ ተኛሁ። በዚህ አይነት ድግግሞሽ ቀኑ መሸና ለሽንት ተከፈተልኝ። ተመስገን! አይኔ ብርሃን ተቀብሎ የሚያስተናግድ ህልው መሆኑን አረጋገጥኩ። ከሽንት ቤት መልስ ደግሞ መልሶ ተዘጋብኝ። ሌሊቱም እንዲሁ ስቆም፣ ስተኛ አለፈ። እናም ወፍ ጭጭ ሳይል ለሽንት ተከፈተልኝ። ወጣሁ፤ ተመልሼ ገባሁ።ይህን ጊዜ የዝነኛው አሽሙረኛ አቤ ቶኪቻው ‹‹ከምገባ ወጣሁ›› ፅሁፍ ውልብ አለብኝና ድንገት ደርሶ ፈገግ አሰኘኝ። የጨለማ ፈገግታ...

ዛሬ እለቱ ቅዳሜ ነው። በተለምዶ እስረኞች በወዳጅ ዘመድ በብዛት የሚጠየቁበት ቀን፤ የእስረኞች ሳምንታዊ ‹‹አውደአመት››፤ በጉጉት የሚጠበቅ ዕለት። በግምት ወደ ሶስት ሰዓት ላይ የእስር ቤቱ የበር ቁልፍ ጥቂት ተንኳኩቶ ወለል አለ። ግራ ገባኝ። ስንቅ የሚመጣበት ሰዓት አልደረሰም። ለምንድር ነው የተከፈተው? ስል አሰብኩ። አንድ የፖሊስ ኃላፊ በፍራሼ ላይ እንደተንጋለልኩ ጥቂት ካስተዋለኝ በኋላ ‹‹ዕቃህን ይዘህ ውጣ›› አለኝ። ‹‹ወዴት ነው የምወጣው?›› ስል ጠየኩት። ‹‹ዝም ብለህ ያዝና ተከተለኝ››... ዝም ብዬ ወዴት ነው የምከተለው? እነዚህ ሰዎች ምን ሊያደርጉኝ ነው? ቀይ ሽብር ሊያፋፍሙብኝ? ወይስ... የተለያዩ ሀሳቦች በውስጤ ተመላለሱ።

ይቀጥላል።

## የኦሮሞ.... *(ከገፅ 33 የዞረ)*

አስገርሟል። ከሃገሪቷ አጠቃላይ ህዝብ 35 በመቶ ከመሆናቸው ባለፈ ምድራቸው እጅግ በጣም ሰፊና ሀብታም ሆኖ ሳለ፤ ዛሬ ለኦሮሞ ህዝብ ዝቅ ያለ ግምት እየተሰጠው ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው ለምንድን ነው? የጥያቄው መልስ ያለው ኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ነው። ኦሮሞ ሙሉ የዴሞክራሲ መብቱን የሚጠይቅበት ጊዜ ቅርብ ነው። ኦሮሞንና የደቡብ ህዝቦችን ማጥቃትና መናቅ በምንም ዓይነት መንገድ ፍትሀዊ አይሆንም። የሚመጣው የኦሮሞ ትውልድ እንደዛሬው ትውልድ ዓይናፋርና ዝምተኛ አይሆንም።

ፓርላማ ውስጥ እኔና ጓደኞቼ ለምንድን ነው ኦሮሞ የሚጠመደው? ለምንድን ነው ኦሮሞ እንደ ጠላትት የሚታየው? ብለን ስንጠይቅ መልስ አላገኘንም። ነገር ግን በሽብርተኝነት ህጉ መሠረት ኦነግን ትደግፋላችሁ በማለት በፍፁም ከኦነግ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ሰዎች በብዛት ታስረው ዛሬ እስር ቤት ውስጥ ይማቅቃሉ። ፍርድ ቤት የእነኚህን ሰዎች ጥፋት በጥልቀት ቢመረምር አንድም የሚያስከስስ ስራ አልሰሩም። አንዳንዶቹ የፖለቲካ ነፃነት ያለ መስሏቸው ህዝብን ለማደራጀት እንዲሁም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትምህርት ለመስጠት ሲሞክሩ ያለአንዳች ጥያቄ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወስደው ብዙ ቀናት ከማቀቁ በኋላ ፍርድ ቤት ይቀርቡና ለረጅም ጊዜ እስር ቤት እንዲቆዩ ይደረጋል። በቀለ ገርባ የሚባል የኦፌዴን ም/ፕሬዝዳንት እነሆ ያለአንዳች ጥፋት ዛሬ ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ይማቅቃል። የተያዘው ስለ ሰብዓዊ መብት ኢትዮጵያን ሲጎበኙ የነበሩ ፈረንጆች ስለአነጋገሩት ነው። በሕገ መንግሥቱ የተፃፈው ታምኖበት ነው ወይንስ አንዳንድ ገር ሰዎችን ለማታለል ነው። ዜጋ የሚያዝበት ሁኔታ፣ ተይዞ ፖሊስ ጣቢያ የሚቆይበት ጊዜ፣ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት ጊዜ፣ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በቀጠሮ የሚያቆይበት ጊዜ ሁሉ በሕገ መንግሥትና በሲቪልና ክሪሚናል ፕሮሲጀር ኮድ ተጽፏል። እነኚህ ሕጎች ሁሉ በየቀኑ እየተጣሉ ነው፤ በትንሹ ሳይሆን በብዛት ነው። ይህን ሁሉ አቶ መለስ ከዕረፍታቸው በፊት ያውቁ ነበር። እኔ ራሴ ከእኔ ቢሮ ስለሚሞቱት ሰዎች፣ ስለሚያዙ ሰዎች፣ ስለሚታሰሩ ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ ለክልሉ ፕሬዚዳንት እና ለጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ጽፌአለሁ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዛሬም በእሳቸው ቦታ የተተኩ ሰዎች በኦሮሞ ላይ የሚደርሰውን ግፍ ያውቃሉ። ነገር ግን የሕዝብ መብት እንዳይደፈር አንድ ወገን ለይቶ ማጥቃት ተገቢ አለመሆኑን የወጣ አዲስ ትዕዛዝ አላየንም። ለወደፊትም ላናይ ነው?

### ማስታወሻ

ከዚህ አጭር ጽሁፍ ጋር አያይዤ ለአንባቢያን የማሳስበው ነገር አለ። አንዳንድ ወዳጆቼ አንድ ጥያቄ ሁልጊዜ ይጠይቁኛል። “ለምን ሁልጊዜ ስለ ኦሮሞ ብቻ ትጽፋለህ?” መልሶቼ ባያጠግቡም ሁልጊዜ ተመሳሳይ ናቸው። “እኔ ደህና አድርጌ የማውቀው ስለ ኦሮሞዎች ስለሆነ ነው። የኢህአዴግ መንግስትም ኦሮሞን ለይቶ ስለሚያጠቃ ነው። ሌላውንም ህዝብ አጥቅቷል። ለምሳሌ ሲዳማና ጋምቤላ በጣም ተመቷል። ስለነሱ በዝርዝር የሚያውቁት መጻፍ ይገባቸዋል። እኔ ስለ ኦሮሞ ስጽፍ ኦሮሞ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም በማለት አይደለም። ነገር ግን ህግና ሥርዓት ባለበት ሀገር ማንም ቡድን፣ ብሔር ወይም ሌላ ስብስብ መጠቃት የለበትም። ፌደራሊዝም ስራ ላይ እንዲውል እንደዚህ አይነቱን የተዛባ አመለካከት እና አያያዝ ለመከላከል ነበር። እኔ ለኦሮሞ የምፅፍበት ሌላ ምክንያት የለኝም። ግን ሌላም የኢትዮጵያ ጉዳይ ደጋግሜ እጽፋለሁ።

## ደቡብ....

(ከገፅ 9 የዞረ)

አለመግባባቶች የሚያስከትሏቸው የሰው ህይወት መጥፋት ለግጭቶች መባባስ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ደቡብ ሱዳን ከዚህ ቀደም ለእንደዚህ አይነት ድንበር ዘለል አለመግባባቶች ትሰጠው የነበረው ትኩረት አናሳ ከመሆኑም በተጨማሪ ራሳቸውን ከሰሜኑ የሱዳን ክፍል ለመገንጠል ያደረጉ የነበረው መራራ ትግል ደቡብ ሱዳንን በድንበር አካባቢ ለሚነሱ አለመግባባቶች ዋጋ እንዳትሰጥ አድርጓታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ በታሪክ ደቡብ ሱዳን ነፃ አገር እንድትሆን ያደረገችውን አስተዋፅኦ ከግምት ስናስገባ ለግጭቶቹ ትኩረት ሰጥቶ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ለመነታረክ የሚደረግ ማንኛቹም ሙከራዎች ከጥቅማቸው ይልቅ የሚያስከትሏቸው ኪሳራዎች መብዛታቸው ሌላኛው ለኢትዮጵያ የጠቀመ የማሰሪያ ፖለቲካ ካርድ ነበር፡፡

ጥያቄው ይሄ የፖለቲካ ካርታ እስከመቼ ያጫውታል? የሚለው ነው፡፡ ደቡብ ሱዳን ከዛሬ ነገ እየጠነከረች ስትመጣ ለዜጎቿ የምትሰጠውም ትኩረት የዛኑ ያህል እየጨመረ መምጣቱ አይቀርም፡፡ ‹‹በፖለቲካ ዘላቂ ወዳጅም ይሁን ዘላቂ ጠላት የለም›› የሚለው መርህ ተግባራዊ መሆን ሲጀመር፤ አልፎም ‹‹አገራት በአለም አቀፍ መድረክ በማንኛውም የሉዓላዊነት መስፈርት እኩል ናቸው›› የሚለው መርህ በተግባር ሲተረጎም ደቡብ ሱዳን ለዜጎቿ ጥበቃ እና ከለላ ለማድረግ በሚል ከአገራችን ጋር የተካረረ ግጭት ውስጥ ልትገባ የምትችልባቸው አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ፡፡

በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን ድንበር በዘላቂነት ከተለያዩ ድንበር ዘለል አደጋዎች ለመጠበቅ ሊወሰዱ የሚገባቸው ቅድመ ጥንቃቄዎች መኖር እንደሚገባቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ለዚህም ቀላል እና አፋጣኝ ወቅታዊ እርምጃዎች ሊሰጥባቸው የሚገቡ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡ የማዕከላዊውም ይሁን የክልሉ መንግስት አስቀድሞ በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን የድንበር ወሰን ጥርት ባለና ሁለቱንም ሊያግባባ በሚችል መልኩ ከደቡብ ሱዳን ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ መግባት ቀዳሚው ሲሆን (በሁለቱ አገራት መካከል ድንበርን በሚመለከት ያሉትን አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦች ለመረዳት ዶ/ር ወንደሰን ተሾመ የፃፉትን ‹‹colonial Boundaries of Africa the case of Ethiopia's Boundry with suda›› የሚለው ፅሁፍ መመልከት በቂ ነው፡፡)፤ በሁለቱ አገራት አዋሳኝ ድንበር ላይ ባሉ ዜጐች መካከል የሚነሱትን አለመግባባቶች በባህላዊው የግጭት አፈታት መንገድ እልባት እንዲሰጣቸውና በቀጣይም ለግጭት የሚጋብዙ ምክንያቶችን ከምንጩ ለማድረቅ መስራት ይጋባል፡፡

በተጨማሪም በድንበሮች አካባቢ የሚኖሩ የሁለቱ አገራት ዜጎችን ኢኮኖሚ ከአርብቶ አደር ወደ ተረጋጋና የተሻለ ወደሚባለው የግብርና መር ኢኮኖሚ እንዲሻገሩ በማድረግ ግጦሽ መሬትን ፍለጋ በሚል ሰበብ ይከሰቱ የነበሩትን እንቅስቃሴዎች መግታት ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም እንደከዚህ ቀደሙ ሳይሆን የጋምቤላን ክልል በሚመለከት አዲስና የተለየ የፖሊሲ አቅጣጫ ትግበራ ማድረግ ይገባዋል፡፡ አለበለዚያ አዲሲቱ አገር ደቡብ ሱዳን ከበረከት ይልቅ ለቀንዱ አካባቢ ተጨማሪ መርገምት መሆኗ አይቀርም፡፡

### "Irredentism"

ደቡብ ሱዳን በተጠናከረ መልኩ ወደ ቀጠናው እጇን እያሳረፈች ስትመጣ በቀጣይ ስጋት ልትሆን ትችላለች ብዬ ከማስብባቸው ምክንያቶች መካከል ከዚህ በፊት የገጠመን የሱማሌያ ተሞክሮ ሌላው ነው፡፡ ሱማሊያውያን ለረጅም አመታት በኢትዮጵያ ከተፈራረቁ ወሪዎች ጋር ደም አፋሳሽ ጦርነቶችን አድርገዋል፡፡ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ከፍተኛ የታጠቀ ኃይል መኖሩ ዙሪያ ገባው አገራችን ክፍል ለተለያዩ ጥቃቶች እንድትጋለጥ አድርጓታል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በአገራችን ላይ ከሶማሊያ መንግስት የተቃጡብን ጦርነቶች ምክንያታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ሶማሊያዊያኑ የግዛት ይገባኛል ጥያቄን በማንሳት በአገራችን ላይ ጦረነቶችን አውጀዋል፡፡ የግጭቶች መነሻ በኢትዮጵያ ስር ተጠልለው የሚገኙትን ሶማሌዎች የሚኖሩበትን አካባቢ (ኦጋዴን) በኢትዮጵያ መንግስት በጉልበት ተነጥቀናል የሚል ታሪካዊ ጥያቄን በማንሳት ነው፡፡ እነዚህ ኃይሎች ይህንን ጥያቄ መነሻ ምክንያት በማድረግ ‹‹ህዝባችን እና መሬታችንን እስካልተመለሰልን ድረስ ትግላችንን እንቀጥላለን›› የሚል ወጥ የሆነ አቋም ያራምዳሉ፡፡ ይህ ተደጋጋሚ ጥያቄ ለሶማሌያውያኑ የአንድ ወቅትና የአንድ ትውልድ ብቻም ሳይሆን የዘመናትም እስከመሆን ደርሷል፡፡ ይሄ በሶማሌያውያኑ የተሰነዘረው የመሬት ይገባኛል ጥያቄ (Irredentism) በቀጣይም ከደቡብ ሱዳን ሊቃጣ እንደሚችል መጠርጠር ተገቢ ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ በደቡብ ሱዳንም ዘንድ ሊያስነሳ የሚችል ተመሳሳይ አይነት ተሞክሮ በጋምቤላና መኖሩን ማየት እንችላለን፡፡

አብዛኞቹ በጋምቤላ አካባቢ የሚኖሩ ብሔሮች በአንድም ይሁን በሌላ ከደቡብ ሱዳን ጋር የሚያመሳስሏቸው የተለያዩ ነገሮች አሉ፡፡ በተለይ በህዝብ ለህዝቡ ግንኙነት ዙሪያ ኑዌሮች እና አኙዋኮች ቤተሰቦቻቸውን ደቡብ ሱዳን አስቀምጠው የመጡ ናቸው፡፡ ረጅም አመት ያስቆጠረው የሱዳን እርስ በርስ ጦርነት ለብዙ የደቡብ ሱዳን ነዋሪዎች ከቀያቸው መፈናቀልና በጋምቤላ ቋሚ ኑሮ ለመጀመር አይነተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የደርግ መንግስት ለደቡብ ሱዳን ይሰጥ በነበረው ቀጥተኛ ወታደራዊ እርዳታ ምክንያት ከጋምቤላ ተቆርሶ በተሰጠው መሬት ላይ ደቡብ ሱዳናውያኑ ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያ ከፍተው ይጠቀሙ እንደነበር ይታወቃል፡፡

እነዚህ ምክንያች በቀጣይ ምን መዘዝ ይዘው ሊመጡ ይችላሉ? የሚለውን ማየት ተገቢ ነው፡፡የደቡብ ሱዳን መንግስት ይነስም ይብዛም ጋምቤላ ውስጥ ባሉ ብሔሮች መካከል ይፈጠሩ በነበሩ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ውስጥ እጁ እንዳለበት የተለያዩ ፀሐፊያን ይስማማሉ፡፡ በተለይ በኑዌሮች እና አኙዋኮች መካከል ሲነሱ ከነበሩ ግጭቶች ጀርባ የደቡብ ሱዳን ጦር ኑዌሮችን በመርዳት ግጭቱን ያባብስ እንደነበር እነዚሁ ፀሐፊያን ያትታሉ፡፡ በቀጣይም የኢትዮጵያ መንግስት በአካባቢው ላይ በሚወስዳቸው ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ እርምጃዎች ዙሪያ የደቡብ ሱዳን መንግሥት አንዳንድ አፀፋዊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ጆን ያንግ "Armed groups along sudan's Eastern frontiees: An over view and analysis" በሚለው ፅሁፋቸው ሁለቱን አገራት በሚያዋስነው ድንበር አካባቢ ለሚኖሩ ዜጐች አንዳንድ ማስተካከያዎች እስካልተደረጉ ድረስ ግጭቶቹ ተባብሰው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡ በተለይ በጋምቤላ አካባቢ ያሉ ዜጐች ወደ ድንበር የተጠጉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከማዕከላዊ አስተዳደሩ እና ማህበረሰቡ ጋር ያላቸው ቁርኝት የላላ ነው፡፡ ከዚህ ውጭም በተለያዩ አጋጣሚዎች በክልሉ የተቀሰቀሱ ግጭቶችን ተከትሎ የተወሰዱባቸው እርምጃዎች ፊታቸውን ከማዕከላዊው አስተዳደር እንዲያርቁ አስገድዷቸዋል፡፡ ይህንና ሌሎች መሰል አጋጣሚዎች በጋምቤላ አካባቢ መከሰታቸው ደቡብ ሱዳን በቀጣይ በአገሪቷ ላይ ያላትን ተፅዕኖ ለማስፋት ልትጠቀምበት እንደምትችል መገመት ይቻላል፡፡ ከነዚህ ተጠባቂ ስጋቶች መካከል አንደኛው እንደ ሶማሊያ ሁሉ የግዛት ይገባኛል ጥያቄ የማንሳቷ ሁነት ነው፡፡ አብዛኛው የጋምቤላ ነዋሪ በደቡብ ሱዳን ውስጥ ከሚኖሩ ዜጎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ያለው ከመሆኑ አንፃር የደቡብ ሱዳን መንግስት በቀጣይ የጋምቤላን መሬት ከራሳቸው ጋር ይቀላቀል ዘንድ ሴራ ሊሸርብ ይችላል፡፡ ለዚህም ሲል በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ህዝቦች መካከል ‹‹የተገፋው ማህበረሰብ›› በመንግስት ላይ እንዲያምፅ የማድረግ እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገባ ይችላል የሚለው ቀዳሚው ሲሆን፤ ሌላኛው ስጋት የኢትዮጵያ መንግስት እንደከዚህ ቀደሙ በአኙዋኮች ላይ ወታደራዊ እርምጃ የሚወስድ ከሆነ ደቡብ ሱዳን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖሩ ዜጐች ላይ የተቃጣውን ጥቃት ለመከላከል በሚል ድንበር ዘለል ድጋፍና ከለላ ልታደርግ ትችላለች የሚለው ስጋት ነው፡፡ይሄ ክስተትም ቀጣናውን ወዳልተፈለገ ብጥብጥ ይዞት ጭልጥ እንዲል ያደርገዋል፡፡

አዲሲቷን ደቡብ ሱዳን የምንመለከትበት የተለየ መነፅር ያስፈልገናል፡፡ ከመርገምቱ ይልቅ በረከቱን እንድንቋደስ የአገራችን መንግስት ብልጠት የተሞላበት ፖሊሲ ሊቀርፅ ይገባዋል፡፡

ኢትዮ-ምኅዳር


- በፖለቲካዊ ጉዳዮች
- በማህበረሰባዊ እውነታዎች
- በምጣኔ ሀብት
- በባሕልና ኪነጥበባት
- በፍትሕ እና ርትዕ
- በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች

እና ሌሎች ነጥቦች ላይ የምታተኩር የእናንተ ጋዜጣ- ኢትዮ-ምኅዳር!

በቅርብ ቀን ይጠብቋት!!!

# የኦሮሞ ፖለቲካ ጉዳይ

## (ከትናንት እስከ ዛሬ)



ቡልቻ ደመቅሣ

የኦሮሞ የፖለቲካ ጉዳይ በየዘመኑ አንድ እርምጃ ወደፊት ሁለት እርምጃ ወደኋላ ሲመሏ ለዘመናት ቆይቷል። ይህ የሆነው ከአፄ ሚኒሊክ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚያ በፊት፣ የኢትዮጵያ ነገስታት ኦሮሞን ለማሸነፍ ስላልቻሉ በየጊዜው እየተጋጩ እንደምንም አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ፋዘር አልሜዳ የሚባለው የፖርቱጋል ቄስ በዚህ ጉዳይ በሰፊው ጽፏል። ነገር ግን አብሮነታቸው እንደ ገዥና ተገዥ አልነበረም። ከአጼ ልብነድንግል ጀምረው እስከ ንጉስ ሳህለ ስላሤ የነበሩት አፄዎች ሁሉ ኦሮሞን ለማሸነፍ እና ለመግዛት ያላደሩጉት ጥረት አልነበረም።

ኦሮሞንና ሀገሩን አሸንፈው ለማስገበር የቻሉት አፄ ሚኒሊክ ብቻ ነበሩ፡፡ እሳቸውም ኦሮሞን ለማሸነፍ የቻሉት ከኦሮሞዎች ቀደም ብለው ከፈረንጆች የጦር መሳሪያ ስላገኙ ነበር። መሣሪያ ያገኙበትም ምክንያት ከእሳቸው ቀድሞ የነበሩት አንዳንድ አፄዎች ለአውሮፓ መንግስታት “ኢትዮጵያ ብቻዋን ክርስቲያን ሆና በአፍሪካ ውስጥ የምትኖር ሀገር ነች” ብለው የአውሮፓውያን መንግሥታትን ስለለመኑና ስላስረዱ የጦር መሣሪያ ማግኘት ቻሉ። በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አፄ ሚኒሊክ ሸዋን በሙሉ ለመቆጣጠር ሲነቃነቁ ደብረብርሃን አጠገብ በምትገኘው አብደላ በምትባል መንደር ውስጥ ከጎበና ዳጮ ጋር ተገናኙ። ጎበና ዳጬም በዚያን ጊዜ በኦሮሞ ገዳ ሥርዓት የሉባና የነበዙ አባ ደክር ወዳጅ የነበሩ። ከአፄ ሚኒሊክ ለጎበና ዳጬ አንድ ነገር ተናገሩ። “ወደታች ወደደቡብ እንሂድ። ወደአቢቹ፣ ገላን፣ ጉለሌ፣ አርሲ አብረን እንዝመት። አንተ የጋላ ንጉስ ትሆናለህ፣ እኔ የኢትዮጵያ ንጉስ እሆናለሁ ተከተለኝ” አሏቸው፡፡ እንደተባባሉትም ወደታች ወደደቡብ መጥተው የኦሮሞን ጎሣዎች መውጋት ጀምሩ። ጎበናም ራስ ተባሉ። ነገር ግን አፄ ሚኒሊክ ለጎበና የገቡትን ቃል ሳይጠብቁ ቀሩ። ጎበናም ብዙ ጊዜ ከተዋጉ በኋላ እየተዳከሙ ሄዱ። ነገር ግን የሸዋን፣ የወለጋን (በሰላም የገቡ) እና የከፋን (ከፋም በሰላም ገባ) ኦሮሞዎች ካሸነፉ በኋላ አፄ ሚኒሊክ እራሳቸው ጦርነቱን መምራት ጀመሩ። ራስ ጎበና በቀየሱት መንገድ ሄደው ሌሎች ያልተያዙትን ሀገሮች ያዙ። ለምሳሌ ሀረርን፣ ውጋዴንን፣ ሱማሌን፣ ቦረናን ያቀኑት ከዚያ በኋላ ነው። (እኔ አቀኑ እላለሁ አንዳንድ ሰዎች ግን “ኮሎናይዝ” አደረጉ ነው የሚሉት። እውነቱን ለታሪክ ተንታኞች እንተዋለን፡፡) ይህ ታሪክ አፈታሪክ ነው። የታሪክ ምሁራን እንደሚሉት አፈታሪክ የተፃፈ ታሪክ ያህል ዋጋ አለው። አሁን ልክ አይደለም ብሎ መከራከር ዋጋ ቢስ ይሆናል። ምክንያቱም ኦሮሞዎች ሁሉ ይህን ያምናሉ። ያም ሆነ ይህ የታሪኩን እርግጠኛነት የሚያረጋግጠው የራስ ጎበና ሕመም ነው። (በብስጭት እንደሆነ በእርግጠኝነት የሚናገሩ የእሳቸው ተወላጆች አሉ።)

እኔ እንደብዙ ወገኖቼ ጎበናን አላብጠለጥልም ሰው ስራ መስራት አለበት። ቤተሰቡን የሚደግፈው የሰራ እንደሆነ ነው። አለስራ መኖር አይቻልም። ስለዚህ ራስ ጎበና ስራ አግኝተው ቢሰሩም የፈለጉት ሳይሆን ቀርቶ ታመው ሞቱ። ይሄ ማንኛቸውም መሪ የሚያረገው ነገር ነው። አንዳንዱ አላደርግም ብሎ ይሞታል። ግን ብዙ ሰው ሞትን አይመርጥም። አፄ ሚኒሊክ ጎበናንም ባያገኙ ማሸነፋቸው አይቀሬ ነበር። ምክንያቱም በዚህ ጊዜ ከአውሮፓውያን ብዙ የጦር መሣሪያ አግኝተዋል።

ራስ ጎበና ከሚኒሊክ ጋር ያደረጉት ስምምነት ለጊዜው ለኦሮሞ አንድ እርምጃ ወደፊት የሚሄድ መስሎ ነበር። ከዚያም በኋላ አፄ ሚኒሊክ ኦሮሞን የገዙበት የባሪያ አገዛዝ ሁለት እርምጃ ወደኋላ እንዲሄዱ አደረጋቸው። ኦሮሞ ደርግ ላይ ምንም ተስፋ ስላልነበረው የጀነራል ተፈሪ ባንቴ ፕሬዝዳንት መሆን ምንም አልመሰለውም። ዶክተር ነጋሶ ፕሬዝዳንት ሲሆኑ ለኦሮሞ የተሻለ መስሎ አልታየውም። ዶክተር ነጋሶም እራሳቸው በስርዓቱ ባለማመን ረግጠው ወጡ።

ከዚያ በኋላ የአፄ ሚኒሊክን የጦር ኃይል መመከት ያልቻለው ኦሮሞ፣ ገባርነትን ለመቀበል ተገደደ። ሆኖም ግን አፄ ሚኒሊክ ከዚያ በፊት ኦሮሞ ይዞት የነበረውን መሬት ማስለቀቅ ስላልቻሉ ኦሮሞ በአፄ ልብነድንግል ጊዜ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይዞት የነበረውን መሬት እንደያዘ ቀረ። እዚህ ላይ እናስታውስ። የወሎ አሮሞና ትግራይ ውስጥ ያሉት ራያና አዘቦ ኦሮምኛ ቋንቋቸውን እየረሱ አማርኛ ወይም ትግሪኛ መናገር ጀምረዋል። በአማራ ክልል ውስጥ ያለው ኦሮሞ ዞን ከተፈጠረለት ለምን የራያና አዘቦ ዞን በትግራይ ውስጥ አልተፈጠረም። ይኼ የሚያሳየው ሕገ መንግስቱ በተፃፈበት ጊዜ (በ1986 ዓ.ም) ህወሓት የነበረውን ፍጹም የበላይነት ነው።

ዛሬ የኦሮሞ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያንስ 35 በመቶ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። ሕዝቡም ወደ ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን ይገመታል። የኦሮሞ መሬት ስፋቱ 387,000 ኪሎ ሜትር ይሆናል። ማለትም ጀርመንን ያክላል ማለት ነው፡፡

ኢህአዴግ በ1983 ዓ.ም. አዲስ አበባ በገባ ጊዜ ኦነግ አብሮት ስለነበረ ኦሮሞ አንድ እርምጃ ወደፊት እንደሄደ ሊገመት ይችላል። ምክንያቱም ኦነግ አስራ ስድስት አመት ከታገለ በኋላ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋር አብሮ ሲመለስ አንድ የፀና ስምምነት ተፈራርሞ የመጣ መስሎ ለኦሮሞዎች ታየ። ስለዚህ ኦሮሞዎች ለጊዜውም ቢሆን ተረጋጉ። ነገር ግን ሳይቆይ ኦነግ ወደ ትግል ተመለሰ። በአገር ውስጥ ያሉ ኦሮሞዎች ኦነግ ፌደራሊዝምን የተቀበለ - መስሎአቸው ስለነበር ካገር በመውጣቱ አዘኑ፡፡ ከዚህ ይልቅ በሀገር ውስጥ ሆኖ ስለሰብዓዊ መብት፣ ስለእኩልነትና፣ ስለዲሞክራሲ መታገል ነበረበት ብዬ አስባለሁ።

ኦነግ ተመልሶ ከአገር ሲወጣ “ኢህአዴግ ውስጥ ገብቼ አባል አልሆንም” የሚለውን ኦሮሞ ሁሉ ‹‹የኦነግ አባል ነህ›› እያሉ በጅምላ ማሰር፣ አንዳንዱን መግደል፣ የእለት ተዕለት ትእይንት ሆነ። በዚች አጭር ጽሑፍ ውስጥ የሞቱትን፣ የታሰሩትን መቁጠር አይቻልም። ነገር ግን እኔ የኦፌዴን መሪ በነበርኩበት ጊዜ ከትልልቆቹ ስራዎቼ መካከል ዋናው ስለኦሮሞ መሞት፣ መታሰር እና መሰቃየት ለኦሮሚያና ለፌዴራል መንግስታቱ እድፍ ነበር። እንዲያውም አንድ ጊዜ ለማስመሰል የፌዴራል መንግስቱ፣ ኦፌዴንና ኦህዴድ የጋራ ኮሚቴ አቋቁመው ስለነኚህ ችግሮች ያጥኑና የጥናታቸውን ውጤት ያቅርቡ ተብሎ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር፡፡ መጀመሪያውኑ ከልብ ስላልሆነ ኮሚቴው ቶሎ ፈረሰ።

ኦሮሞ የገዳን ሥርዓት ለመተው የተገደደው በመንግስት እና በዘመኑ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለውጦች ምክንያት ነው። የገዳ ሥርዓት እንዳለ ሥራ ላይ መዋል በአሁኑ ዘመን አይቻልም። ምክንያቱም በአሁኑ ዘመን ወጣቶች ሁሉ በተወለዱበት ሥፍራ አይቆዩም። ለስራና ለትምህርት ከተወለዱበት ወጥተው ወደሌላ ስፍራ ይሄዳሉ። አንዱ ትውልድ ሌላውን ትውልድ በሙሉ ካልተካ የገዳ ሥርዓት አይሰራም።

ብዙ የኦሮሞ ምሁራን የገዳን ሥርዓት የሚወዱበት ምክንያት ሥልጣን ላይ ያለው ትውልድ አዲሱ ትውልድ ለስራ ሲዘጋጅ ቦታውን ለቆ መሄዱ ለዲሞክራሲ ጥሩ አስተዋጽኦ ያደርጋል በማለት ነው። ለሁሉም በአሁኑ ጊዜ ማንም በተወለደበት ቦታ ለብዙ ጊዜ ቀጥሎ ስለማይኖር የገዳ ሥርዓት ሃሳቡ ሲፀነስ በሰራበት መልኩ አሁን ሊሰራ አይችልም።

የኦሮሞ ጥንታዊ ሀይማኖት ዋቄፈታ ሲሆን፤ ይኼም ብዙ ሰዎች እንደሚሉት ወይም እንደሚመስላቸው ለፍጥረት መስገድ አይደለም። ወንዝ አጠገብ፣ ታላቅ ተራራ አጠገብ፣ ታላቅ ዛፍ ስር ዋቄፈታ ማድረግ እንደዚህ አይነት ታላቅ ፍጥረትን ለፈጠረው አምላክ መስገድ ነው፡፡ አማኞቹ እንደሚሉትም እግዚአብሔር ራሱን የሚገልፀው በታላላቅ ፍጥረቶች በኩል ነው፡፡ እዚህ ላይ ስለዋቄፈታ ያነሳሁት ባለፈው አስር ቀን ውስጥ ኦሮሞዎች ቢሾፍቱ ሀይቅ አጠገብ የተለመደውን ኢሬቻ ለማድረግ የተሰበሰበውን ህዝብ (ሶስት ሚሊየን ህዝብ ነበር ተብሏል) ፖሊስ በሀይል በህዝቡ መሃከል ለብሶ የለበሳችሁት ልብስ የኦነግ ባንዲራ ነው በማለት በመደብደብ፣ በመርገጥ እና ልብሳቸውን በማስወለቅ ጭምር ከባድ ጉዳት አደረሰባቸው። ይሄ አድራጎት በኦሮሞዎች ዘንድ እንደ ታላቅ ሀጢያት እና እግዚአብሔርን እንደ መዳፈር መስሎ ታየ። ይህ ሥርዓት በጠባዩ ለእነርሱ ሀይማኖታዊ ነው።

የህዝብን ድምፅ የሚሻ፣ ሰላምን የሚፈልግ እና ትብብርን ከህዝብ የሚጠብቅ መንግስት እንዲህ አይነት ፀረ-ባህልና ፀረ-ህዝብ ወንጀል አይፈፅምም። ለጊዜው ለዚህ አድራጎት የምናየው ምላሽ ላይኖር ይችላል። ነገር ግን ኦሮሞ ይሄንን አድራጎት ይረሳል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ማንም ህዝብ ይህ ቢደርስበት ዝም የሚል አይመስለኝም። የፌደራሊዝም ፅንሰ-ሀሳብ የተዋወቀው ይህን መሰሉን በደል ለማስቀረት ነበር።


ይህ ሁኔታ በፌዴራሊዝም ስርዓት የሚያምኑትን የኦሮሞ ምሁራን አቋም የሚፈታተን ነው። ምክንያቱም ኦሮሞ ከሌላው ህዝብ ሁሉ ተለይቶ እንደባእድና ጠላት እየታየ መኖር ቢመረውም ከቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር ተስማምቶ በፍቅር መኖር ይፈልጋል።

የኦሮሞ ጥንታዊ ሃይማኖት ዋቄፈታ ነበር። አሁንም በዋቄፈታ የሚያምኑ ኦሮሞዎች ቁጥራቸው በጣም ብዙ ነው። ዋቄፈታ ከክርስትናም ሆነ ከእስልምና የተለየ የኦሮሞ የጥንት እምነት ነው። እነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ቢኖሩም ብዙዎቻችን የኢትዮጵያ አካል ሆነን በፌዴራሊዝም ሥርዓት እንኖራለን ብለን በቆራጥነት ተነስተናል፡፡ እንዲህ የሚለው ወገን ግን ዛሬ ድምፁ እየተዳከመ ሄዷል። ህዝብ መናቅ እንደ ቀላል ነገር ሆኖ እየታየ ነው። ቢሾፍቱ ላይ ለኢሬቻ የመጡትን አማኞች የኦነግን ባንዲራ ለብሳችኋል በማለት ደብድበው ልብሳቸውን የነጠቋቸው ሰዎች ራቁታቸውን ከስፍራው ሲወጡ ታይተዋል።

የኢሬቻን በዓል መንግስት ለምን እንደፈራው አይታወቅም። ከዚህ በፊት ለዘመናት በየዓመቱ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ አሁን የመንግስት የፀጥታ ሰራተኞች አንድ ቡድን ያደመው ወይም ያዘጋጀው ተንኮል ኖሮ የደረሱበት ነገር ኖሮ ይሆን? አናውቅም። ጨርሶ ኢሬቻን ለማጉላት አይመስለኝም።

ሌላ የኦሮሞ ቅሬታ አለ፡፡ ከአቶ መለስ ሞት በኋላ የመንግስት ብወዛ ተደርጎ ነበር። ለጊዜውም ቢሆን የመንግስትን አቅጣጫና ፕላን የሚያመላክቱ ብወዛዎች ተፈፅመዋል፡፡ እዚህ ውስጥ ኦሮሞዎች ምንም ሚና አለመጫወታቸው ብዙ ሰዎችን

ወደ ገፅ 31 ዞሯል



በሚካኤል ዲኖ /ቦምቦሊኖ/

# ቂሳርና ሴራ

በአሜሪካው የቡድን ስምንት ስብሰባ ላይ ‹‹ያ›› አበበ ገላው የተባለ ድምፀ ቀጭን ጋዜጠኛ በአለም አለቆች ፊት

“Meles Zenawi is a dictator

Meles Zenawi is a dictator…. እያለ ካስፎገራቸው በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመጨረሻ ጊዜ በቴሌቪዥን የተመለከትኳቸው በሚያስደነግጥ ሁኔታ እጅግ ከስተውና ተጎሳቁለው ነበር፡፡

አልፎ አልፎ በውስን ቦታ ሽው ይል የነበረው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመታመማቸው ወሬ ጉልበቱን ጨምሮ መላ ሀገሪቱን ይንጣት ጀመር፡፡ ለዚህ ህዝባዊ ሹክሹክታ ገዢው ቡድን በግልፅ የ‹‹ራሱን›› መታመም እውቅና ሳይሰጥ ሳምንታት አለፉ፡፡

ዘግይቶም ቢሆን የጠቅላዩን መታመም የግዱን ሲያምንና የደበቀበትን ምክንያት ሲያስረዳ ‹‹የጫካ ባህላችን ነው›› በማለት ነበር፡፡

ይሄ አባባል ሁለት ገፅታ አለው፡፡ አንድም ነፃ አውጪዎቻችን ከበረሃ ወደ ከተማ ገብተው ለሃያ አንድ አመታት ከህዝቡ ጋር ከርመው ዛሬም ነገሮችን የሚመለከቱበት አቅጣጫና የሚመሩበት ሀሳብ የተመሰረተው በትናንቱ ባህላቸው እንጂ ዛሬ ከህዝቡ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያገናዘበ እንዳልሆነ…

አንድም ደግሞ ‹‹የአቶ መለስ ጉዳይ የሳቸውና የድርጅቱ እንጂ እናንተን አያገባችሁም›› እንደማለት ነው፡ ፡ (እኔ መቼም በዚህ ምግባሩ ግንባሩን አልቀየመውም፡፡ ይልቅስ ቅር የሚለኝ በጤናማው የጉብዝናቸው ወራት በደስታው ጠጋ ብለው ሊያወያዩት ካልፈቀዱት፤ የመታመማቸውንም እውነት ከባዕድ አንደበት እንደ ባዳ የሰማው ህዝብ ሀዘን መቀላወጡ ነው፡፡ እርግጥ ነው ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል የታዘብናቸው አይን ያወጡ ግፈቶች የነበሩ ቢሆንም እኔ ግን ደስታም ባይሆንም ህዝባዊ ቸልተኝነት (Public ignorance) እጠብቅ ነበር፡፡)

ጊዜ የማይፈታው ነገር የለምና እኚህ ለሃያ አንድ አመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጨዋታ ላይ የአጥቂነቱን ድርሻ ይዘው የከረሙት ሰው ህልፈተ-ህይወት ይፋ ሆነ፡፡

በማህበረሰባችን የአስተሳሰብ ባህል ‹‹ሙት አይወቀስም›› የሚል ስር የሰደደ እምነት አለ፡፡ ይሄ ግን በህይወት ያለሰው ለዚህ እሳቤው መሰረት የሆነው ለሟቹ ያለው ፍቅር ወይም ሟቹ ያሳለፈውና የኖረበት ሃቅ ሳይሆን የህይወት ሌላኛው ምዕራፍ ለሆነው ሞት ያለውን ፍርሃት የተተገነና ራሱን ችሎ መቆም የማይችል በተጠየቅም ያልነጠረ ተራ ሀሳብ ነው፡፡

እንደ አቶ መለስ ያለ የእያንዳንዳችንን የህይወት አቅጣጫ የመወሰን አቅም የነበረው አድራጊና ፈጣሪ፣ በሚገርም ሁኔታ ደግሞ ህይወቱ አልፎም ቢሆን መንፈሱና ራዕዩ በሌሎች አድሮ በቀጣይም ሊገዛን እየተዘጋጀ በመሆኑ… በፓርቲውና በተከታዮቹ መወደሱ፣ በሰፊው ህዝብ ደግሞ መወቀሱ አስገራሚ አይሆንም፡፡

እኚህ በስራና በፖለቲካ ሳይሆን በ‹‹ሴራ ፖለቲካ›› ብቃታቸው ለሃያ አንድ አመታት የገነኑት ሰው፤ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ቀስ በቀስ ከግለሰብነትም፣ ከተቋምነትም አልፈው ወደ አማልክትነት እየተሸጋገሩ እንደነበር እያየነው የነበረ ሃቅ ነው፡፡

እድሜ ዘመናቸውን ያሳለፉትም የሚመሩትን ግንባርም ሆነ የሚገዟትን ሀገር ዕጣ ፈንታ በማያጠራጥር መልኩ በመዳፋቸው ስር ለመክተት ሲጥሩ ነው፡፡ እውነቱን ለመናገር አልተሳካላቸውም ማለት ይከብዳል፡፡

ሀገር በጤናማ የእድገት አቅጣጫ እንድትገሰግስ ፖለቲካ ያልተጣባቸው ነፃ ተቋማት ይኖሩ ዘንድ ግድ ነው፡፡ የእነዚህ ተቋማት ህልውና በዕውቀት ተመስርቶ፣ በተጠያቂነት እየነጠረ የሚዘወር፣ ከአገዛዝ መውደቅና መነሳት ጋር ያልተቆራኘ የጠራ መዋቅር መሆን ሲገባው… እሳቸው ግን ተቋማቱን ሲያዋቅሩ በመስፈርትነት የተመለከቱት የትግል አጋርነት፣ የብሄር አንድነትና የፓርቲ ታማኝነት መሆኑ የሚያሳዝን ሃቅ ነው፡፡

እንዲህ የተዋቀረው ስብስብ በፖለቲካ እውቀት የነቃ፣ በአስተዳደር እውቀት የበቃ አይደለምና ከጌታው የሚወርዱለትን ሀሳቦች ያለአንዳች ማንገራገርና መመርመር ከመፈፀም ውጪ ለመገዳደር የሚያስችል ሞራላዊ ብቃትም ሆነ ነፃነት የለውም፡፡

በዚህ መልኩ አቶ መለስ ከሃይማኖት ተቋማት እስከ ስራ ማህበራት ያሉትን ለስልጣናቸው ዘላቂነት አመቺ በሆነ መልኩ ቃኝተዋቸዋል፡፡ በኚህ ሰው የአገዛዝ ዘመን ከተሸመደመዱት በርካታ ተቋማት አንዱ የትምህርት ዘርፍ ነው፡፡

እናማ ከደደቢት በረሃ ተነስተው አራት ኪሎ ከደረሱበት ማግስት ጀምሮ ህይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ የከወኗቸውን ተግባራትና የተናገሯቸውን ቃላት ስመረምር ነው… ‹‹ባለራዕዩ መሪ››፣ ‹‹አባይን የደፈረ ጀግና›› የሚሉት ተቀጥላ መጠሪያዎች የሚተናነቁኝ፡፡

ታጋይ መለስ አዲስ አበባ ገብተው ቤተ-መንግስቱን በተቆጣጠሩ ማግስት ከፈፀሙት አሳፋሪ ተግባር አንዱ በወጣትነታቸው የአዕምሮ ቀዶ-ጥገና ህክምና መማር ጀምረውበት ወደ ነበረው አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመሄድ የረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ ያላቸውን አርባ ሁለት ያህል መምህራን ከስራ ገበታቸው ማፈናቀል ነበር፡፡

እንደኛ ያለች በዘመናዊነትና በስልጣኔ ግስጋሴ ክፉኛ ለተቀደመች ሀገር የበለፀገውንና እጅግ እርቆ የሄደውን የሰለጠነ አለም ዱካ ለመከተል ሙሉ ተስፋዋን የጣለችበት ዋነኛ ማዕከል ዩኒቨርስቲ ይባላል፡፡

ይሄ በየዘርፉ በጨለማ የሚዳክር ማህበረሰብ ከዚህ ማዕከል የመፍትሄ ብርሃን ይጠብቃል፡፡ ለዚህም ነው ሁሉም ቤተሰብ ካፈጠጠው ድህነቱ፣ ከተራቆተው ጥሪቱ አሟጦ ባይማርም እንኳ ልጁን አስተምሮ ለዚህ ማዕከል ለማብቃት የሚታገለው፡፡

ማህበረሰባችን እውነቱን ነው፡ ፡ ቦታው በየወጣቱ ልብ የታመቁ ተሰጥኦዎችና የሚፍለቀለቁ ክህሎቶች የሚገሩበትና ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚቀየዱበት፣ በተዘዋዋሪም የሀገር መፃኢ መልክ የሚነደፍበት ወሳኝ ስፍራ ነው፡፡

ወደዚህ የዕውቀት ማዕከል የገባ የትኛውም ወጣት ሀገራዊውን ዳፍንት የሚገፍ የየራሱን ችቦ ይዞ እንዲመጣ ይጠበቅበታል፡፡ መዘንጋት የሌለበት መሰረታዊ ሃቅ ይሄ ተስፋ እውን መሆን የሚችለው በማዕከሉ የሚካሄደው ተራክቦ አላማው እውቀት ብቻ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

መቼም ጤናማው ትርጉሙ ፖለቲካ ማለት ሀገር ብለን በከበብናት ምድር ላይ የሚኖረን የእርስ በርስ ግንኙነት ‹‹ፍቅር›› ባይፈስበት ‹‹ፍትሕ›› እንዳይነጥፍበት ዜጎችም በስብስቡ ውስጥ ማህበራዊ ዋስትናቸው ተረጋግጦ ይኖሩ ዘንድ የተቀመረ ማህበራዊ ሳይንስ ይመስለኛል፡፡

ይህን የወል የስምምነት ህግ የታደሉት ሀገሮች በየዕለቱ እየመረመሩት፣ እያሻሻሉት የመጨረሻውንና በየትኛውም ዘርፍ ሊገለጥ የሚችለውን ችግር ምንጩ ድረስ በመዝለቅ ለማድረቅ ሲተጉበት እኛ ሀገር ግን በግልባጩ ከታመመው ፖለቲካ የሚነሳው ወረርሽኝ ሌሎችን ዘርፎችና መላ ሀገሪቷን ሲበክል የተመለከቱት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከአፄው ስርዓት ጀምሮ ህዝቡን ወክለው ህይወታቸውን ጭምር አደጋ ላይ ጥለው ሞግተዋል፡፡

ይሄ የሰለጠነው አለም የደረሰበትን አስተዳደራዊ ስልጣኔ በዋቢነት ያነገበ፣ ስለተሻለች ኢትዮጵያ ያሰበ፣ በወጣትነት ንዳድ የተግለበለበ የተማሪዎቹ ንቅናቄ በፖለቲካው ላይ የራሱን ተፅዕኖ መፍጠር ከመቻሉም በላይ በማህበረሰቡ ስነ-ልቦና ላይም ‹‹እውነተኛ ልጆቻችን ናቸው›› አይነት አመኔታን መፍጠር ችለዋል፡፡

ለዚህም ነው ታጋይ መለስ ጊዜ ሳያባክኑ ወደዚህ ለአምባ-ገነናዊ ስርዓት የጎን ውጋት የሆኑት የህዝብ ልጆች መሰብሰቢያ ወደ ሆነው የዕውቀት ማዕከል ያቀኑት፡፡

ከዚያማ ወዳጄ በረሃ ሆነው በጥንቃቄ ያፈሉትንና እድሜ ልካቸውን በየተገኙበት ሲተክሉና ሲያፀድቁ የከረሙትን የብሄርተኝነት ችግኝ፣ የለመለመውን የኢትዮጵያዊነት አፀድ መንጥረው በብዛት ተከሉትና በአንዳንድ ‹‹ፀረ-ልማት ሀይሎች›› እንዳይነቀልም ፕ/ር እንድርያስን የመሰለ የነበልባል ሰይፍን የታጠቀ ጠባቂ በቦታው ሰየሙ፡፡

> ‵…ከደደቢት በረሃ ተነስተው አራት ኪሎ ከደረሱበት ማግስት ጀምሮ ህይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ የከወኗቸውን ተግባራትና የተናገሯቸውን ቃላት ስመረምር ነው… ‹‹ባለራዕዩ መሪ››፣ ‹‹አባይን የደፈረ ጀግና›› የሚሉት ተቀጥላ መጠሪያዎች የሚተናነቁኝ…

ወቅታዊ ዘገባ

# አዲስ ተስፋ ለኦጋዴን

የዛሬ ሁለት አመት ገደማ የኢትዮጵያ መንግስት አምስት ድርጅቶችን በሽብርተኝነት መወንጀሉ የሚታወስ ነው፡፡ በሽብርተኝነት ከተፈረጁት ድርጅቶች መካከል ሁለቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅ ሲሆኑ የተቀሩት ሦስቱ ደግሞ የአገር ውስጥ ቡድኖች ናቸው፡፡

ፓርላማው በሽብርተኝነት ፈርጆ ያፀደቀባቸውን ድርጅቶች በሚመለከት በወቅቱ ከተለያዩ ወገኖች የተለያዩ አስተያየቶችን አስተናግዷል፡፡ በመንግስት የወጣውን አዋጅ ተከትሎ አንዳንዱ ‹‹በትክክለኛ ጊዜ፣ ትክክለኛ እርምጃ›› ተወስዷል የሚል እምነታቸውን ሲገልፁ ሌሎቹ በተለይም በአገር ውስጥ ያሉት አስተያየት ሰጪዎች መንግስት ይህን አዋጃ ተከትሎ ሊከውነው ያሰበው ተጨማሪ የፖለቲካ አጀንዳ ይኖረዋል ብለው እንደሚያምኑ ጥርጣሬያቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡

ለዚህም በዋቢነት ሁለት ማስረጃዎችን ያቀርባሉ፡፡ የመጀመሪያው ማስረጃ በአገር ውስጥ ሽብርተኛ ተብለው የተፈረጁ ተቋማትና ተቋማቱን በኃላፊነት እየመሩ ያሉት ግለሰቦች ይህንን ተግባር ለመፈፀም በሚኖሩባቸው አገራት ያላቸውን በነፃነት የመኖር መብታቸውን በመጥቀስ ሲሆን ሌላው ማስረጃ ብለው የሚያነሱት ድርጅቶቹን ከመፈረጅ ባሻገር የፖለቲካ ተቀናቃኞቻችውን ይሁን ጋዜጠኞችን በተከታታይ ለማሰር የወሰደውን እርምጃ በመጥቀስ ነው፡፡ እነዚህ ሶስቱ ድርጅቶች መቀመጫቸውን ያደረጉት በአለም አቀፍ ደረጃ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በርትታ እየሰራች በምትገኝ አገር ውስጥ የመሆኑ አንዱ ጉዳይ ነው፡፡ አሜሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሽብርተኝነትን ለማክሰም በሚደረገው ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ግንባር ቀደም ተሰላፊ ናት፡፡ የዚህች አገር ወዳጅነትን ለማግኘት የሚሹ አገራትም ይሁኑ በአሜሪካ ጥቁር መዝገብ ላይ መስፈር የማይፈልጉ የአገራት መሪዎች ያላቸው ብቸኛ አማራጭ በሽብርተኝነት ላይ ‹‹ተከፍቷል›› በሚባለው ዘመቻ ውስጥ በአጋርነት ራሳቸውን ማስገባት ማመናቸው ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በተለይም በሱማሊያ ጉዳይ ላይ ከአሜሪካ መንግስት ጋር በቅርበት ከሚሰራባቸው ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ከሽብርተኝነት ጋር የተያያዘው ነው፡፡ አሜሪካ በሱማሊያ የነገሰውን ስርዓት አልበኝነት ተከትሎ አልቃይዳ የራሱን ዋና መቀመጫ ሊያመቻች ይችላል የሚለው ዋነኛው ስጋቷ ነው፡፡ በሶማሊያ እና በቀንዱ አካባቢ ያለው አለመረጋጋት እልባት እስካልተሰጠው ድረስ በአፍጋኒስታን እና በኢራቅ ላይ የተከፈቱት ዘመቻዎች ሁሉ ከንቱ ይሆኑባታል፡፡ አንዱን ቀዳዳ ሲደፍኑት በሌላኛው ቀዳዳ እንዳይፈስ ለመከላከል በቀጠናው የጣምራ ወዳጃዊ ግንኙነት አስፈላጊ ሆኖ በመታመኑ የተነሳ የኢትዮጵያ መንግስት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ፊት ትልቅ ክብርና ሞገስን እንዲያገኝ አስችሎታል፡፡

ከላይ የተገለፁት ማስረጃዎችን በሙሉ ጠቅለል አድርገን ስንወስደው በኢትዮጵያ መንግስት አሸባሪ ተብለው የመፈረጃቸው እውነታ ድርጅቶች በአሜሪካ መንግስትም እውቅና ሊቸረው ይገባ ነበር ማለት ነው፡፡ የአልቃይዳ አሸባሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ መሽገው ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ እነዚህን ግለሰቦች ለአሜሪካ መንግስት አሳልፎ የመስጠት ግዴታ ነበረባት ማለት ነው፡፡ ጥያቄው የኢትዮጵያ መንግስት አሸባሪ ብሎ የፈረጃቸውን ግለሰቦች እና ድርጅታቸውን የአሜሪካ መንግስት እስከ አሁን ድረስ አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ ሽብርተኝነት አለም አቀፍ መልክ ያለው እንደመሆኑ አገራት በጋራ ካልተዋጉት በስተቀር በተናጠል መፍትሄ ሊያበጁለት አይችሉም፡፡ አደጋው ከሚያስከትለው ጥልቅ ጥፋት አንፃር አሸባሪ ተብለው የተፈረዱትን ድርጅቶች እና አመራሮች በአሜሪካ በነፃነት እየኖሩ ‹‹አላማቸውን›› እንዲያስፈፅሙ ፍቃድ የሰጣቸው ማን ነው? የሚለው መከራከሪያ ብዙዎቹን ታዛቢዎች የኢትዮጵያ መንግስት የወሰደው እርምጃ ፖለቲካዊ እንጂ አለም አቀፋዊ ይዘት የለውም እንዲሉ እንዳስገደዳቸው ገልፀዋል፡፡

በአሸባሪነት ከተፈረጁት አገር በቀል ድርጅቶች መካከል በቅርቡ የአንደኛውን አሸባሪ ድርጅት መልክ ሊለውጥ የሚችል እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ መንግስት በማድረግ ላይ መሆኑን ሰምተናል፡፡ በሽብርተኝነት አዋጅ ከአገር ውስጥ ፖለቲካ ለማጥፋት ተሞክሮ የነበረውን ድርጅት አሁን በጠረጴዛ ዙሪያ አግባብቶ በማምጣት ከተሰማራበት አጥፊ ተግባር ለመመለስ በመሞከር ላይ ይገኛል፡፡ ነገሮችን ከኃይል እና ከመጠፋፋት ይልቅ በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ለመነጋገር መፍቀድ ትልቅ ፖለቲካዊ እርምጃ ነው፡፡ የሃይል እርምጃ አገሪቷን ወደሚፈለግበት ደረጃ አያደርሳትም፡፡ በተደጋጋሚ የተሰሩ ጥፋቶች ዘመን ሲተካም መደገም የለባቸውም፡፡ የአገራችንም ትልቁ የወደፊት እጣ ፈንታ ተደብቆ የሚገኘው አሸባሪው ድርጅት ተሸሽጎበታል ሶማሌ ክልል ውስጥ ነው፡፡ በዚሁ ክልል ፖለቲካዊና ታሪካዊ ጥያቄ አለኝ ብሎ የተነሳው የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ድርጅት (ኦብነግ) በአካባቢው እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረ አመታት አልፏል፡፡ እስከአሁን ትጥቅ ለማስፈታት በተደረገው ግብግብ የብዙ ንፁሃን ዜጎች ደም ደመ-ከልብ ሆኗል፡፡ እንዲህ አይነትም ዋጋ ተከፍሎ ቢሆን ክልሉን ከአደጋ ቀጠናነት ለመታደግ አልተቻለም፡፡ ሁሉንም አገር በቀል ድርጅቶችን ወደ ሰላም መንገድ መጋበዝ የመንግስት ትልቁ የቤት ስራው ነው፡፡ የአመራሩ ብቃትም ቢሆን መፈተሽ ካለበት መስፈርቱ መሆን የሚገባው ስንቱን ተቀናቃኝ ከአገር እንዲወጡ ገፍቷል ሳይሆን የጠፉትን ለመመለስ የት ድረስ ተጉዟል የሚለው ነው፡፡

አዲሱ ተስፋ


ከሁለት አመታት በኋላ የኢትዮጵያ መንግስት አሸባሪ ብሎ ከፈረጀው ኦብነግ ድርጅት ጋር በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ለመነጋገር ኬንያ መክረሙን ሰምተናል፡፡ ሁለቱን ተደራዳሪዎች በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ለማምጣት ኬንያ ቅድሚያውን ወስዳለች፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ኬንያ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እያደረገችው ያለው ንቁ ተሳትፎ፣ ምን አልባትም በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ እና ልምዷም እየካበተ ከመጣ አገራችን በቀጠናው ላይ የነበራትን የመደመጥ እድል ልትቀማት እንደምትችል መገመት ከባድ አይሆንም፡፡ በቅርቡ ሶማሊያን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ጦርነት የመጨረሻ ደረጃ ላይ ለማድረስ አገሪቷ የተጓዘችበትን የኃላፊነት መንገድ አንዱ ማሳያ ሊሆነን ይችላል፡፡ አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ መንግስት እና በኦብነግ መካከል የሚደረገውን የሰላም ስምምነት በማዘጋጀትና በማደራደር ዙሪያ የጀመረችው እንቅስቃሴ ይበልጥ ተደማጭነቷን ያጠነክሩላታል፡፡

‹‹የኢትዮጵያ መንግስት እና ከኦብነግ ቡድኖችየተውጣጡ ወደ አስር የሚጠጉ ተደራዳሪዎችን ያሳተፈው የናይሮቢው ድርድር የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትር የሆኑት አቶ ሲራጅ ፈጌሳ የኢትዮጵያ መንግስትን ሲወክሉ ኦብነግ ደግሞ አብዱረህማን መሃዲ በተባሉ የግንባሩ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ተወክሏል፡፡ ምንአልባት ድርድሩን ከውጭ ሆኖ ለሚመለከት ማንኛውም የፖለቲካ ታዛቢ የሚያየው አንድ ነጥብ ይኖራል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሸባሪ ተብሎ ከተፈረጀ ድርጅት ጋር ለመደራደር ሲባል የመከላከያ ሚኒስትርን ስልጣን የጨበጠ ትልቅ ሰው መላክ ለምን አስፈለገ? አልያም የአገር ውስጥ ጉዳይ እና የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቶች ይህንን ኃላፊነት ለምን ሊወስዱ አልቻሉም? የሚሉት አነጋጋሪ ነጥቦች ይመስሉኛል፡፡ የአሸባሪው ድርጅት ለድርድሩ የላከው ግለሰብ እና በድርጅቱ ውስጥ የጨበጠውን የኃላፊነት ደረጃ ስንመለከት በተወከሉ ግለሰቦች አለመመጣጠን በነገሩ ይበልጥ ግር እንድንሰኝ ያደርገናል፡፡

የሆነው ሆኖ በሁለቱ ተደራዳሪዎች መካከል ለመደራደር የሚያስችሉ ባለስድስት ነጥብ ሀሳቦች ተቀምጠዋል፡፡ የተቀመጡትን ነጥቦች ተከትሎ ተከታታይ ውይይቶች እና ድርድሮች ይኖራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በተለይ ክልሉ ካለው እምቅ የነዳጅ ሀብት አንፃር (4 ትሪሊዮን ኪዩቢክ የሚጠጋ) ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ፈትቶ ለጋራ መጠቀሚያነት እንዲውል ማድረግ የሁለቱ ተደራዳሪዎች ግዴታና ኃላፊነት ነው የሚሆነው፡፡ ከሁሉም አስቀድሞ ግን ሊታሰብባቸው የሚገቡ አንዳንድ ጉዳዮችንም ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ በተለይ ከሰብዓዊ መብት አያያዝ አንፃር፡፡

በተደጋጋሚ የሚወጡ የተለያዩ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ቡድኖች ሪፖርት እንደሚያመለክተው የኦጋዴን አካባቢ ነዋሪዎች በተለያየ አጋጣሚ ሁለቱ ቡድኖች በሚያደርጓቸው ተደጋጋሚ ጦርነቶች የተነሳ በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ድርድሩን ከመጀመር በፊት ከሁለቱም ተወካይ ተደራዳሪዎች ትኩረት ሊቸራቸው ይገባሉ ከሚባሉት መካከል ሁለቱም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እና ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ የተኩስ አቁም ስምምነት በአካባቢው ማድረግ፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲቆምና በዚህም ወንጀል እጃቸው ያለበትን ግለሰቦች ለፍርድ ማቅረብ፣ የፖለቲካ እስረኞችን በሚመለከት በጋራ ሊያግባባ የሚችል እና ዘላቂ መፍትሄ የሚያስገኝ ውሳኔ ላይ መድረስ፣ የሰብዓዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን እና ግለሰቦች ወደ አካባቢው በነፃነት በመዘዋወር ስራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ እንዲፈቀድላቸው ነገሮችን ማመቻቸት የሚሉት ወሳኝ ጉዳዮች መሆን ይኖባቸዋል፡፡

ለሰላም የሚከፈለው መስዋዕትነት ዋጋ የሚኖረው ሰላም ሲመጣ ብቻ ነው፡፡



# ‹‹ቃሊቲ››ን በጨረፍታ

## ክፍል-፪

*ተመስገን ደሳለኝ*

የዛሬ አስራ አምስት ቀን የቃሊቲ ትርክቴን ያቆምኩት ምን ላይ ነበር? ... ያን አስከፊ እስር ቤት አንስቼ ለመጣል ከአፋፍ ደርሼ ነበር መሰለኝ፡፡ እረ እንዲያውም በፍርድ ቤት ፖሊስና በቃሊቲ ፖሊስ መካከል ርክክቡ ሁሉ ተፈፅሟል፡፡ ያውም ሰውን ያህል ክቡር ፍጡር በአንዲት ብጣቂ ደረሰኝ! (ልውውጡ እንዲህ ነው፡- የፍርድ ቤቱ ፖሊሶች እኔን ሰጡና በልዋጩ ከቃሊቲ ፖሊሶች አንዲት ካርኒ ተቀበሉ) መቼም የአገሬ መንግስት በሚጠቅመውም በማይጠቅመውም ንፉግ መሆን ስለሚወድ እንጂ ደረሰኙን ሁለት ቢያደርገው ምን ይጎዳ ነበር? ጥራዝ ሙሉ ቢሆንስ? ለሰው ልጅ...? የሰው ልጅ መሆኔ ነው...

‹‹የሰው ልጅ መሆኔ ነው...››የሚል ዘፈንህ በሬዲዮን፣ አሊያም በሌላ መንገድ ሰምተኸው ይሆናል፤ ቃሊቲ ግን ይሄ አይታሰብም፡፡ ምክንያቱም ‹‹ወንጀለኛ›› ነህ፡፡ በወንጀለኛና በሰው ልጅ መካከል ደግሞ ትልቅ ልዩነት አለ-በቃሊቲ፡፡

...ዕድሜዋ በግምት ወደ 50 የሚጠጋ፣ በክንዷ ላይ የአስር አለቃ ማዕረግ የለጠፈች (ሳጅን) በጥያቄ ታጣድፈኝ ጀመር፤ ለነገሩ በጥፊ ከመጣደፍ በጥያቄ መጣደፍ በብዙ የተሻለ ነው ብዬ ስለገመትኩ ያለቅሬታ ነበር የጠየቀችኝን ሁሉ የመለስኩላት፡፡

‹‹ስምህ ማነው?›› የተረከብሽበት ወረቀት ላይ አለልሽ ልላት አሰብኩና ተውኩት፡፡ በምትኩ ሙሉ ስሜን ነገርኳት፡፡

‹‹ብሔርህ ምንድን ነው?››፣ ‹‹እግዜሩ ይይልህ ኢህአዴግ!›› በሆዴ ያልኩት ነው፡፡ በአፌ ግን እንደምንም ቀጣጥዬና ሰፋፍቼ ብሄሬን ተናገርኩ፡፡ መቼም በብሶት ተወልዶ፣ ለበርካታ ብሶቶች መወለድ መንስኤ የሆነው ኢህአዴግ በእግዜር ፊት ለፍርድ ቢቀርብ (በሰው ፊት እንኳ ይቀርባል ብሎ ማሰቡ አዳጋች ነው) ከሚከሰስባቸው ክሶች መሀከል ዋነኛው ሀገሪውን በአያት ቅድማያቱ (አያት ቅድማያቱን የማያውቀውን ደግሞ በሩቅ ዘመዱ) በመከፋፈሉ ይመስለኛል፡፡ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ሐረሪ፣ አፋር...

የሆነ ሆኖ የሳጅን ጥያቄ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምን አስታወሰኝ፡ ‹‹ፕሮፍ›› ከሚጠሉት ጥያቄ ሁሉ ‹‹ብሔርዎት ምንድን ነው?›› የሚል እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ዛሬም ድረስ የሚጠቀሙበት የቀበሌ መታወቂያ ‹‹ብሔር›› የሚለው ቦታ ላይ ‹‹ኢትዮጵያዊ›› የሚል ውድ ቃል ተፅፎበት ይገኛል፡፡ ይህ የሆነው ግን በቀበሌዎቹ በጎ ፍቃድ አይደለም፡፡ በፕሮፍ የማይታጠፍ ብርቱ ተቃውሞ እንጂ፡፡ እናም ከ80 ሚሊዮን ህዝብ የቀበሌ መታወቂያም ላይ ሆነ የምርጫ ካርድ ላይ ብሔሩን ሳያፅፍ የወሰደ ብቸኛ ሰው ቢኖር ፕሮፍ ይመስሉኛል፡ እንዲያውም እርሳቸው ይንገሩኝ፣ ከመጽሐፎቻቸው ወይም ከቃለ መጠይቆቻቸው ላይ በአንዱ ላንብበው ማስታወስ ተሳነኝ እንጂ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹የ10ኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ አንድ መምህር ነበሩ፡፡ ሁልጊዜም ክፍል ገብተው ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ‹እናንተ ምንድር ናችሁ?› ሲሉ ይጠይቁናል፤ ‹የሰው ልጅ› ስንል እንመልስላቸዋለን፡ ይህ ሁኔታም ሶስት ጊዜ ከተደጋገመ በኋላ ነው ትምህርት የምንጀምረው፡፡›› እንግዲህ ፕሮፍ የሚሉን በአንድ ሀገር ውስጥ ተከልለው በአንድነት የሚኖሩ ህዝቦች ሊተሳሰሩበት የሚችሉት ‹‹ሰው›› በሚለው ክቡር ቃል ብቻ ነው፡፡

ኢህአዴግ ከዚህ አይነቱ አመለካከት ደም የተቃባ ነው፡፡ የሉሲ ዘሮች እንደሆንን ይደሰኩርልናል እንጂ አማራ የሚባል ዝንጀሮ፣ ኦሮሞ የሚባል ዝንጀሮ፣ ትግሬ የሚባል ዝንጀሮ... የት እንደሚገኝ አይነግረንም፡፡ ስለዚህም የየብሄራችንን አባወራ ዝንጀሮ ካልነገረን በብሔር መከፋፈላችንንም አለመቀበል እንችላለን፡፡ ወይም ‹‹ሉሲ›› የተሰኘችው ምንጃላታችን የዝንጀሮ ዝርያ አይደለችም የሚል ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ሊሰጠን ይገባል፡ ይህ ካልሆነ ግን ራሱ ኢህአዴግ አቶ መለስ እንደሚሉት (ነፍሳቸውን ይማረውና) አጥር ላይ ተንጠልጥሏል፡

መቼም ሳጅን ብሔሬን የጠየቀችኝ ልትጎዳው ወይም ልትጠቀመው የምትፈልገውብሔርኖሮአይመስለኝም፡ ትዕዛዝ ሆኖባት እንጂ፡፡ (በነገራችን ላይ ቃሊቲ ያለው አድሎና መድሎ በብሔር ላይ የተመሰረተ ነው ብዬ አላስብም፡፡ ወይም ለአጭር ጊዜ ብቻ በመታሰሬ ሳላስተውል ቀርቼ ይሆናል፡ ሆኖም በጥቂት ቀናት ቆይታዬ እንዳየሁት ከሆነ በቃሊቲ ያለው ግልፅ አድሎ እና መድሎ ተከሳሹ በፈፀመው ወይም በተጠረጠረበት ወንጀል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ለምሳሌ የሶስት ዓመት ህፃንን አስገድዶ የደፈረ ወይም የሰው ገንዘብ ለመዝረፍ ሲል ንፁሃንን የገደለ ከየትኛውም ብሔር ቢመጣ ከእስረኝነት መብቱ ላይ ጥቂት እንኳ አይሸረፍበትም፡፡ በግልባጩ የተከሳሹ ወንጀል ከኢህአዴግ ጋር የተያያዘ አሊያም መንግሥትን አስከፍቶ ከሆነ እውነት እውነት እልሀለሁ ለእርሱ ቃሊቲ የተረገመ ምድራዊ ሲኦል ነው፡ መብቱ ብቻ ሳይሆን ከራሱ ላይም አንዳች ነገር ሊጎድል ይችላልና፡፡ ለምሳሌ እስክንድር ነጋ ከቤተሰቡ ውጭ ሌላ ዘመድ ወዳጅ እንዳይጠይቀው ፅኑ ዕግድ ተጥሎበታል፡፡ አንዱአለም አራጌ፣ በቀለ ገርባ፣ ናትናኤል መኮንን እና ስማቸውን የማላስታውሰው ሌሎች ለውጥ ፈላጊዎች የዚህ ገፈት ቀማሽ ናቸው፡፡ ርዕዮት አለሙ ደግሞ ጠያቂ ባይቀነስባትም፣ የመጠየቂያ ሰዓት ተቀንሶበታል፡ ርዕዮት አብረዋት እንደታሰሩ ሴቶች ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ እንድትጠየቅ አልተፈቀደላትም፡፡ የርዕዮት መጠየቂያ ሰዓት ከስድስት ሰዓት እስከ ስድስት ተኩል (ለ30 ደቂቃ) ብቻ ነው፡፡ እናም በየመንደሩ ሳይቀር የሚሹለከለኩ የባቡር መስመሮች እዘረጋለሁ፣ አባይን እገድባለሁ የሚለው ኢህአዴግ እንዲህ ነው፡ ግለሰብን ሳይቀር ለማበሳጨት፣ ለማማረር የማያንቀላፋ መንግስት፡፡ የዚህ ሁሉ መነሻ ደግሞ ታሳሪዎቹ ፀባቸው ከመንግስት ጋር ስለሆነ ብቻ እንደሆነ ደግሜ እነግርሃለሁ፡፡

‹‹የምትሰራው ምንድን ነው?››

‹‹ጋዜጠኛ ነኝ›› ካቀረቀረችበት ቀና ብላ አየችኝ፡፡ እንደገና አይኗን ወደ ክስ ቻርጁ መለሰች፡፡ ደግማ ከላይ እስከታች ገረመመችኝ፡ አንዴ ወደ ክስ ቻርጁ፤ አንዴ ወደእኔ እያፈራረቀች ስትመለከት ነገረ ስራዋ ግራ አጋብቶኝ ‹‹ምነው! ችግር አለ?›› ስል ጠየኳት፡፡

‹‹ምንም ችግር የለም፡፡›› ጫን ባለ ድምፅ ቀጠለች ‹‹ምን አድርገህ ነው የታሰርከው?››

‹‹ክስ ቻርጁ ላይ አለልሽ››

‹‹ክስ ቻርጁ በደንብ አይገልፅም››

‹‹ደጋግመሽ እይው፤ እኔም ስራሴ አልገባኝም›› ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ በተመሳሳይ መልኩ አንድ እስረኛን እያናዘዘ ላለ ጎልማሳ ፖሊስ ክስ ቻርጁን አቀበለችው፡ እሱም ለደቂቃ ካተኮረበት በኋላ እንዳልገባው ገልፆ መልሶ እኔኑ ጠየቀኝ፡፡

‹‹ለእኔም ግልፅ አይደለም›› ለእርሷ የነገርኳትን ደገምኩለት፡፡ ይህን ጊዜ ‹‹ዝም ብለሽ ቻርጁ ላይ ያለውን ፃፊው›› አላት፡፡ ሳጅኗም በክስ ቻርጁ መሰረት ‹‹የሰውን ሃሳብ ማናወጥ እና ማሳመፅ›› በሚል መዘገበችው፡፡ የሰውን ሃሳብ በምን ይሆን የናወፅኩት?

ከዚህ በኋላ አሻራ እንድነሳ ተደረገና ከሰባት እስረኞች ጋር ወደ ሌላ ክፍል ተወሰድኩ፡፡ በክፍሉ ውስጥ ያለው ፖሊስ ቁጡ ይመስላል፡ ገና ከመድረሳችን ‹‹ውጡ፣ ተሰለፉ....›› በሚሉ ትዕዛዛት በጩኸት አጣደፈን፡፡ ይኸው ፖሊስ በረድፍ አሰልፎን ሲያበቃ በየተራ እያስገባ ፎቶ እንድንነሳ አደረገና ግዴታውን ጨርሶ ወደ ሌላ ክፍል አስገባን፤ አሁን የተረከበን ፖሊስ ደግሞ ‹‹ፈታሽ›› ነው፡፡ የያዝናቸውን እያንዳንዷን እቃ ልምድ ባካበቱ እጆቹ በጥንቃቄ በርብሮ ሲያበቃ ኪሶቻችንን ፈተሸና ስራውን ጨረሰ፡ እነዚህ ሂደቶች የሚያጥሩት እንዲህ በአጭሩ ሲተረኩ እንጂ ሲተገበሩማ ከአንድ ሰአት ከግማሽ በላይ ይወስዳሉ፡፡

ከዚህ በኋላ የቀረው በቦታው ያለነውን እስረኞች ወደመታሰሪያ ቤት ማስገባት ነውና ሰባቱን እየነዱ ከወሰዱ በኋላ ለእኔ ‹‹አንተ እዚሁ ቆይ!›› የሚል ፖሊሳዊ ትዕዛዝ ሰጡኝ፡፡ ሁኔታው ግራ ቢያጋባኝም እንደታዘዝኩት ክፍሉ ውስጥ ባለ አግዳሚ ወንበር ላይ አረፍ ብዬ ከእስረኞች ለምን እንደተለየሁና ቀጥሎ ምን ሊከሰት እንደሚችል ማንሰላሰል ጀመርኩ፡፡ እንዲህ እያንሰላሰልኩ ለካስ እንቅልፍ ወስዶኝ ኖሯል፡፡ እናም በግምት ከአንድ ሰአት በኋላ ‹‹ተነስ!›› የሚል የፖሊስ ትዕዛዝ ከሸለብታዬ አናውጦ ቀሰቀሰኝ፡፡ ዕቃዬን ይዤ እንድወጣ ተነገረኝ፡፡ እኔም ወጣሁ፤ መጀመሪያ ከሳጅን ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ያገኘሁት ፖሊስ እየመራ እኔ እየተከተልኩ አንድ አነስተኛ ግቢ ጋ ስንደርስ ‹‹እዚህ ጋ ቁጭ በል›› ብሎኝ እርሱ ወደ ግቢው ውስጥ ገባ፡፡ (በነገራችን ላይ ቃሊቲ እጅግ በጣም ሰፊ ግቢ ቢሆንም ውስጡ በበርካታ ግቢዎች የተከፋፈለ ነው) ጥቂት ቆይቶ ተመልሶ መጣ፡ እኔን አልፎም ከግቢው በር ፊንጠር ብለው ወደቆሙ ሁለት ‹‹ኮማንደሮች›› አጠገብ ሄዶ ወደእኔ አቅጣጫ በጣቱ እየጠቆመ የሆነ ነገር ነገራቸው፡፡ ኮማንደሮቹም ለደቂቃ ያህል ከተመለከቱኝ በኋላ ፖሊሱ የሚነግራቸውን ማዳመጥ ጀመሩ፡ በእኔ ጉዳይ እየተነጋገሩ እንደሆነ ቢገባኝም ምን እያሉ እንደሆነ ሳውቅ አልቻልኩም፡፡ ከሁኔታቸው ግን አንድ ያልተግባቡበት ጉዳይ ያለ ይመስለኛል፡፡ ከጥቂት መወዛገብ በኋላ ሰውነቱ ደንደን ያለው ኮማንደር በመገናኛ ራዲዮኑ ተነጋግሮ ሲያበቃ ወደእኔ ተጠግቶ ከፊት ለፊት ባለው የጥበቃ ማማ ላይ የተቀመጠውን ፖሊስ ጠርቶ በቁጣ ይፈትሸኝ ዘንድ አዘዘው፡፡ ይህ ኮማንደር ከፍርድ ቤት የተረከበውን እስረኛ ሳይሆን በከባድ ውጊያ ላይ የማረከውን ጠላቱን የሚያናግር እስኪመስል ድረስ ምንጭቅጭቅ አደረገኝ፡ በምን ተከስሼ እንደመጣሁና ማን እንደሆንኩ ይዞኝ የመጣው ፖሊስ ሳይነግረው አልቀረም፤ እንደ ክፉ ባላጋራው አየኝ፡፡ በድጋሚም ዕቃዬ ተመነቃቅሮና ኪሴ ተበርብሮ ተፈተሸ፡፡ ኮማንደሩ ፍተሻውን በጥንቃቄ እየተከታተለ ነው፡፡ ፈታሹ ፖሊስ ከያዝኩት ፌስታል ውስጥ ቲሸርቶችን ማውጣት ሲጀምር ‹‹ቲ-ሸርቶቹ ፅሁፍ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው አረጋግጥ›› ሲል ኮማንደሩ ትዕዛዝ ሰጠ፤ መቼም

*ወደ ገፅ 31 ዞሯል*